የብሉይ ኪዳን አሰሳ

# Old Testament Survey

ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

**World Vision - East Africa**
**Sub-Regional Office**
**Kenya**
**2001**

# የብሉይ ኪዳን አሰሳ

## ማውጫ


ምዕራፍ ገጽ

መግቢያ

I የሕግ መጻሕፍት (ፔንታቱክ).......... 2

ዘፍረት

ዘጸአት

ዘሌዋውያን

ዘኁልቁ

ዘዳግም

II የታሪክ መጽሐፍት.......... 37

መጽሐፈ ኢያሱ

መጽሐፈ መሳፍንት

መጽሐፈ ሩት

1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል

1ኛ እና 2ኛ ነገሥት

1ኛ እና 2ኛ ዜና

መጽሐፍ ዕዝራ

መጽሐፍ ነህምያ

መጽሐፍ አስቴር

III የቅኔ መጽሐፍት.......... 80

መጽሐፈ ኢዮብ

መዝሙረ ዳዊት

መጽሐፈ ምሳሌ

መጽሐፈ መክብብ

መኃልዩ መኃልዩ ዘሰሎሞን

IV ታላላቅ ነቢያት.......... 95

ትንቢተ ኢሳያስ

ትንቢተ ኤርምያስ

ትንቢተ ሰቆቃው ኤርምያስ

ትንቢተ ሕዝቅኤል

ትንቢተ ዳንኤል

ምዕራፍ ገጽ


ደቂቀ ነቢያት ........................................ 128

ትንቢተ ሆሴዕ

ትንቢተ አሞጽ

ትንቢተ ሚክያስ

ትንቢተ ኢዩኤል

ትንቢተ አብድዩ

ትንቢተ ዮናስ

ትንቢተ ናሆም

ትንቢተ ዕንባቆም

ትንቢተ ሶፎንያስ

ትንቢተ ሐጌ

ትንቢተ ዘካርያስ

ትንቢተ ሚልክያስ

ዋቢ መጻሕፍት


# የብሉይ ኪዳን አሰሳ

## መግቢያ

የታሪክ የበላይ፣ ተቆጣጣሪና ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ የምናውቀው እውነታ ነው። ከዚህም በላይ የሚደንቀው ነገር ደግሞ በታሪክ ሂደት ላይ የሰው ልጆች ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረጉ ነው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ይኸን ክንዋኔ ደረጃ በደረጃ ያትታሉ። ከሰውና ከዓለም አፈጣጠር ጀምሮ ካለው አጠቃላይ ታሪክ ተነስተው እስከ አብርሃም ትውልድ /የእስራኤል ሕዝብ/ ልዩ ታሪክ በሰፊው ይዘግባሉ። በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ባህርይ ማለትም ሉዓላዊነቱ፣ ሁሉን ቻይነቱ፣ መሐሪነቱ፣ ጌትነቱ፣ ፈራጅነቱ፣ ወዘተ... በግልጽ ይታያል።

በመሆኑም ይኸ ኮርስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ታሪካዊ ዳራና ለነመለኮታዊ ይዘት ከማሳየቱም በተጨማሪ ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለውን ግንኙነት በመጠቆም ለክርስትና ኑሮ ታላቅ ትርጉም ያላቸውን ዘላለማዊ የሕይወት መመሪያዎችን ለማብራራት ሞክሯል።

# ምዕራፍ አንድ

# የሕግ መጻሕፍት (ፔንታቱክ)

በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ አምስት የኦሪት መጻሕፍት ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቁና ዘዳግም ሲሆኑ፣ እነዚህም የሕግ መጻሕፍት፣ የሙሴ መጻሕፍት ወይም የሙሴ ሕግ መጻሕፍት በመባል በአይሁድ ዘንድ ይታወቃሉ (2ኛ ዜና 25፥4፣ ዕዝ. 6፥18፣ ነህ. 13፥1፣ 8፥1)። ይህም ሕግ ወይም ትእዛዝ ማለት ሲሆን ከዕብራይስጡ ቶራ (Torah) የሚለው ቃል የተወሰደ ነው (ሉቃ. 16፥17፣ 1ኛ ቆሮ. 9፥8)። እነዚህ አምስት መጻሕፍት መጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበሩ። በግሪክ ቋንቋ ፔንታቱኮስ (ፔንታቱክ) ማለት ትርጓሜው አምስቱ መጻሕፍት ማለት ነው። ስለዚህም ፔንታቱክ የሚል ስያሜ ተሰጣቸው፡

የሕግ አራት መጻሕፍት እያንዳንዳቸው በተለያየ ደረጃ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ዕቅድ ቢናገሩም ወጥነት ያላቸው መጻሕፍት ናቸው። ለምሳሌ ዘፍጥረት የፍጥረት ጅማሬ፣ የሰውን ውድቀት፣ በእግዚአብሔር ስለተመረጡ ሰዎች ሲናገር፣ ዘሌዋውያን ደግሞ ሙሴ ሕጉን መቀበሉን፣ የማደሪያውን ድንኳን መሥራቱን፣ በዘኍልቁ ሕዝቡ ሰተዞ መዘጋጀቱን፣ ባለማመናቸውም ምክንያት ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባት መዘግየታቸውን በዘዳግም ደግሞ በቅርቡ በሚገቡበባት በተስፋይቱ ምድር ድንበር ላይ ሆነው የሙሴን ስንብት ስንመለከት ተከታታይነታቸውንና ፍጹም አንድነታቸውን እንረዳለን።



# ዘፍጥረት

## መግቢያ

ዘፍጥረት ከአምስቱ የሕግ መጻሕፍት የመጀመሪያው ሲሆን የስሙም ትርጓሜ በዕብራይስጥ በኩር፣ ቀዳሚ ወይም የመጀመሪያ የሚል ነው። የእግዚአብሔር ፈጣሪነትና እግዚአብሔር አልፋና ኦሜጋ ስለሆነ ጅማሬ እንደሌለው ሌሎች ነገሮች ግን ጅማሬአያቸውን በእርሱ እንዳገኙ ይተርካል። የሁሉን ነገር ማስትም የህያዋንን የፍጥረትን፣ የህዋን፣ ሕይወት ያለውን፣ የጋብቻን (የቤተሰብን) የትውልዶችን፣ የኃጢአትን፣ የመርገምን ጅማሬ ይዘግባል። እግዚአብሔር ሰውን ከውድቀት ለመቤዠት ያደረገውን የደህንነትን ታሪክ የሚተርክልን መጽሐፍ ነው። የግሪኩን ትርጉም ስንመለከት ጀነሲስ (Geneseos) ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን በሰብዓ ሊቃውንት ትርጓሜ ከእብራይስጡ ቃል የትውልድን/የፍጥረትን ጅማሬ የሚያሳይ ወይም ትውልድ (Toledot) ልደት ከሚለው የተወሰደ ነው። ቁልፍ ጥቅሱም «እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን ባደረገ ቀን በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው» የሚለው ነው (ዘፍጥ. 2፥4)። ከዚህ ቃል እንደምንረዳው የዘፍጥረት መጽሐፍ የትውልድ ዝርዝር የያዘ መሆኑን እንመለከታለን (ዘፍጥ. 2፥4፣ 5፥1፣ 6፥9፣ 10፥1፣ 11፥27፣ 25፥19፣ 36፥1፣ 37፥2)። ስለዚህም ከመጽሐፉ ይዘት እንደምናየው የሁለቱም የዕብራይስጡና የግሪኩ ትርጉም ለመጽሐፉ ርዕስ ተስማሚ መሆኑን ነው።

## ጸሐፊ

በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የሙሴን ስም ስለማናገኝና በዘዳግም 34 ስለሙሴ ሞት ስለሚናገር የፔንታቱክ ጸሐፊ ሙሴ አይደለም የሚሉ ክርክሮች ተነስተዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎችን ስናይ፣ ከታሪክና በዱሮ ዘመን ከነበሩ ዕብራውያን ክርስቲያኖች ዝንባሌ ስንረዳ ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነና በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንደጻፈው እንረዳለን። ሙሴ እንደሚለው ከሚቀርቡት መረጃዎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የዘፍጥረት መጽሐፍ ታሪክ ሙሴ ከመወለዱ ሦስት መቶ ዓመታት ያህል ቀደም ብሎ እንደተከናወነ ግልጽ ነው። ሆኖም ሙሴ ይህን መረጃ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ተገልጦለት ወይም በዚያን ዘመን በግብጽና በፍልስጤም ይገኙ ከነበሩት የፅሑፍ መረጃዎች እንደጻፈው ይገመታል (ኦሪ. 3፥7)። ሙሴ የጽሕፈትን ሥራ ይሠራ ነበር እናነባለን (ዘጸአ. 34፥27፣ ዘኍል. 17፥2፣ ዘዳግ. 6፥9፣ 24፥1፣ 3 ኢያ. 8፥32)።

ለ/ ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም አምስቱም መጻሕፍት ፔንታቱክ የሙሴ መጻሕፍት፣ የሕግ መጻሕፍት በመባል በአይሁድ ዘንድ መታወቃቸው ሙሴ እንደጻፈው የሚያስረግጥ ተጨማሪ መረጃ ነው።

ሐ/ የአምስቱም የሕግ መጻሕፍት ተመሳሳይነታቸውና አንድነታቸው ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነ ያሳዩናል። ለምሳሌ ያህል ዘጸአት ታሪኩን የሚጀምረው ከዘፍጥረት 50 በመቀጠል ነው። (ዘፍጥ. 50፥22፣ ዘጸአ. 1፥7)

መ/ ፔንታቱክን በራሱ ስንመለከተው ሙሴ እንደጻፈው የሚያስረዱ ጥቅሶች አሉ። (በጸአ. 17፥14፣ 24፥4፣ ዘኁል. 33፥1፣ 2)

ሠ/ የተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሙሴ እንደጻፈው ያስረዱናል። (ኢያ. 1፥7፣8፣ 8፥32፣ 34፣ 1ኛ ነገ. 13፥2)

ረ/ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስ ስለሙሴ የተናገረው አንዱ መረጃ ነው። ጌታም ራሱ ሙሴ እንደጻፈው ምስክርነት ተናግሯል (ሉቃ. 24፥27፣ ዮሐ. 7፥19፣ ማቴ. 19፥8፣ ማር.12፥26)።

ሰ/ በዓይን ምስክር የተጻፉ መሆናቸው (ዘጸአ. 15፥27፣ ዘኁል. 1፥31)

ሸ/ ስለ ግብጻውያን ስሞች፣ ቃሎችና የተንፀባረቀ ባህል (ዘፍጥ. 13፥10፣ 16፥1- 33፥18 (ዘፍጥ. 40፥9-11፣ 41፣ 43፣ 46፣ 50) መረጃዎች ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነ ያስረዳሉ።

## የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

ሙሴ በኖረበት 120 ዓመታት (በዳግ. 34፥7) የመጀመሪያዎቹ አርባ ዓመታት (1525-1485 ዓ.ዓ. በፈርኦን ቤት (የሐዋ. 7፥22)፣ የሚቀጥሉትን አርባ ዓመታት (1485-1445 ዓ.ዓ.) በምድያም በግ ጥበቃ (ዘጸአ. 2፥15) ተብሎ ተከፋፍሏል። የተሻለ ጊዜና ቦታ ተብሎ የሚታሰበው በበረሃ ጉዞ አያሉ በመጨረሻዎቹ የሕይወቱ አርባ ዓመታት ከ1445 ዓ.ዓ. በኋላ ነው።

## የመጽሐፉ ዓላማዎች

መጽሐፉ በመጀመሪያ የተጻፈው ለእስራኤላውያን እንደመሆኑ መጠን፦

- የእግዚአብሔርን የፍጥረት ሥራ ለመመዝገብ፣ ከግብጽ ከወጡ ኃይል፣ አምላክነቱን እንዲያውቁና ጣኦት ከሚያመልኩ አህዛብ ተለይተው እርሱን ብቻ እንዲያመልኩት፣ ለማሳየት ነበር።



- የፍጥረት ውበት እንዴት ባለመታዘዝ በመጣ ኃጢአት ምክንያት ሊበላሽ እንደቻለ ለማስገንዘብ ነው።

- እግዚአብሔር በኃጢአት የተበላሸውን ዓለም በአብርሃም ዘር እንዴት ለመባረክ እንደጀመረና የመሢሑ የመምጣቱ መነሰጥ የተገለጸበት መጽሐፍ ነው።

## የዘፍጥረት መጽሐፍ ባሕርይ

- የፍጥረትን ሁሉ ጅማሬ ዘግቧል።
- ለታሪክና ለሌሎች መንፈሳዊ ጽሑፎች መሠረት ነው።
- የዕብራውያንንም ሕዝብ ታሪክ ይናገራል። (ዘፍጥ. 12)

**በዘፍጥረት ሰባቱ ታላላቅ ሰዎችና መልእክቶቻቸው**

**አቤል** - መስዋዕት ለአምላኩ በማቅረቡ

**ሄኖክ** - አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ ሞትን ሳያይ ተወሰደ

**ኖኅ** - ኃጢአት በሞላበት ዘመን አምላኩን በመታዘዝ ስለጽድቅም ሰበከ

**አብርሃም** - አምላኩን አምኖ ተለይቶ ወጣ ስበረከትም ሆነ

**ይስሐቅ** - እግዚአብሔር የበረከት አምላክ መሆኑን ስለአስበ ምንጮችን በእምነት ቆፈረ

**ያዕቆብ** - የእግዚአብሔርን ክብር አየ

**ዮሴፍ** - ኃጢአትን የሚጠላ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው

## በዘፍጥረት ቁልፍ ቦታዎች

**የአራራት ተራራ** - (ዘፍጥ. 8፥4) እግዚአብሔር ዓለምን በጥፋት ውሃ ከቀጣ በኋላ መርከቢቱ ያረፈችበት ተራራ

**ባቢሎን** - (ዘፍጥ. 11፥8፣ 9) የሰዎችን ቋንቋ ጌታ የደበላለቀበት ሥፍራ

**የከለዳውያን ዑር** - (ዘፍጥ. 11፥28) አብርሃም በዚህ ሥፍራ ተወለደ

**ሀራን** - (ዘፍጥ. 11+31) ታራ፣ ሎጥ፣ አብርሃም፣ ሣራ፣ ወደ ከነዓን ለመሄድ ያረፉበት ቦታ

**ሴኬም** - (ዘፍጥ. 12÷1፣ 2፣ 6) አብራም ዑርን ትቶ የአሕዛብ አባት ሊሆን የሄደበት ቦታ

**ኬብሮን** - (ዘፍጥ. 13+18) አብራም ድንኳኑን ነቅሎ የተቀመጠበት ሥፍራ (ከሎጥ ተለይቶ) አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ኖረው የሞቱበት


**ቤርሳቤህ** - (ዘፍጥ. 21+31) በንጉሥ አቤሜሌክና በአብርሃም መካከል ምስክር እንዲሆን የተቆፈረ የውሃ ጉድጓድ:: የአብርሃም ቃልኪዳን ለይስሐቅ ያለፈበት ቦታ ነው (ዘፍጥ. 26+23-25)::

**ቤቴል** - (ዘፍጥ. 28+10-22) ጌታ ለያዕቆብ በሕልም ተገልጦ የአብርሃምንና የይስሐቅን ቃል ኪዳን ያስተላለፈበት ቦታ (35+1) እግዚአብሔር ተነስተህ በዚያ ሄደህ ኑር ብሎ ለያዕቆብ የተናገረበት ስፍራ::

**ግብጽ** - (ዘፍጥ. 46+34) ዮሴፍ ተሸጦ የግብጽን ሕዝብ ከረሀብ ያዳነበትና፣ መላ ቤተሰቡ ሄደው ያረፉበት ሥፍራ ነው::



## ሰዎች የትውልድ ሐረግ በዘፍጥረት



## የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

የዘፍጥረት መጽሐፍ ሌሎች መጻሕፍትን በግልጽ ለመረዳት የሚያስችል መሠረታዊ እውቀት የምናገኝበት መጽሐፍ ነው:: በተለይም የመጀመሪያዎቹ አስራ አንድ ምዕራፎች የተቀሩትን አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ስምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ለመረዳት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: የተለያዩ ጅማሬዎችን የምናገኘው በዚህ መጽሐፍ ላይ ስለሆነ ሁሉም ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የመጡ መገለጦች በዚህ መሠረት ላይ ተገንብተዋል:: ለምሳሌም ያህል በፍጥረት (አዳም) በውልደት (ቃየን) በሞት (አቤል) ሣይሞት በመወሰድ (ሄኖክ) የመጀመሪያዎቹ ሰዎችን ይዘግባል:: (ዘፍጥ. 1+26፤ 4+1፤ 4+8፤ 5+24):: የዓለም ሥልጣኔ ጅማሬ (ዘፍጥ. 4+17) የመጀመሪያው ጋብቻ (ዘፍጥ. 2+23-25) ስለ መሚሑ ቃል ኪዳን (ዘፍጥ. 3+15) እና የመሳሰሉትን ታላላቅ ጅምሮችም እናገኛለን::

## ዋና አሳቦች

- የሕያው እግዚአብሔርን መለኮትነት፤ በአምሳሉ ሰውን መፍጠሩ፤ የፍጥረት ሁሉ መልካምና ውብ ሆኖ መገኘቱ፤ ዓለምን የሚንከባከብና የሚቆጣጠር መሆኑ፤ ያለመታዘዝ ጠንቅ የኃጢአት ጅማሬ ፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ሕይወትን ውጤታማና የተሟላ እንደሚያደርግና ኃጢአተኛን የመቤዠት ተስፋ (ዘፍጥ. 3+15) እና ለእስራኤል በአብርሃም በኩል የተገባውን ቃል ኪዳን (ዘፍጥ. 12+1-3፤ 15+18-21) ያካትታሉ::

## ክርስቶስ በዘፍጥረት

ዘፍጥረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ መልእክት በመሆኑ በጥላነት ያሳየናል (ዘፍጥ. 1+1 ዮሐ. 1+1-59፤ ቆላ.1+13-20)::

**ለምሳሌ** - የሴቲቱ ዘር - ቅድመ ወንጌል (ዘፍጥ. 3+15)
የአቤል መስዋዕት (ዘፍጥ. 4+4)
የደህንነት መርከብ (ዘፍጥ. 7+1-7)
የይስሐቅ መስዋዕት የክርስቶስ ምሳሌ (ዘፍጥ. 22)

## የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

ዘፍጥረትን በተለያዩ አቅጣጫዎች በመከፋፈል ማጥናት ይቻላል::

| ሀ. በዋና ገጸ ባሕርያት ሲከፋፈል | ለ. በተለያዩ ክስተቶች ሲከፋፈል |
|---|---|
| ዘፍጥ. 1 እግዚአብሔር | ዘፍጥ. 1-2 ስነፍጥረት |
| ዘፍጥ. 2-5 አዳምና ሔዋን/ሰይጣን | ዘፍጥ. 3-5 ስለውድቀትና መቤዠት |



| | |
|---|---|
| ዘፍጥ. 6-10 ኖኅ | ዘፍጥ. 5-9 ስለጥፋት ውሃ |
| ዘፍጥ. 11-23 አብርሃም | ዘፍጥ. 24-27 ይስሐቅ |
| ዘፍጥ. 24-27 ይስሐቅ | ዘፍጥ. 10-11 የባቢሎን ግንብ |
| ዘፍጥ. 28-35 ያዕቆብ | ዘፍጥ. 12-38 የአብርሃም መጠራት |
| ዘፍጥ. 36 ዔሳው | ዘፍጥ. 39-50 ወደ ግብጽ መውረድ |
| ዘፍጥ. 37-50 ዮሴፍ | |

| ሐ. በቦታ ሲከፋፈል | ለ. በዘመን ሲከፋፈል |
|---|---|
| ዘፍጥ. 1 ሕዋው | ዘፍጥ. 1-11 ከአይሁድ አባቶች በፊት የነበረው ዘመን |
| ዘፍጥ. 2-3 ዔደን ገነት | 12-50 የአይሁድ የእምነት አባቶች ዘመን |

| | ሠ. በባሕል ሲከፋፈል |
|---|---|
| ዘፍጥ. 4-11 መካከለኛ ምሥራቅ (ሜሶፓታሚያን ሱምርያን) | ዘፍጥ. 1-38 የሜሶጳጣሚያ ባህል |
| ዘፍጥ. 12-28 ከነዓንና ግብጽ | ዘፍጥ. 39-50 የግብጽ ባህል |
| ዘፍጥ. 29-31 ሜሶጶጣሚያ | |
| ዘፍጥ. 32-38 ከነዓን | |
| ዘፍጥ. 39-50 ግብጽ | |

**የእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራ (ዘፍጥ. 1-2)**

1. ስነ ፍጥረት ዘፍጥ.1+3-19
2. ህያዋን ፍጥረታት 1+20-25
3. የሰው ልጅ (የፍጥረት ጉዥ) 1+26፤27

የእግዚአብሔር በስድስት የፍጥረት ቀናት አከናውኗል:: ከውስብስብ ጽንፈዓለም (complex universe)፤ ወደ ውሱን ሰው ከተለያዩ ፍጥረታት በኋላ የከበረውን ሰው ለአምሳሉ መፍጠሩን እናያለን:: እግዚአብሔር ዘላለማዊ፤ መለኮታዊ አምላክና የሁሉም ነገር ፈጣሪ፣ መሆኑን ፍጥረትን ከባዶ ነገር በዓላማና በዕቅድ መፍጠሩን እናያለን (ዘፍጥ. 1+1፤ ዕብ.1+1):: እግዚአብሔር ለፍጥረቱ መልክና ውበት የሰጣቸው የሁሉ በላይ ሆኖ የሚኖር ነገር ግን ከፍጥረቱ ሳይርቅ የሚንከባከባቸውና የሚጠብቃቸው አምላክ ነው (ዘፍጥ. 1+1-27፤ ዕብ.1+1-3):: እንዲሁም የዘፍጥረት መጽሐፍ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር ሰውን ከሌላው ፍጥረት ሁሉ በተለየ ሁኔታ እንዳበጀው፣ ከፍተኛ እውቀትንና ገዥነትን እንደሰጠው፣ በራሱ አምሳልም ካለው ነገር በመነሳት መፍጠርን እንደሰጠው እናያለን (ዘፍጥ. 2+4፤ ቆላ. 1+16 እና ዕብ. 1+2):: ከአምሳኩም ጋር ህብረት እንዲኖረው በኤድን ገነት ትዕዛዝን ሰጥቶ አኖረው (ዘፍጥ. 2+17):: ነገር ግን በዘፍጥረት 3+8 እንደምናየው ሰው በኃጢአት ምክንያት ራሱን ከአምሳኩ ለየ፤ ከሰውም ጋር ተለያየ ከአምሳኩ ጋር ያለው ህብረት ሲበላሽ ከሰውም ጋር ያለው ኅብረት ተበላሽቶአል (ዘፍጥ. 11+1፤ 3)::

ስለዚህም ይህን ኅብረት እንደገና ለማደስ ኃጢአት መወገድ ነበረበት የዘፍጥረት መጽሐፍ የሰውን ውድቀት የዘገበልን መጽሐፍ ነው። በተለያየ ሁኔታና ምክንያት ሰው ቢወድቅም እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱና በጸጋው ሰዎችን ከውድቀት ሲያነሳና ሲቤዥ ያሳየናል። ስለዚህም ጌታን በሕይወታችን የመጀመሪያ ሥፍራ ሰጥተን ስተፈጠርንበት ዓላማ እንደሚገባ መኖር እንድንችል የኃጢአትን፣ የአለመታዘዝን ውጤትና አዳኙ ጌታ ከውድቀት እንደሚያነሳ የሚያመለክተን ታላቅ መጽሐፍ ነው።

## የሰው ውድቀትና ውጤቱ (ዘፍጥ. 3-4)

አዳምና ሔዋን በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት መኖር ሲገባቸው ሰይጣን በአባብ ተመስሎ ባመጣው ፈተና በመሸነፍ ኃጢአት ሠሩ። (ዮሐ. 8፥44፣ ሮሜ 16፥20፣ 2ኛ ቆሮ. 11፥3፣ ራዕ. 2፥9 እና 20፥2) ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል እንደመሆኑ ነፃ ፈቃድ ያለው ንፁህ ህሊናና ልብ ትክክለኛውንም የማድረግ ኃይል የተሰጠው ከአምላኩ ጋር በእርሱ መገኘት ለመኖር እንዲችል ሆኖ ነው። ነገር ግን ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲጠራጠሩ ተፈታተናቸው። እጅ በመስጠትም ወደቁ በዚህም ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ። በኃጢአትም ምክንያት አዳምና ሔዋን እንዲሁም በሰው ዘር ሁሉ ጉዳት ደረሰ (ዘፍጥ. 3፥7-13፣ 16-21፣ ሮሜ 5፥12)። ከእግዚአብሔር ተለዩ፣ ምድር ተረገመች፣ ሀዘንና መለያየት በመካከላቸው ሆነ፣ ዐመፅ ወደ ልጆቻቸው ተላለፈ. ሰው ተስፋ ቢስ በሆነ ሁኔታ ቢቀመጥም እግዚአብሔር ግን ከፍቅር የተነሳ የሰውን ልጆች በምህረቱ አሰበ። የተቋረጠውንም ኅብረት ለመቀጠል ወደ ተሸሸጉበት መጣ።

ጻድቅ ፈራጅም ስለሆነ ለሁሉም ፍርድን ሰጠ (ዘፍጥ. 3፥8)። ምህረትንም በማወጅ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በእምነት የሚገኘውን ታላቅ መዳን ለሰው ልጆች አዘጋጀ (ዘፍጥ. 3፥15)። የሴቲቱ ዘር ከድንግል የሚወለደው ኢየሱስ የሰይጣንን ሥራ ሊያፈርስ እንደሚገለጥ በዚህ የውድቀት ሰዓት የመጨረሻ ድልን አወጀ (1ኛ ዮሐ. 3፥8)። የመሢሑ ቃል ኪዳንም በዘፍጥረት 12፥1-3፣ ላይ ጉልቶ ይታያል። የአዳም ልጆችም በእርሱ የውድቀት አምሳል ተወለዱ። ከውድቀት በኋላ ሰው ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ማቅረብን ጀመሩ (ዘፍጥ. 5፥3) አቤልና ቃየል መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ሲያቀርቡ፣ የአቤል መስዋዕት ተቀባይነትን ሲያገኝ የቃየል ተቀባይነት በማጣቱ ቃየን በብስጭትና በቅናት የመጀመሪያውን ግድያ በወንድሙ ላይ እንደፈጸመ እናያለን (ዕብ. 11፥4)።

## የጥፋት ውሃ (ዘፍጥ. 5-9)

በዘፍጥረት ምዕራፍ አምስት ላይ የምናገኘው የትውልድ ዝርዝር የአዳም ልጅ የሆነውን የሴትን ሐረግ ነው (ዘፍጥ. 5፥4)። እነዚህም የሴት ወገኖች እግዚአብሔርን የሚፈሩ ነበሩ። ለምሳሌ ያህል ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ ሞትን



ሳያይ ተወሰደ፣ ኖኅ ጥፋትና እርኩሰት በበዛበት ዘመን እግዚአብሔርን በመፍራት ኖረ፣ 120 ዓመት ምንም ደመናና ነፋስ ባይታይ እንኳን መርከብን ለመሥራት ታግሶ የጌታን ትዕዛዝ አከበረ። ይህም የሴት ትውልድ ክርስቶስ ሰው ከሆነበት ዘር የሆነ የተመረጡት የነገዶች አባት ነው (ዘፍጥ. 5፥32፣ 11፥10)። የሰው ልጆችም እየበዙ ሲሄዱ የእግዚአብሔር ልጆች ማለትም የሚያምኑት የሴት ትውልድ ከማያምኑት የቃየል ትውልድ ጋር ተጋቡ።

እነዚህም በዐመፅ እግዚአብሔርን በማሳዘን ሲበረቱ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ብዙ ጊዜ ዕድል ቢሰጣቸውም በማመጻቸው 120 ዓመት መርከቡ ተሰርቶ እስኪያልቅና ካለቀም በኋላ የ7 ቀናት ጊዜ ቢሰጣቸውም በንስሐ ለመመለስ አልወደዱም። ክፉው ነገር በዝቶ መልካሙን ሁሉ ከመዋጡ በፊት እግዚአብሔር ቁጣው እንደተገለጸ እናያለን (ዘፍጥ. 6፥7)። ኖኅ ከሚስቱና ከልጆቹ ሚስቶች ጋር እንዲሁም ከእንስሳት ዘር ከየወገኑ ወደመርከቡ የገቡት ሲተርፉ ሌሎቹ ግን በጥፋት ውሃ አለቁ። ወደፊትም በንስሐ ወደ እግዚአብሔር በማይመለሱት ላይ የእሳት ፍርድ እንደሚመጣ 2ኛ ጴጥሮስ 2፥3 ይናገራል። ይህም መርከብ የክርስቶስ ምሳሌ ከጥፋት ማምለጫ መሸሸጊያ ጥላ ነው። (ዕብ. 11፥7፣ 2ኛ ጴጥ. 2፥5) ኖኅም ከመርከብ ወጥቶ በአራራት ተራራ (ባሬ የሩሲያና የኢራቅ ድንበር) ካረፈ በኋላ ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ሠርቶ ጌታን አምልኮ ነበር (ዘፍጥ. 8፥20)። ጌታም በምህረቱ ብዛት እንደገና ቃልኪዳን በመግባቱ ባርካቸዋል (ዘፍጥ. 9፥1-7)። እነዚህም ከጥፋት የተረፉ የኖኅ ልጆች በምድር ላሉ ለሰው ልጆች የዘር ግንድ ሆኑ። የሴም ዘሮች (ሴማውያን፣) የካም ነገዶች (ከነአናውያን፣ አፍሪቃውያን ጥቁሮች) የያፌት ዘር (አውሮጳውያን) ናቸው። እግዚአብሔር ደግሞ ምድርን እንዳያጠፋ ኖኅ በእምነት ባቀረበው በሚቃጠል የመስዋዕት ደም ቃልኪዳን ገብቶ የቀስተ ደመና ምልክትን አደረገ (ዘፍጥ. 9፥8-17)።

## የባቢሎን ግንብ (ዘፍጥ. 10፣11)

በምዕራፍ አስር እና አስራ አንድ የሦስቱን የኖኅን ልጆች ትውልድ ያሳየናል (የሴም ዘፍጥ. 10፥21-32 የካም ዘፍጥ. 10፥6-20 የያፌት ዘፍጥ. 10፥2-5)። እግዚአብሔርም አስቀድሞ ለአዳም የሰጠውን ትዕዛዝ (ዘፍጥ. 1-28) ዳግም ለኖኅ (ዘፍጥ. 9፥1) ምድርን እንዲሞሉ አዘዘ። ሰዎች ግን የራሳቸውን ምኞት ለመፈጸም፣ ስማቸውን ለማስጠራት ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ሰርተው ለራሳቸው ከተማና ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ተባባሉ (ዘፍጥ. 11፥4)። ራሳቸውን ከፍ ከፍ ለማድረግ ተነሱ። የወደቁት መላእክትም ስህተት የዚሁ ዓይነት ነበር (ሉቃ. 10፥18፣ ኢሳ. 14፥12-14)። ይህም ውድቀትንና መለያየትን እንዳስተከለ እግዚአብሔርም እንዳይግባቡ ቋንቋቸውን ደበላልቆታል።

በመቀጠልም የእግዚአብሔር ሕዝብ አጀማመር (ዘፍጥ. 12-50)፣ የእስራኤል አባቶች ታሪክ ማለትም የአብርሃም፣ (ዘፍጥ. 12-38) የይስሐቅ፣ (ዘፍጥ. 21-24) የያዕቆብና

(ዘፍጥ. 25-49) የዮሴፍ (ዘፍጥ. 30፥24፤ 37-50) ደግሞ ቅደም ተከተላቸውን ይዘው ቀርዘዋል።

## የአብርሃም መጠራት (ዘፍጥ. 12-38)

እግዚአብሔር ለራሱ የለየውን ሕዝብ ሲጠራ ከሰው ዘር ሁሉ ወደመረጠው ወደ አብርሃም ቤተሰብ ትኩረት እንዳደረገ እናያለን። ምንም እንኳ ሰዎች ደካሞችና በየጊዜው የሚወድቁ ቢሆኑም እግዚአብሔር ጸጋውንና ምህረቱን ለማሳየት ሰዎችን መርጦ በእነርሱ መሥራት ፈለገ።

ይህም የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያስተላልፉ ለሌላው ትውልድ ምስክሮች እንዲሆኑ ነው። በእነርሱም በኩል የተመረጠው መሢሕ እንዲመጣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላቀደ አብርሃምን ከዑር ተለይቶ እርሱ ወደ ሚያሳየው መንገድ እንዲሄድ አዘዘው (ዘፍጥ. 2፥1-3፤ ዕብ. 11፥8-19) የእግዚአብሔር የተመረጠው የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ መጀመሪያ ይህ ነው። አብርሃምም በደረሰበት ሁሉ መሰዊያን አበጅቶ የሰማይና የምድርን አምላክ ያመልክ ነበር። እግዚአብሔርም ራሱን በፍቅሩ ይገልጥለት ነበር። በእግዚአብሔርና በአብርሃምም መካከል ልዩ ወዳጅነት ነበር። በዘፍጥረት 18 እና 19 እንደምናየው ሰለሰዶምና ገሞራ ሚስጥር እንደማለደም እናነባለን።

### የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለአብርሃም

1. ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ
2. እባርክሃለሁ
3. ስምህን ታላቅ አደርገዋለሁ
4. ለበረከትም ትሆናለህ
5. የሚባርኩህን እባርካለሁ የሚረግሙህንም እረግማለሁ
6. የምድርም ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ

እግዚአብሔር በዘፍ. 17፥1-27 ለአብርሃም ዳግም ቃልኪዳን ቢያደርግለትም፣ /በ99 ዓመቱ እንደፈጸመ እናያለን (ማቴ.1፥1፤ ከገላ. 6፥3-9) አብርሃም የተስፋውን ልጅ ካገኘ በኋላ እግዚአብሔር መልሶ እንዲሰጠው ሲጠይቀው በእምነት ታዘዘ (ዕብ.11፥19) አብርሃም ለይስሐቅ «የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ሲያረጋግጥለት እናያለን (22፥1-19)።

ያዕቆብ በተለያየ ችግር አልፎ ታላቅ ሰው ሆነ ስሙም እስራኤል ማለትም የእግዚአብሔር ልዑል ተባለ (ዘፍጥ. 32፥28)። ስለዚህም በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች በዚህ ስም እስራኤላውያን ተብለው ይጠራሉ። የያዕቆብም 12 ልጆች የእስራኤል ነገድ መሪዎች ይባላሉ (ዘፍጥ. 49)።

### ወደ ግብጽ መውረድ ዘፍ. 39-50

እግዚአብሔር በዘፍጥረት 15፥13 እና 14 ለአብርሃም እንደነገረው በያዕቆብ ልጆች የራሱን ሕዝብ ለማቋቋም ዮሴፍን ተጠቀመበት። በ17 ዓመቱ ባሪያ እንዲሆን



የተሸጠው ዮሴፍ በ30 ዓመቱ የግብጽ ገዥ ሆነ። ከአሥር ዓመት በኋላም ያዕቆብና ቤተሰቡ በአጠቃላይ ሰባ ሰዎች ሆነው በረሀቡ ምክንያት ወደ ግብጽ ወረዱ (ዘፍጥ. 50፥20) በጌሤምም እንዲኖሩ በፈርዖን ተፈቅዶላቸው ከብት በማርባት እየበዙ ኖረዋል፡

### እስራኤላውያን ወደ ግብፅ እንዲወርዱ የእግዚአብሔር ዓላማ፡-

1. እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን የከነዓንን ምድር ሕዝቡን አጥፍተው እንዲወርሱ አስቀድሞ ለአራት መቶ ዓመታት ወደ ግብፅ እንዲወርዱ አደረገ።
2. የእግዚአብሔር ሕዝብ በከነዓን ምድር ከአህዛብ ጋር ተደባልቀው እንዳይረከሱ ጣኦትን አምላኪ ከነበሩት ከአህዛብ ጋር በጋብቻ አስቀድመው መርከስ ጀምረው ስለነበር ጌታ ለያቸው (ዘፍጥ. 46፥10፤ 38፥2) ግብጻውያን ግን እረኛ ስለሚፀየፉ አይቀርቧቸውም ነበር (ዘፍጥ. 46፥3-5)።

## ማጠቃለያ

የዘፍጥረት መጽሐፍ እግዚአብሔር ዘላለማዊና ሕይወት ሰጪ መሆኑን ሁሉም ሰዎች አንድ አምላክ ፈጣሪ ያላቸውና በአምሳሉ የተፈጠሩ መሆናቸውን ያስታውሰናል። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ በኃጢአት ላይ መቆጣቱንና በምህረቱም ሰውን ከውድቀት ማንሳቱን ያስገነዝበናል።

የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን በማድረግ በመታዘዝ፣ በማመን፣ ስመደገፍና የተፈጠርንለትን ዓላማ በኑሮአችን እንዲያከናውን ማስተዋልን እንድናገኝ የሚረዳን ታላቅ መጽሐፍ ነው።

# ዘጸአት

ዘጸአት በግሪኩ «ኤክሶዶስ» ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን በእንግሊዝኛው «ኤክሶደስ» (Exodus) በግዕዙ መልቀቅ ወይም መውጣት ማለት ነው። (ሉቃ.9፥31፣ ዕብ. 11፥22) የዕብራይስጡን ትርጉም ስናይ ከዘጸአ. 1፥1፣ «እነዚህ ስሞች» በሚለው ላይ ያተኩራል። ልክ አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ቀጣይ ሆኖ እንደምናገኘው ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የገባውን ቃል ኪዳን ሲፈጽመውና እስራኤልን ነጻ ሲያወጣ ከዘፍጥረት የሚቀጥል ታሪክ ነው። ዘፍጥረት በተለያዩ ሁኔታዎችና ፈተና የሰውን ልጆች ውድቀት ሲያመለክት ዘጸአት ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን ነጻ በማውጣት፣ መታደጉንና ማዳኑን ያመለክተናል።

## ጸሐፊው

የዘጸአት ጸሐፊ ሙሴ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች አሉ (ዘጸአ. 17፥14፣ 24፥4፣ 34፥27)። ከብሉይ ኪዳን ኢያሱ 8፥31፣ ከአዲስ ኪዳን ማር.7፥10፣ 12፥26፣ ሉቃ፥22፣ 23 መረጃዎች ናቸው።

## የተጻፈበት ዘመን

በ1445 ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት አካባቢ እንደሆነ ይገመታል። ይህም ከሁለት መረጃዎች አንጻር ነው።

ሀ/ ያዕቆብና ቤተሰቡ ግብፅ የደረሱት 1875 ዓ.ዓ. ሲሆን በዚያ የቆዩበት ጊዜ 430 ዓመታት ነው። (ዘጸአ. 12፥40፣ ገላ. 3፥17) ከዚህ የሚቀረው ደግሞ (1875-430 = 1445) ይሆናል።

ለ/ የሰለሞን ቤተ መቅደስ የተጀመረበት ዓመት 965 ዓ.ዓ. ሲሆን ከዘጸአት እስከ ነገሥት ያሉት ዓመታት ሲቆጠሩ 480 ከግብፅ ከወጡ በድምሩ (965480) 1445 ዓ.ዓ. ይሆናል (1ኛ ነገ. 6፥1)

## ዓላማው

የእስራኤልን ከግብፅ ነጻ መውጣትና እንደ አንድ ነጻ መንግሥት ያለው ሕዝብ ሆነው ያደጉበትን ታሪክ ዘግቧል። በቁጥር ሰባ ሆነው ወደ ግብፅ የገቡት እስራኤላውያን ከ2-3 ሚሊዮን በሚገመት ቁጥር ጨምረዋል። በዚህ ምክንያት ጭቆናና ተጽዕኖ ስለበዛባቸው እግዚአብሔር በሙሴ መሪነት እስራኤላውያንን ከባርነት ነጻ እንዳወጣቸው ለማሳየት ነው።



## የሙሴ ታሪክ በሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል

**የመጀመሪያው አርባ ዓመት** - ይህ ዘመን ማንነቱንና ክብሩን ሲያስብ በግብፅ ራሱን ትልቅ አድርጐ የቆጠረበት ዘመን ነው።

**ሁለተኛው አርባ ዓመት** - በምድያም ምድረበዳ ማንም እንዳይደለ ተምሮበታል (ዕብ. 11፥23-29)

**ሦስተኛው አርባ ዓመት** - ጌታ በደካማው ሰው እንደሚጠቀም የተረዳበት ጊዜ ነው።

## የሙሴ ጥሪ

ሙሴ ጥሪው እንደደረሰው ለአገልግሎት ብቁ እንዳልሆነ ለእግዚአብሔር ምክንያቶችን ሲደረድርና ከእግዚአብሔርም የተሰጠውን መልስ ከቃሉ እናያለን።

| የሙሴ ምክንያት | የጌታ ምላሽ |
|---|---|
| **ችሎታ** የለኝም (ዘጸአ. 3፥11) | «እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ» (ዘጸ.4፥12)። |
| **መልዕክት** የለኝም (ዘጸአ. 3፥13) | «ያለና የሚኖር» ላከኝ (ዘጸ.3፥14)። |
| **ሥልጣን** የለኝም (ዘጸአ. 4፥1) | «በእጅህ ያለችው ምንድናት?» (ዘጸአ. 4፥1)። |
| **መናገር** አልችል (ዘጸአ. 4፥10) | .....«ሂድ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፤ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ» (ዘጸአ. 4፥12)። |
| **ሌሎችን** ተጠቀም (ዘጸአ. 4፥13) | «በትርህን በእጅህ ይዘህተ ሂድ» (ዘጸአ. 4፥17)። |

**ቁልፍ ቃል** - «የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፣... ሕዝቤን ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሀለሁ» (ዘጸአ. 3፥7-10)።

## ዋና ዋና መልእክቶች

የሕዝቡን ከባርነት ነጻ መውጣት ስለሚነግረን ዘጸአት የደህንነት መጽሐፍ ይባላል (ዘጸአ. 15፥13-16)። የመጽሐፉ ታላላቅ ርዕሶች ነጻ መውጣትና አምልኮ ናቸው።

**አምሳያ**

ሙሴ፡- የክርስቶስ ተምሳሌት ሲሆን (ዘዳግ. 18÷15) በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 720 ጊዜ ስሙ የተጠቀሰ የእግዚአብሔር ሰው ነው።

## አስተዋጽኦ

### I. በእግዚአብሔር ባሕርይና ከሰዎች ጋር ባለው ኅብረት፡-

1. የእግዚአብሔር ስምና ባህርይ ዘጸአ. 3፤13-15 «ያለና የሚኖር» ያህዌህ በሚለው ስሙና ክብሩ እንደተገለጸው የመገኘቱ እርግጠኝነት በዘጸአት 3፥6፣ 33፣ 34 ተገልጿል።

| | | |
|---|---|---|
| ትኩረቱም | ምህረቱ (ዘጸአ. 20÷6) | ታማኝነቱ (ዘጸአ. 2÷24-25፤ 3÷6) |
| | ጽድቁ (ዘጸአ. 3፤13-15) | ቅዱስነቱ (ዘጸአ. 3÷2-5) |
| | እውነተኝነቱ (ዘጸአ. 3÷5) | ለሰው ሕይወት አስፈላጊነቱን ለመግለጽ ነው (5÷1-18)። |

ስለዚህ ስሙን ማወቅ ጌትነቱንና ባህርይውን ማወቅ ነው። የታሪክ ባለቤት በቅድስና በክብር ተዓምራትን በማድረግ የሚመስለው የሌለ መሆኑን (ዘጸአ. 3÷13-15፣ 15÷11፣ 6÷3)።

2. ሰው ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ሊኖረው የሚገባው ኅብረት (ዘጸአ. 20-23)

ሀ/ የሕግ መሰጠት (ዘጸአ. 20÷1-17)

ለ/ የሥነ ምግባር መመሪያ (ዘጸአ. 20÷22-23÷33)

ሐ/ የእስራኤል መመረጥ (ዘጸአ. 19÷5-6)

3. የመገናኛ ድንኳን እግዚአብሔርን ለማክበርና ከእርሱ ጋር ለመኖር የጌታ በሕዝቡ መካከል መገኘት። (ዘጸአት 25-40)

### II. የዘጸአት አስተዋጽኦ በዋና ትምህርቶቹ

(1) እግዚአብሔር ሕዝቡን ከጭቆና ነጻ ለማውጣት ሙሴን አዘጋጀው (ዘጸአ. 1-4)



(2) ሙሴ ከግብፃውያንና ከፈርዖን ጋር ያደረገው ድርድርና መቅሰፍቶቹ (5-12)

የመስፈርቶቹ ዓላማ - ፈርዖንና ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ማንነት እንዲያውቁና የእስራኤል ሕዝብ የአምላኩን ሉዓላዊነት በመረዳት እንዲያመልከው ነው። መቅሰፍቶቹ ጌታ በግብፃውያን አማልክት ላይ አሸናፊ መሆኑን ያሳስያሉ።

**የተመታ አማልክት   የግብፅ አማልክት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ዘጸአ. 7÷20 | የወንዙ ውሃ ደም መሆን | የናይል ጣኦት | OSIRIS |
| ለ. ዘጸአ. 8÷6 | የጓጉንቸሮች ወረራ | የጓጉንቸሮች አምላክ | Hekt |
| ሐ. ዘጸአ. 8÷17 | በቅማል መወረስ | የመሬት አምላክ | Seb |
| መ. ዘጸአ. 8÷24 | የዝንብ መንጋ | የነፍሳት አምላክ | OSIRS Wife Hatkok |
| ሠ. ዘጸአ. 9÷6-7 | የከብቶች ሞት | የከርማ መስዋእት | Apis |
| ረ. ዘጸአ. 9-10 | በሰውና በእንስሳት ላይ ቁስል | የበሽታ መናፍስት | Typhon |
| ሰ. ዘጸአ. 9÷24 | ታላቅ በረዶ ከእሳት ጋር | የአየር አምላክ | Shu |
| ሸ. ዘጸአ. 10÷13 | አንበጣዎች | የአንበጣ ተከላካይ አምላክ | Scrapia |
| ቀ. ዘጸአ. 10÷22 | ጽኑ ጨለማ ለሦስት ቀናት | የፀሐይ አምላክ | Ra |
| በ. ዘጸአ. 12÷29 | የበኩር ሁሉ ሞት | የሁሉን ነገር አማልክት ለመምታት | |

(3) የእስራኤላውያን ጉዞ ወደሲና (12-15)

- ሙሴ የጌታ መልእክተኛ ሆኖ ከፈርዖን ጋር እየተመላለሰ የቆየበት ጊዜ አንድ ዓመት ያህል እንደሆነ ይገመታል። ይሁን እንጂ ፈርዖን ተሸንፎ ሲለቅ 600,000 ያህል እግረኛ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች ሲጨመሩ ከ2-3 ሚሊዮን የሚደርሱ እስራኤላውያንን እንደወጡ ይገመታል (ዘጸአ. 12÷37፣ 38)። እግዚአብሔር ሕዝቡን መርቶ ከፈርዖን ባርነት ነጻ አውጥቶአል።

<u>**ፋሲካ (ዘጸአ. 12)**</u> - ይህ ምዕራፍ የመጽሐፉ መካከለኛ ሥፍራ ሲሆን የክርስቶስ ኢየሱስ ሕዝቡን መቤዥቱን በአምሳያነት ያሳየናል። ከዚህም የተነሳ ፋሲካችን ክርስቶስ ስለእኛ መታረዱ ተገልጿል (1ኛ ቆሮ. 5÷7)። ሌላ መዳኛ መድኃኒት ስለሌለ ደሙን በጉበናቸው ላይ የቀቡ የዕብራውያን ሰዎች ብቻ ሲድኑ ሌሎች ግን በበኩር ሞት እንደተቀጡ እናያለን (ዘጸአ. 12÷12-13)።

የመቅሰፍቱ ውጤት እጅግ አስቃቂ ስለነበር በፍጥነት እስራኤላውያን እንዲወጡ ተለምነው ይወጣሉ:: እግዚአብሔር በቀን የደመና አምድ በሌሊት የእሳት አምድ እየሆነ ለጥበቃና ለችግር ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመንገዳቸው ምሪትንና የሚያስፈልጋቸውንም ሁሉ በመስጠት ይመራቸው ነበር::

በዘጸአት 12 እንደምናነበው የፋሲካው መስኮታዊ ሥርዓት ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የሚሰጠን መልዕክት ይህን ይመስላል::

ሀ/ ነውር የሌለውን ጠቦት አረዱ (በዘጸ. 12፥3-6፣ 13):: ነገር ግን ነውር የሌለው መሆኑ ብቻ አያድናቸውም ከሞት መልአክ ለመሰወር/ለመዳን መቃኑንና ጉበኑን መቀባት ነበረባቸው:: ነውር የሌለበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ በመስቀል መሞቱን እምነን መቀበል ለደህንነታችን ያስፈልገናል:: (ዕብ. 1፥15፣ 28 ኢሳ. 53፣ ዮሐ. 19፥14-16፣ 1ኛ ቆሮ.5፥7)::

ለ/ ደሙን መርጨት (12፥7፣ 12፥21-22) በጉን ማረድ ብቻ ሳይሆን ከበራቸው ውስጥ ሆነው የታረደውን በግ ምልክት በመርጨት የሞት መልአክ እንዲያልፍ ማድረግ ነበረባቸው::

4. የመተዳደሪያ ሕግና መመሪያ በሲና ተራራ መስጠቱ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን በታላቅ ድል ካወጣቸው በኋላ በምሥጋና ተሞልተው ለሦስት ቀን ወደ ሲና ምድረበዳ ተጓዙ (ዘጸአ. 15):: መራራውም ውሀ ወደ ጣፋጭነት ተለወጠ (ዘጸ. 15-25) ጌታ በተለያየ ተዓምራት እየመራቸው በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ወደ ሲና ተራራ ደረሱ (ዘጸአ. 19፥1-3) በዚያም ለአንድ ዓመት ጊዜ ቆይተው ከእግዚአብሔር ሕግን፣ የአኗኗር ሥርዓትን፣ የክህነት ሥርዓትን፣ የመባና የአሥራት ሕግጋትና በዓላት ተደነገጉ:: እግዚአብሔርም ከህዝቡ ጋር የሚያድርበት ወይም የሚኖርበት ማምለኪያ ሥፍራ ተሠራ::

የሕጉ መስጠት (20-24)

የተሰጠው ሕግ ለሕዝቡ ስርዓትን የሚያስይዝ፣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረው ግንኙነትና (20፥1-4) የሰው ከሰው ጋር የሚኖረው ኅብረት (20፥5-10) ምን መሆን እንደሚገባው የሚያሳይ ነው:: ነገር ግን ሕግን በመጠበቅ ማንም ፍጹም አልሆነም:: ሕጉ የእግዚአብሔርን ቅድስና አይቶ ሰው የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደሚያስፈልገው እንዲያውቅ የሚረዳ ነው (ሮሜ 3፥10-31፣ ገላ.3፥15-18፣ መዝ.18፥7-11፣ ዕብ.9፥13-15፣ ገላ.4፥4-5፣ ሮሜ 8፥1-4)::

ሕጉቹ ሦስት ዓይነት ናቸው::

ሀ/ የስነ ምግባር ሕግ (ዘጸአ. 20፥3-17፣ 1ኛ ቆሮ. 10፥4)::



የስነ ምግባር ሕግጋት ዓላማ ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን የሚለዩበት አሥርቱ ትዕዛዛት፣ ከጌታ የሆነውን መገሰጥ በመገንዘብ እውነተኛውን አምላክ ብቻ በመረዳት ማምለክና መታዘዝ እንዲችሉ ነው::

ለ/ የሕዝቡ መተዳደሪያ ደንብ (ዘጸአ. 21፥1-23)

ይህ ክፍል የእስራኤልን የአመጋገብ፣ የመሬት አጠባበቅ፣ የቀረጥ፣ የውትድርና አገልግሎት የጋብቻ፣ የመውረስ፣ የፍቺና ሌሎችም መተዳደሪያዎችን ያጠቃልላል::

ሐ/ የአምልኮ ሕግ ወይም የሃይማኖት ሥርዓት - ይህ ክፍል የክርስቶስን አዳኝነት በጥላነት የሚያመለክቱ እንደመገናኛው ድንኳን፣ ክህነቱን፣ ሰባቱን የሌዋውያን በዓላትን፣ አምስቱን የሌዋውያን መስዋእትና የመሳሰሉት ስርዓቶች ናቸው (ዘጸአ. 35-40፣ ዘሌዋውያን፣ ማቴ. 5፥17፣ 18 ሮሜ 10፥4፣ 1ኛ ቆሮ. 5፥7)::

ጌታ እነዚህን ሕጉች በመስጠት ከአካባቢያቸው ጣዖት አምላኪ ሕዝብ የሚለያቸውንና ለራሱ የሚቀድሳቸውን መተዳደሪያ ሰጣቸው:: የሥነ ምግባር ሕጉች ቋሚ ሲሆኑ አብዛኞቹ የመተዳደሪያና የአምልኮ ሕጉች ግን ጊዜያዊ ነበሩ (ዘሌዋ. 17፣ ዘዳግ. 12፥20-24):: ሰው በራሱ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይፈልጋል:: ነገር ግን አይችልም ምክንያቱም ከሕግ አንዱቱን ያፈረሰ ሁሉንም አፍርሷልና::


4. **የመገናኛው ድንኳን** (ዘዳግ. 25-40) - እግዚአብሔር ለሙሴ አንድ ቅዱስ ማደሪያ ሥፍራ እንደሚፈልግ ነገረው:: ባስልኤልና ኤልያብ በእግዚአብሔር መንፈስ ጥበብና ብልሀት ተሞልተው መገናኛ ድንኳኑን ሲሠሩ (ዘጸአ. 31፥1-10) ሕዝቡም በፈቃዱ ስጦታን ሲሰጡ ጠሰኑ (ዘጸአ. 31፣ 35፣ 36)::

የመገናኛው ድንኩን አሠራር:-

ሀ/ አደባባዩ

የመገናኛው ድንኳን የሚያርፍበት ክልል የውጪ አደባባይ ይባላል:: ርዝመታቸው 13.7 ሜትር በሆኑ መጋረጃዎች ይሸፈናል:: መጋረጃዎቹም በነሐስ አምዶች የሚሰቀሉ ሲሆን አንዱ ከሌላው በ2.3 ሜትር ይራራቃል:: መግቢያው በር በስተምሥራቅ አንድ ብቻ ሆኖ 9 ሜትር ያህል ስፋት ነበረው::

# የመገናኛው ድንኳን




ሀ - አደባባይ
  I. መሠዊያ
  II. የመታጠቢያ ሳህን

ሰ- የመገናኛው ድንኳን

ሐ- ቅድስት ሥፍራ
  III. ገበታ
  IV. የወርቅ መቅረዝ
  V. የዕጣን መሠዊያ

መ- ቅድስተ ቅዱሳን
  VI. የቃልኪዳኑ ታቦት

**የመጽሐፉ አስተዋጽኦ**

1. መለኮታዊ መቤዥት /1-18/
2. ቃልኪዳን በሲና /19-24/
3. አምልኮ /25-40/



**I. መሠዊያ**

ይህ አንድ እስራኤላዊ ወደ አደባባዩ ከገባ በኋላ መስዋእት የሚያቀርብበት ገላጣ ሥፍራ ላይ ይገኛል። ከነሐስ የተሸፈነ ሆኖ እንደሌሎቹ የመገናኛ ድንኳን ዕቃዎች ሁሉ ተንቀሳቃሽና አገልግሎቱም መስዋእቶችን በማቅረብ የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት ነበር (ዘጸአ. 27+1-8፣ 38+1-7)።

**II. የመታጠቢያ ሳህን**

ከነሐስ የተሠራና ካህናቱ ወደ ቅድስት ከመግባታቸው በፊት ለመንጻት የሚታጠቡበት ሥፍራ ነው (ዘጸ. 30+18፣ 38+8፣ 40+30)።

**ሰ/ የመገናኛው ድንኳን**

በአደባባዩ በስተምዕራብ ይገኛል፣ ቁመቱ 13.7 ሜትር ሲሆን ስፋቱ 4.6 ሜትር ነው፣ ቅድስት ሥፍራና ቅድስተ ቅዱሳን በመባል በሁለት ይከፈላል።

**ሐ/ ቅድስት ሥፍራ**

በዚህ ሥፍራ ሦስት በወርቅ የተለበጡ ዕቃዎች ይገኛሉ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

**III.** ገበታው ይህ በቅድስት ሥፍራው ውስጥ በሰተሰሜን ይቀመጣል፣ (ዘጸአ. 25+25-30)። እርሾ የሌለባቸው ካህናቱ የሚበሏቸውን 12ቱን የእስራኤል ነገድ ቁጥር የሚወክሉ ቂጣዎች ይዟል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሕይወቱ ምግብ ያስፈልገዋል።

**IV. የወርቅ መቅረዝ**

ይህ የወርቅ መቅረዝ ሰባት ራስ አለው (ዘጸአ. 25+31-40)። ሌሊቱንም በሙሉ ያበራል፣ የሚገኘውም በስተደቡብ ነው። ወደዚህ ሥፍራ የሚገቡት ካህናት ብቻ ናቸው።

**V. የእጣን መሰዊያ** ይህ ቅድስትንና ቅድስተ ቅዱሳኑን በሚከፍለው መጋረጃ ፊት ለፊት ይገኛል (ዘጸ. 30+1-10)። ካህናቱም ሁልጊዜ ያጥኑበታል።

**መ. ቅድስተ ቅዱሳን**

ይህ 4.6x4.6 ሜትር ስፋት ገደማ ክፍል ነው። በቅድስትና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መጋረጃ አለ። ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ የሚገባው በዓመት አንድ ጊዜ

የማስተሰርያ በዓል ዕለት ሊቀካህኑ ብቻ ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን ክርስቶስ ሊቀካህናችን ብቻ ሳይሆን ኃጢአታችንንም ያስተሰረየልን ስለሆነ መስዋዕት በማንኛውም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት አለን።

## IV. የቃል ኪዳኑ ታቦት

በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የቃልኪዳኑ ታቦት ይገኛል (ዕብ. 7፥23-25)። በክርስቶስ በኩል ወደ መሰዊያው ሥፍራ የመግባት እድል እንዳገኘን ቃሉ ይመሰክራል (ዕብ.10፥11-23 ዘጸአ. 25፥8)። ታቦቱ በብሩህ አስደናቂ ደመና የተሸፈነው እግዚአብሔር በክብር በሕዝቡ መሃከል መገኘቱን ያመለክታል (1ኛ ዮሐ. 2፥2)።

የታቦቱ ሽፋን የስርየት መክደኛ ተብሎ ይጠራል (ዘጸ. 25፥10-22፣ 37፥1-9) በማስተሰርያውም ቀን ሊቀካህኑ ስለእስራኤል ሕዝብ ኃጢአት በዚያ ደም ይረጭ ነበር (ዘጸአ. 25፥22 ዘኁል. 7፥8-9)። የሥርየት መክደኛው ከንፁህ ወርቅ ይሠራል። ሁለት መላእክቶች (ኪሩብ) በስርየቱ መክደኛ ጠርዞች ላይ ፊታቸውን እንዱ ወደሌላው መልሰው ክንፉቻውን በስርየት መክደኛው ላይ ይዘረጋሉ። ሁለቱም መላእክት ጉንበስ ብለው የስርየት መክደኛውን ያመለክታሉ። በዚህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ክብር ያድር ነበር። የእግዚአብሔር ክብር ሲነሳም እርሱን በመከተል ሕዝቡ ይጓዙ ነበር።

በምህረቱና በቸርነቱ ፊቃዱን ለሕዝቡ በመግለጽ ይመራቸዋል። በዚህ ክዳን ያለው ሣጥን በሚመስል ታቦት ውስጥ ሙሴ እንዲያስቀምጥ የተነገሩት ነገሮች አሥርቱ ትዕዛዛት ያሉበት የድንጋይ ጽላት ናቸው (ዘጸአ. 16፥21፣ ዕብ. 9፥4)። መና ያለበት የወርቅ መሶብ (ዘጸ. 16፥33፣ ዕብ. 9፥4) የበቀለች የአሮን በትር (ዘኁል. 17፥10፣ ዕብ. 9፥4)።

| ሌዋዊ ሊቀ ካህን | ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ |
|---|---|
| ወደ ምድራዊው መገናኛ ድንኳን ይገባ ነበር | ወደ ሰማይ ገባ (ዕብ. 9፥12) |
| በዓመት አንድ ጊዜ ይገባ ነበር | አንድ ጊዜ ፈጽሞ ገባ (ዕብ. 9፥12) |
| ከመጋረጃው ጀርባ ይቆም ነበር | መጋረጃውን አስወገደ (ዕብ. 10፥20 ማቴ. 27፥51) |
| ለራሱ የኃጢአት መስዋዕት አቀረበ | ስለእኛ ኃጢአት ብቻ መስዋእት አቀረበ (ዕብ. 10፥11፣ 12፣ ዮሐ. 3፥16) |
| የኮርማና የፍየል መስዋዕት አቀረበ | የገዛ ደሙን መስዋእት አቀረበ |

በተጨማሪም የዘጸአት መጽሐፍ ስለክህነት አኗኗር፣ አገልግሎትና አለባበስ ያስተምራል (ዘጸአ. 28፣ 29) ካህኑ ስለሕዝቡና ስለራሱ በእግዚአብሔር ፊት መስዋዕት ለማቅረብ የደም መስዋዕት ይዞ ለይቅርታ ለመማለድ ወደ ቅድስተ



ቅዱሳኑ ይገባል (ዕብ. 5፥6፣ 8፥1-7፣ 9፥12፣ 1ኛ ጢሞ. 2፥5)። ካህናቱም እንዲለብሱ የታዘዙት ልዩ ልብስ ነበራቸው (ዘጸአ. 28፥40-43፣ 39፥27-29)። በአባቶች (በአብርሃም) ዘመን አንድ ካህን መልከጼዴቅ ብቻ ተጠቅሶ እናያለን (ዘፍጥ. 14፥18)። ሊቀ ካህኑ አሮንም የተለየ ልብስ ነበረው (ዘጸአ. 28፥4-39)።

# ዘሌዋውያን

የዚህ መጽሐፍ ታሪክ ከዘጸአት የሚቀጥል ሲሆን ነጻ የወጣውና አምላኩም ቃል ኪዳን የገባለት ሕዝብ በሥርዓት ቅዱሱን ጌታ በማምለክ ሕይወቱን መምራት እንዳለበት ያስተምር (ዘጸአ. 40፥26-33፤ ዘሌዋ. 1፥1-2)።

መጽሐፉ በአብዛኛው ጌታ ለራሱ ጠርቶ የለየውን የሌዋውያንን ክህነታዊ አገልግሎት መመሪያና ሕግ የሰጠበት ስለሆነ የመጽሐፉ ርዕስ ዘሌዋውያን ተሰኗል። ትኩረት የሚሰጠውም እግዚአብሔር ወደ ቅድስናው መጥራቱን ነው (ዘሌዋ. 11፥45)። መጽሐፉ ከሌዊ ወገን ለሆኑ ካህናት የአገልግሎት መመሪያ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ሕጉቹ ለሁሉም እስራኤላውያን ናቸው።

### ጸሐፊው

እግዚአብሔር እነዚህን ቃሎች ለሙሴ እንደተናገራቸው በዚሁ መጽሐፍ ብቻ 56 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ሙሴ እንደጻፈው ተናግሯል (ዘጸ. 14፥1፤ 6፥1፤ 8፥1፤ 11፥1፤ 12፥1፤ ማር. 1፥44፤ ዘሌዋ. 13፥49)።

### ቁልፍ ቃላት

- የዘሌዋውያን መጽሐፍ ዋነኛ ቁልፍ ቃል ቅድስና ነው። (ዘሌዋ. 19፥2፤ 11፥44-45፤ 7፥26) **«እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ።»** ይህም ቃል ከሌሎች መጽሐፎች ይልቅ ተደጋግሞ ለ152 ጊዜ ተጠቅሷል። ሌሎች ተጨማሪ ቁልፍ ቃሎችም «መስዋእት» 42 ጊዜ ያህል፤ «ካህን» 189 ጊዜ፤ «ደም» የሚለውን 86 ጊዜ፤ «ማስተሰረይ» 45 ጊዜና በአጠቃላይ ከዘሌዋውያን መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን 90 ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን።

### የመጽሐፉ ዓላማ

የተጻፈበት ምክንያት፤ ሥነ ሥርዓትንና እውነተኛ አምልኮን ለማስተማር ነውና በእግዚአብሔር ቤት ሥርዓት እንደሚያስፈልግ ይገልጻል።

### የተጻፈበት ዘመን

የተጻፈውም ከግብጽ ከወጡ ከተወሰነ ወራት በኋላ በሲና ተራራ የአንድ ዓመት ቆይታ ጊዜ ነው። መጽሐፉ በአብዛኛው ሕግና ደንብን ከታሪክና ምሳሌዎች ጋር ያሳየናል ይህም ሁለት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል ከእግዚአብሔር ጋር የጠራ ግንኙነትን ስለማግኘትና በመስዋእትና በመንጻት ሕግ፤ ማድረግ በሚገባቸው ላይ ሲያተኩር የመጨረሻው ክፍል ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በመኖር ላይ ያተኩራል። የእግዚአብሔር ሰዎች እንዴት ማምለክ እንደሚገባቸውና ከሌሎች ጋር



ማኅበራዊ ኑሮን በተመለከተ የሚተዳደሩበት ደንብ ነው። (ዘሌ. 19፥18፤ ማቴ. 22፥39፤ ማር. 12፥31፤ ሉቃ. 10፥27)። እነዚህን ሕጉች እግዚአብሔር ለእስራኤል ሲሰጥ ሁልጊዜ የሚከናወኑትን፤ ወቅታዊ ግብረገባዊና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የተሰጡ ቢሆኑም ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ ዓላማው ለመታዘዝ ለማድረግና ለመኖር መመሪያን መስጠት ነው።

በአዲስ ኪዳን የመንጻት መስዋእት ማቅረብ የማያስፈልገን ፍጹም የሆነው መስዋእት ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም መንጻትን ስላመጣልን ነው። እነዚህ ሥርዓቶች ግን የክርስቶስ ሞት እንዴት ከኃጢአታችን እንዳነጻን ለመረዳት ያስፈልጉናል።

### የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

I. እምስቱ መስዋእቶች (ም. 1-7)
II. የአሮንና የልጆቹ ሲቀክህነት (ም. 3-10)
III. የመቀደስና የመንጻት ሕጉችና ደንቦች (ም. 11-15፤ 17-22)
IV. የሥርየት ቀን (ም. 16)
V. የዳነው ሕዝብ የሕይወት መመሪያ (ም. 18-20)
VI. የክህነት ደንቦችና የተለያዩ የአይሁድ በዓላት (ም. 21-23)
VII. ተጨማሪ ሕጉች ተስፋዎችና ማስጠንቀቂያዎች (ም. 24-27)

### የመስዋእት ዓይነቶች (ዘሌዋ. 1-7)

- እነዚህ መስዋእቶች ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ የሚያስችሉ ለማመስገን፤ ለጸሎት፤ የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት የሚቀርቡ መስዋእቶች ናቸው።

1. <u>የሚቃጠል መስዋእት (ም. 1)</u> - ተባዕት ሆኖ ነውር የሌለበት እንስሳ፤ እንደሚያቀርበው ሰው አቅም ለእግዚአብሔር በውዴታ/በፍቅር የሚቀርብ ነው። ዓላማውም ጌታን ለማክበር ከአጠቃላይ ኃጢአት ለመንጻትና ራስን ለእግዚአብሔር የማቅረብ ምልክት ነበር። የእንስሳው ሁሉም ክፍል ይቃጠላል። (ዘሌ. 1፥3-17፥5፤ 7፤ 6፥9-13፤ ከዕብ. 10፥1-3፤ 10፤ 11)።

2. <u>የእህል ቁርባን መስዋእት (ም. 2)</u> - እግዚአብሔርን ለማመስገን በፈቃደኝነት የሚቀርብ ስጦታን ሁሉ ያጠቃልላል። ለምሳሌም እርሾ የሌለበት ቂጣ፤ ጨው ያለበት ዳቦ ወዘተ. የበኩራትን ፍሬ ለእግዚአብሔር በመስጠት ሕይወታቸውን ለጌታ ለማስገዛትና አክብሮትን ለመስጠት ክፊሉ ሲቃጠል ከፊሉን ካህናት ይበሉታል (ዘሌዋ. 2፥1-16፤ 6፥14-23)።

ይህ መስዋእት ብቻውን ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲያገኝ ከሌሎች የኃጢአት ማስተሰሪያ መስዋእቶች ጋር የሚቀርብ ስጦታ ነው።

3. <u>የደህንነት (የሰላም) መስዋእት (ም. 3)</u> - በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ኅብረትን ለመጠበቅ ሲሆን ከችግር ስለመዳን፣ ስለመሐላ፣ ስዕለትና በረከት ምሥጋና ለማቅረብ በበጐ ፈቃድ የሚቀርብ ነው። እንደእቅም ተባዕት ወይም እንስት እንስሳ መስዋእት ቀርበው፣ ስቡ ተቃጥሎ ሌላው በኅብረት ይበላል (ዘሌዋ. 19፥5-8፤ 22፥21-25)።

4. <u>የኃጢአት መሥዋእት (ም. 4)</u> - የኃጢአት ይቅርታን ከእግዚአብሔር ለማግኘት ነው። (ዘሌ. 4፥1-35፤ 6፥24-30)። ይህ መስዋእት በሊቀ ካህኑ ብቻ በዓመት አንድ ጊዜ ይቀርባል።

5. <u>የበደል መስዋእት (ም. 5-7)</u> - ሰውን ወይም እግዚአብሔርን በመበደል ለተፈጸመ ስህተት ማስወገጃ የሚቀርብ፣ የተበደለው ሰው ካሣ ይሰጠዋል። ለእግዚአብሔር ነውር የሌለበት አውራ በግ መስዋእት ይቀርባል። ስቡ ይቃጠልና የቀረውን ካህናት ይበሉታል (ዘሌዋ. 5፥14-6፤ 7፥1-7)።

<u>ክህነትና የክህነት ሥርዓቶች (8-22)</u>

የክህነትን አገልግሎትና ያሳቸውን የሥራ ድርሻ ያመለክታል። ካህናት ራሳቸውንና ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር በንስሐ ለማምጣት የሚያቀርቡ መካከለኛ ሆነው እንዲቀርቡ እግዚአብሔር አሮንና ልጆቹን እንዴት በመቅደሱ ውስጥ እንደሚያገለግሉ ምሪትን ሰጥቷል።

ይህም ታላቁ ካህናችን ክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም እምላክና ፍጹም ሰው ኃጢአት የሌለበት መካከለኛ ሆኖ ወደ ሰማያት በራሱ ደም የገባውን ርህሩህና ንፁህ ጌታ የራሱን ደም በማቅረብ ለሰው ዘር በሙሉ አንድ ጊዜ ለዘላለም መስዋእት መሆኑን ያመለክተናል። በእርሱም ተቀድሰን ከአምላካችን ጋር በመጽናት እንድንመላለስ ያስተምረናል (ዕብ. 9፥24፤ 25 ዮሐ. 3፥16፤ ዘሌ. 18፥30፤ 19፥2፤ 18፤ 30፤ 34፤ 20፥26፤ 21፥1-4)።

<u>የእስራኤላውያን ታላላቅ በዓላት (ዘሌዋ. 23፥6-25)</u>

የበዓላት ዓላማ እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው። በእነዚህ የተለያዩ በዓላትና ወቅቶች እስራኤላውያን በተደጋጋሚ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ እንደሆኑ ይነገራቸው ነበር። ከኃጢአት በመለየት፣ በፍጹም መስጠት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ፣ ውለታውን በመቁጠር ማምለክና ምስጋና ማቅረብ የሁልጊዜ ተግባራቸው እንዲሆን ይጠበቅባቸዋል።

1. የሰንበት በዓል - (ዘሌዋ. 23፥1-3) በማረፍና ከሥራቸው በመለየት የእግዚአብሔርን የፍጥረት ሥራ እንዲያስታውሱና ከግብጽ ባርነት ነፃ መውጣታቸውን እንዲያስቡ ነው (ዘዳ. 5፥12-15ን ከማር. 2፥27-28)።



2. የፋሲካና የቂጣ በዓል

(ዘሌዋ. 23፥4-8) ከግብጽ የወጡበትን ቀን ምክንያት በማድረግ እያንዳንዱን ለማስታወስ በየዓመቱ በአንደኛው ወር በ14ኛው ቀን የሚከበር የመቤዠታቸው በዓል የፋሲካ በዓል ነው። ክርስቶስ በእኛ ምትክ መሞቱን ያስተምረናል።

3. የመከር በኩራት በዓል (ዘሌዋ. 23፥9-14፤ ዘኁል. 28፤ በጸ.23) በመከር ወቅት መከሩን በሙሉ ያጭዳሉ እስቀድመው የመጀመሪያውን ነዶ ለጌታ ከፍ አድርገው በመያዝ ይወዘውዛሉ። በኩሩን ለጌታ የመስጠት በዓል ነው።

4. የጴንጠቆስጤ (የመከር) ወይም የቂጣ መወዝወዝ በዓል (ም. 23፥15-22) ይህ በዓል ሁለት ቂጣዎች ለእግዚአብሔር የሚቀርቡበት በዓል ነው። ከፋሲካ በኋላ በ50 ቀን ይከበር ነበር።

5. አዲስ ጨረቃና የመለከት ድምጽ በዓል (ዘሌዋ. 23፥23-25) ይህም በመጨረሻ ዘመን እስራኤል መንግሥቷን እንደምታቋቁም የሚገልጽ ትንቢት ነበር (ኢሳ. 18፥3፤ 7፤ ኢዩ. 2፥15-32)። በእያንዳንዱ ወር መጀመሪያ መለከት በመንፋት ሲያውጁ የ7ኛው ወር መጀመሪያ ቀን የመለከት በዓል ይባላል።

6. የማስተሰርያው ቀን በዓል - (ዘሌዋ. 3፥26-32) ይህ በዓል የመለከት ድምጽ መታሰቢያ በዋለ በ10ኛው ቀን ይውላል። ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ቀን የደም መስዋእት ይዞ ወደቅድስተ ቅዱሳኑ የሚገባበት ቀን ነው። በዚህ በዓል እስራኤላውያን ሁሉ ተጸጽተው ያለቅሱ ነበር። ይህ በዓል እሳባቸውን ሥራቸውን ትተው በንስሀ የሚውሉበት ቀን ነው። ያለዚያ ግን በሞት ፍርድ ይቀጣሉ።

7. የማደሪያው ድንኳን በዓል - (ዘሌዋ. 23፥33-34) ከግብጽ ባርነት ወጥተው ወደከነዓን ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባታቸውን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በመሆን መምራቱን ያሳስባቸዋል (ዘዳግ. 31፥9-13)።

8. የሰባተኛው ዓመት በዓል (ዘሌዋ. 25፥1-7፤ 18-22) ስድስት ዓመት ከዘሩ በኋላ ሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን የሚያሳርፉበትና እነርሱም የማይሠሩበት ድሆችንም የሚያስቡበት አገልጋዮች ሁሉ በፀጥታ የሚያርፉበት ዓመት ነው።

9. የኢዮቤልዩ (50ኛ ዓመት በዓል) - (ዘሌዋ. 25፥8-21) እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠው ልዩ የነጻነት ዓመት በየ50 ዓመቱ የሚከበር ባሪያዎቻቸው ነጻ የሚያወጡበት ከ7 ጊዜ 7 ዓመት በኋላ ወደየቤተሰቡ ርስት የሚመለሱበት በዓል ነው። ይህም የእነርሱን የባርነት ዘመን የሚያስታውሳቸውና ነጻ ሳወጣቸው ጌታ እንዲኖሩ የሚያስተምራቸው ነው።

በሲና ተራራ የተሰጡአቸው ሕጐች ሥርዓቶች ደንቦችና በዓላት የእስራኤልን ሕዝብ ከሌሎች ጣዖት አምላኪዎች የተለየ ያደርጋቸዋል። ይህም ከእግዚአብሔር

ሃሣብ ጋር የሚያስማማቸው ስቃልኪዳኑም ሕዝብ ያለውን መልካም ዕቅድ እንዲፈጽሙ የሚያዘጋጃቸው ጥርጊያ መንገድ ነው። በእምነትና በመታዘዝም የቃልኪዳን ግንኙነትን ማጽናት ለጥቅም እንደሆነ በረከትን ስመውረስም እንደሚያስችል ከዘሌዋውያን መጽሐፍ እንረዳለን።

## ማጠቃለያ

የዘሌዋውያን መጽሐፍ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር እንደሆነ ያስረዳል (ዘሌዋ. 1+1-6፣ 7+18፣ 1-22+16)። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ሕዝቡም እንዲቀደስለት ይፈልጋል (ዘሌዋ. 11+41፣ 45፣ 19+2)። ኃጢአት እንዲስተሰረይ የደም መስዋእትን እንደሚያስፈልግና እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ግድ የሚሰው ሥርዓት የተሞላና ሕዝቡ በሥርዓት እንዲሄድ የሚፈልግ አምላክ እንደሆነ ያሳውቃል። ብቻውን ጌታ የሆነውን የሚመስከውን አምላክ መታዘዝና ማገልገል ከሕዝቡ እንደሚጠበቅ (ዘሌዋ. 17+1-9፣ 20+1-5) የሚያስረዳን መጽሐፍ ነው።



# ዘኍልቁ

## የዘኍልቁ - የግዕዝ ትርጉም መሳፍርት

ዘኍልቁ - «የቆጠራ መጻሕፍት» በግሪክ «አሪትሞይ» ይባላል። ትርጓሜውም ቁጥር ማለት ሲሆን፣ ስያሜው በምዕራፍ 1፣ በ2ኛው ዓመት ከግብጽ ከወጡ በኋላና በምዕራፍ 26 በ14ኛው ዓመት በተደረጉት ሁለት ቆጠራዎች ላይ የተመሠረተ ነው። የዕብራይስጡ «በሚድባር» ማለትም በምድረበዳ ውስጥ ከሚለው የመጀመሪያ ቁጥር (1:1) የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም ደበረ፣ ብቸኛ ሆነ፣ ገለልተኛ ሆነ ማለት ነው። ይህም የምድረበዳውን ገለልተኛ ጉዞ ያመለክታል። ዘኍልቁ ከአንድ ዓመት የሲና ቃልኪዳን ምስረታ በኋላ የ39 ዓመት የምድረበዳ ጉዞ ልምምዳቸውን ያሳየናል። (ዘኍል. 1+1፣ ዘዳግ. 1+1)።

## የመጽሐፉ ዓላማ

እስራኤል የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ እንደተዘጋጀች፣ በኃጢአት ምክንያት እንደተቀጣችና እንደዘገየችና እንደገና ጉዞው እንደቀጠለ ታሪኩን ለማስጸ ጽፏል።

## ጸሐፊው

ሙሴ በ1450 - 1410 ዓ.ዓ. በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ በሞአብ እንደነበረ ይነገራል። ይህም ከግብጽ ከወጡ ከአንድ ዓመት በኋላ እስከ ከነዓን መግባት ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። ሕግንና ሥርዓትን ከተቀበሉበት ከሲና የሚቀጥል ታሪክ ነው።

## የቦታ አቀማመጡ

በሲና በረሃማ ሁኔ ደቡብ ምሥራቅ በሚገኘው ክፍል - ዘጸአት እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው መመሪያ የመገናኛውን ድንኳን በመሥራት ሲደመድም፣ በዘሌዋውያን አጠቃቀም ይገልጻል። ዘኍልቁ ደግሞ ከሲና የተነሳውን የእስራኤላውያንን ጉዞ ያሳየናል።

## ቁልፍ ጥቅስ

«...ተዓምራቴንና ክብሬን ያዩ እነዚህ ሰዎች ሁሉ ዐሥር ጊዜ ስለተፈታተኑኝ ነገሬንም ስላልሰሙ በእውነት ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን ምድር አያዩም። ከእነርሱም የናቀኝ ሰው ሁሉ አያያትም» (ዘኍል. 14÷22-23)።

## ዋና ገጸ ባሕርያት

ሙሴ - ታላቁ መሪ
አሮን - ሊቀ ካህን የሙሴ ወንድም
ማርያም - የሙሴና የአሮን እህት

ኢያሱና ካሌብ - ጌታን የታመኑ ሰላዮች፣ ከትውልዳቸውም መካከል የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን የወረሱ።

በታዎች 1. ከሲና ወደ ቃደስ
2. ከቃዴስ ወደ ቃዴስ
3. ከቃዴስ ወደ ከነዓን

## ዋና ርዕሶች

**ቆጠራ** የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥርዓት ያለው፣ የተደራጀ፣ የተለየና ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆን ሙሴ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሁለት ጊዜ ሕዝቡን በመቁጠር ለመከላከልና ለውጊያ አዘጋጅቷል።

**ዐመፃ** የዘኁልቁ መጽሐፍ የሰውን አመፀኝነትና አለመታዘዝ፣ በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ ማመጽ፣ በዓመፃቸው ለ40 ዓመት በምድረበዳ እንዳንከራተታቸው ኃጢአትን የሚቀጣ አምላክ ነው።

**ቃልኪዳን** ቃልኪዳን አክባሪው እግዚአብሔር የተሰፋ ቃሉን ለመፈጸም ሕዝቡን ታግሦ ተሸክክሟል። ለእውነተኛ አምልኮ የለያትን የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ለሕዝቡ እንዳወረሰ በፍቅር እየመራ ከፍጻሜ የሚያደርስ እንደሆነ እናነባለን።

### ከእስራኤል ጉዞ የሚገኙ ትምህርቶች

1. በተለያየ ችግር ውስጥ የማይተወውን አብሮ የሚያልፈውን እግዚአብሔርን መታመን (መዝ(3)+5፣ ዘኁል. 13+26-14+250)።

2. እግዚአብሔር አምላክ እንደቸርነቱ መጠን የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጣል (ፊልጵ. 4+19)

መሪዎች ሰጣቸው - 1+1፣3
ምግብ » - 11+6-9
ሥጋ » - 11+31-33
ውሃ » - 20+8
የተስፋይቱን ምድር - 14+7፣ 8

3. እግዚአብሔር እንደመመሪያውና እንደትዕዛዙ ሲመለክ ይገባዋል። እስራኤላውያን ግን ትዕዛዙን ባለመቀበላቸው በበረሃ አለቁ (ዘኁል. 26+1)።



### የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

1. እስራኤል ከሲና ወደተስፋይቱ ጉዞ ዝግጅት (1+1-10+10)

2. ከሲና ወደ ቃዴስ (10+11-12+16)

3. እስራኤል በቃዴስ በዓመጽ ምክንያት ዘገየ (13+1-20+13)

4. ከሞዓብ ሜዳ የተስፋይቱን ምድር ተዋግቶ መውረስ (22+2-32+42) የተለያዩ መመሪያዎችና ሥርዓቶች (33-36)

## ዋና ዋና ትምህርቶቹ

### ለጉዞ መዘጋጀት (1-12)

- እስራኤል ወደ ሲና ተራራ ከመውጣታቸው በፊት ተቆጥረው ነበር፣ ሴቶች፣ ልጆችንና ሌዋውያንን ሳይጨምር ቁጥራቸው 600,000 ያህል ነበር። ከአርባ ዓመታት በኋላም ዐመፀኛው ትውልድ በምድረበዳ አልቆ ተመሳሳይ ቁጥር እናገኛለን። እግዚአብሔር በነገድ እንዲቆጠሩ ሲያደራጅ ካህናትንና ሌዋውያንን ሲመርጥና ተግባራቸውን ሲያመለክት ለሕዝቡ መመሪያን እንደሰጠ ይህ ክፍል ያመለክተናል (ዘሌዋ. 1፣ 2)።

- ዘሌዋውያን በኵር ልጅን በመተካት የማደሪያውን ድንኳን እንዲያገለግሉ ተመረጡ (ዘጸአ. 40+1-5 ዘኁል. 6+22-9+14)። የማደሪያው ድንኳን በሕዝቡ መካከል ሲሆን ሌዋውያን በሦስት ቤተሰብ ተከፍለው (የጌድሶን የቀዓትና የሜራሪ ልጆች) በየአቅጣጫው በመገናኛው ድንኳን አደባባይ አጠገብ ሲሰፍሩ ሙሴ አሮንና የካህናት ወገን የመግቢያውን በር ይጠብቁ ነበር። በከነዓን ጉዞአቸውም ወዴት እንደሚሄዱ አያውቁምና እግዚአብሔር ምሪትንና ስኬትን ለመስጠት ቀን በደመና ሌሊት በእሳት አምድ ይመራቸው ነበር (ዘኁል. 19+15-23) የእግዚአብሔርን ሁልጊዜ በመካከላቸው መገኘት ያሳየናል (ዘኁል. 10+33)። ይሁን እንጂ የእስራኤል ሕዝብ በተደጋጋሚ ማጉረምረምና በእግዚአብሔር ቁጣ የማስፈሩን አሳዛኝ ታሪክ ዘጸአት ይተርክልናል።

### ጉዞ እስከሞዓብ ሜዳ ድረስ (13-20)

ከአንድ ዓመት የሲና ተራራ ቆይታ በኋላ እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱም ምድር ለመግባት ወደ ቃዴስ በርና ጉዞ ሲጀምሩ ፍርሃት ከበባቸው። የአሥሩ ሰላዮች የአለማመን ሪፖርት የሕዝቡን ልብ እንዳቀለጠና ከቃዴስም ወደ ቃዴስ ሲመላለሱ

ብዙ ዓመታት እንደፈጁ በማጉረምረም ባለመታመንና ባለመታዘዝ ብዙዎቹ በምድረበዳ እንዳለቁ እንረዳለን፡፡ በዚህም ምክንያት ከችግሩ በስቲያ ጌታን ማየት ከቻሉት ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር የሌሎቹ ታሪክ በምድረበዳ ተደመደመ፡፡ ይህ የምድረበዳ ጉዞ በሙሴ ላይ በማመጽ ከጠላቶቻቸው በማፈግፈግ ድል ተመትተው ከነቤተሰቦቻቸው ጠፉ (ዘኁል. 14፣ 15፣ 16)፡፡ በዓላማ የወጣ ይህ ሕዝብ በብዙ ተስፋ መቁረጥ ሲወድቅ የተስፋ ቃሉን የማያጥፈው የምህረት አምላክ ቅሪትን እንዳስቀረና ድልን እንደሰጣቸው በሚቀጥለው ክፍል እናነባለን፡፡

## የተስፋይቱ ምድር መግቢያ (21-36)

ወደ ከነዓን ለመግባት ከተነሱ ከ20 ዓመት በላይ የሆኑት ሙሴ አሮንና ማርያምንም ጨምሮ ከሞቱ በኋላ የቀሩት ከ20 ዓመት በታች የነበሩትና ኢያሱና ካሌብ ብቻ በእግዚአብሔር ታላቅ ምሕረት እንደገና የሚቀጥል የድል ጉዞ የተስፋ ቃሉን አክባሪ በሆነው ጌታ በድል ሲከናወን የተስፋይቱን ምድር ሲወርሱ የእግዚአብሔርን ታጋሽነትና ጌታ ቃሉን ማክበሩን በግልጽ እናያለን፡፡

## ማጠቃለያ

ከዘኁልቁ መጽሐፍ የምንማራቸው ትምህርቶች እግዚአብሔርን በቸርነቱ ለሕዝቡ ግድ ስለሚለው በሁሉን ቻይነቱ በምድረበዳ ምንም አላጐደለባቸውም አሻግሯቸዋል፡፡

- በዓመጸና በአለማመን ሰዎች ከመንፈሳዊ ጉዞአቸውና እድገታቸው እንደሚታቀቡ፣ በሚታዩት ነገሮች ላይ ልብን ከመጣል ይልቅ በእምነት መመላለስ በድል ያራምዳል፡፡ ዜሴዋውያንና እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ እንደሆነ (ዘኁል. 1-4)፣ በአለማመን አመፀኝነትና፣ የቅናት ኃጢአት ጌታን እንዳስመረሩና እንዳስቆጡት ይዘግባል፡፡



# ዘዳግም

## ርዕሱ

ዘዳግም የማስታወስ መጽሐፍ ነው፡፡ በእብራይስጡ «ኤላህ ሃድዲባሪም» «እነዚህ ቃሎች» የሚል ሲሆን በግሪኩ ሰብቱዋጀንትና በላቲን ዘዳግ. 17፥18 ሌላ አዲስ ሕግ ሳይሆን ያንኑ ሕግ እንደሆነ ያመለክታል፤ ትርጉሙም «ሁለተኛ ሕግ» «ዳግማዊ ሕግ» ማለት ነው፡፡ ሙሴ ለእስራኤላውያን በዘጸአት 20 የሰጣቸውን ሕግ በዘዳግም ለአዲሱ ትውልድ እንደሚስማማ አድርጐ ይደግመዋል፡፡

## የመጽሐፉ ዓላማ

እስራኤል ከግብጽ ከወጡ በኋላ በሞአብ ሜዳ ላይ እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃልኪዳን ለማደስ፣ የእርሱ ሕዝብ እንደሆኑ ለማጽናት ነው፡፡ እነርሱም በተስፋይቱ ምድር ሲገቡ ምን እንዳደረገላቸውና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ የሚገባቸውን እንደ እስራኤል ሃይማኖት ይዘትና ትርጉም፤ በመታዘዝ የሚገኘውን መልካም ሕይወትና ደስታ፣ ቃል ኪዳኑን በመተው የሚመጣውን አሳዛኝ ውጤት የመሳሰሉትን የሚያሳይ፤ ሕይወታቸውን ለጌታ እንዲሰጡ አዲሱን ትውልድ የሚያበረታታ መጽሐፍ ነው፡፡

## ጸሐፊው

የዘዳግም መጽሐፉ እንደሚመሰክረው ሙሴ ነው (1፥5፣ 31፣ 9፥22-24)፡፡ በሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (1ኛ ነገ. 2፥3፣ 8፥53፣ 2ኛ ነገ. 14፥6፣ 18፥12)፣ የጌታ ኢየሱስ ምስክርነት (ማቴ. 19፥7-8፣ ማር. 10፥3፣ ዮሐ. 5፥46-47) በሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች (ሐዋ. 3፥22-23፣ 7፥37-38 ሮሜ 10፥19)፡፡ ሁሉም የሙሴን የአሪት ዘዳግም ጸሐፊነት ይጠቁማሉ፡፡

ሙሴ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ አይደለም የሚሉ ሰዎች በዘዳግም 34 ስለሞቱ ስለተጻፈና፣ አጻጻፉ እርሱ የጻፈው ትንቢት ሳይሆን ከሞተ በኋላ የተጻፈ ስለሚመስል ነው ይላሉ፡፡ በእርግጥ ይህ ክፍል በሙሴ በራዕይ ወይም ኃላፊነቱን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሊረከብ በቅርብ ባለው በኢያሱ ቢጻፍ ሌላው ክፍል በሙሴ መጻፉን የሚቃረን አይሆንም፡፡

## የተጻፈበት ዘመን

1407/6 ዓ.ዓ.

### የመልክዓ ምድር አቀማመጡ

ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ከነዓን ዳርቻ በሚገኘው ሞአብ ሜዳ ላይ ነበር።

### ቁልፍ ጥቅስ

አንተም አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደሆነ ለሚወዱትም ትዕዛዙንም ለሚጠብቁ ቃልኪዳኑንና ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደሆነ እወቅ (ዘዳ. 7+9)።

### ዋና ገጸባሕርያት

ሙሴና ኢያሱ

### ቁልፍ ቃላቶች

ማስታወስ፣ መታዘዝ፣ በረከት፣ መርገም፣ ቃልኪዳን (4+23፣ 29፣ 8+11፣ 10+12-13፣ 11+26-28፣ 28+1፣ 29+1)

### የመጽሐፉ ልዩ ባህርይ

- ጌታችን ኢየሱስ ብዙ ጊዜ የጠቀሰውና ለሰይጣን/ለፈታኙ መልስ ለመስጠት የተጠቀመበትና ጠላትን የጣለበት ቃል (ዘዳግ. 8+3፣ 6+16፣ 6+13፣ 10+20፣ ማቴ. 4+1-11፣ ሉቃ. 4+1-13)።

- ሕግን የገለጸበት ቃል (ዘዳ. 6፤5፣ ማቴ. 22+37)።

- እግዚአብሔርን ስለመታዘዝ የሚናገር መጽሐፍ በመሆኑ፣ የቃልኪዳኑን ሕዝብ ኃላፊነትና በዘጸአት፣ በዘኁልቁ፣ በዘሌዋውያን ያሉ ህጐችና ተአምራቶች አብዛኛ ዎቹ ተደግመዋል፣

- ከ27ቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት 17ቱ ጠቅሰውታል፣

### የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

1. ለአዲሱ ትውልድ የቀደመውን የ40 ዓመት ታሪክ ማስታወቅ (1-4)

    - የእስራኤል ውድቀት (1+1-3+29)
    - መታዘዝና ውጤቱ (4+1-40)
    - ከተሞችና መመሸጊያዎች (4+41-43)



2. ሕጉን በድጋሚ ማስተማር (4+44-28+68)

    - ቃልኪዳንና ባርኮት (4+44-11+32)
    - በከነዓን ለመኖር - ሕግ (12+1-28+68)
    - በረከትና መርገም (27+1-28+68)

3. የመጨረሻ ዝግጅት፣ ትንቢታዊና ምክርና ስንብት (29+1-34+12)

    የእስራኤል ምርጫ ለበረከት ወይም ለመርገም (29+1-30+20)
    የኢያሱ መጠራት (31+1-29)
    የሙሴ ዝማሬና በረከት (31+30-33+29)
    የሙሴ ሞት (34+1-12)

ይህ ትውልድ (ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር) የእግዚአብሔርን ታላላቅ ተዓምራቶች፣ እስራኤል ነጻ መውጣታቸውን፣ የቀይ ባሕርን መከፈልና የተሰጣቸውን ሕግ ያላዩ በምድረበዳ የተወሰዱ ነበሩ። አዲስ የሕይወት ምዕራፍ (ጦርነትና ፈተና) የገጠመውን ይህን ሕዝብ አዲሱን መሪ ኢያሱን ለማደፋፈርና ለማበረታታት ከሙሴ የተሻለ የሚረዳቸውና የሚያውቃቸው ስለወደፊቱም ሊናገር የሚችል ሰው አልነበረም። ዮርዳኖስን ከመሻገራቸው በፊት ሰባት ቀን በማከታተል መክሯቸዋል።

## 1. ታሪክን ማስታወቅ - (1-4)

ሙሴ የእስራኤልን ታሪክ በመከለስ ወደኋላ እያየ እንዴት ከግብጽ እንደወጡና ወደሲና እንደደረሱ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ታላቅነት፣ በዐመፅና በማጉረምረም በጉዞአቸው ብዙ እንደዘገዩ ጌታ በትዕግሥት ተሸክሞ ማስተማሩን ያመለክታቸዋል። ደግሞም ያለማመናቸው ለሕይወታቸው እንቅፋት እንደሆነባቸውና ወደተስፋይቱ ምድር ሳይገቡ ብዙዎች በምድረበዳ እንደቀሩም ያሳያቸዋል (ማቴ. 13+58)። እግዚአብሔርን በመፈለግ፣ በመታዘዝ የሚገኘውን በረከትና ሞገስ ተገልጾበታል (ዘዳግ. 2+7፣ ዘዳግ. 2+14፣ ዘኁል. 15፥1-20) በበረሀም እንዳላጡ የእግዚአብሔርን ታማኝ እረኝነት ሙሴ በመጨረሻው ዕድሜ ላይ ሆኖ መስክሮላቸዋል።

### 2. ሕጉን ማስተማር (4-28)

በሁለተኛው ነጥብ ላይ እስራኤል ሙሴ የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ሕዝብ ስለሆኑ እግዚአብሔር የሚቀበለውን ሕይወት ለመኖር እንዲችሉ በሚገቡበት አዲስ ምድር አምላካቸውን በመታዘዝ፣ በመውደድ፣ በማስተዋልና በማክበር የሕግን ፍጻሜ አሳይቷቸዋል። በጣዖት አምልኮ ተይዘው ስነበሩበት ከክፉ ነገር ራሳቸው በማራቅ ለሌሎች በጉነት እንዲያሳዩ፣ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ቅዱስ እንዲሆኑ ያሳስባል። በተጨማሪም የሚኖሩበትን የሕብረተሰብ የማኅበራዊና

የእርስ በርስ ሕግና ደንብ በመስጠት በሥርዓት እንዲኖሩ መክሯቸዋል (ዘዳግ. 16)። መሰብሰባቸውንና አብረው ማምለካቸውን እንዲቀጥሉ ልጆች ሥርዓት ያላቸውና ለወላጆቻቸው ታዛዦች እንዲሆኑ (ዘዳ. 21+18-21) ያሳስባቸዋል።

## 3. የሙሴ ስንብት (29+1-34+12)

ሙሴ ከሚወደውና ለ40 ዓመታት ከመራው ሕዝብ ከመለየቱ በፊት ለኢያሱ የአመራር ኃላፊነት ሰጥቷል (ዘዳግ. 31+7፤ 8፤ 14) እጁንም ጭኖ በመፀለይ የጥበብ መንፈስ እንዲሞላና የእስራኤል ልጆች እንዲታዘዙለት ሞገስን እንዲያገኝ ባርኮታል። እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሲያደርግ የሕጉንም ግልባጭ በመስጠት በሕዝቡ ፊት እንዲያነቡ ለካህናትም በማስተማር አገልግሎት እንዲተጉ ኃላፊነትን ሰጥቷቸዋል (ዘዳግ. 34+9)። ሙሴ ለእያንዳንዱም ነገድ በረከት በመስጠት እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ስለሆነ ምንም አያስፈራችሁም ታማኝነቱን እስቡ ብሎ በማጽናናትና እምላኩን የመባረክ ዝማሬን ዘምሯል (ዘዳ. 22+1-3+27-29፤ ዘዳግ. 3+19፤ 32+3፤ 4፤ 9-11፤43)። ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የብሉይ ኪዳን አንድ አራተኛ የሚሆነውን መለኮታዊ መልዕክት ያበረከተልን ሙሴ በቃዴስ በርኔ ባሳየው አለመታዘዝ ወደከንዓን እንዳይገባ ተከልክሎአል (ዘኁል. 20+10)። ጌታ እንደተናገረው በኔቦ ተራራ በመውጣት የተስፋይቱን ምድር በዓይኑ አይቶ በዚያው በሞአብ ምድር እንደሞተ የመቃብሩን ቦታ ግን ማንም እንዳላወቀ ዘመተረክ ታሪኩን ይደመድመዋል (ዘዳግ. 34+4-6)።

በዚህም የኦሪት መጽሐፍ ፍጻሜ እንደሆነ እንገነዘባለን (ዘዳግ. 31+9፤ 24)። ሙሴ የእነዚህ መጻሕፍት ጸሐፊ ይሁን እንጂ በኦሪት መጻሕፍት ውስጥ ያለው ተከታታይነትና አንድነት ከ500 ጊዜ በላይም «እግዚአብሔር ተናገረ» «እግዚአብሔር አለ» የሚሉት ገለጻዎች የመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ደራሲ እግዚአብሔር እንደሆነ ያስረዳናል።

### ማጠቃለ

- እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ሉአላዊና ባለብዙ ምህረት፣ ዐመፅን የሚቀጣና ጻድቅ አምላክ ነው። ይህ መጽሐፍ ከፈጣሪ ጋር የግል ግንኙነት እንደሚያስፈልገን፣ በሙሉ ልብና በማይለወጥ ፍቅር፣ ልናመልከው ልናገለግለው እንደሚገባን፣ ያለፍቅር ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንደማይኖር ይጠቁማል።
- ቃል ኪዳንን በመጠበቅ የሚገኘውን በረከትና ጥቅም፣ ቃልኪዳንን በማፍረስ የሚኖረውን ጥፋት በማየት ኅብረታችንን እቅልለን እንዳናይ ትምህርት ይሰጠናል። በመጨረሻም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ፍጹም መሰጠትን እንደሚፈልግና የመሳሰሉትን መልእክቶች በግልጽ የሚያስረዳን መጽሐፍ ነው።



# ምዕራፍ ሁለት

# የታሪክ መጻሕፍት

# መጽሐፈ ኢያሱ

### መግቢያ

የመጨረሻውን የዘዳግም ምዕራፍ በጥንቃቄ ስናነብ መጽሐፈ ኢያሱ በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ውስጥ የተጀመረው ታሪክ ተከታይ ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ደኅንነት ያለውን ዕቅድ ጨምሮ የሚገልጽ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ መጽሐፍ ነው። የኦሪት መጻሕፍት እጥርጥር እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ❖ ዘፍጥረት:- የእስራኤል ሕዝብ መወለድ እግዚአብሔር ለአብርሃም «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ» ዘፍጥ. 12+2 አለው። የከነዓን ምድር እንደሚሰጣቸው የተስፋ ቃል ገብቶላቸው ነበር (ዘፍጥ. 12+7፤ 15+18-21)።
- ❖ ዘጸአትና ዘሌዋውያን:- ከባርነት እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲታደግና ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲመራቸው እንመለከታለን። እንዲሁም የሚኖሩበትን ሕግጋት እንደሰጣቸው ጭምር እናገኛለን።
- ❖ ዘኁልቁ:- የእስራኤል ጉዞ ማለትም ከምድረበዳ ጀምሮ እስከ ከንዓን ደጃፍ ድረስ ያለውን ታሪክ ይዘግባል።
- ❖ ዘዳግም:- ወደ ተስፋይቱ ምድር ከነዓን ለመግባት የተደረገውን የመጨረሻ ዝግጅትን አስፍሯል።

ከዚህ በመቀጠል መጽሐፈ ኢያሱ ከንዓንን ለመያዝ የተደረጉትን ውጊያዎችና የእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ታሪክ ይዘግባል። መጽሐፈ ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ አንድ የታሪክ ምዕራፍ ታላቅ ፍጻሜና የአዲስ ልምምድ ጅማሬ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ መጽሐፈ ኢያሱ ዋና መጽሐፍ ሆኖ እናገኘዋለን።

### 1. ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን

የዚህ የስድስተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ጸሐፊ ማን እንደሆነ በግልጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ አናገኝም። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ግን የመጽሐፉ ዋና ገፀ ባሕርይ የሆነውን ኢያሱን የመጽሐፉ ጸሐፊ ለመሆኑና ላለመሆኑ የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀርባሉ። ጸሐፊው ማንም ይሁን ማን

እንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ስለጸሐፊው የሚጠቁሙ እውነታዎችን አብረን እንመልከት፡፡

1. ጸሐፊው በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ድርጊቶች ሲፈጸሙ የተመለከተ የዓይን ምስክር ነበር (ኢያሱ 5፥1-6)፡፡
2. መጽሐፉ የተጻፈው በመጽሐፉ ውስጥ የተጻፉት ገጠመኞች ተከናውነው ካለፉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ቁልፍ ሐረግ፡- «..... እስከ ዛሬ ድረስ....» የሚለው ነው (6፥25፤ 28-29፤ 9፥27፤ 10፥27፤ 13፥13፤ 14፥14፤ 15፥63)፡፡
3. በመጽሐፉ ውስጥ ኢያሱ እንዳንድ ጽሑፎችን እንደጻፈ የሚጠቁም ሃሣብ እናገኛለን፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- ኢያ. 24፤25-26፤ 8፤32

- እንዲሁም ኢያሱ የከንዓን ምድር ቅየሳ እንዲካሄድ በማድረግ መረጃው በመጽሐፍ እንዲጻፍ ማድረጉን በኢያሱ 18፥9 ላይ እናነባለን፡፡
- እንዳንድ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ያሉት ክፍሎች ግን በኢያሱ እንዳልተጻፉ ግልጽ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ስለዕረፍቱ (ሞቱ) የሚናገረው ክፍል፡- (ኢያ. 24፥29-30)

- እስራኤል ከኢያሱ ሞት በኋላ ለእግዚአብሔር የነበራትን ታማኝነት በተመለከተ በኢያሱ 24-31 ተዘግቧል፡፡
- እነዚህ ተጨማሪ ጽሑፎች ምናልባትም በካህኑ አልዓዛር ተጽፈው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ፡፡ (እንዲሁም የካህኑ የአልዓዛር ሞት በልጁ በፊንሐስ ተጽፎ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል (ኢያ. 24፥33፡፡)
- መጽሐፉ በ1400 ዓ.ዓ. ገደማ ተጽፎ ሊሆን እንደሚችል ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡

## የመጽሐፉ ርዕስ

- መጽሐፉ የተሰየመው በጸሐፊው በኢያሱ ስም ነው፡፡ «ኢያሱ» የሚለው በዕብራይስጥ አዳኝ ማለት ሲሆን፤ በግሪክ «ኢየሱስ» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የኢያሱ ትርጓሜ «ጌታ እግዚአብሔር ያድናል» ወይም «ጌታ ድልን ይሰጣል» ማለት ነው (ማቴዎስ 1፥21)፡፡



- ኢያሱ በመጀመሪያ «አውሴ» በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ትርጓሜውም «ደህንነት» ማለት ነው (ዘኁል. 13፥8፤16) ስሙንም ከአውሴ ወደ ኢያሱ የቀየረው ሙሴ ነበር፡፡
- በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ» ይለዋል፡፡ ይኸም በግዕዝ «የነዌ ልጅ የኢያሱ መጽሐፍ» እንደማለት ነው፡፡

## ኢያሱ

### ሀ. የሕይወቱና የአገልግሎቱ ጅማሬ

- ኢያሱ የተወለደው በግብጽ አገር ነበር፤ ስለሆነም በወገኖቹ እስራኤላውያን ላይ የደረሰውን የፈርዖን ብዝበዛ አይቷል፤ ችግሩንም ገፈት ቀምሷል፡፡ በምድረበዳው ጉዞ ዘመን ወጣት ነበረ (ዘጸአ. 33፥11)፡፡ እያቱ ኤሊሳማ ኤፍሬም ነገድ መሪና የጦር አዛዥ ነበር (ዘኁል. 1፥10፤ 2፥18)፡፡

### ለ. የሙሴ ረዳት

- በምድረበዳው ጉዞ ዘመን ሁሉ ኢያሱ ከሙሴ ጐን ሆኖ ሲረዳውና ከእርሱ ሲማር ቆይቷል (ዘጸአ. 17፥8-16)፡፡
- በተጨማሪ በዘጸአት 24፥2-13 በሲና ተራራ ሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዐሥርቱ ትዕዛዛት በተቀበለበት ወቅት የነበረውን ታሪክ በተመለከተ የተጻፈውን እናገኛለን፡፡
- ከካሌብ ጋር አብሮ በመቆሙ ወደተስፋይቱ ምድር የመግባትን ታላቅ ዕድል ፈንታ ተሰጥቷል (ዘኁል. 13፥1-16፤ ዘኁል. 14፥26-35)፡፡

### ሐ. የሙሴ ምትክ

- ሙሴ በኢያሱ ላይ እጁን በመጫን እደራውን ሰጠው (ዘኁል. 27፥17፤18፤ ዘዳግም 34፥9)፡፡

| ሙሴ | ኢያሱ |
|---|---|
| - ለማገልገል የተሾመው - በሆሬብ | - ለማገልገል የተሾመው-ብኢያሪኮ |
| - እስራኤልን ከግብጽ የመራ | - እስራኤልን ወደ ከንዓን የመራ |
| - የቀይ ባሕር መከፈል | - የዮርዳኖስ መከፈል |
| - የመጨረሻ የስንብት ንግግር | - የመጨረሻ የስንብት ንግግር |
| (ዘዳግ. 31፥30-33፥29) | (ኢያ. 23፥1-24፥28 |

* ሁሰቱም የእግዚአብሔር ሰዎች ከሞቱ በኋላ በነበረው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት በመልካም ሁኔታ ይገኝ ነበር፤ ሕዝቡም በሙሉ ልብ እግዚአብሔር አምላካቸውን ለማገልገል ቆርጠው የተነሱበት ጊዜ ነበር (ዘዳግ. 34፤ 9፤ ኢያ. 24፤ 24)።

**መ. ሕይወቱ**

- እምነቱ ስር የሰደደ፣ ጠንካራ፣ እና ጽኑ ነበር።
- በሕዝቡ ዘንድ ታላቅ ከበሬታንና ታማኝነትን አትርፏል (ዘኍል. 27+18) ዘዳግ. 34÷9)።

## አስተዋጽኦ

**1. የከንዓን መወረር 1+1-5+12**

ሀ. ለኢያሱ የተሰጠ አደራና መመሪያ (ምዕራፍ 1)
ለ. የሰላዮች ወደ ኢያሪኮ መላክ (ምዕራፍ 2)
ሐ. የዮርዳኖስ ወንዝ መሻገር (ምዕራፍ 3)
መ. የመታሰቢያ ድንጋዮች (ምዕራፍ 4)
ሠ. የእስራኤላውያን መቀደስ (5+1-12)

**2. በከንዓን ላይ የተደረገ ውጊያና የተገኘ ድል (5+13-12+24)**

ሀ. መግቢያ (5+13-15)
ለ. የመሀከለኛው ውጊያ (6-8)
ሐ. የደቡብ ውጊያ (9-8)
መ. የሰሜኑ ውጊያ (11+1-15)
ሠ. የድል ታሪኩ ክለሳ (11+16-12+24)

**3. የከንዓን መሬት ክፍፍል (13-21)**

ሀ. የሁለት ተኩል ነገዶች የርስት ድርሻ (13)
ለ. የካሌብ የርስት ድርሻ (14)
ሐ. የዘጠኝ ተኩል ነገዶች የርስት ድርሻ (15+1-19+48)
መ. የኢያሱና የሌዋውያን የርስት ድርሻ (19+49-21+45)

**ማጠቃለያ**

ሀ. የድንበር ጥል/ክርክር/ 22
ለ. የመጨረሻዎቹ የኢያሱ ቀናት 23+1-24+28
ሐ. ተጨማሪ 24+29-33



## የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት

* መጽሐፈ ኢያሱ የአንድ ሕዝብና ምድር ታሪክ ነው። ምድሪቷ እንደ እግዚአብሔር ተስፋ ቃል መሠረት የምትወረስ ስትሆን፣ ሕዝቡ ደግሞ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነገር ግን ምድሪቷን እንዳይወርስ ከአሕዛብ ተግዳሮት የሚጠብቀው ነበር። ስለዚህም ከሕዝቡ በኩል የተደቀነው ተግዳሮት የግድ ጦርነትን ያውም «ቅዱስ ጦርነትን» የሚቀሰቅስ ነበር።

➔ ሕዝብ ➔ ምድር ➔ እንቅፋት (የአሕዛብ ተግዳሮት) ➔ ቅዱስ ጦርነት

* አስቀድሞ እንደተጠቀሰው «የከንዓን ምድር» በመጽሐፈ ኢያሱ ታሪክ ውስጥ ቁልፍ ሚናን ይጫወታል። ምድሪቷ ለእስራኤል ሕዝብ ርስት እንድትሆን በተስፋ ቃሉ መሠረት የተሰጠችው እንዲኖሩባትና እንዲያርፉባት ነበር። ስለዚህም በምድሪቷ ምንነት ላይ በመመርኮዝ የኢያሱ መጽሐፍ አራት ዓበይት ክፍሎችን ይዟል።

1. ወደ ምድሪቷ መግባት
2. ምድሪቷን ለመውረስ የሚደረግ ጦርነት
3. ምድሪቷን መከፋፈልና መውረስ
4. በምድሪቷ ውስጥ መኖር

በዚህም መሠረት ኢያሱ ምድሪቱን በተመለከተ ከእግዚአብሔር ዘንድ ግልጽ ትእዛዝና ምሪት ተሰጥቶት ነበር (ኢያ. 1+6)።

1. **የጦርነት ዝግጅት፡-** የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለሕዝቡ ሲሰጥ፣ ኢያሱ በመለኮታዊ ውሳኔ የሕዝቡ ወታደራዊ መሪ እና አስተማሪ ነበር፤ ዮርዳኖስን መሻገር እምነታቸውን ለማጠናከር፤ የመገረዝና የፋሲካ ስርዓቶችም ለዝግጅታቸው አስፈላጊ ነበሩ።

2. **ጦርነትና ድሉ፡-** ድሉ በሕዝቡ እምነትና መታዘዝ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ያጋጠሟቸው ሽንፈቶች ደግሞ በኃጢአታቸው ምክንያት ነበር።

3. **የርስቱ መወረስ፡-** የርስቱ ክፍፍል ለሕዝቡ ሲሆን፤ በዚህም የነገዳቸው ቀጣይነት በተሰጣቸው የርስት ምድር ሆነው ማረጋገጥ ነበረባቸው።

4. **መቀደስ/መለየት/፡-** በሚቀጥሉት ዘመናት ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነትና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግና መጠበቅ እንደነበረ የሚጠቁም ነበር።

**ቁልፍ ጥቅስ**

ኢያሱ 11+23 ሲሆን፤ የእስራኤልን ታሪክ በተመለከተ ጥቅሱ አራት ዓበይት እውነታዎችን በውስጡ ይዟል፡፡

1. ውጊያውና ድሉ፤ «...ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ...»
2. የተስፋው ቃል ፍጻሜ፤ «...እግዚአብሔርም ለሙሴ እንደነገረው ሁሉ»
3. የርስቱ መሬት ክፍፍል፤ «ኢያሱም ለእስራኤል እንደ ክፍላቸውና እንደ ነገዳቸው ርስት አድርጐ ምድሪቱን ሰጣቸው»
4. ዕረፍቱ፤ «ምድሪቱም ከሰልፍ ዓረፈች»

**የምድሪቷ አጭር ታሪክ**

- ለመጀመመሪያ ጊዜ አብርሃም ወደ ከንዓን ሲመጣ ያገኛቸው ሕዝቦች ዘላኖች ወይም ግማሽ ዘላኖች ነበሩ፡፡ በዘፍጥረት ውስጥ ከተጠቀሱት አሕዛብ አንዳንዶቹ፣ ፌርዛውያን፣ አሞራውያን፣ ፍልስጤማውያን፣ ሐሲታውያን፣ ቀኔዛውያን ኬጢያውያንንም ወዘተ... ነበሩ፡፡ (ዘፍጥ. 14+5-7፤ 15+19-21) አሁን ግን ኢያሱና ሕዝቡ ወደምድሪቷ በተመለሱ ጊዜ ሁኔታዎች በአመዛኙ ተለውጠው ነበር፡፡ ይኸውም ጥቂት የነበሩት የከንዓን ሕዝቦች አሁን ግን በዝተውና ተደራጅተው ከተሞችም መስርተው እንዲያውም በግንብ የታጠሩ ጠንካራ ምሽግ ያሏቸው ከተሞች ጥምር ነበሯቸው፡፡

  ነገር ግን እነዚህ ሕዝቦች አንድ ወጥ የሆነ የጋራ አገር አልመሠረቱም፤ በየወገናቸው ተበታትነው በምድሪቷ ውስጥ ሰፍረው ነበር፡፡

**የምድሪቷ የአየር ፀባይና በውስጧ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች:-**

- እግዚአብሔር ስለምድሪቷ ሲናገር ኮረብቶችና ሸለቆዎች ያሉባት ነገር ግን ዝናብ የማያቋርጥባት ውብ ምድር እንደሆነች ገልጿል፡፡ ዘዳግ. 11+11-12፣ ዘዳግ. 8+7፣ ዘጸአ. 8+7፤ ዘሌዋ፣ 20+24፤ 4፣ ሕዝ. 20+6፣ ዘዳግ. 8+8፣ 9፣ 2ኛ ነገ. 18+32
- መጽሐፈ ኢያሱ የተጻፈው እግዚአብሔር ፍጹም ስልጣን ያለው አምላክ መሆኑንና ልጆቹን ወደ ተስፋይቱ ምድር መርቶ ለማድረስ የሚችል ታማኝ አምላክ መሆኑን ለማሳየት ነው፤ (ኢያ. 11+23 እና 21+43+45)፡፡



**መጽሐፉ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለው ሥፍራ**

የሰላሳ ዘጠኙ የአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ቅንጅት የላቲኑን (400 ዓ.ም) እና የግሪኩን (ሁለተኛ እና ሦስተኛው ዓ.ም.) ቅንጅትን የተከተለ ሲሆን አራት ዋና ዋና ክፍሎችን አካቷል፡፡ እነርሱም አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ፔንታቱክ)፣ የታሪክ መጻሕፍት፣ የግጥም፣ ስነምግባር ነክ መጻሕፍት፣ እና የትንቢት መጻሕፍት ናቸው፡፡

ማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠና ሰው በተለይ ስለ ብሉይ ኪዳንን፣ ማወቅ ያለበት አስፈላጊ ነጥብ የእስራኤል ታሪክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በ«መሬት» እና በ«አመራር/አስተዳደር/» ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ነው፡፡

- መሬት ስንል ከንዓንን ማለታችን ሲሆን አመራር/አስተዳዳር ስንል ደግሞ የእግዚአብሔር/ገዢነት/አመራር (Theocracy) ማለታችን ነው፡፡

| I | II | III |
|---|---|---|
| ለምድሪቷ | በምድሪቷ | ከምድሪቷ |
| • የተሰጡ የተስፋ ቃላት፣ | • ወደ ምድሪቷ መግባት | • የሕዝቦቿ ወደ ምርኮ አገር መወሰድ |
| • ወደምድሪቷ የተደረገ ጉዞ | • በምድሪቷ ውስጥ ኑሮ መጀመር | • የእግዚአብሔር ምሪት መቋረጥ |
| • የእግዚአብሔር ምሪት (እግዚአብሔር የሕዝቡ ገዥ) ነበር፡፡ | • ምድሪቷ | • የእግዚአብሔር ቀጥተኛ ገዥነት መስተጓጎል |
| | • የእግዚአብሔር ምሪት (እግዚአብሔር የሕዝቡ ገዥ/መሪ ነበር፡፡ | |

- አምስቱ የሙሴ መጻሕፍትና (ፔንታቱክ) የትንቢት መጻሕፍት ከላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን የእስራኤል ሕዝብ የታሪክ ዘመናትን በሰፊው ይዳስሳሉ፡፡ የሚቀጥለው ሠንጠረዥም ይህንኑ ያመለክታል፡፡

| (ፔንታቱክ) አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት | ነቢያት | |
|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 |
| (ሕግ) | (ፊተኞች ነቢያት) | (ኋለኞች ነቢያት) |
| ከዘፍጥረት - ዘዳግም | ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት | ከኢሳይያስ - ሚልክያስ |
| ለምድሪቷ | በምድሪቷ | ከምድሪቷ |

# መጽሐፈ መሳፍንት

## መግቢያ

በዕብራይስጥ ቋንቋ የመጽሐፉ ርዕስ «ሾፈጢም» ሲሆን በግሪክ ቋንቋ «ክሪታይ» ይባላል:: የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው:: ይኸውም «ፈራጆች» ወይም ዳኞች» ማለት ነው:: ይህ ቃል ከኢያሱ ቀጥሎ እስከ ንጉሡ ሳኦል ድረስ የነበረው የእስራኤላውያን ነገዶች የመስተዳድር ወይም የአመራር ሁኔታን ያመለክታል:: የመጽሐፉ ዋና መልዕክትም እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ተጽዕኖ ነጻ እንዲያወጣቸው በሾማቸውና ባበነሳቸው ሰዎች መሪነት ስር የቃል ኪዳኑን ቃል መጠበቅ እንዳልቻሉና በዚህም እርሱን እንደበደሉ ያትታል::

ቀደም ብለን የኢያሱን መጽሐፍ ስናጠና እንደተመለከትነው ኢያሱ በመጨረሻ የመሰነባበቻ ንግግሩ ላይ የእስራኤልን ሕዝብ ወደፊት ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት እጅጉን እንዲጠነቀቁ አሳስቧቸው ነበር:: «እግዚአብሔርን ትታችሁ እንግዶችን አማልክት ብታመልኩ መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደርግባችኋል፣ ያጠፋችሁማል አላቸው:: ሕዝቡም ኢያሱን እንዲህ አይሁን ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን አሉት (ኢያ. 24፥20፣ 21)::

ነገር ግን በመጽሐፈ መሳፍንት ላይ የምናየው እውነታ ከዚህ በጣም የተለየ ነበር:: ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔርን ከማሳዘናቸው የተነሳ በየጊዜው በጠላቶቻቸው እጅ ሲወድቁና እግዚአብሔር በቸርነቱ መሳፍንትን (መሪዎችን) እያስነሳ ሲታደጋቸው ነው::

«በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፣ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር» (መሳ. 21፥25)::

ይኸ ሁኔታ እግዚአብሔር ማዕከላዊ አሠራር ያለው ዘውዳዊ (ንጉሣዊ) አገዛዝ እንዲመሠርት አድርጎታል:: (የዚህን ታሪካዊ ሂደት ዘገባ በ1ኛ ሳሙኤል እሰፋ በስፋት እንመለከታለን::)

## የመጽሐፉ ጸሐፊና የተጻፈበት ዘመን

መጽሐፈ መሳፍንት ስሙ ባልተገለጸ ነቢይ በ1000 ዓ.ዓ. ገደማ ማለትም በመጽሐፉ ውስጥ በስተመጨረሻ የተጠቀሰውና በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ዋና ተዋናይ ከነበረው ከሳምሶን ሞት (1051 ዓ.ዓ.) ከጥቂት ዓመታት በኋላ እንደተጻፈ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ያስረዳሉ:: መጽሐፉ የተጻፈው እስራኤላውያን በንጉሥ መመራት ከጀመሩ በኋላ እንደሆነ የሚጠቁም ሐረግ እናገኛለን::



«በዚያም ዘመን ንጉሥ አልነበረም» (መሳ. 17፥6፣ 18፥1፣ 19፥1፣ 21፥25) ይህ የሚያሳየን ታሪኩ በተጻፈበት ዘመን በእስራኤል አገር ንጉሥ ነግሶ እንደነበር ነው:: አይሁድና ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የመጽሐፉ ፀሐፊ ሳሙኤል ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ::

## የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

1. የከነዓን ምድር ከፊል ወረራ (1፥1-2፥5)
2. የከንዓናውያን እንዲኖር የተደረገበት ምክንያት (2፥6-3፥6)
3. በኩሰርሰቴም እጅ መገዛት እና በጎቶንያል የተገኘ ዕረፍት (3፥12-30)
4. በሞአባዊው ዔግሎም እጅ መገዛት እና በናዖድ የተገኘ ዕረፍት (3፥12-30)
5. በሰሜጋር የተገኘ ድል (3፥31)
6. በአሶራዊው በኢያቢስ እጅ መገዛትና በዲቦራና በባራቅ የተገኘ ዕረፍት (4፥1-24)
7. የዲቦራ ቅኔ (5፥1-31)
8. በምድያማውያን እጅ መገዛትና በጊዴዎን የተገኘ ዕረፍት (6፥1-8፥35)
9. የዐመፀኛው አቢሜሌክ ዘመን (9፥1-57)
10. የቶላ እና የያዕር የዳኝነት ዘመን (10፥1-5)
11. በአሞናውያን እጅ መገዛትና በሳምሶን የተገኘ ዕረፍት (13፥1-16፥31)
12. የኢብዳን፣ ኤሎም፣ እና የዓብዶን ዳኝነት (12፥8፣ 15)
13. በፍልስጥኤማውያን እጅ መገዛትና በሳምሶን የተገኘ ዕረፍት (13፥1-16፥31)
14. የሚካ ካህን እና የዳን ነገድ ፍልሰት (17፥1-18፥31)
15. በጊብዓ ምድር የተፈፀመ እርኩሰት እና በብንያም ነገድ ላይ የተከፈተ ጦርነት (19፥1-21፥25)

## የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት


ከዚህ በመቀጠል የመጽሐፉን ጠቅላላ ይዘት በሚከተሉት ሠንጠረዦችና ስዕላዊ መግለጫ እንዳስሳለን::

በመጽሐፈ መሳፍንት የተጠቀሱ መሳፍንት በቅደም ተከተል እንደሚከተሰው በሠንጠረዥ መልክ ማየት ይቻላል፡፡

| ስም | ነገድ | ጠላቶች | የተገዙበት ዘመን | የዕረፍት ዓመታት | የተጠቀሰበት ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. ጉቶልያ | ይሁዳ | (ንጉሥ ኩስርቴም) መሰጴጦምያዊያን | 8 | 40 | 3+9-11 |
| 2. ናእድ | ብንያም | (ንጉሥ ዔግሉም) ሞአባውያን | 18 | 80 | 3+12-30 |
| 3. ሴሜጋር | ንፍታሴም | ፍልስጤማውያን | | | 3+31 |
| 4. ዲቦራ | ኤፍሬም | (ንጉሥ ኢያቢስ) ከንዓናዊያየን | 20 | 40 | 4+4-5+31 |
| 5. ጌዴዎን | ምናሴ | ምድያማውያን | 7 | 40 | 6+11-8+35 |
| 6. ቶላ | ይሳኮር | | | 23 | 10+1-2 |
| 7. ኢያዕር | ገሰዓድ | | | 22 | 10+3-5 |
| 8. ዮፍታሄ | ገሰዓድ | አሞናውያን | 18 | 6 | 11+1-12+7 |
| 9. ኢብዳን | ቤተልሔም | | | 7 | 12+8-10 |
| 10. ኤሎም | ዛብሉን | | | 10 | 12+11-12 |
| 11. ዓብደን | ኤፍሬም | | | 8 | 12+13-15 |
| 12. ሳምሶን | ዳን | ፍልስጤማውያን | 40 | 20 | 13+2-16+31 |

በመጽሐፈ መሳፍንት ላይ የምናየው አንድ ተደጋጋሚ የእስራኤላውያን ልምምድ አለ፡፡ ይህ ልምምድ ተደጋጋሚ ከመሆኑ የተነሳ ዑደታዊ ሂደትን ተከትሎ በአሥራ ሁለቱ መሳፍንት ዘመን ሲከናወን ታይቷል፡፡

## የእስራኤላውያን ልምምድ ዑደታዊ ሂደት






ይህ የእስራኤላውያን ቀጣይ ዐመፅ የሚያሳይ ዑደታዊ ልምምድ በመጽሐፉ ላይ እንደሚከተሰው ተጽፎ እናገኘዋሰን፡፡

| ዑደት | ጥቅስ | የእስራኤላውያን ጠላቶች | መሳፍንት |
|---|---|---|---|
| 1 | 3+8-11 | ልርጴጦምያውያን | ጉቶንያል |
| 2 | 3+12-31 | ሓአባውያን | ናእድ፣ ሴሜጋር |
| 3 | 4+1-5+31 | ከንዓናውያን | ዲቦራና ባራቅ |
| 4 | 6+1-10+5 | ሐንዲያማውያን | ጌዴዎን፣ ቶሳ፣ ኢያኢር |
| 5 | 10+6-12+1 | አሞናውያን | ዮፍታሄ፣ አብዳን፣ ኤሎም፣ ዓብደን |
| 6 | 13+1-16+31 | ፍልስጤማውያን | ሳምሶን |

## የመጽሐፉ ዋና ዓላማ

በመጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደምናየው እግዚአብሔር የተሰያዩ መሳፍንትን በማስነሳት የእስራኤልን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው እጅ ታድጓል፡፡ መሳፍንቱ ካከናወኑት የመታደግ ሥራ በስተጀርባ የእግዚአብሔር አዳኝነት መታየት አሰበት፡፡ መሳፍንቱ እንደማንኛውም ሰው የራሳቸው የሆነ ድካም የነበራቸው ሆነው ሳስ ነገር ግን እግዚአብሔር አብሯቸው በመቆሙ ብቻ ታሳሳቅ የማዳን ሥራዎችን ሲሠሩ ችለዋል፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የተሰጠው ሌላ እውነታ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ጌትነት ሥፍራ እንደነበራቸውና ይገዙለት እንደነበር የሚያትተው ክፍል ነው፡፡ ነሐፊው እስራኤልን የሚወቅስበት አንዱና ትልቁ ጉዳይም እስራኤላውን የአምላካቸውን ንጉሥነት በተደጋጋሚ የተጋፉበት ዘመን ነበር፡፡ በመሆኑም የቃል ኪዳኑ ስምምነት በሚያዘው መሠረት እግዚአብሔር ቁጣውን በሕዝቡ ላይ አወረደ (ዘሌዋ. 26+14-45፣ ዘዳግ. 28+15-68)፡፡ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው ተመልሰው ወደ እርሱ በሚጮሁበት ጊዜ እግዚአብሔር መሳፍንትን በማስነሳት የእስራኤልን መንግሥት ከፍጹም ጥፋት ጠብቋል፡፡

እሰመረጋጋት በበዛበት በዚያ ዘመን የእግዚአብሔርን አዳኝነት፣ ታማኝነት፣ ታጋሽነት እና መሐሪነት ከምን ጊዜውም በበሰጠ ሰሕዝቡ ጉልቶ የታየበትና የተገሰጠበት ወቅት ነበር፡፡ ያ ዘመን በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ የሠራበት አንድ ራሱን የቻለ በእስራኤላውያን ኑሮ የተከሰተ የታሪክ ምዕራፍ ነው፡፡ ይኼን የምንልበት ምክንያት በመጽሐፉ እንደምናየው የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች አልፎ ታሳሳቅ ሥራዎችን እንደሠራ በግልጽ ሰሰምንመስከት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈሱ ተሞልተው ታሳሳቅ ውጊያዎችን አካሂደዋል፣ አሸንፈውማል (መሳ. 3+10፣ 6+34፣ 11+29፣ 13+25፣ 14+6፣ 19፣ 15+14)፡፡

## መደምደሚያ

መጽሐፈ መሳፍንት የታሪክ መጽሐፍ እንደመሆኑ መጠን በከንዓን ምድር መውረስና በንጉሳዊው የአገዛዝ ዘመን መጀመር መሐል ገብቶ እንደድልድይ ያገለግላል፡፡ ሥነ-መለኮታዊ ይዘቱ አንድ ታላቅ የማይቀየር መንፈሳዊ መርሆ ላይ ተመስርቷል፡፡ ዘላለማዊ እውነታውም የእግዚአብሔር ሕግ መጠበቅ ሰላምና ደህንነት ያመጣል፤ አለመጠበቁ ደግሞ በጠላት እጅ መውደቅንና ሞትን ያስከትላል የሚል ግልጽ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ታላቅ ምህረትና ርህራሄ ራሳቸውን አዋርደው በንስሃ ለሚቀርቡት ሁሉ እጆቱን እንደበዛም አይተናል፡፡

በመጽሐፉ ላይ እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያት መሳፍንትን በማስነሳት ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው እጅ እንደታደገ አይተናል፡፡ እነዚህ በየጊዜው የተነሱ መሳፍንትም ቢሆን የራሳቸው የሆነ ድካም ነበራቸው፡፡ ቢሆንም በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልተውና በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ቆመው ጠላቶቻቸውን ድል ነስተዋል፡፡ ይኼ ወደፊት ለሚመጣው ታላቁ አዳኝና መሢሕ እንደጥላ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ በመጽሐፉ ላይ የይሁዳ ነገድ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በመለኮታዊ ኃይልና ቅባት ሕዝቡን ሊያሳርፍ ወደሚችለው ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመላክታል፡፡



# መጽሐፈ ሩት

መጽሐፈ ሩት በዘመነ መሳፍንት ይኖር ስለነበር አንድ ቤተሰብ ታሪክ የሚናገር መጽሐፍ ነው፡፡ በዚያን ዘመን መኖር ከባድ ነበር፡፡ ምክንያቱም ያለንጉሥ ያለሕግ ሁሉም እንደራሱ ፈቃድ ይመላለስ የነበረበት ዘመን በመሆኑ ነው (መሳ. 17+6)፡፡

## ጸሐፊው

ጸሐፊው ማን እንደሆነና የት እንደሆነ አይታወቅም፣ ብዙዎች ሳሙኤል እንደተጻፈ ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ውስጣዊ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሳሙኤል ሞት በኋላ የተጻፈ ነው፡፡

## የተጸፈበት ዘመን

1375-1050 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ይገመታል፡፡

## ታሪካዊ አቀማመጡ

በእስራኤል ታሪክ የጨለማ ዘመን የሚባልበት ሰዎች እግዚአብሔርን ሳይሆን ራሳቸውን ለማስደሰት ያለሥርዓት በኖሩበት ጊዜ ነበር (መሳ. 17÷6)፡፡

## ቁልፍ ጥቅስ

1+16 «ወደምትሄጂበት እሄዳለሁና በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ፣ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል፡፡»

## ዋና ገጸባሕርያት

ሩት፣ ኑኃሚንና ቦኤዝ

**ቁልፍ ቦታዎች፦** ሞአብ፣ ቤተልሔም

## ቁልፍ ቃላት

ዕረፍት፣ መቤዠት፣ ዋርሳ

## የመጽሐፉ ዓላማ

ሞአባይቱ ሩት ለምራትዋ ለኑኃሚን ታማኝ እንደነበረችና የዳዊት አያት በመሆን የኢየሱስ የዘር ግንድ ውስጥ እንደገባችና ጌታ ታማኞችን እንደሚያከብር ለማሳየት ነው፡፡

## የመጽሐፉ ልዩ ባህርይ

መጽሐፈ ሩት የዚያን ዘመን በነበረው ነው የጋብቻ ሁኔታ መሠረት ባል ሲሞት የቅርብ ዘመድ የሆነው የሟቹን ኃላፊነት እንደሚረከብ፣ ንብረቱን በመውሰድ፣ መዋጀትና መውረስ እንደነበረበት ያሳየናል:: ይህ ብዙ ጊዜ ወንድምን የሚመለከት ኃላፊነት ነው (ዘዳግ. 25፥5-10):: የሩት ባል የሞተው ያለ ልጅ ነበር:: ቦኤዝ የሩት የባልዋ ወንድም ሳይሆን ዘመዷ ነበር (ሩት 2፥1):: ሩት ቦኤዝን ልታገባውም እንደምትፈልግ ገለጸችለት (ሩት 3፥1-18) መሬትን መቤዠትም ስለሚያስፈልግና ሌላ የቅርብ ዘመድ ስለነበረእ ቦኤዝ ይጠቀማል:: ነገር ግን ሌላው የቅርብ ዘመድ ይህን ለማድረግ ባለመፍቀዱ (ሩት 4፥6፣ 7፣ 8) ቦኤዝ ፈቃደኛ ሆኖ እንዲያገባት መብቱን ይለቃል:: ስለዚም ህጉን ጠብቆ ቦኤዝ ሩትን አገባት የሟቹንም ስም ለማቆየት ወንድ ልጅ ወለደ (ሩት 4፥9-15)::

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ሁለት በሴት ሥም የተሰየሙ ጽሑፎች አንዱ ሩት ሞአባይቱ ሴት በእስራኤልና እስራኤላዊቷ አስቴር በባዕድ ምድር ናቸው:: አሕዛብን (ሞአባዊትና ከሎጥ ትውልድ የሆነችው እግዚአብሔርን በመፈለግ) እንዴት ዓለምን የሚያድነው የመሢሑ የዘር ግንድ ውስጥ እንድትገባ እንዳደረጋት ያሳየናል (ሩት 1፥16፣ ማቴ. 1፥5) ::
- የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት፣ ሁሉን ቻይነት፣ ምህረት፣ ቸርነትና ፍቅሩን የሚያሳይ ነው:: የመጽሐፉ ዋና ቃል መቤዠትን ሲያመለክት ወደ 23 ጊዜ ይህ ታሪክ ተጠቅሷል::

## አስተዋጽኦ

I. የኑሐሚንና የሩት ወደ ቤተልሄም መመለስ (1፥1-22)
II. የሩት ከቦኤዝ ጋር መተዋወቅ (2፥1-23)
III. የቦኤዝ ምላሽ ለሩት (3፥1-18)
IV. የቦኤዝ ሩትን ማግባት (4፥1-22)

1. የኑሐሚንና የሩት ወደ ቤተልሄም መመለስ (1፥1-22) ኑሐሚን ባልዋንና ልጆችዋን አጥታ እርዳታ በሚያስፈልጋት እድሜ ብቻዋን ወደ ሀገሯ ለመመለስ ስትነሳ ምራትዋ የሆነችው ሩት ልትተዋት ፈቃደኛ አልሆነችም:: ምንም እንኳን ከቤተሰቦቿ ከሀገሯና ከባህሏ ከምድሯ መለየት ከባድ ቢሆንም በፍቅር ኑሐሚንን ለመከተል እና አምላክኳን ለማምለክ ወስና ስትወጣ እናያታለን::

2. የሩት ከቦዔዝ ጋር መተዋወቅ (2፥1-23) ሩት በቦኤዝ ፊት ሞገስ ማግኘቷ ከነመተችው በላይ ብዙ ቸርነትን እንዳደረገላትና ሩትና ኑሐሚን ደስተኞች ሆኑ::

3. የቦኤዝ ምላሽ ለሩት (3፥1-18) ኑሐሚን በሰጠቻት መመሪያ መሠረት ሩት ወደ ቦኤዝ ወረደችና እግዚአብሔር በፊቱ ሞገስን ሰጣት:: በዚህም ምክንያት አትፍሪ



ብሎ እንዳጽናናትና ከእርሱ የቅርብ ዘመድ ቢኖርም እንኳን እርሱ ዋርሳ ካልሆናት ዋርሳ ለመሆን ፈቃደኛ እንደሆነ ነገራት ወደእማትዋም ባዶዋን እንዳትሄድ ገብስ ሰፍሮ አሸክሞ እንደላካት እናነባለን::

4. የቦኤዝ ሩትን ማግባት (4፥1-22) ቦኤዝ ሩትን ለመውሰድ ሽማግሌዎችን ስሙ ያልተጠቀሰ ሰብስቦ በደንቡና በአገሩ ሕግ መሠረት የቅርብ ዘመድዋን ፈቃደኝነት ጠይቆ ያም ሰው ፈቃደኛ ባለመሆኑ እርሱ አገባት:: ከዚያም ወንድ ልጅም እንደወለዱ፣ የንጉሥ ዳዊት አያቶች እንደሆኑና በመሢሑ የዘር ግንድ ሩት እንደጨመረች ታሪኩ ያስረዳናል::

## የመጽሐፈ ሩት ዋና ዋና ትምህርቶች

- ኑሃሚን ችግራቸውን ለመፍታትና ሩትን ለመርዳት ብልህ አማካሪ እንደሆነችና ሩትም የተሰጣትን ምክር ተቀብላ ሥራ ላይ በማዋሏ መልካም ኖላቸዋል:: በዚህ የመልካም ምክርንና የታዛዥነትን ጥቅም እንመለከታለን:: ቦኤዝ ስርዓትን ለማክበር በሚሠራው ሥራ እግዚአብሔር እንደረዳውና ሁኔታዎችን ሁሉ እንዳመቻቸለት እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ እንደሆነና ከምንፈልገው ነገር በላይ ሥርዓትንና ሕግን ለማክበር ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን እንረዳለን::
- ሩት ባታስበውም እንኳን እግዚአብሔር ዓላማውን እንደፈፀመባት ሁሉ በሰዎች ሕይወት ውስጥ እንደሚገባና ሁኔታዎችን እንደሚጠቀም፣ ለሰዎች ግድ እንደሚለውና የጌታን ሉዓላዊነት እናያለን::
- በምንም ዓይነት ሁኔታ ሰዎች ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር እስከሰጡ ድረስ ሁኔታዎችን ሁሉ እግዚአብሔር ለውጦ መልካም ነገር በማድረግ ሕይወታቸውን ሊከብርበት እንደሚቻለው ከዚህ ታሪክ እንገነዘባለን:: በመጨረሻም ሞአባዊቷ ሩት ከእስራኤል ጋር በደም ትውልድ ሳይሆን በእምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ተካፋይ እንደሆነች ስናጠና እግዚአብሔር ከባዶነት ወደ ሙላት ከሀዘን ወደ ደስታ ሁኔታዎችን የሚቀይር አምላክ እንደሆነ እንማራለን::

# 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል

## መግቢያ

የሁለቱም መጻሕፍት አርዕስት የተሰየመው የንጉሥ አገዛዝ በእስራኤል እንዲመሠረት እግዚአብሔር በተጠቀመበት በሳሙኤል ነው:: ነቢዩ ሳሙኤልም ሳኦልንና ዳዊትን ለንጉሥነት መቀባት ብቻ ሳይሆን ከንጉሥነት አገዛዝ ጋር ተጣምሮ በእሥራኤል የተጀመረውን አዲሱን የእግዚአብሔርን አመራር ያስተዋወቀ የመጨረሻው መስፍን ነበር:: ይህም ሳሙኤል በአገዛዙ ውስጥ እግዚአብሔርን በመወከሉ ምክንያት እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ ያለውን የአገዛዝ ድርሻ ግልጥ ያደርገዋል:: በዚህ አገዛዝ ሥርዓት ውስጥ የሳሙኤል ውክልና ከሙሴ ታሪክ ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው ቀጥለው ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይጠቁሙናል (መዝ. 99+6፣ ኤር. 15+1)::

ሳሙኤል የመጨረሻው መስፍን ሆኖ ብቅ ያለው 350 ዓመታትን በሸፈን የመሳፍንት አገዛዝ መጨረሻ ላይ ነበር:: የመጀመሪያው መጽሐፍ የ115 ዓመታትን ሂደት ሸፍኗል:: ይህም ከሳሙኤል የልጅነት ጊዜ እስከ ዳዊት አገዛዝ መጀመሪያ ያለው የጊዜ ገደብ መሆኑ ነው:: ሁለተኛው መጽሐፍ እስከ ዳዊት ሽምግልና ዘመን ያለውን ጊዜ ይሸፍናል (1ኛ ነገ. 1+1):: የጊዜ ገደቡ ግን በውል ያልታወቀ ነው:: ሳሙኤል በተጠራበት ዘመን እስራኤል በመንፈሳዊ ሕይወቷ ጨልማ የነበረችበት ጊዜ እንደሆነ መጽሐፉ ያስታውቃል:: ይህም ዘመን ዔሊ በክህነት እግዚአብሔርን ሲያገለግል የነበረበት ጊዜ ነው:: ስለዚህ ሳሙኤል ሕዝቡን ወደ እውነተኛ አምልኮ ይጣራ ነበር (የሐዋ. 3+24):: ሳሙኤልም ለመሳፍንትና ለንጉሥ አገዛዝ አገናኝና አያያዥ ድልድይ ነበር:: የመጽሐፉም ገጽታ በሳኦልና በዳዊት የአገዛዝ ታሪክ የተሞላ ሲሆን ሳኦል ባለመታዘዙ ፍጻሜው አሳዛኝ እንደሆነና ዳዊት ግን በመታዘዙ ፍጻሜው እንዳማረለት ይናገራል::

## የመጽሐፉ አከፋፈል ታሪክ

የሳሙኤል ሁለቱ መጻሕፍት ማለትም 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ቀደም ሲል በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚታወቁት እንደ አንድ መጽሐፍ ብቻ ነበር:: በኋላ ግን ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ ተብሎ የተከፈለ ሲሆን ይህም በጊዜ ሂደት ሰዎች የከፈሉት እንጂ አንድ በመሆኑ እንደስህተት ተቆጥሮ አይደለም:: ስለሆነም መጽሐፉ በሁለት መከፈል የጀመረው በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈውን ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ ቋንቋ በተረጐሙት ምሁራን ዘመን እንደሆነ ይታመናል:: ይህም አዲሱ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ሴፕቱዋጀንት በመባል ይታወቃል:: ሴፕቱዋጀንት የሚለው ቃል በግሪክኛ ሰባ ማለት ነው:: ይህም ስም የተሰጠው ብሉይ ኪዳንን ሰባ የሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በሰባ ቀናት ውስጥ መተርጐማቸው ስለሚታመን ነው:: በመሆኑም



እነዚህ ምሁራን መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ መጻሕፍት በማለት ከፋፍለውታል::

የመጽሐፉ አከፋፈል ከላይ በተገለጠው ብቻ አላበቃም:: ስለሆነም አከፋፈሉ ሊቀጥል ችሏል:: በዚሁ መሠረት ጄሮም የተባለው ሰው ከ382 እስከ 405 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ መካከል ሴፕቱዋጀንትን ወደ ላቲን ቩልጌት (Vulgate) በሚተረጉምበት ጊዜ እንደገና መጽሐፈ ሳሙኤልን አንደኛና ሁለተኛ ነገሥት በማለት ከፍሎታል:: በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን «ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ» ይባላል:: ይህ አባባል በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠውን መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ ማለት አይደለም:: ከሁለቱም መጻሕፍት አርዕስት ሥር ተጽፎ መገኘቱም የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችንም ከላቲኑ መጽሐፍ እንደተተረጐመ ያመለክታል:: በመጨረሻም መጽሐፉ በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስና (ከ500-900 ዓ.ም. እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር) በዘመናዊ ዘዴ በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ በመባል ተከፋፍሎ ይገኛል::

## ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን

የሁለቱም መጻሕፍት አርእስት በሳሙኤል የተሰየመ ቢሆንም ሳሙኤል ግን የጻፈው የመጀመሪያውን መጽሐፍ አብዛኛውን ክፍል ብቻ እንደሆነ ይታመናል:: ቀሪው ግን በእርሱ እንዳልተጻፈ ይታሰባል:: ይህን አመለካከት የሚከተሉ ስለሞቱ የሚናገረውን 1ኛ ሳሙኤል 25+1ን በመጥቀስ አስቀድሞ ስለሞተ በዚህ ምክንያት ቀሪው ክፍልና ሁለተኛው መጽሐፍ በርሱ የተጻፈ አይደለም በማለት ይህን ክፍል እንደማስረጃ ይጠቀሙበታል::

ሌላው አመለካከት ሁለቱም መጽሐፍት በሳሙኤል የተጻፉ ናቸው የሚል ሲሆን ማስረጃቸውም በ1ኛ ሳሙኤል 10+25 ላይ የተጻፈው ቃል ነው:: ቃሉም «ሳሙኤል የመንግሥቱን ወግ ነገረ በመጽሐፉም ጻፈው:: በእግዚአብሔርም ፊት አኖረው» የሚለው ነው::

በሦስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ሃሣብ በእርግጥ ሳሙኤል ሁለቱንም ጽፏል:: ነገር ግን ናታንና ጋድ ደግሞ በሳሙኤል መጻሕፍት የተደረጉትን አንዳንድ ድርጊቶችን በመጻፍ ተካፋይ ሆነዋል የሚል ነው:: የዚህ ሃሣብ መሠረቱ በ1ኛ ዜና 29+29 ነው:: «የንጉሡም የዳዊት የፊተኛውና የኋለኛው ነገር እነሆ በባለራእዩ በሳሙኤል ታሪክ፣ በነቢዩም በናታን ታሪክ በባለራዕዩም በጋድ ታሪክ ተጽፏል»:: ይህ ሃሣብ ራሱን ሲጠቀልል ሁለቱም መጻሕፍት በሳሙኤልና በሌሎችም ተጽፈዋል የሚለውን ሃሣብ ይይዛል:: በሌላ አባባል ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ሁለቱ የተጠቀሱት ሰዎች የቀረውን ክፍል ጽፈውታል ከሚለው ሃሣብ ጋር ተመሳሳይነት አለው:: የተጻፈበት ዘመንም በ930 ዓ.ዓ. እንደሆነ ይገመታል::

አራተኛው አመለካከት ጸሐፊው በእርግጠኝነት አይታወቅም የሚለው ነው። የዚህ አሣብ ማስረጃ መጻሕፍቱ ጸሐፊውን አይገልጡትም ይላል። ይህ አመለካከት በ1ኛ ሳሙኤል 10፥25 ላይ የተጻፈውን አሳብ ያልተመለከተ ይመስላል። ምክንያቱም በጽሑፉ የሳሙኤል እጅ እንዳለበት ይጠቁማል።

አንዳንዶች የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ ማን እንደሆነ አይታወቅም የሚለውን አመለካከት ይመርጣሉ። ምክንያታቸውን ጨምረው ሲሰጡም የ1ኛ ሳሙኤል መጨረሻ አካባቢና የ2ኛ ሳሙኤል ታሪክ በሙሉ የተፈጸመው እርሱ ከሞተ በኋላ በመሆኑ ነው ይላሉ።

## የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ አስተዋጽኦ

I. የዔሊና የሳሙኤል ታሪክ (1ሳሙ. 1-7)
II. በሳሙኤል መሪነት የንጉሣዊ አገዛዝ ምስረታ (1ሳሙ. 8-12)
III. የሳኦል መንግሥት ውድቀት (1ሳሙ. 13-15)
IV. የዳዊት መንግሥትና የሳኦል አሳዛኝ ፍጻሜ (1ሳሙ. 16፥1-2ሳሙ. 5፥5)
V. የዳዊት የመንግሥቱ ክንውንና ክብር (2ሳሙ. 5፥6-9፥12)
VI. የዳዊት የአገዛዝ ድክመትና የውድቀት ገጽታ (2ሳሙ. 10-20)
VII. የዳዊት መንግሥት የመጨረሻ ገጽታው (2ሳሙ. 21-24)

ገና ከጅምሩ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል አንድ መጽሐፍ እንደነበረ አስቀድመን ተመልክተናል። ስለዚህም የሁለቱን አስተዋጽኦ አንድ ላይ ማየቱ ችግር የለውም።

### 1. የዔሊና የሳሙኤል ታሪክ (1ኛ ሳሙ. 1-7)

ሳሙኤል የተወለደው ዔሊ ካህን ሆኖ እግዚአብሔርን ያገለግል በነበረበት ዘመን ስለነበር 1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 1 የሁለቱን ታሪክ በጣምራ ያነሳል። ሆኖም 1ሳሙ. 1-2 በሳሙኤል መወለድ ላይ በማተኮር ታሪኩን ያነሳዋል። በምዕራፍ 2-3 የወጣትነት ዘመኑንና ጥሪውን የምናይበት ሲሆን ከእግዚአብሔር የሆነውንም ፍርድ በዔሊ ላይ ማስተላለፉንም በዚሁ ክፍል ተገልጦ እናገኘዋለን። ይህም ፍርድ የልጆቹ ኃጢአት ውጤት ነበር (1ኛ ሳሙ. 3፥11-18)።

የእግዚአብሔር ፍርድ በዔሊና በቤቱ ላይ ሊጀምር ሲል እስራኤል በፍልስጥኤም ተሸነፈ። የእግዚአብሔር የቃልኪዳኑ ታቦት ተማረከ ዔሊና ልጆቹም ሞቱ። ከዚህ ነገር በኋላም የታቦቱን መመለስና ሳሙኤል እስራኤልን ከፍልስጥኤም ማዳኑ ተዘግቦ እናገኘዋለን (1ኛ ሳሙ. 4-7)።



### 2. በሳሙኤል መሪነት የንጉሣዊ አገዛዝ ምስረታ (1ኛ ሳሙ. 8-12)

እንደምኞታቸው እንዲሆንላቸው ለሳሙኤል ምላሹን አሳወቀ (1ኛ ሳሙ. 8)። ሳሙኤልም ሳኦልን ለብቻው ለንጉሥነት ቀባው (1ኛ ሳሙ. 9፥1-10፥16) ሳኦል እንደገና በምጽዳ ዕጣ ወድቆበት በአደባባይ በሕዝብ ፊት ተመረጠ (1ኛ ሳሙ. 10፥17-27)። በዚህ ክፍል የሳኦል የመደበቅ ምስጢሩ የትህትና ጉዳይ እንደሆነ ብዙዎች የሚናገሩት ነው (1ኛ ሳሙ. 9፥20)። ሳኦል ከዚህ በኋላ አሞናዊያንን መምታት መቻሉ በእስራኤላዊያን ዘንድ የንጉሥነቱ ማረጋገጫ ሆነለት (ቁጥር 11-13)። በመጨረሻም የሳኦል ንግሥና ታድሶ እንደቀጠለ እንመለከታለን። ይህም በሳሙኤል አማካይነት በጌልጌላ ተፈጻሚነትን አገኘ። ይህ የንግሥና ክንውን የንጉሥ አገዛዝ በእስራኤል በይፋ መጀመሩን የሚያመለክት ነው (1ኛ ሳሙ. 11፥14-15)። ቀሪው ክፍል የሚያተኩረው በሳሙኤል የስንብት ቃል ላይ ነው (1ኛ ሳሙ. 12)።

### 3. የሳኦል መንግሥት ውድቀት (1ኛ ሳሙ. 13-15)

በዚህ ክፍል የምናገኘው የሳኦልን ውድቀት ዝርዝር ሁኔታ ነው። ሳኦል መውደቅ የጀመረው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣስ እንደሆነ ተጽፎአል (1ኛ ሳሙ. 13፥8-14)። ወደ እግዚአበሔርም ቢጸልዮም አልተሰማለትም (1ኛ ሳሙ. 14፥37)። ከዚህ በኋላ ሳኦል በራሱ መንገድ በመሄድ ውድቀቱን አፋጥኗል (1ኛ ሳሙ. 15)።

### 4. የዳዊት መንገሥና የሳኦል አሳዛኝ ፍጻሜ (1ሳሙ. 16፥1-2 ሳሙ. 5፥5)

ሳኦል ካለመታዘዙ የተነሳ የእግዚአብሔር መንፈስ ራቀው። ለክፉ መንፈስም ሥቃይ ተጋለጠ ከዚህም የተነሳ ዳዊት ከተቀባ በኋላ ሳኦልን ለማገልገል ወደ ቤተመንግሥት እንደተጠራ ታሪኩ ተጽፎ ይገኛል (1ኛ ሳሙ. 16-26)። ብዙ የተለያዩ አከራካሪ ሃሣቦች የተሰጡበት ነጥብ በዚሁ ክፍል የሚገኝ ሲሆን ቃሉም «የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ። ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሠቃየው» የሚለው ነው። ይህንንም ቃል ለመተርጐም ከባድ እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይናገራሉ። ስለዚህም የተነሳ ቀጥሎ ያሉት የአመለካከት ልዩነቶች ሊፈጠሩ ችለዋል።

ሀ. በሳኦል ርኩስ መንፈስ ገብቶበታል። ምክንያቱም በቅጣት መልክ ከእግዚአብሔር የተላከው ይህ ርኩስ መንፈስ ስሜቱን፣ ሃሣቡንና አስተሳሰቡን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር ስላደረገው ነው በማለት ይደምድማሉ።

ለ. ሌሎች ደግሞ ይህ ክፉ መንፈስ ሀሰተኛ መልእክተኛ ነው በማለት ይናገራሉ። ለዚህም 1ኛ ነገ. 22፥20-23ን ይጠቅሳሉ።

ሐ. ሌላው አመለካከት ደግሞ ይህ ክፉ መንፈስ ተብሎ የተነገረው እግዚአብሔር በሳኦል ልብ ውስጥ የፈጠረው ያስመርካትና ያስመደሰት መንፈስ ነው ይላሉ:: መሳፍንት 9÷23 «እግዚአብሔር በአቤሜሌክና በሴኬም ሰዎች መካከል ክፉን መንፈስ ሰደደ:. የሴኬምም ሰዎች በአቤሜሌክ ላይ ተንኰል አደረጉ» (መሳ. 9÷23)::

የተጠቀሰው ክፉ መንፈስ በሰው ልብ መሸጉ ክፋትን እንደሚሠራ ለመግለጽ የተጠቀሰ ይመስላል::

መ. ይህ ክፉ መንፈስ ሳኦልን እንዲያስቃይ ከእግዚአብሔር የተላከ እንደሆነና ባለመታዘዙም ምክንያት የደረሰበት ፍርድ እንደሆነ የሚናገር ሃሣብ ነው:: እግዚአብሔርም በኢጋንንት ላይ ባለሥልጣን እንደሆነ ራሱን የገለጠበት ነው የሚል ሃሣብ ነው:: ይህን አመለካከት የሚከተሉ ሰዎች በተጨማሪም ክፉ መንፈስ የሚለውን የሳኦል ሕይወት በጨለማና በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ መውደቁን ለመግለጽ የተሰጠ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ይላሉ::

ሠ. ሌሎች ደግሞ ክፉ መንፈስ ሊሆን አይችልም ይላሉ:: ምክንያታቸውም ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ሊወጣ አይችልም የሚለው ነው::

የዳዊት መሰደድ፣ የሳኦልና የልጆቹ ሞትም በዚሁ ክፍል ውስጥ ተገልጧል (1ኛ ሳሙ. 27-31):: ከስደቱም ባሻገር ዳዊት አስቀድሞ በይሁዳ ላይ የነገሠ ሲሆን (2ኛ ሳሙ. 1-4) በመጨረሻም በመላው እስራኤል ላይ ነግሦአል (2ኛ ሳሙ. 5÷1-5)::

## 5. የዳዊት የመንግሥቱ ክንውንና ክብር (2ኛ ሳሙ. 5÷6-9+12)

በአገዛዝ ሂደቱ ዳዊት ከኢያቡሳዊያን ጋር በመዋጋት ኢየሩሳሌምን ሊይዝ ቻለ (2ኛ ሳሙ. 5÷6-10) ዳዊትም ዘመቻውን በመቀጠል ፍልስጥኤማዊያንን መታ:: ከዚህም የተነሳ ድንበሩ ሊሰፋና ሊስፋፋ ችሏል (2ኛ ሳሙ. 5÷17-25):: ከዚህ ሁሉ በኋላ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም አመጣ (2ሳሙ. 6):: እግዚአብሔርም ደግሞ ዘሮቹ በእስራኤል ላይ የመንገሥ መብታቸው ለዘላለም እንደሚቀጥል ቃል ገባለት (2ኛ ሳሙ. 7):: በመጨረሻም ይህ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ በመፈጸም እግዚአብሔር በዳዊት ቤት በኩል ያቀደውን ዘላለማዊ ዕቅድ ገለጠ:: ኢየሱስ እንደ ዳዊት በእስራኤል ላይ ብቻ ሳይሆን በሕዝቦች ሁሉ ላይ ንጉሥና ጌታ ነው:: ይህም ደግሞ እንደገና በሺህ ዓመቱ የምድር አገዛዝ የሚረጋገጥ ይሆናል (ራዕ. 20÷4):: የክርስቶስ ተምሳሌት የሆነው ዳዊት መንግሥቱን ከእስራኤል ድንበር ውጪ ማስፋቱና የተሾመበትን ሕዝብ በጽድቅ መምራቱ ተዘግቧል (2ኛ ሳሙ. 8):: ከዚህም ሌላ ዳዊት ከዮናታን ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነበረ (2ኛ ሳሙ. 9)::



## 6. የዳዊት የአገዛዝ ድክመትና የውድቀት ገጽታ (2ኛ ሳሙ. 10-20)

የዳዊት አመራር በአብዛኛው ጽድቅን የተላበሰ ቢሆንም በሂደት ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይቃረን ክፉ ነገር እንደፈጸመ ከላይ በተጻፈው ክፍል ውስጥ ተጽፎ እናገኘዋለን:: ይህም ከአሥርቱ ትዕዛዛት መካከል አንደ አንዱ የተደነገገውን አታመንዝር የሚለውን ትዕዛዝ በመጣስ የኦርዮ ሚስት ከሆነችው ቤርሳቤህ ጋር በማመንዘር ውድቀት ውስጥ ተገኝቷል (2ሳሙ. 11፥1-5)::

ዳዊት ከላይ በተገለጠው የኃጢአት ድርጊት ብቻ አላበቃም:: ነገር ግን ኃጢአቱን ለመሸፈን የቀየሰው ዘዴ ውድቅ ሆኖ ስላገኘ የሴቲቷን ባል ኦርዮንን በማስገደል ሁለተኛውን አስከፊ የኃጢአት ድርጊት ፈጽሟል (2ኛ ሳሙ. 11÷6-21):: ይህም ከባድ የኃጢአት ሥራው በመንግሥቱ ላይ ጥቁር ነጥብ ከመጣሉም በላይ ያከበረውን እግዚአብሔርን እጅግ አሳዝኖታል (2ሳሙ. 12÷1-10):: ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ቅጣትን እንደበየነበት ተጽፎ ይገኛል (2ሳሙ. 12÷10-14):: እግዚአብሔር የተናገረው ክፉ ነገር ሁሉ በዳዊት ሕይወት አልፏል:: የተወለደው ሕፃን ሞቷል (2ኛ ሳሙ. 12÷15-23):: አምኖን እህቱን ትዕማርን አስነወራት (2ሳሙ. 13÷7-14):: በዚህም ምክንያት በአቤሴሎም ትዕዛዝ ተገደለ (2ኛ ሳሙ. 13÷23-36):: አቤሴሎም ደግሞ ከአባቱ ቁባቶች ጋር ተኛ (2ኛ ሳሙ. 16÷22) በመጨረሻም አቤሴሎም ሞተ (2ኛ ሳሙ. 18÷9-15):: ይህ ሁሉ የሚያመለክተን እግዚአብሔር በዳዊት ላይ የላከውን ፍርድ ነው::

## 7. የዳዊት መንግሥት የመጨረሻ ገጽታው (2ሳሙ. 21-24)

ምንም እንኳን ዳዊት በአገዛዙ ሂደት ውስጥ በአንድ አጋጣሚ፣ የፈጸመው ኃጢአት ቢኖርም የመንግሥቱ ፍጻሜ ግን አስከፊ ገጽታ አልነበረውም:: ይልቁንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈፀመ (2ኛ ሳሙ. 21) እግዚአብሔርን ስለማዳኑ እያመሰገነና መስዋዕት እያቀረበ በጽድቅ አመራር የመንግሥቱን አገዛዝ ጠቅልሏል (2ሳሙ. 22-24):: ሉቃስ የጻፈውም ሃሣብ ከዚህ ጋር የሚስማማ ነው (የሐዋ. 13÷36)::

## 8. ሥነ መለኮታዊ መልእክት

የእግዚአብሔርን አመራር መናቅ የመከራን ዋጋ እንደሚያስከፍል የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው:: ይህ ሕዝብ በሳሙኤል ዘመን እግዚአብሔርን ወደ ጐን ትተው ምድራዊ ንጉሥን ከመረጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በከባድ ፈተናና ችግር ማለፋቸውንና መኖራቸውን ዛሬም በዘመናችን ደርሰንበት አይተናል:: እግዚአብሔር ደግሞ በባሕርይው ቅዱስ ስለሆነ ኃጢአትን እንደሚፀየፍና እንደሚቀጣም የመጽሐፉ መልእክት በግልጥ

ያስቀምጣል። ለእግዚአብሔር ያለመታዘዝም ውጤት ኪሣራና መጨረሻውም ሞትን እንደሚያስከትል የሳኦል ታሪክ ትልቅ ማስረጃ ነው።

በአንጻሩም ደግሞ ሰው ከኃጢአቱ ንስሃ ቢገባና ቢመለስ እግዚአብሔር ይቅር ባይና ቸር መሆኑን መጽሐፉ ከዳዊት ሕይወት በግልጽ ያስተምራል። በአጠቃላይ ቀምነገሩ ጅማሬው ሳይሆን እስከ መጨረሻው እግዚአብሔርን እየታዘዙ መኖርና ብቻ ከእግዚአብሔር ዋጋ እንደሚያስጥ የሁለቱ ነገሥታት ታሪክ በጥብቅ ያስገነዝበናል። ስለዚህ ፍጻሜአችን እንደ ሳኦል ሳይሆን እንደ ዳዊት ሆኖ እንዲፈጸም መጽሐፍ ቅዱሳችን ያሳስባል። በአገልግሎታችንም ችላ ባይነትን አስወግደን እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ እንድናገለግልና ፍጻሜው ካላማረው ከዔሊ ዓይነት አገልግሎት እንድንጠነቀቅም መጽሐፉ መለኮታዊ መልዕክቱን ያስተላልፍልናል።



# መጽሐፈ ነገሥት (1ኛና 2ኛ)

## መግቢያ

ወደ አንደኛ እና ሁለተኛ ነገሥት መጻሕፍት አሰሳ ከመግባታችን በፊት ስለ መጻሕፍቱ አጠቃላይ ሁኔታ ማየቱ አስፈላጊ ይሆናል። የመጻሕፍቱን ስያሜ ብንመለከት ስለመጻሕፍቱ ይዘት ትንሽ ፍንጭ ልናገኝ እንችላለን። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የመጻሕፍቱ ስም «ነገሥት» ተብሎ ተተርጉሟል። በመጀመሪያ ስሙ የተሰጠበትን ምክንያት ስናይ መጻሕፍቱ ከመስፍኑና ነቢዩ ሳሙኤል በስተቀር ስለነበሩት የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት ሕይወትና የግዛት ዘመን በሰፊው ስለሚዘግቡ ነው። በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱ መጻሕፍት እንደ አንድ መጽሐፍ ሆነው በአንደኛና በሁለተኛ ሳሙኤል መጻሕፍት ላይ የተጀመረው ታሪካዊ ዘገባ ቀጥያ ናቸው።

የመጀመሪያው የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፉን ሳይከፋፍል እንደ አንድ መጽሐፍ ሲያስቀምጥ፤ የግሪኩ ማለትም ሰፕቱአጀንት ደግሞ ለሁለት ከፍሎ ያስቀምጠዋል።

## ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን

የነገሥት መጽሐፍ ጸሐፊ ማንነት በግልጽ አይታወቅም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት መጽሐፉ የተጻፈው በአንድ ሰው ብቻ ሳይሆን ይችላል ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ በአንድ ሰው ነው በማለት የተለያየ አቋም ያንፀባርቃሉ። መጽሐፉ በአንድ ሰው ለመጻፉ እንደማስረጃ የሚቀርቡ ነጥቦችን እንመልከት።

1. የነገሥታቱ የንግስና ዘመን ጅማሬና ፍጻሜ ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል አንድ ዓይነት ነው። ለምሳሌ:- (1ኛ ነገ. 14+31፣ 15+1-3፣ 23-26)

2. በተደጋጋሚ የተጠቀሱ ቃላትና ሐረጎች፣ ለምሳሌ:-
   «... የቀረውም ... ነገር ሁሉ... የተደረገውም ሁሉ ...» (1ኛ ነገ. 15+23፤ 14+19)።
   «... የተጻፈ አይደለምን?...»
   «... ለዓመታት ነገሠ... የእናቱም ስም...» (1ኛ ነገ.14÷21)

## ጸሐፊው

ከጥንት ጀምሮ በአይሁዳውያን ሊቃውንት ዘንድ የመጽሐፉ ጸሐፊ ነብዩ ኤርምያስ እንደሆነ ይታመናል። ይህንን ሃሣብ የሚያጠናክሩ መረጃዎች ከመጽሐፉ ውስጥ ማየት ይቻላል። ለምሳሌ:- 2ኛ ነገሥት 24÷18-25÷20 እና ኤርምያስ 52 ስናስተያየው በሁለቱም ሥፍራዎች ላይ የተጻፈው የቃሉ ይዘት በጣም አስደናቂ የሆነ መመሳሰል ይታይበታል።

ሌላው ደግሞ የኢዮስያስና ከእርሱ ቀጥሎ በነገሡት ነገሥታት ታሪክ በሚያወራው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ የኤርምያስ ስም አለመጠቀሱ አንድ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ኤርምያስ ነው ጸሐፊው ከተባለ ጸሐፊው የራሱን ስም የሚጽፍበት ምክንያት ላይኖረው ይችላልና።

ይሁን እንጂ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የመጽሐፉ ክፍል (በተለይ የመጨረሻ ምዕራፎቹ) በኤርምያስ ሊጻፉ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም ኤርምያስ በስተመጨረሻ የተጻፉት ምዕራፎች ከመጻፋቸው በፊት በግብጽ አገር እንደነበር በትንቢተ ኤርምያስ 43፥1-8 ይናገራል።

ስለዚህም የተወሰነውን የመጽሐፉን ክፍል ለመጻፍ ከኤርምያስ ሌላ አንድ ሰው ወይም ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመቱ ስህተት አይሆንም። ከኤርምያስ ሌላ በቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ዕዝራና ሕዝቅኤል እንደጻሐፍት ተጠቁመዋል።

አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት፣ ጸሐፊው በባቢሎን ምርኮ ውስጥ የነበረ እንደሆነ ይስማማሉ። የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ ለመረጃነት የተጠቀመባቸው ዋቢ መጻሕፍት፦

በ1ኛ ነገሥት 11፥41 → «በሰሎሞን ታሪክ መጽሐፍ»
1ኛ ነገሥት 14፥19፤ 29 → «በእስራኤል ነገስታት ታሪክ መጽሐፍ» ተጠቅሷል።

በእነዚህ ቀደምት ዋቢ መጻሕፍት ጥንቅር ተሳታፊ ከነበሩት ሰዎች ውስጥ አንዳንዶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ስማቸው ተጠቅሷል። ለምሳሌ፦

- 2ኛ ዜና መዋዕል 12፥15 ሸማያና አዶ
- 2ኛ ዜና መዋዕል 26፥22 ኢሳይያስ
- 2ኛ ዜና መዋዕል 32፥32 ኢሳይያስ
- 1ኛ ነገሥት 16፥1 ኢዩ ይገኙባቸዋል።



## የተጻፈበት ዘመን

አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን መጽሐፉ ከ586-539 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ውስጥ ተጽፎ ሊሆን ይችላል በሚለው ሃሣብ ይስማማሉ። የ1ኛና የ2ኛ ነገሥት የጊዜ ቅደም ተከተል በተመለከተ የብሉይ ኪዳን ት.መ.ማ. 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3 ገጽ 4 ላይ ተመልከት።

## የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

## የአንደኛ መጽሐፈ ነገሥት አስተዋጽኦ

1. አንድነቱ የተጠበቀው ግዛት (1፥1-11፥43)

   - የሰሎሞን መንገስ (1፥1-3፥1)
   - የሰሎሞን ጥበብ (3፥2-4፥34)
   - የሰሎሞን ቤተመቅደስ (5፥1-8፥66)
   - የሰሎሞን ዝና (9፥1-10፥29)
   - የሰሎሞን ውድቀት (11፥1-43)

2. የተከፋፈለው ግዛት (12፥1-22፥53)

   - በግዛቱ የተፈጠረው መታወክ (12፥1-24)
   - የኢዮርብአም ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (12፥25፤ 14፥20)
   - የሮብዓም ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (14፥21-24)
   - የአብያም ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (15፥1-8)
   - የአሳ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (15፥9-24)
   - የናዳብ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15፥25-31)
   - የባኦስ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15፥32-16፥7)
   - የኤላ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (16፥8-14)
   - የዘምሪ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (16፥15-20)
   - የዘንበሪ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (16፥21-28)
   - የአክዓብ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (16፥29-22፥40)
   - የኢዮሳፍጥ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (22፥41-50)
   - የአካዝያስ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (22፥51-53)

## የሁለተኛ መጽሐፈ ነገሥት አስተዋጽኦ

**1. የተከፋፈለው ግዛት (1፥1-17፥41)**

   - የአካዝያስ (የአክአብ ልጅ) ዘመ መንግሥት በእስራኤል (1፥1-18)
   - የኢዩራም (የአክዓብ ልጅ) ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (2፥1-8፥15)
   - የኢዮራም (የኢዮሳፍጥ ልጅ) ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (8፥16-24)

- የአካዝያስ (የኢዮራም ልጅ) ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (8+25-29)
- የኢዩ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (9+1-10-36)
- የጎቶልያ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (11+1-16)
- የኢዩአስ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (11+17-1+21)
- የኢዩአካዝ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (13+1-9)
- የዩአስ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (13+10-25)
- የእሜስያስ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (14+1-22)
- የኢዮርብዓም ሁለተኛ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (14+23-29)
- የዓዛርያስ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15+1-7)
- የዘካርያስ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15+8-12)
- የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15+13-15)
- የምናሔም ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15+16-22)
- የፋቂስያስ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15+23-26)
- የፋቁሄ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (15+27-31)
- የኢዮአታም ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (15+32-38)
- የአካዝ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ (16+1-20)
- የሆሴዕ ዘመነ መንግሥት በእስራኤል (17+1-41)

2. የይሁዳ ግዛት፣ መንግሥታት (18+1-25+30)

- የሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት (18+1-20-21)
- የምናሴ ዘመነ መንግሥት (21+1-18)
- የአሞጽ ዘመነ መንግሥት (17+1-41)
- የኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት (22+1-23+30)
- የኢዮአክስ ዘመነ መንግሥት (23+31-33)
- የኤልያቄም ዘመነ መንግሥት (23+34-24+7)
- የዩአኪን ዘመነ መንግሥት (24+8-16)
- የሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት (24+18-25+21)
- የጎቶልያስ ዘመነ መንግሥት (25+22-26)
- የንጉሥ ዩአኪን ከእስር መፈታት (25+27-30)

## የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት

ስለመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት በምንናገርበት ጊዜ በመጽሐፉ ውስጥ የሚንፀባረቀው አንድ ወጥ የሆነ አመለካከት አይደለም። ነገር ግን የተለያዩ ሐሳቦችና ክንዋኔዎች ድምር ውጤትን በሚያሳይ መልኩ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከእስራኤላውያንና ከአሕዛቦች ጋር የነበረውን ግንኙነት እንደዚሁም በእስራኤላውያንና በአሕዛብ መካከል የነበረውን ግንኙነት ጭምር በሚያሳይ መልኩ ነው። በመሆኑም ከዚህ ቀጥለን በመጽሐፉ ውስጥ ከተጠቀሱት ዓበይት ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹን ለመዳሰስ እንሞክራለን።



## እግዚአብሔር

ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ባሕርይ በመጽሐፈ ነገሥት ላይ በብዛት ተዳሷል። በመጽሐፉ ላይ «እግዚአብሔር» (YAHWEH) የሚለው ቃል ከ500 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። ባሕርይው በስምም በተግባርም ተገልጧል፤ ለምሳሌ:-

- **«የሠራዊት ጌታ» ወይም «የሠራዊት አምላክ»** (1ኛ ነገ. 18+15፣ 19+10፣ 14፣ 2ኛ ነገ. 19+31) ይህ ቃል ታላቅነቱንና ሁሉን ቻይነቱን ያሳያል።
- ብቸኛ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 18+24)
- የሚመስለው ማንም የሌለ አምላክ መሆኑ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 8+23)
- ፈጣሪ እንደሆነ ተገልጿል (2ኛ ነገ. 19+15)
- ሕይወት ሰጪ አምላክ መሆኑ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 17+21)
- ሕያው አምላክ መሆኑ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 18+15) እንዲሁም በቃለ መሐላ መልክ የእርሱ ሕያውነት ተገልጿል፤ ለምሳሌ «ሕያው እግዚአብሔርን» የሚለው አባባል በብዙ ቦታ ተጠቅሷል፣ (1ኛ ነገ. 17+12፣ 18+10፣ 15፣ 22+14፣ 2ኛ ነገ. 2+4፣ 6)።
- ከሁሉም በላይ መሆኑ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 8+27፣ 2ኛ ነገ. 2+1-12)
- በሁሉም ሥፍራ በአንድ ጊዜ የሚገኝ መሆኑ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 8+27፣ 20+28)
- በመንፈሱ አማካኝነት በቤተመቅደስ በሕዝቡ መካከል የሚኖርና ከሕዝቡ አምልኮና ምስጋና የሚቀበል አምላክ መሆኑ ተገልጿል (1ኛ ነገ. 8፣ 3፣ 12፣ 57፤ 2ኛ ነገ. 19+15፣ 1ኛ ነገ. 5+3፣ 5፤ 8+43፤ 1ኛ ነገ. 18+12፤ 2ኛ ነገ. 17+32-34፣ 39፣ 41፤ 1ኛ ነገ. 1+48፣ 8+15፣ 56)።
- ሕግ ሰጪ አምላክ እንደመሆኑ መመሪያንና ትዕዛዝን ወደ ሕዝቡ ያስተላልፋል ስለሆነም ከሕዝቡ ዘንድ መታዘዝንና መታመንን ይጠብቃል (1ኛ ነገ. 9+4፣ 13+21፣ 2ኛ ነገ. 18+5-6)።
- ስሙ ለሌሎች መታወጅና መነገር እንዳለበት ተገልጿል (1ኛ ነገ. 8+60፣ 2ኛ ነገ. 19+19)።
- በተለያዩ አስደናቂ ክንዋኔዎችና ክስተቶች በተግባር ራሱን የሚገልጽ አምላክ ነው (2ኛ ነገ. 20+11)። እንደዚሁም ድምጹን የሚያሰማ እና ለሕዝቡ በነቢያቱ በኩል የሚናገር አምላክ እንደሆነ በመጽሐፉ እናነባለን።

## የእግዚአብሔር የታሪክ ባለቤትነት

«እግዚአብሔር የታሪክ ባለቤት ነው» ስንል በሉዓላዊነቱ የበላይ ገዥ ሆኖ በምድር የሚከናወኑትን ነገሮች በሙሉ ይቆጣጠራል ማለታችን ነው። የእግዚአብሔርን የታሪክ ባለቤትነት ከሚያሳዩ ነገሮች አንዳንዶቹን ከመጽሐፉ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

- በምድር ነገሥታት ግዛት ላይ እግዚአብሔር የበላይ ገዥ ነው (2ኛ ነገ. 19፥15)
- የምድር ነገሥታትን ያስነሳል፤ የታሪክንም ሂደት ይቆጣጠራል (1ኛ ነገ. 17፥20-23፤ 23፥27)
- ሕዝቡን ለመቅጣት የአሕዛብ ነገሥታትን ይጠቀማል (2ኛ ነገ. 24፥2፤ 1ኛ ነገ. 14፥15)
- እግዚአብሔር ቁጣው የሚነድና በሕዝቡ ላይ እውነተኛ ፍርድን የሚያመጣ አምላክ መሆኑ ተገልጿል። የእግዚአብሔር ቁጣ በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፤ ለምሳሌ በበሽታ መልክ (2ኛ ነገ. 15፥5)፤ በረሃብ/ድርቅ/ (2ኛ ነገ. 1፥12)፤ የተለያየ መከራን በመላክ ሊሆን ይችላል (1ኛ ነገ. 9፥9፤ 2ኛ ነገ. 6፥33)
- ጸሎትን ሰምቶ የሚመልስ አምላክ መሆኑ ተነግሯል፤ የሰለሞን ፀሎት (1ኛ ነገ. 8፥22-54)፤ የሕዝቅያስ ጸሎት (2ኛ ነገ. 19፥14-19)፤ የሌሎችም ተሰምቷል (1ኛ ነገ. 19፥4፤ 2ኛ ነገ. 6፥17፤ 13፥4፤ 20፥2፤ 11)
- እግዚአብሔር ታዳጊ አምላክ እንደሆነ ተጠቅሷል (2ኛ ነገ. 13፥5፤ 18፥30-35፤ 19፥6-7፤ 35-37)።
- ድልን ይሰጣል (2ኛ ነገ. 5፥1)፤ ይቅርታን ያደርጋል (2ኛ ነገ. 5፥18)።
  - ጥበብን ይሰጣል (1ኛ ነገ. 3፥28፤ 4፥29፤ 5፥12፤ 10፥24)
  - በመንፈሱ ይሠራል (1ኛ ነገ. 18፥12፤ 2ኛ ነገ. 2፥16)
  - በኃይሉ ያስታጥቃል (1ኛ ነገ. 18፥46፤ 2ኛ ነገ. 3፥15)

## የእግዚአብሔር አዳኝነት

«ሕዝብህ እስራኤል አንተን ስለበደሉ በጠላቶቻቸው ፊት ድል በተመቱ ጊዜ ወደአንተ ቢመለሱ ስምህንም ቢያከብሩ በዚህም ቤት ቢጸልዩና ቢለምኑህ አንተ በሰማይ ስማ፤ የሕዝብህንም የእስራኤልን ኃጢአት ይቅር በል ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠሃት ምድር መልሳቸው» (1ኛ ነገ. 8፥33፤ 34)። ከላይ የተጠቀሰው የሰለሞን ጸሎት የእግዚአብሔር ምህረትና አዳኝነትን ተስፋ የሚያደርግ ጸሎት ነበር። ሕጉን መተላለፍ ቅጣትና ፍርድን እንደሚያመጣ ሁሉ ሕጉን መጠበቅ ደግሞ ምህረትንና



በረከትን ያመጣል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን የተስፋ ቃሎች ማየቱ ይበቃል (1ኛ ነገ. 9፥5፤ 1ኛ ነገ. 11፥32፤ 34-36)።

## የእግዚአብሔር ድምጽ በነቢያት ተስተጋብቷል

በመሪዎቹና በነቢያቱ አማካኝነት እግዚአብሔር ለእስራኤል በሙሉ ድምጹን አሰምቷል። በየዘመኑ የተነሱ (አንድ ወይም ከአንድ በላይ) የእግዚአብሔር ቃል አቀባዮች ወይም ነቢያት ነበሩ። ከእነርሱም መካከል ነብዩ ናትናኤል (1ኛ ነገ. 1፥22)፤ ነቢዩ አኪያ (1ኛ ነገ. 11፥29-39፤ 14፥1-18)፤ ነቢዩ ሳማያ (1ኛ ነገ. 12፥21-24) ይገኙበታል። እንደዚሁም ሁለት ስማቸው ያልተጠቀሰ ነቢያት የቤቴል መሠዊያ የወደፊት እንደሚረከስ ተንብየዋል (1ኛ ነገ. 17-19፤ 21፥8፤ 20፥35-43)፤ በእስራኤል ነብይ የነበረው ነቢዩ ዮናስ (2ኛ ነገ. 14፥25)፤ የሴት ነብይት ሕልዳና (2ኛ ነገ. 22፥14-20) እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

## የእግዚአብሔር ቅን ፈራጅነት ይታያል

እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን የአምላካቸውን ሕግጋት ስላልጠበቁ በየጊዜው የእግዚአብሔር ቁጣ ተቀስቅሷል። ነገሥታት የሠሩት በደል ለገዛ ቤተሰቦቻቸውና ለሕዝቡ ጽዋው ተርፏል (1ኛ ነገ. 12፥26-33፤ 21፥21-22፤ 2ኛ ነገ. 10፥30-31፤ 14፥6)። የእግዚአብሔር ሕግ በመጽሐፉ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ተሰጥቶታል። ነገሥታቱ የተመዘኑበት እና የነገሡበት መመዘኛና ባለሥልጣን የእግዚአብሔር ሕግ ነበር (2ኛ ነገ. 2፥34፤ 12፥28፤ 13፥19፤ ዘዳግ. 3፥14፤ 6፥7-10)።

# የአንደኛና የሁለተኛ ዜና መዋዕል

## መግቢያ

በመጽሐፉ ውስጥ የተሸፈነው የታሪክ ዘመን በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትም ተዘግቧል:: ከዚህም የተነሳ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ዘንድ ጥያቄ ይፈጥራል:: እነዚህ ሲቃውንት የጠየቁት ጥያቄ በአንድነት «ታሪክን እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ መጻፍ ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው?» ይላል:: ከዚህም የተነሳ በየጊዜው ለእነዚህ መጻሕፍት የተለያዩ ስሞች ተሰጥተዋል:: ለምሳሌ በአንድ ወቅት የተሰጠው ስም «የተረሱ ነገሮች» የሚል ነበር:: ይኸ ርዕስ የተሰጠበት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ግልጽ ባይሆንም ቃሉ ሁለት ነገሮችን ሊያሳይ ይችላል:: አንደኛው አሳብ መጻሕፍቱ በሌሎች የታሪክ መጻሕፍት ያልተካተቱ ነጥቦችን እጠቃለው እንደያዙ የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው አሳብ ደግሞ መጻሕፍቱ ከሌሎች የታሪክ መጻሕፍት የተውጣጣና የተቀነባበረ መረጃ መያዛቸውን ለማሳየት ነው:: በሌላ አነጋገር የሌሎች የታሪክ መጻሕፍት አጥርጥር ነው::

በአብዛኞቹ የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች መጽሐፉ «ዕለታዊ ዘገባዎች» የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል:: ይኸውም የእስራኤላውያን ነገስታት ተግባር ዘገባ እንደማለት ነው (1ኛ ነገ. 14+19፤ እሰ. 2+23)::

## ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን

መጽሐፉ የተጻፈበት ዘመን እና የጸሐፊው ማንነት በሁለቱም መጻሕፍት ማለትም በ1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕል አልተጠቀሰም:: በጥንታዊ የአይሁድ አባባል ዕዝራ መጻሕፍቱን እንደጻፈ ይነገራል:: እንደዚሁም በአንድ ወቅት መጻሕፍቱ ከመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ጋር አንድ ላይ ተያይዘው ነበር የሚል ሃሣብም ቀርቧል:: ይሁን እንጂ እነዚህን ሃሣቦች ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል በቂ ማስረጃ ማቅረብ አልተቻለም:: አሁን ባለው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል ከመጽሐፈ ዕዝራ እና ነህምያ ተለይቶ ለብቻው እንደ አንድ መጽሐፍ ተቀምጧል::

የተጻፈበትን ዘመን በተመለከተም አንድ ዓይነት አመለካከት እና መረዳት አይታይም:: ይሁን እንጂ በመጻሕፍቱ ላይ በተሰጡት የትውልድ ሐረጎች ላይ በመመስረት መጻሕፍቱ ከሁለትና ከሦስት ትውልዶች በኋላ! ከምርኮ ወዲህ የተጻፈ ሲሆን እንደሚችል ይገመታል:: በመሆኑም መጻሕፍቱ በአምስተኛው መቶ ዓመተ ዓለም ገደማ ተጽፈዋል ወደሚለው ድምዳሜ ተደርሷል::

## አስተዋጽኦ

1. ስሞችና የትውልድ ሐረጎች (1ኛ ዜና 1+1-10+14)
    - የዳዊት ዘር ሐረግ (1+1-3+24)
    - የእስራኤል ቤት (4+1-7+40)



    - የሳኦል ቤት (8+1-9+44)
    - የሳኦል ሞት/ዕረፍት/ (10+1-14)

2. ዳዊት (1ኛ ዜና. 11+1-29+30)
    - የዳዊት በእስራኤል ላይ መንገስ (11+1-3)
    - የኢየሩሳሌም መያዝ (11+4-8)
    - የዳዊት ኃያላን (11+9-12+40)
    - ዳዊትና የቃል ኪዳኑ ታቦት (13+1-16+43)
    - ዳዊትና የተስፋው ቃል (17+1-29+30)
        - የመጀመሪያው ዙር (17+1-29+30)
        - ሁለተኛው ዙር (22+1-27+34)
        - ሦስተኛው ዙር (28+1-29+30)

3. ሰለሞንና የዳዊት ዘሮች /ትውልዶች/ (2ኛ ዜና 1÷1-36÷23)
    - ሰለሞን (1+1-9÷31)
    - ሮብአም (10÷1-12+16)
    - አብያ (13+1-14+1)
    - አሳ (14+2-16÷14)
    - ኢዮሳፍጥ (17+1-29+37)
    - ኢዮራም (21+1-20)
    - አካዝያስ (22+1-12)
    - ጎቶንያል (23+1-21)
    - ኢዮአስ (24+1-27)
    - አሜስያስ (25+1-28)
    - አዝያን (26+1-23)
    - ኢዮአታም (27+1-9)
    - አካዝ (28+1-27)
    - ሕዝቅያስ (29÷1-32÷33)
    - ምናሴ (33+1-25)
    - አሞጽ (33÷21-25)
    - ኢሳይያስ (34+1-35÷27)
    - መደምደሚያ (36+1-23)

## የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት

የ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል ይዘት በአራት ዋና ዋና ነጥቦች ዙሪያ ለመዳሰስ እንሞክራለን::

## ሀ. የዳዊት ንግሥና

የመጽሐፉ ጸሐፊ ለዳዊት ንግሥና ትልቅ ትኩረት ሰጥቶታል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ የሚተርፍ በረከት ከዳዊት ቤት እንደሚወጣ በግልጽ ተናራግሯል። በሌሎች የታሪክ መጻሕፍት እንደተጠቀሰው ሁሉ በዚህም መጽሐፍ ላይ የንጉሱ በእግዚአብሔር መታመን እና የሕዝቡ በእግዚአብሔር ማመን ቀጥተኛ ተያያዥነት እንዳላቸው አስምሮበታል። ንጉሡ እግዚአብሔርን ከታዘዘና በእርሱ ከታመነ ሕዝቡም ሁሉ የንጉሱን ምሳሌ እንደሚከተሉ በጣም ግልጽ ነው። ከዚህም የተነሳ ለሕዝቡና ለምድሪቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዕረፍት ይሆንላቸዋል።

## ለ. የእግዚአብሔር ቃልኪዳን

ቃል ኪዳኑ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ያስተሳሰረ የስምምነት ቃል ነበር። ስምምነቱ የእስራኤልን መታዘዝና በአምላካቸው መታመንን ይጠይቃል። በሌላ ጐን ደግሞ ስምምነቱ እግዚአብሔር ዕረፍትንና ሰላምን ለሕዝቡ እንደሚሰጥ ያረጋግጣል። ከቃል ኪዳኑ ፈቀቅ ባሉበት ጊዜም ስምምነቱ በሚያዘው መሠረት የእግዚአብሔር ፍርድ በሕዝቡ ላይ ተሳልፏል።

## ሐ. የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ

የቤተ መቅደሱ መኖር የእግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር አብሮ መሆኑን ያመለክታል ስለሆነም እስራኤላውያን እግዚአብሔር አምላካቸውን በመፍራትና በመቀደስ ማምለክ ይጠበቅባቸው ነበር። ከዚህም ጋር በተያያዘ የቤተመቅደሱ መሠራት እና በውስጥ የሚካሄዱት የአምልኮ ሥርዓቶች በሙሉ ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ እንዲሰጥባቸው ሆኗል። በዚህ ረገድ ዳዊትና ሰሰሞን ትልቅ ድርሻ ነበራቸው። እንደዚሁም ከእነርሱ በኋላ የነበሩትም ነገሥታት ቢሆኑ ትልቅ ኃላፊነት ነበረባቸው።

## መ. አሕዛብ

ስለ ዳዊት ንጉሥነትና ስለ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከሚናገረው ክፍል ባሻገር ስለ አሕዛብ የወደፊት መጉብኘት የሚጠቁም አንድምታ አለ። የእግዚአብሔር ሃሣብ በኢየሩሳሌም ላይ በሚመሠረተው መንግሥቱ በኩል የምድርን አሕዛብ ለመጐብኘትና ለመባረክ እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

መጽሐፈ ዜና መዋዕልና መጽሐፈ ነገሥት በይዘት ደረጃ ተመሳሳይነት አላቸው፤ ሆኖም ግን ከዕይታ አንጻር የአትኩሮት ልዩነት አላቸው።



| ነገሥት | ዜና መዋዕል |
|---|---|
| 1. ከትንቢታዊ እይታ አንጻር (ለምሳሌ የተሰያዩ የእግዚአብሔር ፍርዶች) | ከክህነት ዕይታ አንጻር (ለምሳሌ የእግዚአብሔር ተስፋዎች) |
| 2. ለጦርነቶች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል | ለቤተመቅደሱ ትኩረት ተሰጥቷል |
| 3. የነገሥታቱ ዙፋን ብልጽግና | የዳዊት ዘር /በዙፋን ላይ/ ዘለቄታ |
| 4. ስለ እስራኤልና ስለይሁዳ | አብዛኛው ስለ ይሁዳ |
| 5. ሥነ ምግባር | መዋጀት /መታደስ/ |

## የመጽሐፉ ዋና ዓላማ

መጽሐፈ ዜና መዋዕል በውስጡ የያዘው ታሪካዊ ዘገባ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጻሕፍትም በሰፊው ተዘግቧል። ከዚህም የተነሳ «ተመሳሳይ ታሪክን እንደገና መድገም ለምን አስፈለገ?» የሚል ጥያቄዎች ከብዙዎች ዘንድ ይነሳል። ለዚህም አስፈላጊ ጥያቄ ሁለት መልሶች ይኖራሉ። አንደኛው ጸሐፊው ከራሱ ዕይታ አንጻር ታሪካዊ ዘገባውን ለማቅረብ ስለፈለገ ወይም የእግዚአብሔር መንፈስ ይኸን ስላሳሰበው የሚል ነው። ለምሳሌ አራቱን የአዲስ ኪዳን የወንጌል መጻሕፍትን የወሰድን እንደሆነ መጻሕፍቱ ከተሰያየ ዕይታ አንጻር የተጻፉ ናቸው። ማቴዎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነት ላይ ማርቆስ በአገልጋይነቱ ሉቃስ በክርስቶስ አዳኝነት ላይ ያተኩራሉ።

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ጸሐፊው የእስራኤልን ታሪክ እንደገና በስፋት ለማብራራትና ለመተረክ ስለፈለገ ሊሆን ይችላል የሚል ነው። ትክክለኛውና የተሻለ ግምት ሊሆን የሚችለው ግን የእነዚህ የሁለቱ ነጥቦች ጥምር ነው። ይኸውም ጸሐፊው የእስራኤልን ታሪክ ከአዲስ አቅጣጫ አንጻር እንደገና ለማብራራትና ለመተርጐም ስለፈለገ ነው።

## ማጠቃለያ

የ1ኛ እና የ2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ይዘት በማያሻማ ሁኔታ የመሢሑን መምጣትና በሕዝቡ ላይ መንገሥ ይናገራል። በታሪክ፣ በመዝሙረ ዳዊትና በነቢያት መጻሕፍት ላይ «መሢሕ» የሚሰው አባባል ከዳዊት ዘር የሆነውን ንጉሥ ያመለክታል። በመሆኑም መጽሐፉ ከዳዊት ዘር በሆነው ንጉሥ ላይ የሰጠው ልዩ ትኩረት መጽሐፉ ወደፊት ስለተገሰጠው መሢሕ ይናገራል ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል። መሢሕ የሆነው የዳዊት ልጅ፣ እርሱም ክርስቶስ ወደፊት ሕዝቡን በሰላም ሊያሳርፍና አሕዛብን በሕዝቡ በኩል ሊባርክ እንደሚመጣ ጠቁሟል።

# መጽሐፈ ዕዝራ

## መግቢያ

መጽሐፈ ዕዝራ አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ ወጥተው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ ቦኋላ ከተጻፉት መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ከባቢሎን ምድር ተነስተው ወደ እስራኤል እስከገቡበት ጊዜ ድረስ የተከናወነውን ታሪክ የሚያስነብበን መጽሐፍ ነው። ሥፍራውም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ ቀጥሎ ይገኛል። በተጨማሪም መጽሐፉ የያዘው ታሪክ ከዚሁ ከዜና መዋዕል መጽሐፍ ታሪክ ተከታይ ሆኖ እናገኘዋለን።

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የዕዝራ መጽሐፍ ከነህምያ መጽሐፍ ጋር በአንድነት እንደ አንድ መጻሐፍ ሲቆጠሩ የቆዩ ሲሆን ሥፍራቸውም ከዜና መዋዕል መጽሐፍ በፊት ነበር።

## ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን

የመጽሐፉ ጸሐፊ ካህኑ ዕዝራ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል። ዕዝራ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ቁልፍ ሚና ከተጫወቱት ሰዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በእስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ ወደ ምድራቸው በተመለሱበት ጊዜ በሁለተኛው ዙር ማለትም በ458 ዓ.ዓ. ሕዝቡን እየመራ ወደ ምድራቸው ያስገባ ሰው ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም አይሁድ ገና በባቢሎን ምርኮ ሳሉ የምኩራብ አምልኮ ሥርዓትን ያስጀመረው ዕዝራ እንደሆነ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ያምናሉ። ይህ ብቻም ሳይሆን ዕዝራ በምርኮው ዘመን በሊቀ ካህንነት ያገለገለና የሕዝቡን ልብ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ጥረት ሲያደርግ የኖረ እንደዚሁም በጸሐፊነቱ የታወቀ የእግዚአብሔር ሰው ነበር። ከመጽሐፈ ዕዝራ በተጨማሪም ዜና መዋዕል ቀዳማዊና ካልዕን የጻፈውም ካህኑ ዕዝራ እንደሆነ ይታመናል። ዕዝራ የሚለው ቃል «ኤዜር» ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም «ዕርዳታ» ወይም «ረዳት» ማለት ነው። መጽሐፉም ይህንን ስያሜውን ያገኘው ከጸሐፊው ስም በመነሳት ነው። የተጻፈበት ዘመንም አይሁድ ከምርኮ እንደተመለሱ በ450 ዓ.ዓ. ገደማ ነው።

## አስተዋጽኦ

I. የመጀመሪያው ዙር ከምርኮ ተመላሾች በዘሩባቤል መሪነት (1፥1-2፥70)
II. ቤተመቅደሱን መልሶ የመገንባት ሥራ (3፥1-6፥15)
III. የቤተ መቅደሱ ምርቃትና የፋሲካ በዓል (6፥16-22)
IV. በዕዝራ መሪነት ወደ ከነዓን መመለስ (7፥1-8፥36)
V. መንፈሳዊ ተሃድሶ (9፥1-10፥44)



**ቁልፍ ጥቅሶች፡-** ዕዝ. 6፥14፤ 7፥10፤ 9፥4፤ 10፥3-5

**ቁልፍ ቃላት፡-** የአምላካችን ቤት
- የአምላካችን ህግ
- ኢየሩሳሌም

## የመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘት

በአጠቃላይ መጽሐፉን ስንመለከተው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያቹ ስድስት ምዕራፎች በሰላትያል ልጅ በዘሩባቤል መሪነት ስለተመለሱት አይሁድ ይተርካል። ሁለተኛውና ከምዕራፍ ሰባት ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ያለው ደግሞ በዕዝራ መሪነት ወደ እስራኤል ስለተመለሱት አይሁድ ታሪክ የሚያትት ነው። በእነዚህ ሁለት ታሪኮች መካከል የሰባ ስምንት ዓመታት ልዩነት አለ። ይህም ማለት በዘሩባቤል መሪነት የተመለሱበት ጊዜ 536 ዓ.ዓ. ሲሆን በዕዝራ መሪነት የተመለሱት ደግሞ በ458 ዓ.ዓ. ነው። በዚህ መሠረት በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ስናሰላው በመካከል የሰባ ስምንት ዓመታት ክፍተት እናገኛለን ማለት ነው።

በእነዚህም ወቅቶች የተከናወኑት ዋና ዋና ሥራዎች ዘሩባቤል የፈረሰውን ቤተመቅደስ መልሶ ሲሠራ ዕዝራ ደግሞ ሕዝቡን ወደንስሃና ኑዛዜ በመምራት የተበላሸውን የአምልኮ ሕይወት መልሶ በመጠገንና የሕዝቡን ልብ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ላይ ያተኩራል።

ከዚህ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ በመጽሐፈ ዕዝራ ላይ የምናነባቸውን ታሪኮች የተከናወኑበትን ዘመንና በዘመኑ የነበሩትን ነገሥታት ዘመንና በዝርዝር ተቀምጧል።

| ዘመን (ዓ.ዓ.) | በዘመኑ የነበረው ንጉሥ | የተከናወነው ታሪክ | የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ጥቅስ |
|---|---|---|---|
| 539 | ቂሮስ | የባቢሎን መንግሥት መውደቅ | ዕዝ. 1፥1 |
| 536 | ቂሮስ | የአይሁድ መመለስ (በዘሩባቤል መሪነት) | ዕዝ.21፥1-2 |
| 536 | ቂሮስ | የቤተመቅደሱ ዕድሳት መጀመር | ዕዝ. 1፥5-11፤ 3፥8-13 |
| 534 | ቂሮስ | የቤተመቅደሱ ዕድሳት መቋረጥ | ዕዝ. 4፥17-22 |
| 520 | ዳርዮስ (ቀዳማዊ) | የቤተ መቅደሱ ሥራ መቀጠል | ዕዝ. 5፥1-2 |
| 516 | ዳርዮስ (ቀዳማዊ) | የቤተመቅደሱ ሥራ መጠናቀቅ | ዕዝ. 6፥15 |
| 458 | አርጤክስስ (ቀዳማዊ) | የአይሁድ መመለስ (በዕዝራ መሪነት) | ዕዝ. 7፥1 |
| 445 | አርጤክስስ (ቀዳማዊ) | የአይሁድ መመለስ (በነህምያ መሪነት) | ዕዝ. 2፥2 |

## ማጠቃለያ

የዕዝራ መጽሐፍ አጠቃላይ ይዘቱን እንደተመለከትነው በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሆኖ እናገኘዋለን፡ እነርሱም፤

1ኛ/ የአይሁድ ወደ ምድራቸው ተመልሶ መግባትና
2ኛ/ የአይሁድ መንፈሳዊ ሕይወት መታደስ ናቸው።

እነዚህም ታሪኮች የሚያመለክቱን በመጀመሪያ ቅድስትና የእግዚአብሔር ማደሪያ ብለው በሚያስቧት ምድር ላይ በአካል መገኘታቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከዚያው ጋር በተያያዘ መልኩ በአካል መገኘት ብቻ ሳይሆን በውስጣዊ ማንነትም በእግዚአብሔር ሕግና ቃል መታነጽና ለእርሱ መቀደስ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው።

በተጨማሪም የካህኑን የዕዝራን አገልግሎት ስንመለከት እንደመሪነቱ መጠን ሕዝቡን በትዕግሥት በመጠበቅ ሁሉንም በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ሃሣብ ሊያደርሳቸው የቻለ ትጉህ የእግዚአብሔር ሰው ነበር።

ይህ አሠራር በዘመናችን ላሰችውም ቤተክርስቲያን ጠንካራ ትምህርት በውስጡ ያዘለ ነው። በዚህ ዘመን ብዙዎች በየሰንበታቱና የቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች ባሉባቸው ቀናት ሁሉ በዚያ መገኘታቸው በቂ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። ነገር ግን ይህ ብቻውን በቂ እንዳልሆነና በውስጥ ማንነትም ለእግዚአብሔር መቀደስ አስፈላጊ ነገር መሆኑን ከዕዝራ መጽሐፍ እንማራለን። ከዚህ በተጨማሪም በመሪነት ላይ የተቀመጡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ እነርሱ ወደደረሱበት መንፈሳዊ ደረጃ የማድረስ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስገነዝበናል።



# መጽሐፈ ነህምያ

## መግቢያ

እግዚአብሔር አምላክ የእስራኤል ሕዝቦች በሙሉ ልባቸው እርሱን ቢያመልኩ ትዕዛዛቱንም ቢፈጽሙ በፍጹም በረከት እንደሚባርካቸውና ከጠላቶቻቸውም እንደሚያሳርፋቸው የተስፋ ቃል ገብቶላቸው ነበር። በአንጻሩም ትዕዛዛቱን ባይጠብቁና በፍጹም ልባቸው እርሱን ከማምለክ ቢመለሱ ግን ቅጣቱ በእነርሱ ላይ እንደሚሆንና ለምርኮና ለብዝበዛ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው አስጠንቅቆ ተናግሯቸዋል።

ሆኖም እስራኤላውያን በተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን ቃል ሲተላለፉ ኖረዋል። እግዚአብሔር አምላክ በነቢያቱ በኩል በተደጋጋሚ ቢናገራቸውም እንኳን ከክፉ ሥራዎቻቸው ሊመለሱ አልቻሉም። በዚህም መሠረት አስቀድሞ በ931 ዓ.ዓ. የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ። አስሩ የሰሜን ነገዶች በአንድነት የእስራኤል ሕዝቦች ተብለው ሲጠሩ ሁለቱ የደቡብ ነገዶች ማለትም የይሁዳና የቢንያም ነገዶች ደግሞ የይሁዳ ሕዝብ በመባል ተከፋፈሉ። ነገር ግን የደቡብም ሆነ የሰሜኑ ነገዶች በፍጹም ልባቸው እግዚአብሔርን አልተከተሉም።

ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ነደደ በጠላቶቻቸውም እጅ ለምርኮ አሳልፎ ሰጣቸው። የሰሜኑ ክፍል (እስራኤል) በ722 ዓ.ዓ. በምርኮ ወደ አሦራውያን ምድር ሲወሰዱ የደቡቡ ክፍል (ይሁዳ) ደግሞ በ586 ዓ.ዓ. በባቢሎናውያን ተማረኩና ኢየሩሳሌምም ፈረሰች።

በ539 ዓ.ዓ. የባቢሎን መንግሥት በሜዶንና በፋርስ መንግሥታት ከተሸነፈ በኋላ እስራኤላውያንም ወደወጡባት ምድራቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው። በዚህም መሠረት እስራኤላውን በተለያዩ ጊዜያት በመሪዎቻቸው አማካይነት ወደ ምድራቸው ተመልሰዋል።

1ኛ/ በዘሩባቤል መሪነት በ538 ዓ.ዓ.
2ኛ/ በዕዝራ መሪነት በ458 ዓ.ዓ.
3ኛ/ በነህምያ መሪነት በ444 ዓ.ዓ.

ነህምያም የኢየሩሳሌምን መፍረስ ሰምቶ ወደ ሀገሩ በተመለሰ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት በመሆን የፈረሰውን ቅጥሩቸውን እንዲጠግኑ ያበረታታና በመሪነትም ሥራውን የፈጸመ ሰው ነበር (ነህ. 2፥17)።

በመጽሐፈ ነህምያ ላይ ተጽፎ የምናገኘው ታሪክም ይህንኑ ሂደት የሚያትት ሆኖ እናገኘዋለን።

## ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን

ምንም እንኳን አንዳንድ ሰዎች በጸሐፊው ማንነት ላይ የተለያየ አስተያየቶችን ቢሰነዝሩም በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በኩል ጸሐፊው ነህምያ ራሱ እንደሆነና የጻፈበትም ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ420ኛው ዓመት ገደማ እንደሆነ ይታመናል።

ስለዚህም መጽሐፉ በጻፈው ሰው ስም መጽሐፈ ነህምያ ተብሎ ተሰይሟል። ትርጓሜውም በዕብራይስጥ ቋንቋ «ነሄም ያህ» ማለት «ያህዌ እግዚአብሔር ያድናል» ማለት ነው። ጸሐፊው ነህምያም ምንም እንኳን ተወልዶ ያደገው በምርኮ ምድር ቢሆንም እግዚአብሔር በበላት ምድር ያከበረውና ለታላቅ ሹመት ያበቃው ሰው ነበር።

## አስተዋጽኦ

I. የቅጥሩ እድሳት (1፥1-7፥3)

- ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ (1፥1-2፥20)
- የቅጥሩ መታደስ (3፥1-3፥32)
- ከጠላቶች የተሰነዘረ ጥቃት (4፥1-6፥14)
- የሥራው መጠናቀቅ (6፥15-7፥4)

II. የሕዝቡ ወደሥፍራቸው መመለስ (7፥15-13፥31)

- የሕዝቡ መቆጠር (7፥5-7፥73)
- ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቃል ኪዳን ማደስ (8፥1-10፥39)
- በኢየሩሳሌም የተቀመጡት አለቆች (11፥1- 12፥26)
- የቅጥሩ መቀደስ (12፥27-12፥47)
- ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ተሃድሶዎች (13፥1-13፥31)

## የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት

**ቁልፍ ጥቅስ (ነህ. 2፥17 እና 6፥3)**

የነህምያን መጽሐፍ ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው የኢየሩሳሌምን ቅጥር መፍረስ ከሰማ በኋላ ሕዝቡን በማስተባበር የከተማዋን ቅጥር መልሶ ለመገንባት ያደረገውን ጥረት እና በአንጻሩም በተደጋጋሚ በጠላቶቹ የተሰነዘረበትን ተቃውሞ ያስነብበናል።



በነህምያ መጽሐፍ ውስጥ ጸሎት ትልቅ ሥፍራ ተሰጥቶት እናገኛለን (ነህ. 1፥4-11፤ 4፥4-5፤ 5፥19)።

እንደዚሁም ከምዕራፍ 1 እስከ 7 ባለው ሥፍራ ላይ የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር እንዴት እንደተገነባና በቅጥሩም ግንባታ ወቅት የተከሰቱትን ችግሮችና መፍትሄዎቻቸውን እናገኛለን።

ከዚህ በተለየ መልኩም ከምዕራፍ 8-10 ባለው ክፍል ውስጥ የምንመለከተው የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት መልሶ የመገንባቱን ሂደት ነው። የከተማይቱ ቅጥር መልሶ ከተገነባ በኋላ በየሥፍራው የተቀመጠውን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ለማነቃቃት ካህኑ ዕዝራ የሙሴን መጻሕፍት ሲያስተምራቸውና እንደአምላካቸው እንደ እግዚአብሔር ሕግጋት እንዲኖሩ ቃል ሲያስገባቸው እናያለን። ከዚህ በመቀጠልም በመጽሐፉ ኋለኛ ምዕራፎች ላይ የሚገኘው ክፍል (ከምዕራፍ 11 እስከ መጨረሻ) እንደአምላካቸው ቃል ለመጓዝ የወሰኑትን ሰዎች ሕይወት የማበረታታትና የማጠናከር ሂደት ነው።

እንግዲህ አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ሃሳቦች በተጨማሪ ሕዝቡን በማስተባበሩና የኢየሩሳሌምን ቅጥር በማደሱ ሂደት ውስጥ ነህምያን የገጠሙትን ተቃውሞዎችና እርሱም የሰጣቸው ምላሾች በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

## ነህምያን ያጋጠሙት ችግሮችና የሰጣቸው ምላሾች

| ያጋጠሙ ችግሮች | የነህምያ ምላሾች |
|---|---|
| 1. የኢየሩሳሌም ቅጥር መፈራረስና የበሮቿም በእሳት መቃጠል | 1. ሀዘንና ልቅሶ (1+4)<br>የፈረሰውን ቅጥር መልሶ ለመገንባት ሕዝቡን ማነሳሳት (2+17-12) |
| 2. ከጠላቶች የተሰነዘረ የሐሰት ክስ (2÷19) | 2. መከናወንን እንደሚያገኝ በእግዚአብሔር ላይ መታመን (2+20) |
| 3. የጠላቶች ስድብና ስላቅ (4+1-3) | 3. ጸሎት (4+4-5)<br>ጠንክሮ ሥራውን መሥራት (4+6) |
| 4. ሠራተኞችን ለማጥቃት የተደረገ ሴራ (4÷7-8) | 4. ጸሎት እና ጥበቃ (4+9) |
| 5. የሥጋ ድካም እና የሞት ፍራቻ (4፤10-12) | 5. ሕዝቡ ሁሉ ቤተሰቦቻቸውን እንዲጠብቁ ማነቃቃት (4+13-14፣ 16-18፣ 20) |
| 6. ድህነት እና (5÷1-5) ስግብግብነት | 6. ቁጣ (5÷6) ተግሳጽ 5+7 እና የሕዝቡን ገንዘብ ማስመለስ (5+7-11) |
| 7. ነህምያን ለመግደል የተቀነባበረ ሴራ (6÷1-3) | 7. አለመተባበር (6÷3) |
| 8. የነህምያን ስም ማጥፋት (6+5-7) | 8. ጸሎት (6÷9) |
| 9. በነህምያ ላይ ማላገጥ (6÷13) | 9. ጸሎት (6÷14) |
| 10. የጦቢያ ወደ መቅደሱ ጓዳ መግባት (13÷4-7) | 10. የጦቢያን ዕቃዎች ማስወገድ (13፤8) |
| 11. የሌዋውያን ችላ መባልና የሕዝቡም ወደኋላ መመለስ (13÷10) | 11. ተግሳጽ (13+11)፣ ሌዋውያንን በየስፍራቸው ማቆምና መጸለይ (13+14) |
| 12. ሰንበትን አለማክበር (13+15-16) | 12. ተግሳጽ (13+17-18) ጠባቂዎችን ማቆም (13፤19 ጸሎት 13+22) |
| 13. ከእንግዶች ሴቶች ጋር መጋባት (13÷23-24) | 13. ተግሳጽ 13÷25-27 ያልተቀደሱ ካህናትን ማባረር (13÷28 ጸሎት 13+29) |

### ማጠቃለያ

የነህምያን መጽሐፍ የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመጠገን የተደረገውን ርብርቦሽ በሚገባ አመልክቶናል፡፡ ታዲያ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ በጥልቀት ተሰምቶትና እጅግ አሳዝኖት ለመገንባት የተነሳሳውና ሕዝቡን ያስተባበረው ግን በፈረሰው ቅጥር ውስጥ የነበረ ሰው ሳይሆን ባማረው ዘሱሳ ግንብ ውስጥ ነዋሪው ነህምያ ነበር፡፡



ነህምያ ምንም እንኳን ለራሱ የተደላደለና የተመቻቸ ኑሮ ላይ ቢሆንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተማ መፍረስ በእጅጉ ያስቆጨው ሰው ነበረ፡፡ ስለዚህ በቸልተኝነት ይህ አይመለከተኝም ሳይል የራሱን ኑሮና ሥራውን በመተው የኢየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ ለመገንባት ቆርጦ የተነሳ ሰው ነበር፡፡

በዘመናችንም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥም ሆነ በየግል ሕይወታችን ብዙ የፈረሱና የተበላሹ ነገሮች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ እኛም ህያው ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል በመማር «ይሄ እኔን አይመለከተኝም የእነእከሌ ሥራ ነው» ሳንል የእግዚአብሔር ቤት ጉዳይ ከልባችን ተሰምቶን መቆም ባለብን ሥፍራ ላይ ልንቆምና ልንሠራ እንደሚገባን የነህምያ መጽሐፍ ያስተምረናል፡፡

በመጨረሻም ማድረግ የሚገባንን ሁሉ ካደረግን በኋላ ከማንም ሰው ጥቅምንና ምሥጋናን እንድናገኝ ሳይሆን ያደረግነውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር እንዳደረግን ለማወቅ ልክ ነህምያ ሥራውን ሁሉ ካከናወነ በኋላ «አምላኬ ሆይ በመልካም አስበኝ» ብሎ እንደጸለየ፣ እግዚአብሔር ብቻ በበጐነቱ እንዲያስበን መጸለይ ይገባናል (ነህ. 13÷31)፡፡

# መጽሐፈ አስቴር

በብሉይ ኪዳን ካሉት የታሪክ መጽሐፍት አንዱ መጽሐፈ አስቴር ነው። ይህ መጽሐፍ የአይሁድን ብቻ ሳይሆን የፋርስ መንግሥት ታሪኮችን ከ539-331 ዓ.ዓ. ድረስ ያሰሙን ዘግቧል። ይህም ማለት እስራኤላውያን ከምርኮ ተመልሰው ከመጡ በኋላ ባለው ጊዜ የተፈጸመ ታሪክ ነው። አብዛኞዎቹ እስራኤላውያን ከምርኮ ወደ አገራቸው በተመለሱበት ወቅት አንዳንዶቹ ግን በምርኮ ምድር ቀርተው ነበር። ወደ አገራቸው ካልተመለሱ ሰዎች መሃል አስቴርና መርዶክዮስ ይገኙበታል።

በመጽሐፈ አስቴር የተጠቀሰው የፋርስ መንግሥት ንጉሥ ኃያል ሰው እንደነበረ ይነገርለታል። ግዛቱም ከ485-465 ዓ.ዓ. ነበር።

የመጽሐፈ አስቴር ታሪክ ከዕዝራ ም.6-7 ባለው ታሪክ ይጠቃለላል። ስለዚህ መጽሐፉ የ10 ዓመታትን ታሪክ ይዟል። ከአርጤክስስ 3ኛ ዓመት (አስ. 1+3) ማለትም ከ483 እስከ 473 ዓ.ዓ. እስከ አርጤክስስ 12ኛ ዓመት መጨረሻ ድረስ ባለው ጊዜ ነበር (አስ. 3÷7)።

## ዋና መልዕክቱ

ምንም እንኳን በመጽሐፈ አስቴር የእግዚአብሔር ስም ባይጠቀስም ለሕዝቡ ያደረገው መልካም ጥበቃ የጽሑፉ ጉልህ ሃሣብ ነው።

ይህ መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ያለመጠቀሱ እንዲሁም ስለብሉይ ኪዳን ሕግ በውስጡ ተጽፎ ያለመገኘቱ ሌላው ቀርቶ ስለጸም ሲጠቀስ ስለጸሎት አብሮ አለመጠቀሱ መጽሐፉን ከሌሎች የብሉይ መጻሕፍት ልዩ ያደርገዋል።

የመጽሐፈ አስቴር ዓብይ ክስተቶች፣

- አይሁዳዊ ልጃገረድ አስቴር ንግሥት ሆነች
- መርዶክዮስ ንጉሡን አዳነ
- የሐማ ሴራ በራሱ ላይ ወደቀበት
- ንጉሡ እንቅልፍ በማጣቱና የነገሥታትን መዛግብት በማንበቡ ሳቢያ መርዶክዮስ ከበረ፣ ልቡም ለአስቴር ጥያቄ መዘጋጀቱ በንጉሡና በእግዚአብሔር ፊት መማለዷ።



## ቁልፍ ጥቅስ

መርዶክዮስ ለአስቴር፦

«በዚህ ጊዜ ቸል ብትዪ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ሥፍራ ይሆንላቸዋል። አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ፣ ደግሞስ ወደ መንግሥት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?» (አስ. 4+14) በማለት የተናገረው የመጽሐፈ አስቴር ቁልፍ ጥቅስ ነው።

## ጸሐፊው

የመጽሐፉ ጸሐፊ ማን እንደሆነ ባይታወቅም የፋርስን ባሕል በሚገባ የሚያውቅ ሰው እንደሆነ ይገመታል። ምናልባትም አይሁዳዊ ሳይሆን አይቀርም።

## የመጽሐፉ ዓላማ

ወደ ሀገራቸው የተመለሱ የእስራኤል ሕዝቦች (ቅሪቶችን) እግዚአብሔር ቃሉን የሚጠብቅ ታማኝ መሆኑን በመግለጽ የሚያበረታታ ነው። በዚያውም አዲሱን የፉሪምን በዓል ያስተዋውቃል።

## አስተዋጽኦ

- የአስቴር ታላቅ ቦታ ማግኘት (1+1-2+20)
- አይሁድ ሊጠፉ ተወሰነ (2+21-4+3)
- ነገሮች በአስቴ በኩል መስወጣቸው (4+4-9+19)
- የፋሪም በዓል አመሠራረት (9+20-32)
- የመርዶክዮስ መክበር (10)

## ስነመለኮታዊ መልእክት

አስቴር ሕይወቷን በመስዋት ንጉሡ ፊት ቀርባ ሕዝቧን አድናለች። እኛም ከእርሷ የምንማረው ሕዝቡን ለማዳን ሲባል በእግዚአብሔር ላይ በመታመን መድፈርን ነው። ምንም እንኳን ሕዝቡ አስቴርን ጨምሮ ከሀገር ውጭ ቢሆኑም እግዚአብሔር ግን ስለእነርሱ የሚሠራ ስለነበር ከመረዳትም ወደ ኋላ አላለም።

# ምዕራፍ ሦስት

## የቅኔ መጻሕፍት

### መግቢያ

በብሉይ ኪዳን ካሉት ሠላሳ ዘጠኝ መጻሕፍት አምስቱ የቅኔ መጻሕፍት ይባላሉ። እነዚህም ኢዮብ፣ መዝሙረ ዳዊት ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ናቸው። የጽሑፍ ይዘታቸውና የመልዕክት አቀራረባቸው በሰው ልጅ ታሪክ እጅግ ላቅ ያለ ቦታ ይዘዋል።

በቅኔ መጻሕፍት የእግዚአብሔር መልዕክት የተላለፈው እንደሌሎች የትንቢት መጻሕፍት «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በማለት ሳይሆን መለኮታዊ ምላሽን የሚያስገኙ ጥያቄዎችን በማስተናገድ ነው። የቅኔ መጻሕፍት ሰዎች ስሜታቸውንና ሃሣባቸውን በነፃነት የገለጹባቸው መጻሕፍት ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት በአብዛኛው ከእግዚአብሔር ለሰው በቀጥታ የተነገሩ ሳይሆኑ በተዘዋዋሪ ከእግዚአብሔር በሰው በኩል ለሰው የተነገሩ መልዕክቶች ሲሆኑ ቀጥተኛ ትንቢታዊ ቃላቶችንም አካትተዋል። የኢዮብና የመዝሙረ ዳዊት መጻሕፍት የሰውና የአምላክን ምልልስ (dialogue) የያዙ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ የሰውን ምልልስና ጥያቄ በማቅረብ በውስጠ ታዋቂነት መለኮታዊ አሳብን ያንፀባርቃሉ። የእነዚህ መጻሕፍት ጸሐፊዎች በጽሑፎቻቸው በሰው አእምሮ ታምቀው ለዘመናት ጥያቄ ሆነው የሚኖሩትን ጉዳዮች በግልጽነትና በድፍረት ወደ አደባባይ አውጥተዋል።

ጸሐፊዎቹ ከራሳቸው ከአካባቢያቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመረዳት ባደረጉት ጥረት የእግዚአብሔር መንፈስ እርዳታ በላያቸው ነበረበት። የብዙ ሰዎችና ሕዝቦችን ታሪክ ከዘገቡት ሌሎች ቅዱሳን መጻሕፍት በተለየ ሁኔታ የቅኔ መጻሕፍት የግለሰቦችን ሁኔታና ቃል ስለሚተርኩ ማራኪነታቸው ከፍተኛ ነው።

የ«ቅኔ መጻሕፍት» በሚለው በዚህ ምዕራፍ ስር ያሉት ትምህርቶች፣ እያንዳንዱ መጽሐፍ በማን፣ መቼ እና እንዴት እንደተጻፈ፣ የጽሁፉ ይዘትና አስተዋጽኦ፣ የአተረጓጐም መመሪያ፣ ዋና ሐሳቡና ትምህርቶቹ ምን እንደሆነ ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ከአዲስ ኪዳንና ከክርስቲያናዊ ሕይወት አንጻር የጽሁፉ አስፈላጊነትና ተዛማጅነት በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል።



# መጽሐፈ ኢዮብ

መጽሐፈ ኢዮብን የምናጠናው ከፔንታቱክ ጋር በማያያዝ ነው። ምንም እንኳ መጽሐፈ ኢዮብ ከፔንታቱክ ጋር ቢጠናም እንደሌሎቹ የፔንታቱክ መጻሕፍት የታሪክ ስነ ጽሑፍ ሳይሆን በመግቢያው (1፥1-2፥13) እና በመደምደሚያው ላይ (42፥7-17) ብቻ ታሪካዊ ሆኖ ቀሪው ግን የሥነ ግጥም (የቅኔ) መጽሐፍ ነው።

አብዛኛው የኢዮብ መጽሐፍ ሥነ ግጥም ቢሆንም የጥበብ/የሥነ ዕውቀት/ጽሑፍ ነው። የታሪኩ ዋና ገጸ ባሕርይ ኢዮብ የተሳካለት ሕይወት እንደነበረው የሚያሳዩ ነገሮች ማለትም ጥሩ ጤንነት፣ ትልቅ ቤተሰብና ብዙ ሀብት የነበረው ሰው ሲሆን በድንገት ግን ይህን ሁሉ ነገር አጥቶአል። የዚህ መከራ ምክንያት ለኢዮብም ሆነ «የማትጠቅሙ ባለመድኃኒቶች» ላላቸው ወዳጆቹ ግልጽ አልነበረም። ስለዚህም ኢዮብ ከውስብስብ የሕይወት ውጣ ውረድ ጋር መታገል ግድ ሆኖበት ነበር።

በዚህ መጽሐፍ «ቅን ሰዎች ለምን መከራ ይደርስባቸዋል?» ወደሚለው ዘመናትን የፈጀ ጥያቄ ጋር ዳግም እንፋጠጣለን። የኢዮብን መጽሐፍ በስነ ጽሑፍ ይዘቱ፣ በሥነ ግጥሙ፣ በምሳሌዎቹ፣ ከፍተኛ እምቅ ጥበብን ወይም ሥነ ዕውቀትን የያዘ በመሆኑ በምንተረጉምበት ጊዜ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። ምክንያቱም የእያንዳንዱ ሰው ንግግር ከጊዜው ሁኔታ አኳያ ሙሉ በሙሉ ትክክል ላይሆን ይችላል። ተገቢውን ትርጓሜ ለማግኘት በአጠቃላይ ከመጽሐፉ መልዕክት ጋር በማያያዝ ሊጠና ይገባል እንጂ ቁንጽል ሃሣብ ይዞ ለትርጓሜ መፍጠን ለስህተት ይዳርጋል። ስለዚህ እያንዳንዱን ቁጥር (ሐረግ) ሣይነጥሉ በአውደ ምንባቡ መሠረት መተርጐም መጀመሪያ ከተጻፈበት ሃሣብ እንዳንወጣና እንዳንስት ይረዳናል።

### መቼ እና በማን ተጻፈ?

«መቼና ማን ጻፈው?» የሚለው ጥያቄ ብዙ ውዝግብ አስነስቷል። ሆኖም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ታሪኩ የተከናወነበትና የተጻፈበት ጊዜ የተቀራረበ እንዳልሆነና በቀደምት አባቶች በአብርሃም ዘመን እንደሆነ በመጠቆም ከፔንታቱክ ጋር ቢጠና የተሻለ እንደሆነ ይመክራሉ። የኢዮብ መጽሐፍ በእስራኤላውያን ታሪክ ቀደምት መጽሐፍ የሆነበት ምክንያት በፔንታቱክ ውስጥ የሚገኘውን ስነመለኮት በተሳሳተ መንገድ የሚረዱትን ለማረም የሚረዳ መሆኑ ነው።

በፔንታቱክ መጽሐፍ የመጨረሻ ላይ በመታዘዝ ስለሚገኘው በረከትና ባለመታዘዝ ምክንያት ስለሚመጣው ምዕራፍ መርገም ያስተምራል (ዘጸአ. 28)። ታዲያ በዚያ ዘመን የነበሩት የኢዮብ ጓደኞች በዘመናችን እንዳሉት አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ ሰው እግዚአብሔርን በመታዘዝ የሚያገኘው በረከት ውጫዊ ቁሳዊና ቅዐብታዊ በረከት እንደሆነ ያምኑ ነበር። ከዚህም የተነሳ ሀብታም መሆን ከመታዘዝ የተነሳ የሚገኝ የእግዚአብሔር በረከት፣ ድሀና በሽተኛ መሆንን ደግሞ ካለመታዘዝ የተነሳ የሚመጣ

የአርግማን ምልክት አድርገው ይቆጥሩሉ። ስለዚህም የኢዮብ መጽሐፍ ይህን የተሳሳተ ትምህርት ለመቃወምና ለማረም የተጻፈ ነው። ጸሐፊውም ሙሴ እንደሆነ ይገመታል።

## ቁልፍ ጥቅሶች

- «እነሆ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግስት እጠባበቃለሁ» (ኢዮ. 13፥15)።
- «የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ» (ኢዮ. 23፥10)።
- «...እነሆ እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው፤ ከኃጢአትም መራቅ ማስተዋል ነው...» (ኢዮ. 28፥28)።

## አስተዋጽኦ

I. መግቢያ 1፥1-2፥13

II. ክርክር 3፥1-42፥6

* የኢዮብ ዋይታ (ለቅሶ) 3፥1-26
* የውዝግብ ዙሮች 4፥1-27፥23

**ዙር 1** ኤሊፋዝ (5-5) ኢዮብ (6-7) ቢልዳድ (8) ኢዮብ (9-10) ሶፋር (11) ኢዮብ (12-14)

**ዙር 2** ኢሊፋዝ (15) ኢዮብ (16-17) ቢልዳድ (18) ኢዮብ (19) ሶፋር (20) ኢዮብ (2)

**ዙር 3** ኤሊፋዝ (22) ኢዮብ (23-24) ቢልዳድ (25) ኢዮብ (26-27)

III. የኢዮብ የጥበብ ቅኔ (ግጥም) (28፥1-28)

IV. የኢዮብ የመጨረሻ ንግግር (29፥1-31፥40)

V. የኤሊሁ 4 ንግግሮች (32፥1-37፥24)

VI. የእግዚአብሔር ንግግርና የኢዮብ መልስ (38፥1-42፥6)

VII. መደምደሚያ (42፥7-17)

## የመጽሐፉ ዓላማ

በመጽሐፉ መግቢያ «ሰው ለምን እግዚአብሔርን ያመልካል?» «ደግ ሰዎች ለምን ይሰቃያሉ?» «ክፉ (Evil) ከየት ይመጣል?» የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳትና ውይይቶችን በማቅረብ ተገቢ ምላሽ በመስጠት ይደመድማል።



ስለእግዚአብሔር መልካምነት ሰው በሁኔታዎች ላይ ሳይደገፍ እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለበት ያስረዳል። ደግሞም በመከራ ወቀት በመፅናት መባረክ እንዳለ ያሳየናል።

በተለያዩ ዘመናትና በአሁኑም ዘመን ክፋት በእግዚአብሔር አምላክ እንደተፈጠረና እንደሚደረግ፣ የሚያስተምሩ አሉ። አንዳንድ ሃይማኖቶችም እግዚአብሔር ሁለትዮሽ ባህርይ (በጐና ክፉ) ያለው አድርገው ይመለከቱታል።

ሌሎች ደግሞ ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር የሚስተካከል አቱል ኃይል እንደሆነ ያስባሉ። የኢዮብ መጽሐፍ ይህን የተሳሳተ ትምህርት በአጽንኦት ይቃወማል። ጌታ ኢየሱስ በዮሐ.9 ያዕቆብ ደግሞ በያዕቆብ 1 ላይ መከራ (ፈተና) ሁልጊዜ የኃጢአት ውጤት እንዳልሆነ፤ በረከትም ሁልጊዜ ለፃድቃን ብቻ የሚሰጥ አለመሆኑን ተናግረዋል። እግዚአብሔር በባሕርይው መልካም ስለሆነ በክፉ የማይፈትንና የማይፈተን የማይለወጥ አምላክ መሆኑ እውነት ነው። በተጨማሪም ከኢዮብ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ላይ ያለን እውነተኛ እምነት በሁኔታዎች ላይ ያልተደገፈ መሆን እንዳለበት ያስተምረናል።

# መዝሙረ ዳዊት

አብዛኛዎቹ የአይሁድና የክርስቲያን መዝሙሮች ከመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ የወጡ ናቸው። ከአምስቱ የቅኔ (የሥነ-ግጥም) መጻሕፍት በስፋት የሚታወቀውና የሚጠቀሰው መዝሙረ ዳዊት ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህንን መጽሐፍ ለፀሎት ጊዜያቸው ይጠቀሙበታል። እንዲያውም በአገራችን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ብዙዎቹ መቶ ሃምሣውንም ምዕራፍ በቃላቸው በማነብነብ የሚደግሙትም አሉ።

## የጽሑፉ ይዘት

የመዝሙረ ዳዊት ይዘት በዓይነቱ ብዙ ሲሆን በግልና በሕብረት የቀረቡትን የምሥጋና፣ የአምልኮ ቅኔዎች የልመናና የምልጃ ፀሎቶች፣ ጠላቶች እንዲቀጡ ወደ እግዚአብሔር የቀረቡ መማጠኛዎችና የእርግማን ቃሎችን አካቶ ይዟል። መዝሙራቱ ከዚህም አልፈው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በሰዎች የተናገራቸው ምሥጢራት የተከማቹበት ትንቢታዊ ቃላት አሏቸው። የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ስብዛት ከተጠቀሱት የብሉይ መጻሕፍት አንደኛው ነው። ይኸውም በብሉይ ኪዳን ተጽፈው በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት 287 የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች 116 ከመዝሙረ ዳዊት ናቸው። መዝሙሮቹ በአጠቃላይ መልካቸው ሲታዩ የሰውን ልጅ ውስጣዊ ስሜት ገላጮች ናቸው። የሰው ልጅ ሲደክም ሲያዝንም ያንጐራጉራል። ብዙ ጊዜ መዝሙር የሚዘመረው በሙዚቃ መሣሪያ ታጅቦ ነው። ዳዊትም ሲዘምር በበገና ታጅቦ ነበር። መዝሙር ሲባል በአጠቃላይ ሰው ስለራሱ፣ ስለሌሎችና ስለእግዚአብሔር የውስጥ ስሜቱን የሚገልጥበት ነው። ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ስለተጻፈ የእግዚአብሔር ሃሣብም የተገለጠበት መጽሐፍ ነው።

## የመዝሙራት ዓይቶች

- የትንቢት መዝሙሮች

   ሀ. ስለክርስቶስ

      1. ትህትናው (22፣ 31፣ 41፣ 69)
      2. ንግሰቱ (8፣ 16፣ 24፣ 45-47፣110)
      3. መንግሥቱ (9፣ 67፣ 72፣ 89፣ 93፣ 132፣ 142)

ለ. ስለኢየሩሳሌምና እስራኤል

- የመርገም መዝሙሮች

   ምዕ. 4፣ 5፣ 7፣ 10፣ 35፣ 36፣ 52፣ 58፣ 64፣ 109



በጠላት ላይ የመርገም ቃላትን መናገር ትክክለኛውን ስሜት በእግዚአብሔር ፊት መግለጥ ስለሆነ መፍትሄ ይኖረዋል። በአዲስ ኪዳን ያለው የክርስቶስ ትምህርት ግን ጠላቶቻችን መውደድ ይቅር ማለትና በመልካም መበቀልን ያስተምረናል።

- <u>የመታመን መዝሙር</u>
  11፣ 16፣ 23፣ 27፣ 33-34፣ 56፣ 57፣ 62፣ 71፣139
- <u>የታሪክ መዝሙር</u>
  78፣ 83፣ 105-106፣ 114፣ 135-137
- <u>የሕግጋት መዝሙር</u>
  1፣ 12፣ 19፣ 33፣ 119
- <u>የምሥጋና መዝሙር</u>
  75፣ 92፣ 100፣ 118፣ 136፣ 146
- <u>የተፈጥሮ መዝሙር</u>
  8፣ 19፣ 29፣ 65፣ 104፣ 147፣ 148
- <u>የልመና መዝሙር</u>
  4፣ 13፣ 17፣ 25፣ 28፣ 54-55፣ 61፣ 86፣ 141

## ጸሐፊው

መዝሙረ ዳዊት እንደሌሎቹ መጻሕፍት በአንድ ሰው ብቻ የተጻፈ አይደለም። በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ከተካተቱት 150 ምዕራፎች መካከል 73ቱ ምዕራፎች በዳዊት የተጻፉ ሲሆን የቀሩት ግን በተለያዩ ሰዎች የተጻፉ ናቸው። በመጽሐፉ የተካተቱትን መዝሙሮች በአንድ ላይ ስመጠረዝ 1000 ዓመታት ገደማ ፈጅተዋል ለምሳሌ መዝሙር 90 የተጻፈው በሙሴ በ1440 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር።

በሌላ በኩል አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንደሚሉት መዝ. 1 እና 119 ከምርኮ መልስ በ444 ዓ.ዓ. ገደማ በዕዝራ የተጻፉ እንደሆነ ይታመናል። ይህም ማለት ከሙሴ ይጀምርና እስራኤላውያን ከምርኮ እስከተመለሱበት ድረስ ያለውን ዘመን ያጠቃልላል። የአንዳንዶቹ መዝሙሮች ይዘት ከምርኮ መልስን ያመለክታሉ። እንዲያውም መዝሙረ ዳዊት ተጠቃልሎና ተጠናክሮ የተጻፈው በዕዝራ ነው የሚሉም አሉ።

እንዳንዶቹ መዝሙሮች ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ይገናዘባሉ።

ለምሳሌ፡-

- መዝ. 59 - ከ1ኛ ሳሙ.19+1
- መዝ. 56 - ከ1ኛ ሳሙ.21+10-15
- መዝ. 34 - ከ1ኛ ሳሙ.21+10-22+2
- መዝ. 52 - ከ1ኛ ሳሙ.22+9
- መዝ. 54 - ከ1ኛ ሳሙ.23+15-23
- መዝ. 7 - ከ1ኛ ሳሙ.22+-1-2 (1ኛ ሳሙ.24)
- መዝ. 142 - ከ1ኛ ሳሙ.22+1-2 (1ኛ ሳሙ.24)
- መዝ. 60 - ከ1ኛ ሳሙ.19+1
- መዝ. 60 - ከ2ኛ ሳሙ22
- መዝ. 63 - ከ2ኛ ሳሙ.15+23
- መዝ. 30 - ከ1ኛ ዜና 21+1-22+1

## አስተዋጽኦ

ሰዎች የተለያየ ሃሣብ በማቅረብ የመዝሙረ ዳዊትን ክፍፍል በተለያየ መንገድ ይሠሩታል። ነገር ግን በቀላሉ ስመከፋፈል እንዲቻል በየክፍሉ መጨረሻ የሚገኘውን የምሥጋና ቃል እንጠቀማለን።

ምዕራፎች

I. መጽሐፍ (1-41)
II. መጽሐፍ (42-72)
III. መጽሐፍ (73-89)
IV. መጽሐፍ (90-106)
V. መጽሐፍ (107-150)

### የመጽሐፉ ዓላማና ዋና አሳብ

የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ብዙ ስነመለኮታዊ መልዕክቶችን የያዘ በመሆኑ አንድ ወጥ ዋና ሃሣብ የለውም። በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት በሰው በኩል ፍጥረታትን እንደገዛና በቅንነትም እንደሚፈርድ በመግለጽ ፍርድ ሲዛባ ችግርና ግጭት ሲፈጠር እግዚእብሔር እንደሚታደግ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።



# መጽሐፈ ምሳሌ

መጽሐፈ ምሳሌ የሞራልና የሥነ ምግባር መመሪያዎችን የያዘና ከሕይወት ጋር ማለትም ከዕለት ተዕለት የኑሮ ገጠመኝ ጋር የሚገናዘብ የቅኔ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ከማንኛውም መጽሐፍ ይልቅ፣ ሁኔታ፣ ባሕልና ጊዜ ከማይገድበው የሰው ሕይወት ጋር የሚዛመድ ትምህርትን የያዘ በመሆኑ ተግባራዊነቱ ለሁሉም ዘመን አይለወጥም።

የመጽሐፈ ምሳሌ ትምህርት ዋናው ትኩረት በአዋቂና በአላዋቂ መካከል የሚታይ የባሕርይ ልዩነት ሲሆን እንዴት አላዋቂነትን በማስወገድ አዋቂ መሆን እንደሚቻልም ትምህርት ይሰጣል።

### በማንና መቼ ተጻፈ?

መጽሐፈ ምሳሌ የተጻፈው በሰለሞን፣ በአጉር፣ በሊሙኤልና በሌሎችም ጠቢባን ነው። በማንና መቼ ተጻፈ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ግን የመጽሐፉን አስተዋጽኦ መመልከት ያስፈልጋል። በምሳሌ 1+1 ላይ የተጻፈው መግቢያ ከምዕራፍ 1-9 ድረስ ያለውን እንጂ ለመጽሐፉ በሙሉ አይደለም፤ስለዚህ የተለያዩ ሰዎች እንደጻፉት በየክፍሉ ማየት እንችላለን።

መጽሐፉ በአጠቃላይ በስምንት ክፍሎች ይከፈላል።

- 1+1-7 ሰለሞን
- 1+8-9+18 ሰለሞን
- 10+1-22+16 ሰለሞን
- 22+17-24+34 የጠቢባን ሰዎች አባባል
- 25-29 የሰለሞን ምሳሌዎች በሕዝቅያስ ሰዎች የተሰበሰበ
- 30 በአጉር
- 31+1-9 ንጉሥ ሊሙኤል
- 31+10-31 ባልታወቀ ሰው

ንጉሥ ሰለሞን ከ971 እስከ 931 ዓ.ዓ. ድረስ እስራኤልን የገዛ በመሆኑ በዚያን ወቅት ማለትም በ10ኛው ክፍለ-ዘመን ገደማ የእርሱን ምሳሌዎች እንደጻፈ ይነገርለታል። ቀሪዎቹን ደግሞ እሰባሰበው የጻፉት የሕዝቅያስ ሰዎች እንደሆኑ ይነገራል። ስለዚህም በምሳሌ መጽሐፍ በስተመጨረሻ የተጻፈው በሕዝቅያስ ዘመን (25+1) በ700 ዓ.ዓ. ገደማ ነው።

ከሰለሞን የሕይወት ገጠመኝ ጋር ነገሮችን ስናያይዝ፣

⇒ መኃልዩ ማኃልየን - በጉርምስና ዘመኑ

⇒ መጽሐፈ ምሳሌን - በመካከለኛ ዘመኑ
⇒ መጽሐፈ መክብብን - በዘመኑ ፍጻሜ (በእርጅናው) እንደጻፋቸው ይነገርለታል።

## የመጽሐፉ ዓላማዎች

ዓላማውን ለማየት የመጽሐፉን መግቢያ መመልከቱ ይበቃል (ምሳ. 1፥2-7)።

- ጥበብንና መልካም ምክርን ለመገንዘብ
- ጥልቅ ሚስጢር ያለውን ቃል ለመረዳት
- በታማኝነት በቅንነትና በትክክል የመኖርን ጥበብ ለማስተማር
- ዕውቀት የጐደላቸው ማስተዋልን እንዲያገኙ
- ዕውቀትን ለመጨመር (ለማዳበር) ነው።

## ተደራስያን

ለማን ተጻፈ? በተደጋጋሚ «ልጄ» እና «ልጆቼ» የሚል ተጽፎ ስለሚገኝ በፀሐፊው በሰለሞንና በተጻፈላቸው ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንድንጠይቅ ያሳስበናል። «ልጄ» የሚለውን ቃል ከምዕራፍ 1-7 15 ጊዜ በተጨማሪ በ19፤27 እና በ27፥11 ሁለት ጊዜ ተጠቅሞበታል። ሰለሞን «ልጆቼ» የሚለውን 4 ጊዜ ተጠቅሞበታል (ምሳ. 4፥1፤ 5፥7፤ 7፥24፤ 8፥32)።

የጠቢብ ሰው አባባል የሚባለው ክፍል 5 ጊዜ ተጠቅሷል (ምሳ. 23፥15 እና 19፥23፤ 26፤ 24፤13 እና 21)።

«በልሙኤል እናት» ደግሞ 1 ጊዜ ተጠቅሷል (ምሳ. 31፥2)።

ይህ (ልጆቼ) የሚለው አባባል ጠቢባኑ (መምህራኑ) ለተማሪዎቻቸው ወይም ለወለዷቸው ልጆች የተጠቀሙበት ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ መልኩ ይህ መጽሐፍ ወላጆች ልጆቻቸውን በመልካም ሥነ ምግባር ለማነጽ የሚጠቀሙበት መመሪያ ነው።

መጽሐፈ ምሳሌ ከእግዚአብሔር ዘንድ እውቀትንና ጥበብን እንድንሻ ሲመክረን የዕውቀት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ጌታ መሆኑን በማመንና በማስገንዘብ ነው። ለዚህም ዕውቅና ሲሰጥ «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» በማለት እግዚአብሔር በኃይሉና በቅድስናው የተፈራ መሆኑን አመልክቷል። ፍርሃትና እምነት በብሉይ ኪዳን ጐን ለጐን የሚሄዱ ሃሳቦች ናቸው።



ምሳሌዎቹ በግጥም መልክ የተደረደሩ ሲሆን አደራደራቸውም የራሳቸው የሆነ ልዩ ዘይቤ አላቸው። ድርድሮቹም 2 መስመር፣ 3 መስመር፣ 4 መስመር 6 መስመርም ይኖራቸዋል።

### የጽሑፉ ይዘት

1. ተመሳሳይ ንጽጽሮች (synonymous parallelism)

  - የመጀመሪያውና የሁለተኛው መስመር ሃሣብ ሲመሳሰል
    ሙሉ በሙሉ ሲመሳሰል «ጥንቃቄ <u>ይጠብቅሃል</u>። ማስተዋልም ይጋርድሃል።» (ምሳ. 2፥11 ይጠብቅሃል፣ ይጋርድሃል)

  - በከፊል ሲመሳሰል «ለራስህ የሞገስ ዘውድ <u>ለአንገትህም</u> ድሪ ይሆንልሃልና።» (ምሳ. 1፥9 (ለራስህ፣ ለአንገትህ» 4፥14)

2. የተለያዩ (ተቃራኒ) ንጽጽሮች (Antithetical parallelism)

   «ጠቢብ ልጅ <u>አባቱን</u> ደስ ያሰኛል። ሰነፍ ልጅ ግን <u>ለእናቱ</u> ሃዘን ነው።» (ምሳ. 10፥1) አባት፣ እናት

   «<u>አባይ</u> ሚዛን በእግዚአብሔር ፊት አስፀያፊ ነው፤ እውነተኛ ሚዛን ግን ደስ ያሰኘዋል።» (ምሳ. 11፥1) አባይ፣ እውነተኛ (ምሳ. 15፥1)

3. ቀጣይ ንጽጽር (synthetical parallelism)
   የመጀመሪያውን መስመር ሃሣብ የሁለተኛው መስመር ውጤቱን ያሳያል
   «በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፣ እርሱም ጐዳናህን ያቀናልሃል።» (ምሳ. 3፥6፣ 16፥3)

   ሁለተኛው የመጀመሪያውን ይገልጻል።
   «ምናምንቴ ሰው የበደለኛም ልጅ በጠማማ አፍ ይሄዳል።» (ምሳ. 6፥12፣ ምሳ. 15፥3)

4. መወከል፣ (መተካት)

   «ሆምጣጤ ጥርስን፤ ጢስም ዓይንን እንደሚጐዳ እንዲሁም ታካች ላኩት» (ምሳ. 10፥26)።

### አስተዋጽኦ

I. መግቢያ (1፥1-7)
II. የጥበብ መመሪያዎች (1፥8-9፤18)
III. የሰለሞን ምሳሌዎች (10፥1-24፤34)

IV. በሕዝቅያስ ሰዎች የተጻፉ የሰለሞን ምሳሌዎች (25፥1-29፥27)
V. የአጉር ምሳሌዎች (30፥1-33)
VI. የልሙኤል ምሳሌዎች (31፥1-9)
VII. ስለ ልዩዋ ሴት (31፥10-31)

### የምሳሌ መጽሐፍ አጠናን ዘዴ /መመሪያ/

- በአንዴ ብዙ ክፍል ማንበብ ቁምነገሩን በሚገባ እንዳንጨብጥ ስለሚያደርግ አንቀጽ በአንቀጽ ማንበብ ይመረጣል።

  (ለምሳሌ ምሳ. 1፥1-7፣ 18-19፣ 1፥20-33) ከቁጥር ቁጥር መልዕክቱና ርዕሱ የሚለዋወጥበት ጊዜ አለ። እንዲህ ሲሆን አንዷ ቁጥር በራሷ በቂ ትምህርት ትሰጣለች። ሆኖም ግን አውዱን መዘንጋት አይገባም።



## መጽሐፈ መክብብ

### ማን ጻፈው?

የመክብብ መጽሐፍ ፀሐፊ ማን እንደሆነ ለማወቅ ጸሐፊው በጽሁፉ ስለራሱ የተናገረውን ደጋግሞ ማየት በቂ ነው (1፥1-2፣ 1፥12፣ 7፥27፣ 12፥8-10)። የዳዊት ልጅ፣ የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ ባለጠጋ ይህን የማዕረግ ስምና መጠሪያ የያዘ በብሉይ ኪዳን ከንጉሥ ሰለሞን በስተቀር ሌላ ሊኖር አይችልም (2፥4-6)። አንዳንድ ሰዎች የመጽሐፉን አጻጻፍ ዘይቤ በማየት የሥነ-ጽሑፍ ይዘቱ በሰሰሞን ዘመን እንደነበረው ዓይነት ጥንታዊ ሳይሆን ከዚያ ወዲህ ካሉ ሥነጽሑፍ ዘይቤዎች (style) ጋር ስለሚመሳሰል የሰለሞን አይደለም በማለት ይከራከራሉ።

### ቁልፍ ጥቅስ

በመጽሐፉ የመጀመሪያና የመጨረሻ ምዕራፍ እንዲሁም በመጽሐፉ ሙሉ ክፍል በየቦታው ተጠቅሶ እንደሚታየው «ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው።» የሚለው መልዕክት ነው። ይህ አባባል በመጽሐፈ መክብብ 35 ጊዜ የተጻፈ ሲሆን በሌላ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ አንድ ጊዜ ተጽፏል (ኢዮብ 27፥12)።

### የመጽሐፉ ዋና ዓላማ

ሕይወት አጭር፣ ውስብስብ፣ በውጣውረድ የተሞላች ከመሆኗም በላይ ዳግመኛ (ያለፈውን ሕይወት በድጋሚ) መኖር ስለማይቻል በጥንቃቄና በጥበብ መኖር ያሻል። የመክብብ መጽሐፍ በዚህ ዘመን ያለ እንባቢ ሕይወት ከእግዚአብሔር የተበረከተ በጦታ መሆኑን በማወቅ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት፣ ባለፈ ትዝታና በወደፊት ህልም ሳይሆን አሁንን በሚገባ መኖር እንድንችል ይረዳል።

ሰለሞን በዚህ መጽሐፍ የሚዘግበው የህይወትን አጭር መሆን ሰው ከሚገጥመው መከራ ጋር በማገናዘብ ነው። ህይወት በውጣ ውረድ የተሞላች ናት፣ ሆኖም ሰው በሕይወቱ የሚደሰትበት ነገር ቢኖረውም ከዚህ ምድር ሕይወት በኋላ ዘላለማዊውን እንዲያስብ ያደርገዋል። ሰው በሚያስበው በሚናገረው፣ በሚያደርገውና በሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብብሔር በመጨረሻ ወደ ፍርድ እንደሚያመጣው ትምህርት ይሰጣል።

**ብመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ሐረጐች (ኅጥቦች)**

⇒ ነፋስን እንደመከተል ነው። (9 ጊዜ ተጠቅሷል)
1፥14፣ 17
2፥11፣፣ 17፣ 26
4፥4፣ 6፣ 16
5፥16
6፥9

**⇒ በሕይወትህ ዘመን ደስ ይበልህ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና፤**

**2+24-26**
**3+13-22**
**5+18-20**
**9+9-10**
**11+8-9**

**⇒ እግዚአብሔርንና ሊመጣ ያለውን ፍርድ ፍራ**

**3+17**
**5+2-7**
**7+18**
**8+12-19**
**11+9**
**12+13-14**

**«ከፀሐይ በታች» የሚለው ሐረግ 29 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ይህም አባባል ይህችን ምድርና ውስንነቷን ገላጭ ነው፡፡**

**«እግዚአብሔር» የሚለው ቃልም ወደ 30 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡**

## አስተዋጽኦ

**የመጽሐፈ መክብብን ክፍፍል መስራት አስቸጋሪ ቢሆንም ለክፍፍሉ ወጥ ነገር ለመሥራት «እግዚአብሔር በሰጠህ ሕይወት ደስተኛ ሁን» በሚለውን ሃሣብ መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ለመከፋፈል ተሞክሯል፡፡**

**I. መግቢያ**

**የሁሉም ነገር ከንቱነት**
**አሰልቺ ሕይወት (routine) (1+1-11)**

**II. ደስታ፣ እውቀት፣ መከራ፣ ችግርና ፍትህ መጓደል ሁሉ ከንቱ ስለሆነ የሰው ልጅ እግዚአብሔር በሰጠው ሕይወት ደስተኛ ይሁን (1+12-2+26)፡፡**

**III. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ነገር ጊዜን ወስኖለታል፡፡ ስለዚህም የሰው ልጅ ሁሉን ባለመቀበል ከመታገል ይልቅ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን በመቀበል መደሰት ይገባዋል (13+1-5+20)፡፡**

**በራስ ምኞት ላይ ብቻ የተመሰረተ ጥረት ሁሉ ከንቱ ስለሆነ ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ሕይወት ደስተኛ ሊሆን ይገባል (14+4-5+20)፡፡**



**IV. ስእኛ አሰን የምንሰው ነገር ባዶ በመሆኑና ስለወደፊትም እርግጠኞች ባለመሆናችን ምክንያት ዛሬን እግዚአብሔር በሰጠን ሕይወት እንደሰት (16+1-8+15)፡፡**

**- ሀብት፣ ንብረት፣ ክብር፣ ዝና፣ ሌላውም ሁሉ ከንቱ ስለሆነ ባላችሁ ነገር በመርካት ተደሰቱ፡፡**

**- ስለወደፊት እርግጠኞች ባንሆንም፣ ጥበበኛነትና አዋቂነት ከሞኝነትና ከስንፍና ቢሻልም ከንቱ ነው፡፡ ግን ሕይወታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ስጦታ በመሆኑ ደስ ሊለን ይገባል፡፡**

**V. ወደፊት ከሚሆነው ነገር እርግጠኛው ሞት ነው፡፡ ስለዚህም ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ሕይወት ደስተኛ ሆኖ ይኑርበት፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሁሉም ፍርድን እንደሚሰጥ በማሳወቅ እንዲጠነቀቅ ያሳስባል፡፡**

**VI. መደምደሚያ**

**ሕይወት ተሰባሪ፣ ሁሉም ነገር አላፊ፣ ጠፊና ከንቱ በመሆኑ አንባቢ የአዋቂን ቃል በመስማትና ትኩረት በመስጠት የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በፍርሃት ሊጠብቅና ሊመጣ ያለውን ፍርድ፣ ዘላለማዊነትንም ሊያስብ ይገባዋል (12+8-14)፡፡**

**መክብብ ንጉሡ ሰሰሞን በእርጅና ዘመኑ ላይ ከድካሙና ከብርታቱ እግዚአብሔር ያስተማረውን በእርሱ ዕርዳታ የጻፈበት በመሆኑ ብዙ ጥበብን ልንማርበት እንችላለን፡፡**

## መኃልየ መኃልየ

### በማንና መቼ ተጻፈ?

የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ ሰሰሞን መሆኑ ተጠቅሷል (ምሳ. 1÷1):: ለዚህም ማስረጃው በስም ተጠቅሶ መገኘቱ ሲሆን (ምሳ. 1÷5፣ 3÷7፣ 9፣ 11፣ 8÷11-12) ንጉሥ መሆኑም ተጠቅሷል (ምሳ. 1÷4፣ 12፣ 3÷9፣ 11፣ 7÷6):: በተጨማሪም ንጉሡ ሰሰሞን ተፈጥሮን የሚያደንቅና የሚወድ መሆኑ በ1ኛ ነገሥት 4÷33 ተጽፏል::

### የመጽሐፉ ዓላማ

መኃልየ መኃልይ ማለት የመዝሙሮች ሁሉ መዝሙር ማለት ነው:: አይሁድ መኃልየ መኃልየን የእግዚአብሔርና የእስራኤል ታሪክ ነው ሲሉ ብዙ ክርስቲያኖች ደግሞ የቤተክርስቲያንና የክርስቶስ ነው ይላሉ:: ሆኖም ግን በዚህ መጽሐፍ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ስላለ የፍቅር ታሪክ የምንመለከትበት ነው:: በ1ኛ ነገስት 11÷3 እንደተገለጸው ሰሰሞን 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች የነበሩት ሰው ነው:: ምናልባትም ይህን መጽሐፍ የጻፈው የመጀመሪያ ሚስቱን ባገባበት ወቅት እንደሆነ ይገመታል::

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይህች የመጀመሪያ ሚስቱ የግብጽ ንጉሥ የፈርኦን ሴት ልጅ ሳትሆን አትቀርም ይላሉ:: (1ኛ ነገ. 3÷1) ነገር ግን ሌሎች ይህችን ፍቅረኛውን ንግሥት (ልዕልት) ብሎ አይጠራትም ስለዚህም ግብጻዊት ሚስቱ አይደለችም ይልቁንም ከሊባኖስ ሳትሆን አትቀርም ያላሉ (4÷8)::

### አስተዋጽኦ

I. ርዕስ (1÷1)
II. ትጭጭት (1÷2-3÷5)
III. የጋብቻ ወቅት (3÷6-5÷1)
IV. ከጫጉላ በኋላ (5÷2-6÷13)
V. የትዳር ቅርርብ (7÷1-8÷4)
VI. በፍቅር ማደግ (8÷5-14)



## ምዕራፍ አራት

## ታላላቅ ነቢያት

## ትንቢተ ኢሳይያስ

### ፍርድንና መቤዠትን ያመጣው ቅዱስ እግዚአብሔር

የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢቶች የተሰጡት በያዚያን አገዛዝ ዘመን ፍጻሜ ገደማ ነው:: ይህም በ750 ዓ.ዓ. ማብቂያ ላይ ነበር:: ምናሴ ከንጉሥ ሕዝቅያስ ጋር አብሮ ገዢ የሆነበትን ዘመን እስከ (690 ዓ.ም.) ድረስም ቀጥሏል:: የአገልግሎቱ ዘመንም ነቢዩ ሚክያስ ካገለገለበት ዘመን ጋር አንድ ነበር:: ኢሳይያስ ያገባና ቢያንስ የሁለት ልጆች አባት መሆኑ የታወቀ ነው (ኢሳ. 7÷43 ፤ 8÷3):: ይኖርበት በነበረው በኢየሩሳሌም በተለያዩ ጊዜያት ለይሁዳ ነገሥታት ትንቢትን ተናግሯል:: ከሁሉም በላይ ስለ መሚሐ በተናገራቸው ትንቢቶቹ ታዋቂና የመጀመሪያ ነቢይ ነው (ኢሳ.7÷39):: ስለመሚሐ መንግሥና መከራ ማየት ተንብዮአል:: መልእክቶቹም ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር የተያያዙ ናቸው:: ምክንያቱም የቅዱስ እግዚአብሔርን ክብር በመመልከቱ ሕይወቱ ፍጹም ለውጥን ስላገኘ ነው (ኢሳ÷6):: መልእክቶቹም በሚከተሉት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው::

### የኢሳይያስ አስተዋጽኦ

I. የእግዚአብሔር መክበር የሰውን ትዕቢት ያዋርዳል (1-6)
II. የሰላም ኅሉቃ የይሁዳ ጦርነት እንዲያከትም ያደርጋል (7-12)
III. የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እቅድ ለሕዝቦች (13-27)
IV. እግዚአብሔርን ወይም የጦር ኃይልን መታመን (28-39)
V. እቻ የሌለው እግዚአብሔር ደህንነትን ያመጣል (40-48)
VI. የመከራ አገልጋይ ደህንነትን ያመጣል (49-55)
VII. የእግዚአብሔር አጠቃላይ እደሳና ፍርድ (56-66)

ኢሳይያስ የተለያዩ ምሣሌያዊ ንግግሮችን እየተጠቀመ የሚናገርና የተሰጠ ሰባኪ ነበር:: ለምሳሌ ኢሳይያስ 5 ላይ እሥራኤልን (ይሁዳን) ከወይን ተክል ጋር፤ ኢሳ. 1÷10 ላይ ደግሞ የይሁዳ ነገሥታትን ከሰዶም ገዥዎች ጋር ሲያመሳስል እንመለከታለን:: መልእክቶቹም የእግዚአብሔር ኃይል ሰውን ከኃጢአት፣ ነገሥታትን ከኃያላን ማዳን እንደሚችል በግልጽ ለማሳየት ነው:: ሌላ አምላክ የለምና የእሥራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ብቻ እንዲታመን ጥሪ ያደርጋል:: እግዚአብሔርም ዘላለማዊ የሰላም መንግሥቱን እንደሚመሠርት ይናገራል::

## 1. የእግዚአብሔር ክብር የሰውን ትዕቢት ያዋርዳል (ኢሳ. 1-6)

ነቢዩ ኢሳይያስ የጦርነት መከራን እያዩ የተቸገሩትን አመጸኛ የሆኑትን የይሁዳን ሕዝብ ንስሐ እንዲገቡ፣ ፍትህን እንዲያደርጉና በቤተመቅደስ ውስጥ ትርጉም የለሽ መስዋዕት ማቅረብ ያቆሙ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ እያለ ጥሪ አድርጓል (ኢሳ. 1÷1-20)። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጨቋኝ ገዢዎችንና ከያዚያን ዘመን ብልጽግና የተነሳ ራሳቸውን ሸላልመው በትዕቢት የተወጠሩትን የይሁዳን ሴቶች ያስወግዳል (ኢሳ. 3÷1-4÷1)። መልካም ፍሬ የማያፈራውን የራሱን የወይን እርሻ (ይሁዳንም) ጭምር ይደመስሳል (ኢሳ. 5÷1-7)። በመጨረሻም ቀን እግዚአብሔር በክብሩ ሲገለጥ የማይታዘዙትንና ትዕቢተኞችን ሁሉ በምድር ላይ ያዋርዳቸዋል (ኢሳ. 2÷17)። ኢየሩሳሌም ትለወጣለች። የእግዚአብሔር ቁጥቋጦ (መሲሑ) በዚያ ይሆናል፣ የይሁዳ ኃጢአት ይወገዳል እናም ኢየሩሳሌምም ትቀደሳለች (4÷2-6)።

ያዝያን በሞተበት ዓመት ኢሳይያስ በራዕይ የነገሥታት ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር በግርማው በቤተ መቅደሱ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ክብሩን አየ። ከዚያም ራሱን አዋረደ፤ ይቅርታን አገኘና እግዚአብሔርን የማይሰሙትን ሰዎች ልብ ያደነድን ዘንድ በእግዚአብሔር ተላከ (ኢሳ. 6÷1-13)። ኢሳይያስ የሚናገረውን እንደማይሰሙ ደግሞም የሚሰሙ **<u>ቅሬታዎች</u>** እንደሚኖሩ እግዚአብሔር ያውቃል። ሌሎች ግን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ካልታዘዙ ከድንዳኔአቸው የተነሳ ለፍርድ የተዘጋጁ ይሆናሉ።

## 2. የሠላም አለቃ የሆነው ጌታ የይሁዳን ጦርነት እንዲያከትም ያደርጋል (ኢሳ. 7-12)

በክፉው ንጉሥ በአካዝ ዘመን መንግሥት ይሁዳ በጠላቶቹ በሶሪያና በእሥራኤል ተጠቃለች። ንጉሥ አካዝም ማዳን በሚችል በእግዚአብሔር መታመንን እምቢ አለ (ኢሳ. 7÷1-19)። ነገር ግን የእሥራኤልንና የሶሪያን መጥፋት እግዚአብሔር ቢናገርም አሶርን መታመኛው አድርጐ ዕርዳታን ጠየቀ (ኢሳ. 8÷1-7፣ 9÷8-10÷4)። አሶርም እንደሚደመስስ ከትዕቢቱም የተነሣ እንደሚጠፋ እግዚአብሔር ተናግሯል (ኢሳ. 10÷5-19)።

በእንዲህ ዓይነት ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ በአማኑኤል አማካይነት ተስፋንና ሰላምን ሰጠ። አማኑኤልም ከድንግል የሚወሰድ፣ እግዚአብሔር አዳኝ ስለመሆኑ የምልክት ልጅ ነበር። እርሱም ታላቁ ብርሃን የሠላም አለቃ፣ በዳዊት ዙፋን ሆኖ ለዘላለም የሚገዛ ነው (ኢሳ. 9÷1-7) (ማቴ.4÷13-16)። እርሱ በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላ ቁጥቋጥ በመሆኑ የዘላለምን ሰላም መስጠት ይችላል (ኢሳ. 11÷1-9)። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ተስፋዎች ሰዎች



በእግዚአብሔር በአዳኛቸው እንዲታመኑና እርሱንም እንዲያመሰግኑ ያደርጋቸዋል (ኢሳ. 12÷1-6)። ጦርነትንም ለዘላለም ያስወግዳል።

በኢሳይያስ 7÷14...ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች» የሚለው ጥቅስ እግዚአብሔር አዳኝ መሆኑን የሚያመለክት ምልክት ነው። ይህ ምልክት በሁለት አቅጣጫ እንደሚተረጐም ግልጽ ነው። የመጀመሪያው አካዝ ከሚፈራቸው ካስጨነቁትም ነገሥታት እጅ እግዚአብሔር ማዳን መቻሉን ያሳየል። ለዚህም ምልክቱ የነቢዩ የኢሳይያስ ሚስት (ኢሳ. 8÷1-3) ፀንሳ የምትወልደው ሕፃን ክፉውንና መልካሙን ለይቶ ሳያውቅ አካዝ ያፈራቸው ጠላቶች ይደመሰሳሉ። ሁለተኛው ደግሞ የዓለምን ሕዝብ ሁሉ እያስፈራራ በኃጢአት የተበተባቸው ወደ ዘለዓለም ሞት የሚነዳቸው ሰይጣን በመሢሑ፣ ከዳዊት ዘር ከሆነው ከሠላም አለቃ ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የተነሳ በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ሁሉ ታላቅ ብርሃን አይቶነፃ እንደሚወጣ የሚያመለክት ነው (ኢሳ. 9÷4)።

## 3. ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዕቅድ፡- (13-27)

የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ ስለሀብታቸውና ስለመከላከያ ኃይል ጥንካሬያቸው በትዕቢት ተወጥረዋል (ኢሳ. 13÷11-19፣ 16÷6)። ከዚህም የተነሳ ኢሳይያስ የባቢሎንን፣ የአሦርን፣ የፍልስጤምን፣ የሞአብን፣ የሶርያን፣ የግብጽን፣ የኤዶምን፣ የአረብንና የጢሮስ መንግሥታትን ውድቀት ይተነብያል (13-23)። በጌታ ቀን የእግዚአብሔር ቁጣ በሚወርድበት ጊዜ እነዚህ ነገሥታት በቁጣው እሳት እንደሚጠፉ ይናገራል (ኢሳ. 13÷6-13)። ይህም የእግዚአብሔርን ዕቅድ ምንም አይለውጥም። ሕዝቡን (ይሁዳን) መልሶ ለመመሥረት ያለውን እቅዱንም ምንም ነገር አያናጋውም (14÷1-3 6÷5)። የሚያስደንቀው ነገር ብዙ አህዛብ ከግብጽና ከአሦር ወደ ጌታ በመመለስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን ይሆናሉ (ኢሳ. 19÷19-25)።

የኢሳይያስም ንግግር ስለወደፊቱ ግራ የተጋቡትን አይሁዶች አጽናንቶአቸዋል። የአህዛብ ነገሥታትንም የሚፈሩ አይደሉም። ለዓለም ያለው የእግዚአብሔር ዕቅድም ይፈፀማል።

እነዚህ ክስተቶች የሚያመለክቱን በምድር ላይ ያለውን ሁሉን ነገር እግዚአብሔር በእሳት የሚደመስስበትን የመጨረሻውን ፍርድ ቀን ነው። ከክፋቱ የተነሳ እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ፣ ነገሥታትንና በትዕቢት የተወጠሩ ከተሞችን ሁሉ ይቀጣል (ኢሳ. 24÷1-22)። በዚያን ጊዜም እርሱ ከሕዝቡ ጋር በጽዮን ይገዛል፣ ይከብራልም። ሞትና ለቅሶ ለዘላለም ተወግደው ሁሉም በተወደደው በእግዚአብሔር ግብዣ ላይ ሆኖ በደስታ ይዘምራል። ሙታን ሕይወትን ያገኛሉ፤ ደስታና ማዳን ምድሪቱን ይሸፍናሉ (ኢሳ. 25÷1-26 ÷19)።

### 4. እግዚአብሔርን ወይም የጦር ኃይልን መታመን (ኢሳ. 28-39)

ኢሳይያስ ለምድር ነገሥታት ሁሉ ካለው ከእግዚአብሔር የቅጣት ዕቅድ ወደ እሥራኤል (የሰሜኑ ክፍል) በ722 ዓ.ዓ. ከመውደቁ በፊት ወደ ነበረው ሁኔታ ይሸጋገራል:: ከእግዚአብሔር ለመማር ምክሩንም ለመስማት እምቢ ወዳሉ በትዕቢት ወደሰከሩ የእሥራኤል ነገሥታት መሪዎች፣ ካህናትንና ነቢያትን በፍጹምነትና በፍትህ ከሚያስተዳድረው ከእግዚአብሔር ያነጻጽራል:: እግዚአብሔር ለቅሬታው እውነተኛ የሆነ መመሪያ የሚሰጥ ነው (28÷1-29):: እነዚያ እመጻኞች መሪዎች ይደመሰሳሉ:: ይሁዳም ይቀጣል፣ ምክንያቱም ከእሥራኤል ስህተት አልተማረምና:: ነቢያቶቻቸው ያስቷቸዋል:: ሕዝቡም የከንፈር አገልግሎት ብቻ ለእግዚአብሔር እየሰጠ ልቡ ግን ከእግዚአብሔር የራቀ ሆኖአል (29÷9-14)::

ለዚህም በቂ ማስረጃ የሚሆነው መሪዎች ከአሦር ጠላቶች ለማምለጥ (ለመዳን) ከእግዚአብሔር ይልቅ በግብጽ ወደ መደገፍ ማዘንበላቸው ነበር (30÷1-4፤ 31÷1-3):: በእግዚአብሔርም ሆነ በነቢዩ ቃል ለማመን እልፈለጉም (30÷9-12):: ኢሳይያስም ይህን ከንቱ የሆነውን በሥጋ ለባሽ መታመንን ያወግዛል:: እግዚአብሔር ከርኅራኄው የተነሳ ይሁዳን፣ ለማስተማር በብልጽግና ለመባረክና ከአሦር እስጨናቂ አገዛዝም ለመታደግ ይፈልጋል:: ነገር ግን አስቀድሞ የይሁዳ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር መመለስና በእርሱም መታመን ይኖርበታል (30÷18-31÷9):: ይህን መታመንን ሲያበረታታ ኢሳይያስ ሕዝቡን ያሳሰባቸው ነገር ቢኖር አንድ ቀን ጻድቅ የሆነው መሢሐቸውና ንጉሣቸው ይመጣል፣ ዕውር መሆናቸውንም ያስወግዳል (32÷1-8):: ተመቻችተው የተቀመጡትን ሴቶች ለሚመጣው ጥፋት እንዲያዝኑ ጥሪ ያደርግላቸዋል (32÷9-14):: ደግሞም እግዚአብሔር ሲከበር የአሦር መንግሥት በይሁዳ ንጉሥ በእግዚአብሔር እንደሚደመሰስም ይተነብያል (33÷1-24):: ኤዶምንና የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሲያገኛቸው (34÷1-15) ነገር ግን እግዚአብሔር የተቤዣቸው በጽዮን ለመኖር ሲመለሱ በኢየሩሳሌም ትልቅ ደስታ ይሆናል(35÷1-10)::

የአሦር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን በከበቡት ጊዜ ንጉሡ ሕዝቅያስ ይህን መልእክት ተቀብሎ በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን አደረገ (36÷1-22):: በዚያን ጊዜ ሰው ሁሉ ሕዝቅያስ ራሱን ለአሦር መንግሥት ማስገዛት እንዳለበት ቢተማመኑም ሕዝቅያስና ኢሳይያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው እግዚአብሔር የአሦርን መንግሥት በማሸነፍ ለሕዝብ ሁሉ ክብሩን እንዲያሳይ ጸለዩ (37÷11-20):: እግዚአብሔርም ይህን ጸሎታቸውን ሰምቶ ሲመልስ መልእኩን ልኮ 185000 (አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ) የአሦርን ሠራዊት በአንድ ሌሊት እንዲገደሉ አደረገ (37÷36):: ከሕዝቅያስ ጽድቅና የጸሎት ሕይወት የተነሳ ምድራዊ ሕይወቱ በአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜው እንዲረዝም ተደረገ (38÷1-22):: ነገር ግን



በኋለኛው ሕይወቱ ሕዝቅያስ ሰቀደመው እምነቱ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ከእግዚአብሔር ይልቅ በባቢሎን መንግሥት ላይ መታመንን ቀጠለ (39÷1-8)::
በኢሳይያስ መጽሐፍ እስካሁን የተመለከትነው (ም. 1-39) ክፍል አንድ ሆኖ ብዙ ጊዜ የፍርድ ሃሣብ የያዘ ነው:: በመሆኑም እግዚአብሔር የማይታዘዙትን ሁሉ እንደሚቀጣቸው እንመለከታለን:: በመቀጠልም የምንመለከተው (ም. 40-66) የጸጋ ክፍል በመባል ይታወቃል:: ስለዚህም ክፍሉ ያተኮረው የእግዚአብሔር ምህረት ለሁሉም ሕዝብና ለሰው ሁሉ መዳን ምክንያት የሚሆን ክርስቶስ የመወለዱም ትንቢት የተሰጠው፣ በዚህ ክፍል ነው:: ከዚህ ሃሣብ በመነሳት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ትንቢተ ኢሳይያስን ሲከፋፍሉ ከም. 1-39 የብሉይ ኪዳን 39ኙን መጽሐፍት የሚወክል ሲሆን ከም 40-66 በአጠቃላይ 27 መጻሕፍት የአዲስ ኪዳንን 27ቱን መጽሕፍት ይወክላል ይላሉ:: ይህም በመሠረተ ሃሣቡ ትክክል ነው::

### 5. እቻ የሌለው እግዚአብሔር ደህንነትን ያመጣል (40-48)::

እነዚህ ምዕራፎች በሕዝቅያስ ዘመን ፍጻሜና በከፉ ልጁ ምናሴ አገዛዝ ዘመን ጅማሬ እንደተጻፉ ይታመናል:: በዚህ ክፍል በተሰጡት ትንቢቶች አማካይነት የእሥራኤል ቅሬታ እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግን እንዲያፀኑ እግዚአብሔር ያበረታታቸዋል:: ይህም ቀጥሎ ሲመጣ ካለው ከባቢሎን ምርኮም እንደሚታደጋቸው ለማሳየት ነው:: በምዕራፍ 40÷1-11 ባለው ክፍል የተሰጠው የማጽናናት መልእክት እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲገዛ እንደሚመጣ በማመልከት ነው:: ከእህዛብም ይሁን ከእህዛብ አማልክት የእግዚአብሔርን ጥቂቱን ኃይል እንኳ የያዘ የለምና ሊፈሩ የሚገቡ አይደሉም (ኢሳ. 40÷12-16):: ምንም እንኳን ስለእግዚአብሔር ሥልጣን ግራ የተጋባና እውር ሕዝብ ማለትም ተስፋቸውን በጌታ ላይ የሚያደርጉ እንደማያፍሩ የተረጋገጠ ነበር:: (40÷27፤41÷10፤ 42÷18-20):: የእግዚአብሔር ሕዝብ በየትኛውም ዘመን ይሁን ቦታ የሚኖር እግዚአበሔርን የሚታመንና የሚጠባበቅ ቢሆን ምን ጊዜም ጥንካሬን እያጣም (40 ÷27-31)::

እግዚአብሔር የእህዛብ አማልክት ሁሉ ምንም እንዳይደሉ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ፣ የሰው እጅ ሥራዎች እንደሆኑ ይናገራል:: (4÷15-21፣ 7÷21-24 44÷9-20) የባቢሎናውያን ቤል (ማርዱክ) እና ኔቦ የሚባሉ አማልክት፣ ባቢሎንም ጭምር እንደሚወድቁ ይናገራል (46÷1-47፣ 15):: ከይሁዳ ሕዝብ አምላክ ሌላ አምላክ በፍጹም የለም:: እርሱ አልፋና ኦሜጋ ነው:: ቅዱስ፣ ፈጣሪ፣ አዳኝና ንጉሥ ቢኖር እርሱ ብቻ ነው (41÷4፣ 43÷10-15፣ 44÷6-8፣ 48÷12):: በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ ያውቃል:: አስቀድሞም ለሕዝቡ ለሰወደፊቱ ዕቅድ አውጥቷል (43÷18-21)::

ይሁዳ ከተማረከ በኋላ ነገሥታትን ሁሉ አሸንፎ ነፃ የሚያወጣና ኃይለኛን መንግሥት እግዚአብሔር ያስነሳል:: ይህም ንጉሥ፣ ቂሮስ አይሁዶች ከባቢሎን ከምርኮ አገር ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ይፈቅዳል:: ኢየሩሳሌምና የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደገና እንዲገነባ ያደርጋል (ኢሳ. 41÷1-4፣ 44÷24-45÷7፣ 48÷20 1÷1-6):: ይህም የሚያመለክተው እስካሁንም የኢየሩሳሌምን ሕዝብ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ነው:: አገልጋዮቹም ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸውም እርሱ ነውና:: በአህዛብ ሁሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ክብር የሚመሰክሩ የእግዚአብሔር ምሥክሮችም ናቸው::

6. *የመከራው አገልጋይ ደህንነትን ያመጣል (ኢሳ. 49-55)*

ይህ ክላይ የመከራው አገልጋይ የተባለው ሃሣብ ክርስቶስ መከራ የተቀበለ አገልጋይም እንደሆነ የሚያመለክት አሣብ ነው::

ነቢዩ ኢሳይያስ እምቢተኛና የማይታዘዝ አገልጋይ በሆነው በአይሁድ ሕዝብና ፍትህንና ጽድቅን በምድር ላይ ለመመሥረት እግዚአብሔር በመረጠው አገልጋይ (ኢሳ. 42÷19 እና 42÷1-4) መካከል ውድድር እያደረገ ይገኛል:: ከራሱ ሕዝብ መከራን የሚያይ የሚቸገር ቢሆንም በመጨረሻ የእግዚአብሔር ማዳን ለዓለም ሁሉ የሚደርስ የአሕዛብ ሁሉ ብርሃን ነው (ኢሳ. 42÷6፣ 49÷4-6):: በመጀመሪያ የተናቀና የተዋረደ (ኢሳ. 46÷7፣ 50÷6) ፊቱም መልኩም የጠፋ ይሆናል:: ስለዓለም ኃጢአት ሲል በፈቃደኝነት ይሞታል (ኢሳ. 52÷14፣ 53÷3-8) በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ከእግዚአብሔር ዘንድ እርዳታን ይፈልጋል:: እግዚአብሔርም ከሙታን በማስነሳት በታላቅ ሁኔታ ያከብረዋል (ኢሳ. 50÷7-10፣ 52÷13፣ 53÷12):: ምንም እንኳን ኃጢአት የሌለበት ቢሆንም የዓለምን ኃጢአት ተሸክሞ ለእግዚአብሔር የበደል መስዋዕት ሆኖ ይቀርባል (ኢሳ. 53÷9-11):: ይህ መከራ አይቶ ፀኋላ የከበረው አገልጋይ በአዲስ ኪዳን የተገለጠው መሲህና ጌታ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማር. 10÷33-34፣ ዮሐ. 10÷17-18፣ የሐዋ. 8÷32-35)::

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ለማዳን ብቻ ሳይሆን ተስፋ የሰጣቸው ጌታን እንዲፈልጉ፣ ለእግዚአብሔር ሕግ እንዲታዘዙና በማዳኑም ይደሰቱ ዘንድ ያበረታታቸዋል (ኢሳ. 51÷1-3):: አልፎ ተርፎ ሕዝቡን ያጽናናቸዋል:: የምርኮ ዘመናቸውም ፈጥኖ ያልፋል፣ የእስራኤል ቅሬታ ወደ ጽዮን ይመለሳል:: እንደመልካም እርሻም ይለመልማል:: እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ሲታደጋት እርስ በእርሳቸው «አምላክሽ ነግሦአል» እየተባባሉ በዝማሬ ደስታቸውን ይገልጻሉ (ኢሳ. 54÷1-8):: ክፉ መንገዳቸውን ቢተውና እግዚአብሔርን ቢፈልጉ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር ይላል (ኢሳ. 54÷1-8):: አስደናቂ አሠራሩ



ከሰው ግምትና መረዳት በላይ ቢሆንም የእርሱ ቃል ከዳዊት ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ይፈጸማል (ኢሳ. 55÷1-13)::

7. **የእግዚአብሔር አጠቃላይ እድሳትና ፍርድ (ኢሳ. 56-66)**

የታደሰው የእግዚአብሔር መንግሥት ግብረገባዊ ሁኔታው ፍትህን፣ ተገቢ የሆነ የሰንበት አከባበርን (ኢሳ. 56÷1-8)፣ በእግዚአብሔር ፊት በትሁት ልብ የሚደረግ ጾምን፣ የተቸገሩትን መርዳትን (ኢሳ. 58÷1-12) ሰውን ከእግዚአብሔር የሚለየውን የኃጢአትን መንገድ መተውን ያጠቃልላል (ኢሳ. 59÷1-3):: የእግዚአብሔር ክብር በሕዝቡ ላይ የማዳንን ብርሃን ሲያበራ ሲነሳ አሕዛብ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው እግዚአብሔርን ያመልኩታል:: ስጦታቸውንም ያቀርቡለታል (ኢሳ. 60÷1-9):: ሐዘናቸውን ወደ ደስታ፣ ምድረ ባዳቸውን ወደ ልምላሜ፣ ጥፋታቸውን ወደ ልማት ይለውጣል:: ሕዝቡም የጽዮን ቅዱስ እሥራኤል ይባላል:: ደስታዬም በቅዱስ ሕዝቤ ላይ (ኢሳ. 62÷1-12) ይሆናል ይላል እግዚአብሔር::

አገልጋዩም የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት፣ ከእሥራት መውጣትን ያዘኑትም ነጻነትን እንዲያገኙ የማዳን ደስታና ምሥጋና እንደሚሆን ይሰብካል (ኢሳ. 61÷1-3):: እነዚህ ክስተቶች በኤዶምና በአህዛብ ሁሉ ላይ እግዚአብሔርን በተጋፉት ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚወርድም ያጠቃልላል (ኢሳ. 63÷1-7)::

የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ቸርነት፣ ከቀደመው መከራ ማዳኑን በማሰብ ኃጢአትንና የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዘኑትን ሁሉ በመናዘዝ እግዚአብሔር ኃይሉንና ክብሩን በድጋሚ እንዲገልጥላቸው ከሕዝቡም ጋር በድጋሚ እንዳይቆጣ ምልጃ በማድረግ ይጠናቀቃል (ኢሳ. 63÷7-64÷12):: እግዚአብሔርም ይህን ጸሎት አድምጦ ለሚፈልጉት ሁሉ እንደሚገለጥ፣ ከኃጢአታቸውም ለሚመለሱት ራሱን እንደሚገልጥ ተስፋን ይሰጣቸዋል:: ለታማኝ ባሪያዎቹም አዲስ በሚፈጥረው ሰማይና ምድር በረከቱን እንደሚያዝላቸው ይናገራል (ኢሳ. 65÷1-25):: በመጨረሻም ክፉዎች በሙሉ በዘላለም እሳት ውስጥ ይጣላሉ:: ትላቸውም አይሞትም:: ነገር ግን የተቀሩት አህዛብ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣሉ፣ በፊቱም ይሰግዱለታል (ኢሳ. 66÷18-24)::

## በኢሳይያስ ውስጥ ስለመሲሑ የተተነበዩ ትንቢቶች፤

ነቢዩ ኢሳይያስ ከማንም በላይ ስለመሲሑ የተናገረ ነቢይ ነው:: ለምሳሌ ምዕራፍ 53 የያዘው ትንቢት በሙሉ በጥልቀት የሚናገረው ስለመሲሑ ነው:: ከሌሎች የትንቢት መጽሐፍት ሁሉ በበለጠ መልኩ ስለመሲሕ ትንቢቶችን የያዘ መጽሐፍ ቢኖር የኢሳይያስ መጽሐፍ ነው::

የሚከተሉትን የምንባብ ክፍሎች አንብበህ እያንዳንዱ ስለክርስቶስ የተሰጠው ክፍል ከፊት ለፊቱ ስለተሰጠው ርዕስ ምን እንደሚናገር አስተውል።

12፥1-2፣ 40፥10፣ 52፥7፣ 61፥1 ስለደህንነት ምን ይላሉ?

6፥7፣ 40፥2፣ 53፥5፣ 55፥7 ስለይቅርታ ምን ይላሉ?

1፥18፣ 25፥27፥9፣ 52፥15 ስለመንፃት ምን ይላሉ?

9፥6፣ 26፥12፣ 32፥17፣ 53፥5 ስለ ሠላም ምን ይላሉ?

የሚከተሉትን የመጽሐፉን ምንባብ ክፍሎች፣ ስለክርስቶስ ምን እንደሚል በማሰላሰል አንብብ። 7፥14-15፣ 8፥8፣ 9፥1-2፣ 7፥11፥1-2፣ 35፥5-6፣ 40፥12-18፣ 42፥1-3፣ 50፥5-6፣ 51፥13፣ 52፥13-14፣ 53፥1-12፣ 59፥20፣ 61፥2፣ 63፥1-6፣ እና 66፥15-19።

**የመጽሐፉ ቁልፍ ቃላትና ጥቅሶች**

«የእሥራኤል ቅዱስ የሚለው ሐረግ ነቢዩ የሚወደውና በመጽሐፉ ውስጥ ወደ 25 ጊዜ የተጠቀመው ሲሆን ሐረጉም «እግዚአብሔር» የሚለውን ተክቶ የገባ ነው። በመጀመሪያም በም.1 ቁ.4 ላይ ይገኛል።

ቁልፍ ጥቅስ ደግሞ ኢሳይያስ 6፥3 ላይ «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» የሚል ነው።

## ሥነ መለኮታዊ መልእክት

እግዚአብሔር ትዕቢትን ይጠላል፣ ትሁት የሆነውን መንፈስ ይወዳል። ትዕቢተኞችን ሁሉ ይደመስሳል። እግዚአብሔር ብቻ ይከብራል። እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የምድርን ሕዝቦች ሁሉ ይቆጣጠራል። አንዳንድ ነገሥታትን እንደመሣሪያ ተጠቅሞ ሌሎች ነገሥታትን ይቀጣል። ከጦር ኃይል ይልቅ እምነታቸውን በእርሱ ላይ ያደረጉትን ሕዝብ ሁሉ ይታደጋቸዋል።

እግዚአብሔር በዳዊት ዙፋን ላይ ሕዝቡን ያድን ዘንድ የብልጽግናን የሠላምንና የደስታን መንግሥት ይመሰርት ዘንድ የሠላም አለቃ የሆነውን አማኑኤልን ይልካል። እግዚአብሔር አልፋና ኦሜጋ፣ ፈጣሪ፣ አዳኝና የእሥራኤል ቅዱስ ነው። ደግሞም የእርሱ ለሆኑት የሚጠነቀቅላቸውም እርሱ ነው። የአህዛብ ነገሥታት ጉልበት ሁሉ በእርሱ ፊት እንደምናምን ነው።

የመከራው አገልጋይ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዓለም ኃጢአት በመሞቱ ደግሞ ሞትን ድል አድርጎ በመነሳቱ ለኃጢአት ዋጋ ከፍሏል። እርሱ የዓለም ሁሉ ብርሃን ስለሆነ አይሁድና አህዛብ ሁሉ በእርሱ ተቀድሰው በከበረው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በደስታ ይመላለሳሉ።

መጽሐፉ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት፣ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እያሰብን እንድንኖር፣ ከልብ ድንዳኔ ተመልሰን ንስሐ በመግባት፣ እንድንመላለስ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ይነግረናል። በተጨማሪም ኃጢአት ሁልጊዜ ከቅጣት



ጋር የተያያዘ እና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ያደረገውን የመቤዠት አገልግሎት ምን እንደሆነ ያስተምረናል።

# ትንቢተ ኤርምያስ

## መግቢያ

ነቢዩ ኤርምያስ ያገለገለበት ዘመን 627-580 ድረስ ነው። ኤርምያስ የእግዚአብሔር ነቢይ ሆኖ ለይሁዳ ሕዝብ ከነቢዩ ሶፎንያስ ጋር በጻድቁ ንጉሥ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ከነቢዩ ዕንባቆም ጋር በክፉ ንጉሥ በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት እና ከነቢዩ ሕዝቅኤል ጋር በይሁዳ የመጨረሻ ንጉሥ በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት አገልግሏል። ሴዴቅያስ ወደ ዙፋኑ ከመጣበት ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ597 ዓ.ዓ. ለባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ላይ ዐመፀ።

ባቢሎናዊያንም በ586 ዓ.ም. ኢየሩሳሌምን ከበቧት። ከተማይቱንም ሆነ ቤተመቅደሱን አቃጠሉ (2ኛ ነገ. 24፥18-25፥21)። ከጦርነቱ ለማምለጥ አንዳንድ አይሁዶች ወደ ኤዶም አገር ሸሹ፣ ሌሎችም በውጊያ ውስጥ ሞተው አለቁ፣ በሕይወት ከተረፉት አብዛኛዎቹ ወደ ባቢሎን አገር በምርኮ ተወሰዱ ናቡከደነጾር ጉዶልያስ የሚባለውን ለይሁዳ ቅሬታ ሕዝብ ንጉሥ አደረገው። ነገር ግን ጉዶልያስም ወዲያው ተገደለ። የተቀረው ሕዝብም ወደ ግብጽ ኮበለለ (ኤር. 40-44)

## አታላይነትንና ስደትን ማሸነፍ

ኤርምያስ ከካህናት ቤተሰብ የተወለደ የአናቶት ሰው ነበር። አናቶት ከኢየሩሳሌም 4 ማይልስ ርቀት ላይ በስተሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ የብንያም ወገን ሕዝብ ከተማ ናት (ኤር. 1፥1)። በሁሰቱ የይሁዳ የመጨረሻ ነገሥታትና በራሱ ቤተዘመዶች አማካይነት ኤርምያስ ብዙ ስደትን ቀምሷል። እንዲያውም የገዛ ወገኖቹም ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር (ኤር. 11፥18-23)። እግዚአብሔር እርሱን እንዲህ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፍ ማድረጉን በምሬት ይናገራል። በተጨማሪም በብዙ የስቆቃ እንጉርጉሮ ሐዘኑን ይገልጻል (ኤር. 12፥1-6፣ 15፥10-21፣ 18፥19-23 እና 20፥1-13)። በእነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በመሆን ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ ይገነዘባል። (32፥17-18)

## አስተዋጽኦ

I. የኤርምያስ ትንቢቶቹና ጸሎቶቹ (ኤር. 1-20)

ሀ/ ለንስሐ የመጀመሪያ ጥሪ (ኤር. 1-9)

ለ/ ማበረታቻዎቹና ብሶቶቹ (ኤር. 10-20)

II. የኢየሩሳሌምን ውድቀት በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ኤር. 21-29)

III. የተስፋ እድሳት (የመመለስ) ቃልኪዳን (ኤር. 30-33)

IV. የኢየሩሳሌም የመጨረሻ ቀናት (ኤር. 34-45)

V. በግብፅ አገር ምርኮኛ መሆን (ኤር. 40-45)

VI. በአሕዛብ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ (ኤር. 46-51)



የኢየሩሳሌም መውደቅ ታሪካዊ ሁኔታ (ኤር. 52)

ከሁሉም ነቢያት ለስብከት ተጠርቶ እንደ ኤርምያስ በግልጽነት ያጉረመረመ ነቢይ የለም። በአታላይነት መንፈስ ሕዝቡን ወደ ስህተትና የማይሆን የሰላም ተስፋ እየሰጡ ከሚያስቸግሩት የሐሰት ነቢያት ጋር መታገል ነበረበት። (ም .28 እና 29) በመደብደቡና በመታሰሩም ብዙ መከራ ተቋቁሟል (20፥1-6፣ 37፥11-38፥28)። ጸሎቶቹም ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ባልሆነው በይሁዳ ሕዝብ ላይ መበሳጨቱንና በስህተት እየተነዳ ሊጠፋ ላለው ሕዝብ መቃተቱን የሚገልጹ ናቸው። (ኤር. 7፥1-15፣ 8፥18-9፥1)። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም ኤርምያስ ለሕዝቡ የጠለቀ ፍቅር ነበረው። ሕዝቡ በጣዖታት አምልኮ የተሞሉና ሊጠፉ የተዘጋጁ ቢሆኑም ኤርምያስ ይወዳቸዋል፣ ያዝንላቸውማል።

## የኤርምያስ ትንቢቶቹና ጸሎቶቹ (ኤር. 1-20)

ኤርምያስ የእግዚአብሔር ነቢይ ይሆን ዘንድ ከመወለዱ በፊት ተመርጧል። የእግዚአብሔርን አወንታዊና አሉታዊ ቃላትን ለመናገር ብቁ ያለመሆኑ ቢሰማውም እግዚአብሔር አበርትቶታል፣ በጠላቶቹም ፊት እንደተመሸገ ከተማ እንደብረትም አምድ እንደናስም ቅጥር ሊያደርገው ቃል ኪዳን ሲገባ እንመለከታለን (ኤር. 1፥17-19) ።

በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት፣ በመጀመሪያው ስብከቱ የሕዝቡን የመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ልዩ ፍቅርና የተለየ ቅድስና (ኤር. 2፥2-3) አሁን ካላቸው የእግዚአብሔርን ሕግ መዘንጋት፣ ጣዖትን መከተልና ከንቱና ሐሰተኛ የሆነውን እምነታቸውን (ኤር. 2፥4-37) ያነጻጽራል። እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም በመሢሑ የሚመራ መንግሥቱን ይመሠርት ዘንድ ሕዝቡ ኃጢአቱን ተገንዝቦ ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ዘንድ ጥሪ ያደርጋል (ኤር. 3፥11-18፣ 4፥1-4)። ሰዎቹ ግን የእግዚአብሔርን መንገድ የሚያውቁ እና ጠቢባን መስለው ለመታየት ሲሞክሩ እንመለከታለን። ነገር ግን ፍትህን ሲያደርጉ ወይንም እውነቱን ሲናገሩ አንመለከትም። ስለዚህ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር አላላም (ኤር. 5፥1-9፣ 8፥4-9)። የሐሰት ነቢያት «ሠላም አለ» እያሉ ከንቱ ተስፋ እየሰጡ ስላታለሏቸው ሕዝቡ እግዚአብሔርን መፍራት ተስኖአቸዋል (ኤር. 5፥11-13፣ 20-31፣ 6፥13-15፣ 8፥10-12)።

ሕዝቡ በቤተመቅደስ አምልኮም ሁኔታ ተታሏል። ወደ ቤተመቅደስ ከመጡ ሁሉም ነገር የሚስተካከልላቸውም መስሏቸዋል። ክፉ መንገዳቸውን ቀይረው ድሃ አደጉን መጨቆንን፣ መሥረቅን፣ በሐሰት ቃል መታመንን፣ እና እንግዶችን አማልክት መከተልን ማቆም እንዳለባቸው እግዚአብሔር ይፈልጋል (ኤር. 7፥1-10)። በጉልበታቸው፣ ወይም በሀብታቸው ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ መመካት አለባቸው

(ኤር. 9÷23-24)። እግዚአብሔር መንገዳቸውንና ሃሣባቸውን ካልቀየሩ እነርሱንም ሆነ ቤተመቅደስን ይደመስሳል (ኤር. 7÷14-15)። ይህም ለኤርምያስ ትልቅ ሀዘን አመጣ። እርሱም በጣም ያዘነው ለኢየሩሳሌም ፈውስ እንደማይገኝላት በማሰብ ነው (ኤሬ.8÷18-9÷1 እና 10÷19-25)።

በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአቄም (609-597 ዓ.ዓ.) ዘመነ መንግሥት ሕዝቡ በተቀረጹ ምስሎች ማምለካቸው ስህተት እንደሆነ በመጥቀስ ይወቅሳቸዋል (ኤር. 10÷1-5)። እነዚህ ጣዖታት መናገርም መራመድም አይችሉም። ስለዚህም ሰዎችን ከእውነተኛ መንገድ ለማሳሳት የተሠሩ ናቸው። እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ለሚኖሩት ሰዎች አምላክ ነው። የአይሁድ ሕዝብም ርስታቸውና ፈጣሪያቸው እርሱ ነው። እነዚህ ጣዖታት መስማት የማይችሉ ደንቆሮዎች፣ መናገር የማይችሉ ዲዳዎች የእውነት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች ናቸው (ኤር. 10÷6-16)። እነርሱን በማምለካቸው ሰዎች/ሕዝቡ የቃልኪዳን አምላካቸውን እግዚአብሔርን አሳዝነውታል ሕብረታቸው ተቋረጠ (ኤር. 11÷1-13)። ስለዚህም እግዚአብሔር የተወደደውን ሕዝቡን ጣላቸው ምድራቸውንም ባዶ አደረገው (12÷6-13)። ነቢዩ ኤርምያስ በእንባና በልቅሶ የሕዝቡን ኃጢአት ተናዘዘ፤ እግዚአብሔርም ምህረቱን እንዲያበዛላቸው ለመነው (14÷7-22)። የእግዚአብሔር ፍርድ የቀረበ ከመሆኑ የተነሳ እግዚአብሔር ግን የነቢዩን ኤርምያስን ጸሎት ማዳመጥ እምቢ አለ (ኤር. 14÷11 እና 15÷1)።

ኤርምያስ የኢየሩሳሌምን ውድቀት በተነበየ ጊዜ ስደት ተከተለው። የዓናቶት ሰዎች ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ኤርምያስ በጣም ተሳቅቆ አዘኔታውን ገለጠ (ኤር. 11÷18-23)፤ ስለኃጥአን መበልጸግ ቅሬታውን ገለጸ (ኤር. 12÷1-6)፤ ደግሞም ለዚህ ችግር ያጋለጠውን ትንቢታዊ ጥሪውን ጠላው (ኤር. 15÷10-18)። እግዚአብሔርም ኤርምያስን ጠንካራ እንዲሆን ፍርሃቱን እንዲተው አበረታው፤ አስተካከለውም። ከማጉረምረም ተመልሶ እግዚአብሔር ይጠቀመው ዘንድ ምቹ እንዲሆን ፈለገው። በኋላም በተደበደበና በተሰደበ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በጣር ሲጮህ በእርሱ ላይ የመጣበትን አሳዛኝ ሁኔታ መቋቋም እንደማይችል ይናገራል (ኤር. 20÷7-11)። ባይወለድ ይሻለው እንደነበርና እግዚአብሔርም በጠራው ጊዜ እንዳታለለው አድርጐ ቆጠረ (ኤር. 20÷71 14-18)።

በዚህን ጊዜ ኤርምያስ የተለያዩ ምሳሌያዊ ሁኔታዎችን በመፈጸም ተምሳሌታዊ ትምህርቶችን ማስተላለፍ ጀመረ። በኤርምያስ 13÷1-11 የተጠቀሰው የማይጠቅም መታጠቂያ የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብ በማይጠቅም ሁኔታና ደረጃ ላይ መገኘቱን ሲሆን ኤርምያስ ሚስት እንዳያገባ የተላለፈው መልእክት ይሁዳ በምትወድቅበት ጊዜ የሚደርሰውን የሕዝቡን ሃዘን ለማመልከት ነው (ኤር. 16÷1-9)። ሸክላ ሰሪ ገንቦ መሥራቱ እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ የሚቆጣጠር ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው።



**የኢየሩሳሌምን ውድቀት በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ኤር. 21-29)**

በዚህ ክፍል የሚታየው ታሪክ የሚገልጸው ኤርምያስ ከንጉሥ ኢዮአቄም ወይም ሴዴቅያስ ጋር ያሳለፈውን ሁኔታ እንጂ ሰብከት አይደለም። ኤርምያስ ለንጉሡ ሴዴቅያስ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይደመስሳል። ከዚህም ማምለጥ የሚቻለው ለባቢሎናውያን ራስን በማስገዛት ነው ይላል (ኤር.21÷1-10) የይሁዳ ነገሥታት በፍትህ አላስተዳደሩም። በዚህ ፈንታ የንጹሐንን ደም ያፈሳሉ። እግዚአብሔርንም መከተል እምቢ አሉ። ስለዚህም ንስሐ የማይገቡ ከሆነ ሊደመስሳቸው ወሰነ (ኤር. 22÷1-23÷2)። ጻድቃን ቅሬታዎች (መልካሙ በለስ) ወደ ምርኮ ከሄዱት ሰዎች ዘንድ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ (ኤር. 24÷1-10)። ከሰባ ዓመት ፍጻሜ በኋላ አንዳንዶች ወደአገራቸው ይመለሳሉ (ኤር. 25÷12፤ 29÷10)። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ እረኛ ያሠማራል። በፍትህ የሚያስተዳድረውን ከዳዊት ሥር የወጣውን መሢሐዊ ንጉሥንም ይልካል (ኤር. 23÷3-8)።

እግዚአብሔርም እርሱ የተናገራቸው እያስመሰሉ ሕዝቡን የሚያስቱትን ሐሰተኛ ነቢያትን ያስወግዳል (ኤር. 23÷9-40)። የቤተመቅደሱን መደምሰስ በተነበየ ጊዜ አንዳንዶች ኤርምያስን ሊገድሉት ዘንድ ፈለጉ (ኤር. 26÷1-19)። በኋላም ሐናንያና ሌሎች የሐሰት ነቢያት የኤርምያስን ትንቢት በምርኮ ላይ 70 ዓመት እንደሚቆዩ የተነገረውን ተቃወሙ (ኤር. 28-29)።

**የተስፋና የእድሳት (የመመለስ) ቃል ኪዳን (ኤር. 30-33)**

ይህ የኤርምያስ የተስፋ ቃል የተሰጠው የሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት መገባደጃ፣ ኢየሩሳሌም በባቢሎናዊያን በተከበበች ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ የመኖርን ተስፋ በቆረጠበት ወቅት ነው (ኤር. 32÷1)። የሰው ሁሉ ጉልበት ሲያልቅ (ኤር. 30÷5-7) እግዚአብሔር ባቢሎንን በጉልበት እንደሚደመስሳት ለሕዝቡ ያስረግጣል (ኤር. 30÷8-11)። ለአሁን ግን እግዚአብሔር ላመባባቸው ቁስል ፈውስ የለም (ኤር. 30÷12-15)። ነገር ግን ወደፊት እግዚአብሔር ይሁዳን ይፈውሳታል፤ ቅጥሯን እንደገና ይገነባል፤ ከተማዋን ያድሳል ሕዝቡን በደስታ ይሞላል (ኤር. 30÷17-22) ከምህረቱና ከቸርነቱ የተነሳ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ቃልኪዳኑን ያድሳል። ይህም ቃልኪዳን ዘላለማዊ ይሆናል፤ በልብ ጽላት ይጻፋል (ኤር. 31÷1-3፤ 31-37)። ኤርምያስም እግዚአብሔር የተናገረውን የሕዝቡን መመለስ አመነ። ሁሉም ለእግዚአብሔር የሚቻል እንደሆነና ምንም የሚያቅተው ነገር እንደሌለም ተገንዝቧል። ከዚህም የተነሳ በእምነት ከአጐቱ በዓናቶት መሬት ገዝቷል (ኤር. 32÷6-17)። እግዚአብሔር ምድርን እስከፈጠራትና ሁሉንም የሚቆጣጠር እርሱ እስከሆነ ድረስ የይሁዳን ኃጢአት ማንጻት እንደሚችል፣ ሕዝቡን ወደ መሬታቸው በመመለስ እንደሚያስደስት የመሢሑን ቁጥቋጥ በዳዊት ዙፋን ላይ እንደሚያስቀምጥ እና በቤተመቅደስ አምልኮን እንደሚመሠረት አምኗል (ኤር. 33÷1-22)።

**የኢየሩሳሌም የመጨረሻ ቀናት (ኤር. 34-45)**

የናቡከደነጾር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን በመከበቡ ይህም ሕዝቡን በጥቂት ተስፋ አስቀርቶታል (ኤር. 34÷1)። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ዕብራዊ ባሪያን ነጻ ለማውጣት እግዚአብሔርም ይምራቸው እንደሆነ በማለት ቃልኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር አደረጉ (ኤር. 34÷8-16)። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የግብጽ ሠራዊት ወደ ፍልስጥኤም ክልል ሲመጡ የባቢሎን ሠራዊት ደግሞ እነርሱን ለመዋጋት ብለው ኢየሩሳሌምን ለቀው ወጡ (ኤር. 37÷5-11)። ሀብታም አይሁዶች ይህን በተመለከቱ ጊዜ ወዲያው ከባርነት የለቀቋቸውን ባሮች መልሰው ወደ ባርነት ማስገባት ጀመሩ። ለእግዚአብሔር የተናገሩትን ቃላቸውንም ማፍረስ ጀመሩ (ኤር. 34÷11)። እግዚአብሔርም በእነዚህ ሰዎች ላይ በጣም ተናደደ ምክንያቱም እግዚአብሔርን አላከበሩትምም ደግሞም አልታዘዙትምም (ኤር. 35)። ንጉሡ ኢዮአቄም የጌታን ቃል የያዘ የኤርምያስን መጽሐፍ ጥቅልል ካቃጠለበት ጊዜ ጀምሮ የሕዝቡም ሆነ ነገሥታቶቹ ለእግዚአብሔር አይታዘዙም ነበር (ኤር. 36)።

ነቢዩ ኤርምያስ በታማኝነት በተከታታይ በይሁዳ ላይ ሊመጣ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍርድ እስከተናገረ ድረስ መከሰሱ፣ መደብደቡና በወህኒ መጣሉ በኋላም ይሞት ዘንድ በጉድጓድ መጣሉ ስህተት ነበር። ኤርምያስ እስከብብቱ በሚደርስ ጭቃ ተውጦ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባና 30 ሰዎች በገመድ ጐትተው አወጡት።

በመጨረሻም የጠላት ሠራዊት ወደከተማይቱ ገባና የአገሪቱን ብዙ ባለሥልጣናትንም ገደላቸው። የንጉሡን ዓይን ጐልጉሰው አወጡት ዓይነሥውርም አደረጉት፣ የከተማይቱን ቅጥሮችና ቤቶችንም አወደሙ (አር. 39÷1-10)። በእግዚአብሔር ጸጋ እርዳታ፣ ኤርምያስና የንጉሡ አገልጋይ የነበረው ኢትጵያዊው ጃንደረባ እግዚአብሔር ታምነዋልና መልካም ሆነላቸው (ኤር. 39÷11-18)።

## በግብጽ አገር ምርኮኛ መሆን (ኤር. 40-45)

ጐዶልያስ በይሁዳ ለቀሩት አይሁዶች እና ባቢሎናዊያን ኢየሩሳሌምን ሳይወጉአት በፊት ወደ ኤዶምና ሞአብ አገር ለኮበለሉት ሁሉ በባቢሎን ንጉሥ አማካይነት የተሾመ ገዥ ነበር። ብዙም ሳይቆይ እስማኤል ጐደልያስን ገደለው። 80 የሚሆኑ ንጹሐን ሰዎችንም አረዳቸው (ኤር. 40÷13-41÷3)። በከተማይቱ የቀሩት ሕዝብ የባቢሎናዊያንን በቀል ፈርተው ወደ ግብጽ አገር ለመኰብለል ያመች ዘንድ ወደ ቤተልሔም ሸሹ (ኤር. 41÷16-18)። ወደ ግብጽ ከመሄዳቸው በፊት ግን ይህ የእግአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ኤርምያስ ይፀልይላቸው ዘንድ ወሰኑ። ኤርምያስ የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ እንደሚያደርጉም ቃል ገቡ። ወደ ግብጽ ከሔዱ እግዚእብሔር እርግማንን እንደሚያመጣባቸው በይሁዳ በእግዚአብሔር ታምነው ከቆዩ እግዚአብሔር እንደሚባርካቸውና እንደሚጠብቃቸው ነገራቸው። እነርሱ ግን የሚዋሻቸው መስሏቸው እምቢ በማለት ወደግብጽ ሄዱ (ኤር. 40÷1-41÷3)። በመቀጠልም ባሮክ ብቻ ሲቀር በሁሉም ላይ እግዚአብሔር ቅጣትንና እርግማንን



አመጣባቸው (ኤር. 45÷1-5)። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣስ ወደ ግብጽ ከመሄዳቸውም ባሻገር ለግብጻዊያን አማልክት ሰውተዋልና (ኤር. 43÷8-44÷30)።

### በአሕዛብ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ (ኤር. 46-51)

ምንም እንኳን ይሁዳ ብቻ ብትደመሰስም እግዚአብሔር ይህን ያደረገው በዙሪያው ላሉት ሕዝቦች/አሕዛብ ከፍርድ ነጻ መሆናቸውን ለማስተማር አይደለም። ይሁዳ ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ነበራትና ከሌሎች በበለጠ ሁኔታ ተጠያቂ ናት፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ብሔር ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ለሚያደርገው ነገር ተጠያቂ ነው። ይሁዳ እምነቷን ማድረግ ያለባት ነገሥታት ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ኃይለኛውን የግብጽን ሠራዊት በጠንካራው በባቢሎን ሠራዊት አማካይነት ያሸንፋል (ኤር. 46)፣ ከመጠን ያለፈ የሠራዊት ጭፍራ ፍልስጥኤምን ይወራል (ኤር. 47)። አሰደናቂ ጥፋት ትዕቢተኛውን ሞአብን አዋርዶ ልቅሶንና ሀዘንን ያመጣበታል (ኤር. 48)። አሞን፣ ኤዶም፣ ሶርያ፣ ቄዳር እና ኤላም የእግዚአብሔር ሉዓላዊ አስተዳደሩ ምድራቸውን ሲገዛ ተመሳሳይ የሆነ መከራና ጭንቀት ያገኛቸዋል (ኤር. 49)።

ኤርምያስ ለባቢሎን ሕዝብ መልእክት በላከ ጊዜ ታላቅ ሕዝብ የሆነው ባቢሎንም ይወድቃል ይላል (ኤር. 50-51) ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ቅሬታን ሕዝብ ወደ አገራቸው ይመልሳል።

### የኢየሩሳሌም መውደቅ ታሪካዊ ሁኔታ (ኤር. 52)

የኤርምያስ መጽሐፍ የኢየሩሳሌምን የመጨረሻ መደምሰስ በመግለጽ ይደመድማል። በዚህ ምዕራፍ የባቢሎን ንጉሥ የወሰዳቸውን የእግዚአብሔር ቤት ዕቃዎች ዝርዝር፣ ከ37 ዓመት ምርኮ በኋላ ለይሁዳ ንጉሥ ዩአኪን የባቢሎን ንጉሥ ዩርማሮዴክ ያደረገለትን ስናይ የእግዚአብሔርን ምግባርና ምህረቱን እንመለከታለን።

### ሥነ-መለኮታዊ መልእክት

እግዚአብሔር የሚጠራቸውን ያበረታቸዋል፣ ቃሉንም ይሰጣቸዋል። ሰዎች በሐሰተኛ ነቢያትና ሰብከቶቻቸው ሲታለሉ እግዚአብሔርንም መስማት እምቢ ማለት ሲጀምሩ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅርብ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ወገን የሆኑ ሰዎች ምናልባት በብዙ ስደት ውስጥ ሲያልፉ ይችሳሉ፣ ነገር ግን ለሕዝባዊ፣ ሃይማኖታዊና ከባለሥልጣናት ለሚመጣው ተጽዕኖ ራሳቸውን ማስገዛት የእግዚአብሔርን እውነት ከጊዜያዊ ክስተትና ሁኔታ ጋር ማሞቻመች አይኖርባቸውም። በአገልግሎት ውስጥ የሚታዩ ግፊቶች አንዳንድ ጊዜ አገልግሎትን እንድናቆም ሊያስገድደን ይችሳል። ይሁን እንጂ ነገሮችን በእምነትና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ የልብን ሰላም ይሰጣል።

አማኞች እግዚአብሔር አመጸኞችን ሲቀጣ ማዘን አለባቸው እንጂ መደሰት የለባቸውም። ለእግዚአብሔር ምህረትም መጸለይ ይኖርባቸዋል። እግዚአብሔር በሉዓሳዊነቱ ሁሉን ነገር ይቆጣጠራል። ብርቱ ነገሥታትን ማስወገድ ለሕዝቡም ይቅርታ በማድረግ ከምርኮ መመለስ ከድካም ማበርታት ይችሳል። በእርግጥም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።



# ሰቆቃወ ኤርምያስ

ይህ መጽሐፍ በይሁዳና በተወደደው ከተማ በኢየሩሳሌም ለደረሰው ጥፋት አምስት የልቅሶ መዝሙሮችን በመያዝ የሕዝቡን ሐዘን የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። ብዙዎች በ586 ዓ.ዓ. ባቢሎናዊያን ኢየሩሳሌምን ከደመሰሷት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነቢዩ ኤርምያስ ይህን መጽሐፍ እንደጻፈ ያምናሉ። መዝሙሮቹ ከተማዋ ስትደመሰስ ጸሐፊው የተመለከታቸውን ዘግናኝ እና ጭክና የተሞላበትን ጥፋት የሚያብራሩ ናቸው። መዝሙሮቹም በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት አሠቃቂ ቅጣት እንዳመጣባቸውና እግዚአብሔር ወደፊት በምህረቱ ከምርኮ እንደሚመልሳቸው ይናገራሉ።

## የመጽሐፉ አበተዋጽኦ

I. በኢየሩሳሌም መደምሰስ ምክንያት የተከሰተው ሀዘን (ም.1)
II. በኃጢአት ሳይ የተገለጠው የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን (ም. 2)
III. ለእግዚአብሔር ርኅራኄ የተደረገ ጸሎት (ም. 3)
IV. የኢየሩሳሌም መከበብ (ም. 4)
V. እግዚአብሔር ሁኔታውን እንዲያድስ የተደረገ የይቅርታ ጥያቄ (ም.5)

እነዚህ ቅኔዎች (ከምዕራፍ 5 በስተቀር) በቅኔ መልክ ጥበብ በተሞላ መልኩ የተጻፉ ናቸው። እያንዳንዱ ቅኔ በተደጋገመ ሁኔታ የኢየሩሳሌምን ውድቀት በማሳሰብ አይሁዳዊያን ብሔራዊ ጥፋታቸውን እያሰቡ ሀዘናቸውን እንዲገልጹ ተደርገው የተጻፉ ናቸው። በማያስገርም ሁኔታ ቅኔዎቹ ወይም መዝሙሮቹ ለደረሰው ጥፋት እግዚአብሔርን የሚወቅሱ ሳይሆኑ እግዚአብሔር ኃጢአትን በቅን የሚፈርድ እንደሆነ ያመለክታሉ።

### I. በኢየሩሳሌም መደምሰስ ምክንያት የደረሰው ሐዘን (ም. 1)

ይሁዳ በምሬት ታለቅሳለች ምክንያቱም የአሕዛብ ነገሥታት ባሪያ ሆናለችና። በጽዮን አምልኮ፣ መሪዎች ካህናት ወይም ሕዝብ ስለማይኖር ሀዘን በሁሉም ሥፍራ ሆኖአል። በእግዚአብሔር ሳይ ኃጢአት ስለሠሩ እግዚአብሔርም ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል። የቤተመቅደሱን መርከስና መጥፋት እንዲመለከት፣ በሐዘናቸውም ጊዜ ከእነርሱ ጋር በመሆን እጁን ዘርግቶ እንዲያጽናናቸውና ጠላቶቻቸውን እንዲቀጣ ይጮሃሉ።

## II. በኃጢአት ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣ ቀን (ም. 2)

የእግዚአብሔር የሚነድድ ቁጣው ይሁዳን አላተረፋትም። መለኮታዊው ጦረኛ ጦርንና ቀስትን ለነዘረባቸው በቤተመቅደሱም ላይ እሳትን ለደደበት። ቅጥሮችን፣ በሮችንና ቤተመንግሥታትን አወደመ። ነቢያት፣ መሪዎች ደናግልትና እናቶች

የማቅ ልብስ ለብሰው በአመድ ላይ ተቀመጡ። የሐሰት ነቢያቶችዋ ባዶ ተስፋ ስጥተዋታልና ጠላቶችዋ ተሳለቁባት ሳቁባትም።

### III. ለእግዚአብሔር ምህረትና ርኅራኄ የተደረገ ጸሎት (ም. 3)

የተከሰተው ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊቀጣ ካለው ዕቅድ ውስጥ የሆነ መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ ሀዘንተኛው ለተስፋ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል። የሚፈልጉትን ለማዳን በታማኝነቱ ታላቅ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው። አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ቅን ፍርድ በመስጠት ፍትህን ካሳየ ወደ እርሱ ተመልሰው ፊቱን ለሚፈልጉት ርኅራኄው ብዙ ነው። ጠላቶቻቸውን ስለሚፈርድና እነርሱንም ስለሚዋጃቸው ከእንግዲህ መፍራት የለባቸውም።

### IV. የኢየሩሳሌም መከበብ (ም. 4)

ምንም እንኳን ኢየሩሳሌም መልካም ሥፍራ ቢሆንም አንድ ጊዜ ጠላት ከበባ ሲጀምር አጠቃላይ ሁኔታው ተለዋወጠ። ወርቁ ተወሰደ፣ ሕዝቡ ጨካኝ ሆነ፣ ሀብታም ድሃ ሆነ የካህናት ነጭ ልብስ ወደ ጥቁርነት ተለወጠ። አንዳንድ ሰዎች ልጆቻቸውን እስከመብላት ደረሱ። እሳት በኢየሩሳሌም ተቀጣጠለ ምክንያቱም ሕዝቡ በርኩሰት እግዚአብሔርን አሳዝነውታል። ጠላቶች ደመሰሷቸው፣ ኤዶምም ደስታውን ገለጠ።

### V. እግዚአብሔር ሁኔታውን እንዲያድስ የተደረገ የይቅርታ ጥያቄ (ም. 5)

የመጨረሻው መዝሙር ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ነጻነት እንደሌላቸው ይገልጻል። ምግብ የላቸውም የጽዮን ሴቶች ተጕሳቆሉ ከኃጢአታቸውም የተነሳ ደስታ የላቸውም። መዝሙሩ እግዚአብሔር በሕዝብ ሁሉ ላይ ዘላለማዊ ግዛቱን እንደሚያመጣ በማረጋገጥ ይደመድማል። ይህ እውነት እስከሆነ ድረስ እግዚአብሔር ይቅር ብሎአቸው ከምርኮ እንደሚመልሳቸው እርግጠኞች መሆን ይችላሉ።

### *ሥነ መለኮታዊ መልእክት*

- በእግዚአብሔር በቁጣ ክንድ ላይ መውደቅ በጣም የሚያስፈራና ከፉ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ ኃጢአተኛውን በጽድቅ ይቀጣል። በመከራና በመለኮታዊ ቅጣት መካከል ሰው ንስሐ ከገባውና ምህረት ከፈለገ ከእግዚአብሔር ታማኝነት የተነሳ ተስፋ አለ።



# ትንቢተ ሕዝቅኤል

## የዘመነ ምርኮ ነቢይ

### የአገልግሎቱ ዘመን 593-571 ዓ.ዓ.

የይሁዳ ሕዝብ ወደባቢሎን በምርኮ የተወሰደው በ3 የተለያዩ ጊዜያት ነበር። በኢዮአቄም መንግሥት በ4ኛው ዓመት በ605 ዓ.ዓ. ከይሁዳ የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን አይሁዶች ንጉሡ ናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። በዚህን ጊዜ ዳንኤልንና ሦቱን ጓደኞቹን ወሰዳቸው /ዳን. 1÷1-2/። ይህንንም ያደረገው ናቡከደነፆር የግብጽን ሠራዊት በከርከምሽ ጦርነት ባሸነፈበት ወቅት ነበር። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ኢዮአቄም በናቡከደነፆር ላይ ማመጽ ጀመረ። በመቀጠል ባቢሎናዊያን (ከለዳዊያን) ኢየሩሳሌምን ወጉአት፣ ንጉሥ ዩአኪንንም ማርከው ወሰዱ፣ ንጉሥ ኢዮአቄም ሞቶ ነበርና። ከእርሱም ጋር ከ10000 የሚበልጡ አይሁዳዊያንን ማርኮ ወሰዳቸው። ይህም በ597 ዓ.ዓ. ሲሆን ነቢዩ ሕዝቅኤልም የተማረከው በዚያን ጊዜ ነበር (2ኛ ነገሥ. 23÷36-24÷17፣ ሕዝ. 1÷2)። ሴዴቅያስ አዲስ ገዥ ሆኖ ተሾመ፣ ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ እርሱም በናቡከደነፆር ላይ ማመጽ ጀመረ። በመጨረሻም ኢየሩሳሌም በ586 ዓ.ዓ. ላይ ሙሉ በሙሉ ተደመሰሰች (2ኛ ነገሥ. 24÷18-25÷21)። በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት ነቢዩ ኤርምያስ በይሁዳ ነቢይ ሆኖ ሲያገለግል ሕዝቅኤል ደግሞ በባቢሎን ተማርከው ለሄዱት አይሁዳዊያን ትንቢት በመናገር ያገለግላቸው ነበር።

ከሕዝቅኤል መጽሐፍ በባቢሎን ምርኮ ላይ ስለነበሩት አይሁዶች የሚታወቀው በጣም ጥቂት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ሕዝቅኤል በመጽሐፉ እየገለጸ ያለው በይሁዳ እየተከሰተ ያለውን ነገር በመሆኑ ነው። ይህም የሚያመለክተው ባቢሎናዊያን ሕዝቅኤልን ስለእምነቱ አለማሳደዳቸውንና ባሪያም ያለማድረጋቸውን ነው። በተለያዩ ጊዜያት የእስራኤል ወገኖች መሪዎች በሕዝቅኤል ቤት ሲሰበሰቡ ሕዝቅኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ቃል ያካፍላቸው ነበር (ሕዝ. 8÷1፣ 14÷1÷፣ 20÷1)።

ሕዝቅኤል የተወለደው በንጉሡ ኢዮስያስ በመን መንግሥት (640-609 ዓ.ዓ.) እንደሆነ ይታመናል። አግብቷል፣ ነገር ግን ልጅ ስለመውለዱ የሚታወቅ ነገር የለም (ሕዝ. 24÷15-18)። ትውልዱ ከካህናት ቤተሰብ እንደሆነና ወደባቢሎን ሲማረክም የ25 ዓመት ሰው እንደነበረ ይታመናል። ዕድሜው 30 በሞላ ጊዜ በኮቦር ወንዝ አጠገብ ሆኖ እግዚአብሔር ለነቢይነት አገልግሎት ጠራው (ሕዝ. 1÷1-3)። የእግዚአብሔር መንፈስም ሞላበት፣ ከዚያም የተነሳ ዲዳ ሆኖ እግዚአብሔር አፉን ሲከፍት ብቻ ይናገር ነበር (ሕዝ. 2÷1-2፣ 3÷24-27)። ሕዝቅኤል በባቢሎን ቆይታው ወቅት ታምሣሌታዊ የምልክት መልእክቶችን ሰጥቷል። በኢየሩሳሌም ምን እንደተፈጸመ የሚያሳዩ ብዙ ራዕዮችንም አይቷል። ከመልእክቶቹም አንዳንዶቹ በኢየሩሳሌም ሊመጣ ያለውን ፍርድ እየተቃወሙ የሚናገሩትን ነቢያት የሚቋቋሙ ናቸው (ሕዝ.

4-24)፡፡ ሌሎች መልእክቶቹ ከኢየሩሳሌም መደምሰስ በኋላ በሐዘን ሰተመቱ ምርኮኞች ተስፋና ማበረታቻ የሚሰጡ ናቸው (ሕዝ. 34-48)፡፡

## አስተዋጽኦ

I. ለነቢይነት አገልግሎት የሕዝቅኤል መጠራት (ሕዝ. 1-3)

II. የእግዚአብሔር ፍርድ በይሁዳ ላይ (ሕዝ. 4-24)
   ሀ/ ስለጽዮን ውድቀት ምልክቶቹና መልእክቶቹ (ሕዝ. 4-7)
   ለ/ የእግዚአብሔር ክብር ቤተመቅደሱን ለቆ መሄድ (ሕዝ. 8-11)
   ሐ/ የይሁዳ ኃጢአቶች ለከተማይቷ ጥፋትን ማምጣት (ሕዝ. 12-24)

III. የእግዚአብሔር ፍርድ በአሕዛብ መንግሥታት ላይ (ሕዝ. 25-32)

IV. የይሁዳ መመለስ/መታደስ (ሕዝ. 33-48)
   ሀ/ የመታደስ ተስፋና ዳግም ልደት (33-37)
   ለ/ በጐግና ማጐግ ላይ ድልን መቀዳጀት (38-39)
   ሐ/ የእግዚአብሔር ክብር በአዲሱ መቅደስ (40-48)

እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል በተናገረ ጊዜ በተደጋጋሚ «የሰው ልጅ ሆይ» እያለ ይጠራው ነበር፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሕዝቅኤል ሰብዕናው ከእግዚአብሔር ክብር ጋር ሲተያይ ምንም ዓይነት ተነጻጻሪነት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሕዝቅኤል በራዕይ ያየውን የእግዚአብሔርን ፍጹም ቅድስናውንና ታላቁን ክብሩን ተገንዝቧል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የይሁዳ ሰዎች ኃጢአት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነም አስተውሏል፡፡ ሕዝቅኤል ለእግዚአብሔር እንደጠባቂ፣ ሰዎች ንስሐ ካልገቡ በእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚጠፉ የሚያስጠነቅቅ ነበር፡፡

## I. ለነቢይነት አገልግሎት የሕዝቅኤል መጠራት (ሕዝ. 1-3)

ከሕዝቅኤል ጋር በምርኮ ላይ የነበሩ አይሁዶች እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ እንደሚገኝ አድርገው ይገምቱ ነበር፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔር ክብር በምርኮ አገር መገኘትና ለሕዝቅኤልም መታየቱ ትንሽ አስደንግጧቸው ነበር፡፡ ሕዝቅኤል እግዚአብሔርን በራዕይ በተሰየ ሁኔታ አይቶታል፡፡ የእግዚአብሔርም ክብር በእሳት ውስጥ ነበር፡፡ የሚንቀሳቀሰውም በሰማያዊ እንስሶችና በመንኩራኩሮች አማካይነት ነበር (ሕዝ. 1፥4-28)፡፡ ይህን ተመልክቶ ሕዝቅኤል እግዚአብሔርን ለማምለክ ራሱን ባዋረደ ጊዜ ልቡ ደንዳና ለሆነው ለተማረከው ሕዝብ ነቢይ እንዲሆን እግዚአብሔር ላከው፡፡ ሕዝቅኤል እንደጊንጥ ከሚናደፈው ከሕዝቡ ተቃውሞ ወይም መልእክቱን ባለመቀበላቸው መፍራትም ሆነ ተስፋ መቁረጥ አልታየበትም (ሕዝ. 2÷6፣ 2÷3-7)፡፡ ሕዝቅኤል



በዋጠው ጥቅልል ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ነበረበት፡፡ ይህን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ቃል ለሕዝቡ የማያስተላልፍ ከሆነ ተጠያቂ እርሱ ይሆናል፡፡ እርሱ የማስጠንቀቂያ ቃሉን ተናግሮ ሕዝቡ መስማት እምቢ ቢሉ እነርሱ ተጠያቂዎች ናቸው (ሕዝ. 3÷17-21)፡፡

## II. የእግዚአብሔር ፍርድ በይሁዳ ላይ (ሕዝ. 4-24)

ምንም እንኳን በምርኮ ላይ የሚገኙ ብዙ ሕዝቦች ኢየሩሳሌም እንድትደመሰስ እግዚአብሔር ይፈቅዳል ብለው ባያምኑም ሕዝቅኤል ግን ተምሳሌታዊ ክንውኖችንና መልእክቶችን በመጠቀም የኢየሩሳሌምን መጥፋት ሲማሳመን ይጥራል፡፡ በሕዝቡ ክፉ ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ሊቀጣ መዘጋጀቱንም አረጋግጦ ይናገራል፡፡ ኢየሩሳሌም በጠላት የተከበበች መሆንዋን ለማመልከት ጡብን ወስዶ የኢየሩሳሌምን ሥዕል ሰርቶ የተከበበች መሆኗን በምሳሌ አሳይቷል 4÷1-3፡፡ በከበባው ወቅት የነበራትን የኢየሩሳሌምን መጥፎ ሁኔታ ለማመልከት በግራ ጐኑ 390 ቀን ተኝቷል፡፡ መጥፎ ምግብም እየበላ ሰንብቷል (4÷4-17)፡፡ የሕዝቡም ዕጣ ፋንታ በሕዝቅኤል ፀጉር ተመስሏል፣ አንዳንዶች በሰይፍ ሞተዋል፣ ሌሎችም ወደተለያዩ አገሮች ተበትነዋል (5÷1-17)፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ ቀን በይሁዳ ላይ በጣም ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም የይሁዳ ትዕቢት፣ ርኩሰትና አመጽ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲፈጥንባቸው አድርጓል (7÷1-27)፡፡ ይህ በደረሰባቸው ጊዜ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ያውቁታል፡፡ ለነቢይነት ከተጠራ ከዓመት በኋላ ሕዝቅኤል በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ውስጥ ሌላ ራዕይ በተሰይም የእግዚአብሔርን ክብር አየ (10÷1-21)፡፡

በባቢሎን ምርኮ ላይ የነበሩ አይሁዶች ብዙዎቹ ሕያውና ልዑል እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም በቤተመቅደስ ውስጥ ኖሮአልና ኢየሩሳሌም አትደመሰስም ብለው አስበው ነበር፡፡ ነገር ግን ሕዝቅኤል በራዕዩ የእግዚአብሔር ክብር ቤተመቅደሱንና ኢየሩሳሌምን ለቆ ሲሄድ ተመለከተ (9÷3፣ 10÷19፣ 11÷22-25)፡፡ እግዚአብሔር ሥፍራውን ለቆ የሄደበት ምክንያት የይሁዳ 70 መሪዎች በቤተመቅደስ ውስጥ ጣዖትን ያመልኩ ስለነበረ ነው (8÷5-18)፡፡ እግዚአብሔር ጻድቁን ምልክት አደረገበት፣ ኃጢአተኞችና አመፀኞች ግን ተገደሉ፣ ቤተመቅደሱም ተደመሰሰ (9÷1-11)፡፡ ለይሁዳ የሚቀረው ብቸኛው ተስፋ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን አስወግዶ አዲስ ልብ ሲሰጣቸው ነው (11÷14-21)፡፡

የእግዚአብሔር ፍርድ አይመጣም የሚለውን የይሁዳን ሕዝብ የተሳሳተ አመለካከት ሕዝቅኤል ይቃወማል (12÷21-28)፡፡ በይሁዳ ላይ ፍርድና ቅጣት አይመጣም፣ ሠላም ይሆናል እያሉ ሕዝቡን ወደ ስህተት የሚመሩትን ሐሰተኛ ነቢያትን ያወግዛቸዋል (13÷1-23)፡፡ ሰዎች ንስሐ የማይገቡና ከኃጢአታቸው የማይለዩ ከሆነ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደኖህ፣ ዳንኤልና ኢዮብ ቢፀልዩም

ይሁዳን ለመደምሰስ ካለው ዕቅድና ውሳኔ እግዚአብሔር በፍጹም አይመለስም (ሕዝ. 14÷1-23)::

ሕዝቅኤል በምሳሌያዊ ንግግሩ ይሁዳን እግዚአብሔር ከሚጠነቀቅላት ልጃገረድ ጋር ያነጻጽራል:: ነገር ግን ሙሽሪት ባሏን ጠልታ ሌሎችን ትወዳለች (ይህም ይሁዳ ጣዖትንና ለእግዚአብሔር የማይመቹ ነገሮችን መውደዷን ለማሳየት ነው::) ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ጋለሞታ ሚስት የምታስቸግረውን ይሁዳን ይቀጣታል:: ምክንያቱም ኃጢአተኝነቷ ከእህቷ እስራኤል (የሰሜኑ ክፍል) እንዲሁም ከሰዶምና ገሞራ ኃጢአተኝነት የባሰ ስለነበር ነው (ሕዝ. 16÷1-59):: ይህ ምሳሌ በሕዝቅኤል 23 ላይ ከተሰጠው ከሁለቱ እህቶች አሖላ ማለትም ሰማርያ (የሰሜኑ ክፍል) እስራኤል እና አሖሊባ ማለትም ይሁዳ (የደቡቡ ክፍል) ከኢየሩሳሌም ጋር ተመሳሳይ ነው::

ሕዝቅኤል በሌላው ምሳሌ ደግሞ ታላቅ ንስር (ናቡከደነፆር) (ሕዝ. 17÷3፣ 12) ምንም እንኳን ሌላው ታላቅ ንስር (የግብጽ ንጉሥ 17÷7፣ 17) ይሁዳን ለማገዝ ቢሞክርም ታላቁ ንጉሥ (ናቡከደነፆር) የፍልስጥምን ክልል በሙሉ ይቆጣጠራል:: በቅርቡም የአንበሳው (ይሁዳ) ከደቦሎችዋ አንዱን (ንጉሥ ዮአኪንን) ወደ ባቢሎን በምርኮ ሲወሰድ ትመለከታለች (ሕዝ. 19÷1-9):: በቅርቡም የወይን ግንድ (ይሁዳ) ከቅርንጫፎችዋ (ነገሥታት) አንዱ ሲሰበር ታስተውላለች (ሕዝ. 19÷10-14):: ኢየሩሳሌምም በእሳት ላይ እንደተጣደ ብረት ድስት ነው ሕዝቡም እንደሚቀቀል ሥጋ ሆኖአል (ሕዝ. 24÷3-5):: የመጨረሻው የይሁዳን ጥፋት የሚያመለክት ምሳሌ የሕዝቅኤል ሚስት መሞት ነበር:: የምትወደውና የሚወዳት ሚስቱ ነበረች ነገር ግን እግዚአብሔር እንዳያዝንላት ነገረው (ሕዝ. 24÷15-20):: በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ያውቁታል::

ምንም እንኳን የይሁዳ መማረክ እርግጥ ቢሆንም አንድ ቀን እግዚአብሔር የረጅሙን ዝግባ ቁጥቋጦ (መሢሑን) ወስዶ ከፍ ከፍ እንደሚያደርገው ይናገራል (ሕዝ. 17÷22-24):: ሕዝቡም ዳግመኛ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን ስም አያረክሱትም:: በምርኮም አገር ይሰበስባቸዋል ፣ ወደ አገራቸውም ይመልሳቸዋል:: በዚያን ጊዜም እኔ አምላክ እንደሆንሁና የቀጣኋቸውም እኔ እንደሆንሁ ይገነዘባሉ (ሕዝ. 20÷39-44) ይላል እግዚአብሔር::

በዚህ ክፍል ውስጥ እንደምንመለከተው ይሁዳ ስለኃጢአቱ ዋጋ ከፍሏል፣ ተቀጥቷል:: ሰው ሁሉ ለሠራው ኃጢአት ዋጋ እንደሚከፍልም እንመለከታለን:: በምርኮ ውስጥ ከነበሩት እንዳንዶቹ መከራ የሚያዩት ስለኃጢአታቸው ሳይሆን ስለአባቶቻቸው ኃጢአት እንደሆነ ገምተው ነበር (ሕዝ. 18÷2):: እግዚአብሔርም እውነተኛ ፈራጅ አይደለም ብለው ያጉረመርሙ ነበር (ሕዝ. 18÷29)፣ ነገር ግን



እግዚአብሔር ሲመልስ እያንዳንዱ ሰው መከራን የሚያየው ራሱ ስለሠራው ኃጢአት ነው ይላል (ሕዝ. 18÷4-20)::

## III. የእግዚአብሔር ፍርድ በአሕዛብ መንግሥታት ላይ (ሕዝ. 25-32)

ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ፍርድ በአሞን፣ በሞአብ፣ በኤዶምና በፍልስጥኤም እንደሚሆን ከገለጠ በኋላ (ም. 25) ሀብታምና ትዕቢተኛ የሆነች ጢሮስም በእግዚአብሔር እንደምትቀጣ ይናገራል (27)::

እግዚአብሔር የነናቡከደነፆርን መንግሥት አስነስቶ ጢሮስን እንዲያጠፋ ሀብቱንም እንዲወርስ ያደርጋል:: ስለዚህም ይህ ትዕቢተኛው የጢሮስ ንጉሥ ራሱን እንደአምላክ ከመቁጠር ተቆጥቦ ሰው መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል (28÷2፣ 6÷11-15)::

ግብጽም ከኤድን ገነት ሥፍራ ጋር ከተመሰለው ደለል የተነሳ በጣም ልቡ ኮርቷል (ሕዝ. 29÷1-9፣ 31÷1-9):: ባቢሎናዊያን መጥተው ከተማይቱን ሲደመስሱ ልክ እንደምድረበዳ ይሆናል (ሕዝ. 29÷9-30÷26) ሕዝቅኤል በመቀለድ ለግብጽ ንጉሥ ሞት ሙሾ አውርዷል (ሕዝ. 32÷1-8):: የግብጽንም ሁኔታ ወደ ሲዖል እንደመውረድና ሌሎች ነገሥታት እንደተዋረዱ መዋረድ አድርጐ ያቀርባል (ሕዝ. 32÷21-32)::

## IV. የይሁዳ መመለስ/መታደስ (33-48)

የሕዝቅኤል የተስፋ መልእክቶች መጀመርና የእርሱም ዲዳ መሆን ማክተም ተጋጣጣሚ/የአንድ ጊዜ/ክስቶች ሲሆኑ ክስተቱም የተፈጸመው ባቢሎናዊያን ለመጨረሻ ጊዜ ኢየሩሳሌምን መደምሰሳቸውን በሰማ ጊዜ ነበር (ሕዝ. 33÷21-22):: ይህም ክስተት በምርኮ ላይ የነበሩትን ሰዎች ተስፋ የሚያጨልምና «ኢየሩሳሌም አትጠፋም» የሚለውን ከንቱ እምነታቸውን የሚያጋልጥ ሆነ:: ወደ ይሁዳ የመመለስ ተስፋ ይፈጸም እንደሆነ ማንጐራጐር ጀመሩ::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሕዝቅኤል እስካሁንም በምርኮ ላይ ለሚገኙት ሰዎች ትንቢት ተናጋሪ (ጉበኛ/ጠባቂ) እንደሆነ ተነገረለት (ሕዝ. 33÷1-16):: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሕዝቅኤል መልእክት ተስፋ የሚሰጥ ሆነ:: እግዚአብሔር ከቀጣቸው በኋላ ይሁዳን አንድ ቀን እንደሚሰበስብና ወደ አገራቸው እንደሚመልስ ይናገራል:: ባሪያውን ዳዊትን ንጉሥ ያደርግላቸዋል:: የሰላም ቃልኪዳኑን ያድሳል፣ አዲስ ልብ ይሰጣቸዋል፣ ከኃጢአታቸው ያነጻቸዋል:: ደግሞም ይባርካቸዋል (ሕዝ. 34÷1-31፣ 36÷22-38፣ 37÷15-28):: በዚያን ጊዜ ጌታቸው እግዚአብሔር እንደሆነ ይገነዘቡታል::

የይሁዳን ሀሳቶች እግዚአብሔር ያሸንፋል። በይሁዳ ውድቀት የተደሰተችውን ኤዶምን ጭምር እግዚአብሔር ይቀጣል። ይሁዳ በመውደቁ ደስተኛ ከመሆንም አልፎ የይሁዳን መሬት ለመውሰድ ስትቃጣ ነበር (ሕዝ. 35፥1-36፥15)። ስሙን ለመቀደስ እግዚአብሔር ጎግንና ማጎግን ሁሉ ሲደመስስ የአሕዛብ መንግሥታት ሁሉ እርሱ ብቻ አምላክ እንደሆነ ይገነዘባሉ (ሕዝ. 38-39)። በዚህ ክፍል ጐግና ማጐግ ተብለው የተጠቀሱት በዓለም ያሉትን ክፉ መንግሥታትን የሚወክሉ ናቸው የሚል አመለካከት አለ። በአጭሩ ግን እነዚህ የእግዚአብሔርን ሕዝብና እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ኃይላት ናቸው። በዚህ ክፍል ዋናው መልእክት ግን ማንኛውም ኃይል የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይዞ ሊያስቀር አይችልም እግዚአብሔር ያሸንፋቸዋልና።

የመጨረሻው ክፍል (40-48) ከምርኮ ለሚመለስ ሕዝብ ለአምልኮ የሚሆን ትልቅ ቤተመቅደስ መለኪያ ንድፍ የያዘ ክፍል ነው። ለካህኑ ሕዝቅኤል ከእግዚአብሔር ጋር ወደነበረው ኅብረትና ግንኙነት ለመመለስ በጣም ጠቃሚ ሁኔታ ነው። የሄደው የእግዚአብሔር ክብር ወደቤተመቅደሱ መመለስ አስደናቂ የእግዚአብሔር ሥራ መጠናቀቁን ጠቋሚታ የሚያመለክት ነው (ሕዝ. 43፥1-5)። ከሳዶቅ ቤተወገን የሆኑ ሌዋዊ ካህናት በመቅደሱ ውስጥ ያገለግላሉ፣ የሰላም አለቃም ሕዝቡን ይገዛል (ሕዝ. 43፥18-44፥31)። ሕዝቡ የደስታ ግብዣውን በቤተመቅደስ ውስጥ ሆኖ ያከብራል (ሕዝ. 46)። የከተማይቱ ስም «እግዚአብሔር በዚያ አለ» ይባላል (ሕዝ. 48፥35)። ምድራቱም ለየነገዱ ይከፋፈላል፣ ንፁህ ወንዝም ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከሙት ባሕር ከዚያም አልፎ ይፈሳል (45፥-8፣ 47-48)።

## *ሥነ መለኮታዊ መልእክት*

አንድን ሰው የእግዚአብሔርን አስደናቂውን ክብር ማየት እንዲበግድለት፣ እንዲያመልከውና በፈቃደኝነት እግዚአብሔርን እንዲታዘዘው ያደርጋል። አማኞች ኃጢአተኞችን ከሚመጣው ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚያስጠነቅቁ የእግዚአብሔር ጉበኞች/ጠባቂዎች ናቸው። አንድ ጉበኛ/ጠባቂ ሕዝቡን ከሚመጣው ፍርድ እንዲያመልጡ የማያስጠነቅቅ ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ ነው።

እግዚአብሔርን ካልተገነዘቡትና በታማኝነት ካላመለኩ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብና የአምልኮ ሥፍራዎችን ያስወግዳል። እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ገዥና ባለሥልጣን ነው፣ ስለዚህም የማይታዘዙትንና የሚያምጹትን የአህዛብን መንግሥታት ሁሉ ያጠፋል። እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነ እያንዳንዱን ሰው በሠራው ኃጢአት ምክንያት ይቀጣል።



እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል፣ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያነጻል፣ ወደአገራቸው ይመልሳል፣ አዲስ ልብና አዲስ ኪዳን ያሰጣቸዋል። እውነተኛ አምልኮን ይሰጣል፣ መሢሐቸውን ያመጣላቸዋል።

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የሕዝቅኤልን መጽሐፍ ያነበቡ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ እንመለከታለን። በራዕይ 4፥1-11 የሐዋርያው ዮሐንስ ስለእግዚአብሔር ክብር የሰጠው ገለጻ በሕዝቅኤል ምዕ. 1 ላይ ከተሰጠው ገለጻ ጋር በቅርበት ይመሳሰላል። ዮሐንስ በራዕይ 10፥8-11 ላይ የመጽሐፉን ጥቅልል መዋጡ ከሕዝቅኤል ልምምድ ጋር ተመሳሳይ ነው።

ኢየሱስና ጳውሎስም የጠባቂ ወይም የጉበኛ ኃላፊነትን በተመለከተ የሕዝቅኤልን አመለካከት ተቀብለዋል (ማቴ. 10፥5-15፣ ሐዋ. 18፥6፣ 20፥26)። ጎግና ማጎግ በተጨማሪ በራዕይ 20፥8 ላይ ተጠቅሷል። ደግሞም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ዮሐንስ ባየው ራዕይ ውስጥ የምትካተት ሲሆን የኢየሩሳሌም መታደስ በሕዝቅኤል መጽሐፍም አለ።

# ትንቢተ ዳንኤል

## የአገልግሎት ዘመኑ 605-535 ዓ.ዓ.

## ዘመነ ምርኮ ነቢይ

ናቡከደነፆር በትረ መንግሥቱን የጨበጠው በ605 ዓ.ዓ. ነበር። በዚሁ ዓመት ነበር የግብጽን መንግሥት አሸንፎ ባቢሎንን የዓለም ገዥ አገር ያደረጋት። ከግብጽ ጋር ተዋግቶ ካሸነፈ በኋላ ወደኢየሩሳሌም ሄዶ ዳንኤልንና ጓደኞቹን ከብዙ ሕዝብ ጋር ማርኮ ወደባቢሎን ወሰዳቸው (ዳን. 1÷1)። በ597 ዓ.ዓ. ወደይሁዳ ተመልሶ ሄደ ንጉሥ ዮአኪንን አሸንፎ ነቢዩ ሕዝቅኤልን ጨምሮ ከአሥር ሺህ የሚበልጡትን አይሁዳዊያንን ለሁለተኛ ጊዜ ማርኮ ወደባቢሎን ወሰዳቸው። በ586 ዓ.ዓ. የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በናቡከደነፆር ላይ አመጸ። በዚያን ጊዜ ንጉሡ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ሙሉ በሙሉ ደመሰሳት። በመጽሐፉ ውስጥ ያልተጠቀሱት 3 (ሦስት) ነገሥታት ለአጫጭር ጊዜያት ናቡከደነፆርን ተክተው ነገሰዋል። ከዚህም የመጨረሻው ንጉሥ ማርዱክስ ከተባለው ጣዖት ይልቅ የጨረቃ አምላክ የተባለውን ሲን አምላኪ ነበር። ስሙም ነቦኒደስ (556-539 ዓ.ዓ.) በመባል ይታወቃል። እርሱም ብልጣሶር በተባለው ልጁ ተተካ።

በ539 ዓ.ዓ. የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ የባቢሎንን መንግሥት አሸነፈ። ከዚያም የተማረኩት አይሁዶች ወደ አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ አዋጅ አወጣ (ዕዝራ 1÷1-6)። ወደ 50000 የሚሆኑ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ዳንኤልና ሌሎች በባቢሎን ቀሩ።

ዳንኤልና 3ቱ ጓደኞቹ በመጀመሪያ ምርኮ ጊዜ የመጡ ከተማረና ንጉሣዊ ቤተሰብ የተወለዱ የኢየሩሳሌም ሰዎች ናቸው (ዳን. 1÷3)። እግዚአብሔር በምርኮ አገር ያሉትን ሕዝቡን በጥንቃቄ ጠብቆአቸዋል፤ ይህንንም ያደረገው ዳንኤል በባቢሎን ምንግሥት ለ70 ዓመታት በሥልጣን ላይ ሆኖ ባሳደረው ተጽዕኖ አማካይነት ነበር። ምንም እንኳን ዳንኤል በሕይወቱ ብዙ መከራ ማለትም በአናብስት ጉድጓድ ውስጥ እስከመጣል ቢደርስም መልካምነቱን አስመስክሯል (ዳን. 5÷11-16)። ይህን ዝናውን የፋርስ መንግሥት ባቢሎንን አሸንፎ ሥልጣኑን በወሰደበት ጊዜም አስጠብቋል።

የዳንኤል መጽሐፍ፤ ዳንኤል ከባለሥልጣናት ጋር የነበረውን ግንኙነት፣ እና እግዚአብሔር በምድር ሕዝብ ሁሉ ላይ እንዴት እንደሚገዛ የሚያመለክቱ የተለያዩ ራዕዮችን የያዘ መጽሐፍ ነው።



## አስተዋጽኦ

I. እግዚአብሔር የአሕዛብን መንግሥት ሁሉ ይገዛል (ዳን. 1÷1-6÷28)
   ሀ. እግዚአብሔር በባቢሎን አገር ለዳንኤል ጥበብን ሰጠው 1÷1-21
   ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት ሌሎችን መንግሥታት ሁሉ ይደመስሳል(2÷1-49)
   ሐ. እግዚአብሔር 3ቱን የዳንኤል ጓደኞች ከእቶን እሳትም ይታደጋቸዋል (3÷1-31)
   መ. እግዚአብሔር ነገሥታትንና ሰውን ሁሉ ይገዛል (4÷1-37)
   ሠ. እግዚአብሔር የባቢሎን መንግሥት እንዲያከትም አድርጓል (5÷1-31)

II. ለተሰደዱት ሕዝቡ የእግዚአብሔር ጥንቃቄ (ዳን. 7÷1-12÷13)
   ሀ. የተሰደዱት ቅዱሳን መንግሥቱን ይወርሳሉ (7÷1-8÷27)
   ለ. ለእስራኤል ይቅርታና መታደስ እንዲሆን የተደረገ ጸሎት (9÷1-27)
   ሐ. የጦርነትና የሃዘን ጊዜያት (10÷1-12፤13)

የዳንኤልን መጽሐፍ ሁለት የሥነ-ጽሑፍ ባህርይ መኖር ልዩ ያደርገዋል። ዳንኤል 1÷1-2÷4 እና ዳንኤል 8-12 እንደሌሎቹ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ሁሉ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ ነው። ነገር ግን በዳንኤል 2÷4-7÷28 የተጻፈው በአራማይክ ቋንቋ ነበር። ይህ ቋንቋ በጊዜው ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና በማግኘት ያገለግል ነበር። ይህ ሃሣብ የሚያመለክተው ደንኤል መጽሐፉ ዕብራዊያን ባልሆኑ ሰዎችም እንዲነበብ መፈለጉን ነው። ሌላው ልዩ የሚደርገው ነገር ልዩ የሆኑ እንስሳትና ተክሎች፣ ምሳሌአዊ ቁጥሮችና መልኮች ደግሞም ስለወደፊቱ ጦርነትና ስደት ጠለቅ ያሉ ትንቢቶችን መያዙ ነው።

ምንም እንኳን የነቢዩ ዘካርያስ መጽሐፍ የተለያዩ መገለጦችንና ራዕዮችን የያዘ ቢሆንም የዳንኤል መጽሐፍ ግን በበለጠ ሁኔታ እንደአዲስ ኪዳን መጽሐፍት (ራዕይ መጽሐፍ) ብዙ ራዕዮችንና መገለጦችን የያዘ መጽሐፍ ነው። ከእነዚህ ምሳሌያዊ መገለጦችና ራዕዮች በዳንኤል ያልተተረጐሙ ካሉ ምናልባትም በመጽሐፉ አጠቃላይ መልዕክት ላይ ምንም ለውጥ የማያመጡ ቢሆኑ ነው።

ስለዚህም ዳንኤል ትርጉሙን ያልሰጠውን መገለጥ ክፍል ስንተረጉም ዳንኤል ያልሰጠውን ትርጉም እንዳንሰጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። በእግዚአብሔር ወይንም በመልአኩ ካልተተረጐመ በስተቀር ጠቢብና አዋቂ የሆነ

ዳንኤል እንኳን የራዕዩን ቀጥተኛ ትርጉም ማወቅ አይችልም ነበር (ዳን. 7÷16፣ 8÷27፣ 12÷8-9)።

## I. በአሕዛብ መንግሥታት ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር አገዛዝ (ዳን. 1÷1-6÷28)

ዳንኤል እና ሦስቱ ጓደኞቹ (ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ) ለሦስት ዓመታት የባቢሎንን ቋንቋ፣ ባህል፣ የላቀ ጥበብ፣ ሃይማኖትና ታሪካዊ የሥነጽሑፍ ትምህርት እንዲማሩ ተመረጡ። ለዚህ በመንግሥት እየተረዱ ለሚሰጠው የትምህርት ዕድል የሚመረጡ እጅግ መልከ መልካም የሆኑ ጥበብ የሞላባቸውና በቤተ መንግሥቱ ለማገልገል ብቃት ያላቸው ሰዎች ናቸው (ዳን. 1÷4-5)። ዳንኤልና ጓደኞቹ ከንጉሡ መብል ቢበሉ እንደሚያረክሳቸው በመገንዘብ በእምነት እምቢ አሉ። (ምናልባት ምግቡ ለአሕዛብ ጣዖት የተቀደሰ ሊሆን ይችላል)። ከዚህም የተነሳ አለቃቸውን በማግባባት ለ10 ቀናት ጥራጥሬንና ውሃን ብቻ ይመገቡ ዘንድ ዳንኤል ጠየቀ (ዳን. 1÷8)። እግዚአብሔርም የዚህን ታማኝ ወጣት መስጠቱን ተመልክቶ መልካም ጤናና ብዙ ጥበብን ሰጣቸው። ከሌሎች ተማሪዎች ሁሉ ከባቢሎን ጠቢባንም አሥር ጊዜ የሚበልጥ እውቀትና ጥበብ ተሞሉ (ዳን. 1÷17-21)።

በነገሠ በ2ኛ ዓመቱ ናቡከደነፆር አስቸጋሪ ሕልም ተመለከተ። ሕልሙም በድንጋይ የተከሰከሰ ታላቅ ምስል ነው። የባቢሎን ጠቢባንና አስማተኞች ሕልሙን መግለጥ ያለመቻላቸውን አሜን ብለው ተቀበሉ (ዳን. 2÷11)። አማልክቶቻቸው ሕልሙን ለመግለጥ ችሎታ የላቸውምና። ናቡከደነፆርም የአገሩን ጠቢባን፣ ዳንኤልንና ጓደኞቹንም ጨምሮ ለመግደል ወሰነ። ዳንኤል በእግዚአብሔር ፊት ሆኖ ስለይቅርታውና ምህረቱ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ራዕዩን ከነትርጉሙ ገለጠለት። ዳንኤልም እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አደረገ፣ ምክንያቱም ጥበብና ኃይል ስለተሰጠው ምስጢሩን ለሰው መግለጥም ተችሎታልና ነው (ዳን. 2÷20-23)። ዳንኤልም ለንጉሡ ምስጢሩን መግለጥ ጀመረ። እግዚአብሔር በገለጠለት መጠን ለናቡከደነፆር ራዕዩንና ትርጉሙን ገለጠው የምስሉ ራስ ወርቅ ነበር፣ እርሱም የሚወክለው ናቡከደነፆርን ነበር (ዳን. 2÷28፣ 36-38)። የተቀሩት የምስሉ ክፍሎች ቀጥሎ የሚነግሡትን ደካማ መንግሥታትን የሚያመለክቱ ናቸው። የመጨረሻው መንግሥት ግን ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ነው (ዳን. 2÷44-45)። ሕልሙን መተርጎም ስለቻለ



ዳንኤልና አምላኩ እግዚአብሔር ተከበሩ፤ የዳንኤልም ሦስቱ ጓደኞቹ አዲስ ሥራ ተሰጣቸው።

ከጊዜ በኋላም ናቡከደነፆር የወርቅ ምስል ምናልባትም የራሱን ምስል በባቢሎን አስተከለ። የአገሩ ሕዝብ መኳንንቶችና ባለሥልጣናት ሁሉ የጊዜው የፖለቲካ መሪዎች ሁሉ ለምስሉ እንዲሰግዱለት ትዕዛዝ ወጣ (ዳን. 3÷1-5)።

ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ ግን ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ስግደትንና አምልኮን ከማቅረብ በስተቀር ለሌላ ለማንም እንደማይሰግዱ ቆረጡ። ውሳኔአቸውን ለማስቀየር ማንኛውም ዓይነት ጉዳት ቢደርስባቸውም፣ አልፎ ተርፎም በእሳት ውስጥ ቢጣሉም በሚያድን አምላክ ታምነው እምቢታቸውን ገለጡ። በዚህም ምክንያት በእቶኑ እሳት ውስጥ ተጣሉ። የእግዚአብሔርም መልአክ ከእቶኑ እሳት አዳናቸው ለሁለተኛ ጊዜ ናቡከደነፆር የእግዚአብሔርን ታላቅነትና የበላይነት ተገነዘበ (ዳን. 3÷24-30)።

ምንም እንኳን ስለእግዚአብሔር ታላቅነት ብዙ ምስክሮችን (ማረጋገጫዎችን) የተመለከተ ቢሆንም ናቡከደነፆር ትዕቢተኛ ሰው ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር አዋርዶት እርሱ ብቻ በሰው ሁሉ ላይ ገዥና ባለሥልጣን መሆኑን አሳየው (ዳን. 4÷17፣ 25÷32)። በዳንኤል 4÷10-27 ባለው ክፍል የተመለከተው የትልቁ ዛፍ መደምሰስ ራዕይ በራሱ ተፈጸመ። እርሱም ተዋረደ እንደእንስሳም ሆነ (ዳን. 4÷28-33)። ከጊዜ በኋላ ወደማስተዋልና ወደዙፋኑ ተመለሰ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገነ ከፍ ከፍም አደረገው አከበረውም። እግዚአብሔር ብቻ ኃይለኛ፣ እውነተኛ ጻድቅ እንደሆነ መሰከረ ይህንም የተናገረው እግዚአብሔር ትዕቢተኛውን በማዋረድ የተዋረዱትን ከፍ ከፍ ሲያደርግ በተመለከተ ጊዜ ነበር (ዳን. 4÷34-37)።

ናቦኒደስ የተባለ የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶርን ተክቶ ከባቢሎን ወደ ሌላ ሥፍራ በሄደ ጊዜ ከተማይቱ በጦርነት ውስጥ ብትሆንም ብልጣሶር ለመኳንንቶቹ ትልቅ ግብዣ አዘጋጀ (ዳን. 5÷1-4)። በዚህ በስካር ግብዣ ጊዜ የተጠቀሙባቸው የመጠጥ ዕቃዎች ከኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ የተወሰዱ የወርቅና የነሐስ ዕቃዎች ነበሩ። በዚህን ጊዜ የአገራቸውን ጣዖታት እያመሰገኑ የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃዎች ያረክሱ ነበር። በግብዣው ሂደት ውስጥ የሰው እጅ ጣቶች ወጥተው በንጉሡ ቤት በተለሰነው ግንብ ላይ ሲጽፉ ንጉሡ ብልጣሶር ተመለከተ (ዳን. 5÷5)። መልዕክቱንም ከዳንኤል በስተቀር ማንም ማንበብ አይችልም ነበር። መልዕክቱም እግዚአብሔር የባቢሎንን ዘደል እንደቆጠረ እና እንደመዘነ ባቢሎንም በሚዛኑ ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያመለክት ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር መንግሥቱን (ለሁለት መንግሥታት) ለሜዶንና ለፋርስ ከፈለ (ዳን. 5÷25-28)። ይህ ትንቢት በዚያው ሌሊት (በ539 ዓ.ዓ.) ተፈፀመ። ምክንያቱም በዚያው ሌሊት ንጉሡ

ብልጣሶር በሜዶንና በፋርስ መንግሥት አማካይነት ተገደለ:: መንግሥቱም ተከፈለ ሜደናዊው ዳርዮስ ሥልጣኑን ወሰደ (ዳን. 5÷30-31):: የባቢሎን መንግሥት መውደቅም ከብዙ ጊዜ በፊት በነቢዩ ኢሳይያስ የተተነበየውን ትንቢት (ኢሳ. 13 እና 14) እና (በኤርምያስ 50 እና 51) የተተነበየውን ትንቢት ፍፃሜ ሲሆን እንመለከታለን::

የፋርስ መንግሥት ባቢሎንን በወሰደ ጊዜ አገሪቱን በሙሉ ለማስተዳደር እንዲመች በአዲስ መልኩ አደረጀ:: በዚህን ጊዜ አገሪቱን በ120 ክፍለግዛቶች (መሳፍንቶች) ሥር ከፋፈለ:: በሁሉም ላይ ሦስቱ አለቆችን ሾመ (ዳን. 6÷1-2):: ዳንኤል በንጉሡ በጣም የተከበረ ከመሆኑም የተነሳ ከ3ቱ አለቆች አንደኛው ነበር:: ከዚህ የተነሳ ሌሎች በእርሱ ላይ ስህተት ለማግኘት ፈለጉ:: በመጨረሻም ከንገሡ በስተቀር ማንንም ሰው ወይም ማንኛውንም አምላክ ጠያቂ ቢኖር እንዲቀጣ ከንጉሡ ትዕዛዝ እንዲወጣ አደረጉ (ዳን. 6÷7):: እንደዘወትር ልማዱ ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ ተይዞ ተከሰሰ፣ በአናብስት ጉድጓድም እንዲጣል ተደረገ:: እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ መልአኩን ልኮ የአናብስትን አፍ ዘግቶ ዳንኤልን አዳነው (ዳን. 6÷22):: ንጉሡም በዳንኤል መዳን ተደስቶ ጠላቶቹን በአናብስት ጉድጓድ አስወረወረ አናብስትም ሰባብረው በሉአቸው::

## II. ለተለደደው ሕዝቡ የእግዚአብሔር ጥንቃቄ (ዳን. 7÷1-12÷!13)

የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል እግዚአብሔር በሕዝቡ ሁሉ ላይ ያለውን ሉዓላዊ ቁጥጥሩን በራዕይ መልክ የሚያሳይ መልዕክት የያዘ ነው:: ነገር ግን የመልእክቶቹ የትኩረት አቅጣጫ በጣም ከባድና አስጨናቂ በሆነው ስደት ውስጥ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ እንዴት እንደሚጠብቃቸው ነው:: በብልጣሶር አገዛዝ ጅማሬ ከባሕር ውስጥ ስለሚወጡ 4 እንስሳት (አራዊት) ራዕይ አየ (ዳን. 7÷1-8):: ይህም ራዕይ በምዕራፍ 2 ናቡከደነፆር ካየው ራዕይ ጋር ተመሳሳይ ነበር:: በምዕራፍ 7÷1-8 ባለው ራዕይ ትኩረቱ በአራተኛው አውሬ ላይ ነበር:: ይህ አውሬ ግን በቁጣና በትዕቢት የተሞላ ነበር:: ነገር ግን በዘመናት የሸመገለ፣ ኃያሉ እግዚአብሔር አራዊትን ደምስሶ ሁሉንም የመግዛትን ሥልጣን ለሰው ልጅ (ለመሲሕ) ሰጠው:: የምድር ሕዝብ ሁሉ ለእርሱ እንዲገዙለት አደረገ (ዳን. 7÷9-14):: ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው:: ይህ ራዕይ የሚያጽናና ራዕይ ነበር:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቅዱሳን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሚወርሱ ማረጋገጫ የሚሰጥ ነበርና (ዳን. 7÷18፣ 27):: በተጨማሪም ራዕዩ በጣም የሚረብሽ እና የሚያውክ ነበር፣ ምክንያቱም የመጨረሻው አውሬና ትንሹ ቀንድ በሚገዙበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቅዱሳን በከባድ መከራ ውስጥ እንደሚያልፉ ይናገራል (ዳን. 7÷8፣ 19-25):: ይህ ትንሹ ቀንድ ብዙ ጊዜ በዮሐንስ ራዕይ 13 እና 17 ላይ ከተገለጸው ከክርስቶስ ተቃዋሚ ጋር ይመሳሰላል::



ከሁለት ዓመት በኋላ ዳንኤል ተመሳሳይ ራዕይ አየ:: በራዕዩም አውራ በግ፣ አውራ ፍየልና ታናሹ ቀንድ ሲዋጉ ነበር (ዳን. 8÷1-8):: አውራው በግ የሜዶንና የፋርስ መንግሥትን ይወክላል (ዳን. 8÷20):: አውራው ፍየል የግሪክ ንጉሥን ይወክላል (ዳን. 8÷21):: ነገር ግን ቀጠኛውና ታናሹ ቀንድ ማን እንደሆነ አልተገለጸም:: እርሱ ወደፊት ከሚነሡት ነገሥታት አንዱ ነበር (ዳን. 8÷17፣ 19):: በትዕቢት የተሞላ፣ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክል፣ የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ለተወሰነ ጊዜ በኃይል የሚያሳድድ መንግሥት ነበር (ዳን. 8÷9-14፣ 23-26):: በመጨረሻም ይህ ንጉሥ በእግዚአብሔር ይሸነፋል (ዳን. 8÷25)::

ይህ ትንሹ ቀንድ ብዙውን ጊዜ በ165 ዓመተ ዓለም አካባቢ ብዙ አይሁዶችን ከገደለና ካሳደደ ከግሪክ ንጉሥ አንቲዩክስ ኢፒፋነስ ጋር ተመሳስሏል::

በኋላም በከለዳዊያን መንግሥት አገዛዝ ዕድሜው 80 ዓመት የሞላ ሽማግሌው ዳንኤል በኤርምያስ 25÷11፣ 12፤ 29÷10 ያለውን ክፍል እግዚአብሔር ሰባው ዓመት ሲፈጸም ሕዝቡን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመልስ አነበበ (ዳን. 9÷1-2):: በ605 ዓመተ ዓለም ወደ ምርኮ መወሰዱንም አስታወሰ:: አሁን ደግሞ 538 ዓ.ዓ. ሆኖአል:: ይህም እነርሱ ወደ አገራቸው ከመመለሳቸው ጥቂት ዓመታት በፊት ማለት ነበር:: ዳንኤል የሕዝቡን ኃጢአት እየተናዘዘና እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምርኮ አገር በመስደዱ ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነ በመገንዘብ በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት በትጋት ቆይቷል:: እግዚአብሔር ቁጣውን ከሕዝቡ ላይ አንስቶ ሕዝቡንም ወደ አገራቸው እንዲመልስ ይ ባይቃል (ዳን. 9÷3-19):: እግዚአብሔርም በመልአኩ ገብርኤል አማካይነት ለዳ ... ሲመልስ የሕዝቡን ዓመጻ ይጨርስ፣ ኃጢአትንም ይፈጽም እና ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ 70 ሳምንታትን መቅጠሩን አስታወቀ (ዳን. 9÷24):: በዚያን ጊዜ ኢየሩሳሌም ትጠገናለች፣ የተቀባው መሲህ መጥቶ ይገደላል:: የኢየሩሳሌም ከተማም ትደመሰሳለች:: ሕዝቡም በከባድ መከራና ጦርነት ውስጥ ያልፋሉ (ዳን. 9÷25-26):: በመጨረሻው ሱባዔ (70ኛው ሳምንት) አጋማሽ በእግዚአብሔር ቤት የሚደረገውን አምልኮ ያስቀራል፣ ሕዝቡም ይገደላል:: ነገር ግን በሳምንቱ ማብቂያ ቤተመቅደሱን ያፈረሰ እና አሳዳጅ የነበረ ይሸነፋል:: ዳንኤል ከምዕ. 7-9 ባለው ክፍል የተመለከተው ራዕይ በጣም አስደንጋጭ ነበር::

ሱባዔ የተባለው አንድ ሳምንት ሲሆን፤ አንድ ሳምንት ደግሞ 7 ዓመታትን የሚያመለክት መሆኑን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይስማሙበታል:: የቀሩት 3 ምዕራፎች፣ ቀጣዩ ትውልድ ለሚመጣው መከራ የተዘጋጁ ይሆኑ ዘንድ የሚያዘጋጅ እና አንድ ቀን እግዚአብሔር በእርሱ የታመኑትን የዘላለምን ሕይወት በመስጠት እንደሚሸልማቸው የተሰጠውን ተስፋ የሚያጠናክር ክፍል ነው::

በተጨማሪም ክፉዎችን በዘላለም ውድቀት እና ሞት እንደሚቀጣ ይናገራል (ዳን. 12፥1-3)።

ከሦስት ሳምንታት ጾምና ጸሎት በኋላ በመልአኩ ሚካኤል አማካኝነት ስለወደፊቱ የሚናገር ራዕይ አየ። በራዕዩም መንፈሳዊ ጦርነት ይካሄድ ነበር። መልአኩ ሚካኤል በአየር ላይ የፋርስን መንግሥት ከሚቆጣጠሩ ክክፉ ሠራዊቶች ጋር እየተዋጋ ለዳንኤል ይዞ የመጣለትን መልስ ሳያደርስ ዘግይቶ ነበር (ዳን. 10፥1-13፤ 20-21)።

መልአኩ የፋርስ መንግሥታት እንደሚነግሡና በኋላም ግሪኮች አሸንፈዋቸው የቅርቡን ምሥራቅ ዓለም በሙሉ እንደሚቆጣጠሩ ገለጠለት (ዳን. 11፥1-2)። ይህም በታሪክ የተከሰተው ራዕዩ ከታየ ወደ 200 ዓመታት በኋላ በ331 ዓ.ም. የግሪኩ ንጉሥ ታላቁ አሌክሳንደር ዓለምን ሁሉ በተቆጣጠረበት ወቅት ነበር። መንግሥቱም እርሱ ከሞተ በኋላ በ4 ቦታ ለአራት ጄኔራሎች እንዲገዙ ተከፈለ። የፍልስጤምን ምድር ወረሩ፤ እርስ በእርሳቸው ይዋጉ ነበር። በጦርነቱም ወቅት በጣም ክፉ የሆነ ገዥ (ምናልባትም አንታይከስ ኢፒፋነስ) የኢየሩሳሌምን ቤተመቅደስ አረከሰ፤ ብዙ አይሁዶችን ገደለ፤ ከእግዚአብሔርም በላይ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ። በአማልክትም አምላክ ላይ በትዕቢት ተናገረ (ዳን. 11፥29-39)። በጊዜው ማብቂያ የክርስቶስ ተቃዋሚ ልክ እንደዚህኛው ገዥ ይሆናል። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ይሳደባልና (ዳን. 11፥36-45)። ምንም እንኳን በዓለም ከታዩት መከራዎች ሁሉ ያህኛው በጣም መጥፎ ቢሆንም በእግዚብሔር ላይ ታምነው የሞቱ ቅዱሳን ሁሉ ተስፋ አላቸው፤ ምክንያቱም ስማቸው በእግዚአብሔር ሕይወት መዝገብ ላይ ተጽፏልና። ለዘላለም ሕይወት ትንሣኤን ያገኛሉ። በዚያን ጊዜ ክፉዎቹ በእግዚአብሔር ለዘላለም ይፈረደባቸዋል (ዳን. 12፥1-2)። ምንም እንኳን ትርጉሞችንና መቼ እንደሚፈጸሙ ጊዜያቸውን ባያውቅም ዳንኤል እነዚህን የተገለጡለትን ራዕዮች በታማኝነት ጽፏል።

## ሥነ መለኮታዊ መልዕክት

- ጥበብ ሁሉ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ክብሩን ለራሱ ለማምጣት ሲፈልግ ለታማኝ አገልጋዮቹ ጥበቡን ይገልጣል።
- ግለሰቦችንም ሆነ ሕዝቡን ሁሉ በሉዓላዊነቱ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የተዋረዱትን ማንሳትና ከፍ ከፍ ማድረግ፣ ትዕቢተኞችን ማዋረድ ኃይሉን መግለጥና ሕዝብን ሁሉ ለእርሱ እንዲታዘዙ ማድረግም የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው።



- ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ቅዱሳን በታላቅ መከራ ውስጥ የሚያልፉ ቢሆንም እግዚአብሔር አንድ ቀን ይታደጋቸዋልና በሰው ልጅ (በመሲሑ) አገዛዝ ሥር የሚሆነውን መንግሥት ያወርሳቸዋል።

የአዲስ ኪዳን ከዳንኤል መጽሐፍ ብዙ ጥቅሶችን ጠቅሷል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻ ዘመን ስለሚሆኑ ነገሮች ሲናገር የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰችው ሥፍራ እንደሚቆም ሲያነሳ እንመለከታለን (ማቴ. 24፥15፤ ዳን. 9፥27 እና 12፥11)። ዮሐንስ ራዕይ 13 ላይ ደግሞ የተለያዩ አራዊት ከባሕር ውስጥ ሲወጡ በትኩረት ደግሞ የመጨረሻው አውሬ እግዚአብሔርን የሚሳደብና በቅዱሳን ላይ ጦርነትን እንደሚከፍት የሚናገረው ከዳንኤል ምዕራፍ 7 ጋር ተመሳሳይ ነው። ዮሐንስ ራዕይ 14 እግዚአብሔር አውሬውን እንደሚፈርድበት መንግሥቱንም በደመና ለሚመጣው ለሰው ልጅ አሳልፎ እንደሚሰጥ የሚናገረው ከዳንኤል 7፥9-14 ጋር ተመሳሳይ ነው። ጌታ ኢየሱስም በማቴዎስ 24፥30፤ 25፥31-36 ባለው ክፍል በክብር የሚመጣው የሰው ልጅ ክፉዎችን እንደሚፈርድ ጻድቃንን የዘላለምን ሕይወት ያገኙ ዘንድ ከሞት ሲያስነሳ ክፉዎቹም ለዘላለም ይቀጡ ዘንድ ከሞት የሚያስነሳ መሆኑን የሚናገረው በዳንኤል 12፥1-2 ባለው ክፍል ከተሰጠው መልዕክት ጋር ተመሳሳይ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

# ደቂቀ ነቢያት

## መግቢያ

## 1. «ደቂቀ ነቢያት» ማለት ምን ማለት ነው?

«ደቂቀ ነቢያት» እየተባሉ የሚጠሩት፣ ከትንቢተ ሆሴዕ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ድረስ ያሉት መጻሕፍት ናቸው፡፡ እነዚህም አሥራ ሁለት ናቸው፡፡ ይህ አባባል የተጀመረው በአራተኛው (ዓመተ ምህረት) ነው፡፡ ይህን አባባል የሰጠው ከቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ የነበረው አውግስጢኖስ ነው፡፡ ስምን ደቂቀ አላቸው? ከኢሳይያስ፣ ከኤርምያስ፣ ከሕዝቅኤልና ከዳንኤል መጻሕፍት ጋር ሲነጻጸሩ የእነዚህ ነቢያት መጻሕፍት «በመጠን አነስተኛ፣ የትንቢቶቹ ዝርዝርና ጥልቀት ከሌሎቹ መጻሕፍት ያነሰ በመሆኑ ነው፡፡

የእነዚህ የአሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት መጻሕፍት አቀማመጥ በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት አይደለም፡፡ በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ተቀምጠው ቢሆን ኖሮ እንደሚከተለው ሊሆን ይችል ነበር፡፡

- ዮናስ፣ አሞጽ፣ ሆሴዕ፣ ሚክያስ (ከ750-700 .ዓ.ዓ.)
- ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ አብድዩ፣ ኢዩኤል (ከ650-586 ዓ.ዓ.)
- ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስ (ከ520-420 ዓ.ዓ.)

በእንግሊዝኛና በአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ፣ ትርጉሞች የደቂቀ ነቢያት የአቀማመጥ ቅደም ተከተል ልዩነት አለው፡፡ ይህም የሆነው የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ቅደም ተከተል የተወሰደው ከዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን፣ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጐመውን ቅደም ተከተል ነው ተጠቅሟል፡፡ በዚህ አሰሳ ጥናታችን ተየምንከተለው የአማርኛ ውን መጽሐፍ ቅዱስ ቅደም ተከተል ይሆናል፡፡

## 2. የደቂቀ ነቢያት ዋና ዋና ትምህርቶች

የደቂቀ ነቢያት መልእክትና አገልግሎት፣ ታላላቅ ነቢያት ካገለገሉበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል፡፡

እነዚህም ነቢያት

- ትዕዛዝና ምክር አስተላልፈዋል



- በቅርብና በሩቅ ዘመን ሊሆኑ ስላሉ ነገሮች ተንብየዋል

ሀ. ስለራሳቸው ዘመን ተናግረዋል

ለ. ስለአሦር ምርኮና፣ ስለባቢሎን ምርኮ (ከዚያ ስለመመለስም ጭምር ተናግረዋል)

ሐ. መሲሕ ስለሚነግሥበት ሁኔታ ተናግረዋል፡፡

## 3. የአሥራ ሁለቱ ነቢያት አመዳደብ፡፡

| ምድቡ | ጽሐፉ | የምዕራፎች ብዛት |
|---|---|---|
| የእስራኤል ነቢያት | ዮናስ<br>አሞጽ<br>ሆሴዕ | 4<br>9<br>14 |
| የይሁዳ ነቢያት | አብድዩ<br>ኢዩኤል<br>ሚክያስ<br>ናሆም<br>ዕንባቆም<br>ሶፎንያስ | 1<br>3<br>7<br>3<br>3<br>3 |
| ከምርኮ መልስ በኋላ የተናገሩ ነቢያት | ሐጌ<br>ዘካርያስ<br>ሚክያስ | 2<br>14<br>4 |

በዚህ ጥናት የእነዚህን ነቢያት ማንነት፣ የነበሩበትን ዘመንና፣ ያገለገሉትን ሕዝብ፣ እንደዚሁም የመልእክቶቻቸውን ዋና ዋና ይዘት አጠር ባለ መልኩ እንመለከታለን፡፡

# ትንቢተ ሆሴዕ

## ሆሴዕ የብኤሪ ልጅ (1፥1)

የስሙ ትርጉም፡- «እግዚአብሔር ያድናል» «ደህንነት» ማለት ነው።

የኖረበት ዘመን፡- ከ754-714 ዓ.ዓ. ከአሦራውያን ወረራ አስቀድሞ ኖሯል።

**ቁልፍ ጥቅሶች**፡- 3፥1፣ 6፥4፣ 10፥12፣ 11፥3፣ 8፥14።

## ቁልፍ ቃላት

እወቅ፣ ዕውቀት፣ ስሚ፣ ምሕረት፣ ፍቅር፣ መመለስ፣ እስራኤል የሚለው ቃል (44 ጊዜ) ሲጠቀስ፣ ኤፍሬም (37 ጊዜ)፣ ይሁዳ (15 ጊዜ) እንዲሁም ጌታ እንዲህ አደርጋለሁ ያለው አሳብ (57 ጊዜ) ተጠቅሷል።

## ዋና ዓላማዎቹ

- ለኃጢአተኛውና ለዓመፀኛው ሕዝብ የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር፣
- እስራኤል እግዚአብሔርን ትታ ጣዖታትን በመከተል፣ ከእምነት መንገድ ወጥታ በመንፈሳዊ ሕይወቷ እንዳመነዘረች ፣
- ወደ ጌታ ካልተመለሱ እንደሚፈረድባቸው ፣
- የእግዚአብሔርን ታማኝነትና ፍቅር ደግሞም ፣
- ንስሐ መግባት የሚያመጣውን በረከት ለማስገንዘብ ነው።

## አስተዋጽኦ

I. ታማኝ ያልሆነችው ሚስት፣ ታማኝ የሆነው ባል (ሆሴ. 1-3)

- የሆሴዕ ቤተሰብ፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ

II. እስራኤል ወደጌታ ባትመለስ ፍርድ እንደሚጠብቃት መነገሩ (ሆሴ. 4-13)

ሀ. የእስራኤል በከፋት መያዝ (ሆሴ. 4-5)
ለ. የጌታን ፍቅር እምቢ ማለቷ (ሆሴ. 6፥1-8፥6)
ሐ. እስራኤልን ፍርድ እንደሚጠብቃት (ሆሴ. 8፥7- ሆሴ. 10)
መ. የእግዚአብሔር ፍቅር (ሆሴ. 11)
ሠ. እስራኤል ከቅጣት ልታመልጥ አትችልም (ሆሴ. 12-13)

III. ወደ እግዚአብሔር በመመለስ የሚገኝ ፈውስና በረከት (ሆሴ. 14)



## ስለነቢዩ ሆሴዕ

ሆሴዕ ማለት የስሙ ትርጉም «ደህንነት» እንዲሁም «እግዚአብሔር ያድናል»ማለት እንደሆነ ተጠቅሶአል። እርሱ የብኤሪ ልጅ (ሆሴ. 1፥1) ከመባሉ በስተቀር ስለቤተሰቡም ሆነ ስለአገልግሎት እንዴት እንደተጠራ የተጠቀሰ ነገር የለም። የኖረውም ከኢሳይያስና ሚክያስ ጋር በአንድ ዘመን ነበር። የአገልግሎት ዋና ቦታው በሰሜኑ መንግሥት በእስራኤል ነበር። ዋና መልዕክቱ ለዚያ ሕዝብ የተጻፈ ሲሆን ለይሁዳም ሕዝብ የሚሆን መልእክት አስተላልፎአል።

## ሆሴዕ ዘመን የእስራኤል ሁኔታ

በዘመኑ የእስራኤል ሕዝብ በውጭ መልኩ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ቢመስልም፣ በልቡ ከእርሱ ርቆ በአሊምንና ሌሎችን ጣዖታት ያመልክ ነበር። እግዚአብሔርንም መፈለግ ትተዋል፣ ፍቅሩንም በመካድ ወደኋላቸው አፈግፍገዋል። ነገሥታት፣ ካህናትና ነቢያት ሁሉም ከጌታ ፈቃድ በመውጣት ትዕዛዙን ተላልፈዋል።

በነቢዩ ሆሴዕ በኩል የቀረበላቸውን መልዕክት ተቀብለው፣ ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ ጌታ ፈውስንና በረከትን ይልክላቸዋል። በግብጽና በአሶር በመደገፍ ፈንታ በጌታ ቢታመኑ የሚሻላቸው ሲሆን በሁለት ልብ ሆነው በማወላወል ፈቃዱን ሳቱ። በ722 ዓ.ዓ. የአሦር መንግሥት መጥቶ ሰማርያን ደመሰሳት፣ ብዙ ሰዎችን ከገደሉ በኋላ የቀሩትን ወደ አገራቸው ማረኩአቸው። ለእስራኤል ዳግም ወደ ሰሜኑ መንግሥት የመመለስ ተስፋም አልተነገራቸውም።

## የሆሴዕ ቤተሰብ (ሆሴ. 1-3)

ሆሴዕ አሳዛኝ የሆነ ቤተሰብ ነበረው። ጌታ ለሆሴዕ ታማኝ ያልሆነች ሴት እንዲያገባት ነገረው። ሆሴዕም ሚስቱን ጎሜርን ወደዳት። ከእርሷም ሦስት ልጆችን ወለደ። የልጆቹ ስም ትርጉም ለእስራኤል መልእክት የያዘ ነው። ጎሜር ከሆሴዕ በመኰብለል አመንዝራ ሆነች። ሆሴዕ ስለሚወዳት እንደገና እንደሚስቱ አደረጋት።

## ዋና መልእክት

የሆሴዕ ጋብቻ ሁኔታ፣ የእግዚአብሔርንና የእስራኤልን ግንኙነት በሥዕላዊ መልክ ይገልጻል። እግዚአብሔር እስራኤል ታማኝ ባትሆንም ለእርሷ ያለው ፍቅሩ ያው ነበር። እርስዋ ባአሊምንና ሌሎችንም ጣዖታት ተከተለች። ጌታ ከዚያ ተመልሳ ከእርሱ ጋር ያላትን ሕብረት እንድታሳድስ ይፈልጋል። ሆሴዕ ከደረሰበት መከራ የተነሳ ጎሜርን ሊተዋት አልፈለገም። ጌታም እንደዚሁ እስራኤልን ከመውደዱ የተነሳ ሊተዋት ሳይፈልግ መልሶ ሊታረቃት እንደሚሻ ይገልጽላታል። ስለዚህ

ሆሴዕ የእስራኤልን ባዕድ አምልኮ አጥብቆ በማውገዝ ንስሐ ገብታ ከጌታ በረከት ተካፋይ እንድትሆን ይመክራታል።

1. የእግዚአብሔር ፍቅር የማያቋርጥ ነው።
   - ባለፉት ጊዜያት ባርኳአቸዋል፣ ተጠንቅቆላቸዋል (ሆሴ. 2 ፥15፣ 11፥1፣ 13፥4-5)
   - አሁንም እግዚአብሔር እስራኤል ከእርሱ ጋር ያላትን ኅብረት እንድታድስ ይፈልጋል (ሆሴ. 7፥1፣ 11፥8-9)
   - ወደፊትም ከእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ የተነሳ ለመዳን ተስፋ አላት (11፥10- 11፥ 14፥4-9)
2. የእግዚአብሔር ፍቅር በቅድስና መኖርን ይጠይቃል። እርሱ ቅዱስ ነውና። ሕዝቡም በቅድስና እንዲኖርለት ይፈልጋል (ሆሴ. 2፥19 20፣ 4፥7-10፥ 5፥4፣ 11፥5-7)።
3. እግዚአብሔር ኃጢአትን ዝም ብሎ አያልፍም።
   - በእግዚአብሔር ላይ የሚደረገውን እምነት ማቋረጥ፣ ልክ የተቀደሰውን ጋብቻ በጋለሞታነት እንደማርከስ ዓይነት ነው (ሆሴ. 1፥2፣ 2፥1-5)።
   - ሆሴዕ ጎሜርን ቢመልሳትም (ሆሴ. 3፥1-5)፣ ስለኃጢአትዋ ተቀጥታ ወደ ሙሉ ኅብረት መመለስ ይገባት ነበር። ለእስራኤልም እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር ቢወዳቸውም በኃጢአታቸው ምክንያት የሥነ ሥርዓት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል። ጌታ ይቅርታ ሊያደርግላቸው ይፈልጋል፣ በቅድሚያ ግን እስራኤል ንስሐ መግባት ይኖርባታል (ሆሴ. 14፥1-9)
4. ንስሐ መግባትና አገልግሎት እውነተኛ መሆን አለበት።
   - ንስሐ በትክክል በታደሰ ሕይወት በኑሮ ፍሬው መታየት አለበት (ሆሴ. 6፥1-4) በእምነት በመታዘዝ ራስን ለጌታ ፍጹም ሳይሰጡ መስዋዕት ማቅረብ በጌታ ዘንድ ተቀባይነትን አያስገኝም (ሆሴ. 6፥6)።

## የመጽሐፉ ዋና ሃሣብ

1. ሆሴዕ እምነት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ የሆነ ሕብረትን እንደሚጠይቅ በግልጽ ያስቀምጣል (ሆሴ. 7፥1-7፣ 8፥1-5 11፥3-7)።
2. የእስራኤልን ታማኝ አለመሆን ይናገራል።
   - ከጌታ በመመለስዋ በሃይማኖት በኩል፣ በፖለቲካና በግብረገብ፣ እንዲሁም በኢኮኖሚም በኩል ውድቀትንና ጥፋትን አስከትሎባታል። ይህም የኃጢአት ውጤት ነው።
3. የእግዚአብሔር ፍቅር (ምዕ. 11)።

   እርሱ ኃጢአትዋን እንጂ እስራኤልን ፈጽሞ አልጠላትም።
4. እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈላጊ ነው (2፥13፣ 8፥14፣ 3፥6)።

## ስነ መለኮታዊ መልእክት

1. እግዚአብሔር ሕዝቡ ከእርሱ ሌላ ማንንም ምንንም እንዲያመልኩ አለመፍቀዱን እንረዳ።
2. ለነፍስ፣ ለሥጋ መታመንና መደገፍ ያለብን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት ያስተምረናል።
3. እግዚአብሔር ለመረጠው ሕዝቡ፦ እንደ ባል፣ እንደ አባትና እንደ እረኛም ነው።
   - ስለሚወዳቸውም የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ነገር ይሰጣቸዋል። ከእነርሱም ከእኛም የሚፈለግ ነገር ቢኖር፦ ለእግዚአብሔር በመስጠት መታዘዝና እርሱን በመተማመን መጠበቅ ነው።
4. ዛሬም እግዚአብሔር ከእኛ ከሕዝቡ የሚፈልገው፦ ንስሐ መግባትን፣ እርሱን ማወቅን፣ መታዘዝን፣ ለእርሱ ፍጹም ተሰጥቶ ማምለክንና ታማኝ መሆንን ነው።
5. የሆሴዕ መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን መጠቀሱን አስታውስ (ሆሴዕ 1፥9፣ 2፥1፣ 2፥22፣ ሮሜ 9፥25፣ 1ጴጥ. 2፥10፣ ሆሴዕ 6፥6፣ በማቴ.9፥13፣ ሆሴዕ 13፥14፣ 1ቆሮ 15፥55)።
6. ጌታ ኢየሱስ የሆሴዕን መጽሐፍ ሁለት ጊዜ ጠቅሶታል (ማቴ.9፥13 ከሆሴዕ 6፥6፣ ሉቃ. 23፥30፣ ሆሴዕ 10፥8)።
7. ሆሴዕ ም. 6፥6 እግዚአብሔር የሚወደው ምን እንደሆነና ሆሴዕ ምዕ. 11 ደግሞ ጽኑ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ይገልጻል።
8. የሆሴዕ መጽሐፍ ክርስቶስ በንስሐ የሚመጣውን ኃጢአተኛ እንደሚቀበለው ዓይነተኛ ትምህርት ይሰጣል (ራዕይ 2፥4-5)።
9. የሰዎች መንገድ ከሁለት አንዱን በመምረጥ ሲወሰን (ሆሴዕ 11፥9) «የእግዚአብሔር መንገድ ጻድቃን የሚሄዱበት» ሲሆን ሁለተኛው የኃጥአን መንገድ፣ ሰፊ የተባለው ወደ ጥፋት የሚወስደው ነው (ማቴ. 7፥13፥ 14)። ቅን በሆነው በእግዚአብሔር መንገድ እንሂድ።

## የሆሴዕ መጽሐፍ ንድፍ (ሥዕላዊ መግለጫ)

| | | |
|---|---|---|
| ታማኝ ያልሆነችው የሆሴዕ ሚስት፡ ታማኝ የሆነ ባልዋ። የእስራኤል ታማኝ አለመሆን፤ የጌታ ታማኝነትና አፍቃሪነት ምዕ. 1-3 | ከጌታ ርቃ ባእልንና ሌሎችን አማልክት የተከተለች እስራኤል ፍርድ እንደሚጠብቃት መነገሩ ምዕ. 4-13 | ወደ እግዚአብሔር መመለስ ፈውስንና በረከትን ያመጣል። ምዕ.14 |

### ማጠቃለያ

ወደ ኋላ በማፈግፈግ ለእግዚአብሔር ታማኝ ላልሆኑ ሰዎችም ጌታ ፍቅሩ ፍጹም ነው። ወደእርሱ እንዲመለሱ ጊዜ በመስጠት ንስሐ እንዲገቡ ይጠራቸዋል። ሆሴዕ ምዕ. 1-3 እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ኅብረት፤ ለሰው ታማኝ ያልሆነችውን ሚስት አስመስሎ ይናገራል። ታማኝ ባልዋ ሆሴዕ ሲሆን እርሱ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው፤ ጎሜር ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ ምሳሌ ናት። እግዚአብሔርን ትታ ጣዖታትን ተከተለች (በመንፈሳዊ ሕይወቷ አመነዘረች፤ ታማኝ አልሆነችም)። እስራኤል የተሰጣትን የሕግ ቃልኪዳን በማፍረስ ከጌታ ኰበለለች።

በመጨረሻም፤ ሆሴዕ ሁሉንም ንስሐ እንዲገቡ በመጥራት፤ የሚመለሱ ከሆነ ከጌታ ዘንድ ፈውስና በረከት እንደሚያገኙ በመናገር ትንቢታዊ መልእክቱን ያጠቃልላል። ከምዕ. 4-14 ድረስ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የተበላሹ መሆናቸውን ተመልክተናል። በመሆኑም ከጌታ ዘንድ ፍርድ ይጠብቃቸዋል።



# ትንቢተ አሞጽ

## «አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ» (4፥12)

**ጸሐፊው፡-** አሞጽ (1፥1)

**የተጻፈበት ዘመን፡-** 760 ዓ.ዓ. አካባቢ

**አርዕስት፡-** በኃጢአት ላይ ስለሚመጣ ፍርድ

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-** 1፥2፤ 4፥12፤ 5፥4

**ቁልፍ ቃላት፡-** ይላል ጌታ፤ በደል (መተላለፍ)፤ እንዲህ አደርጋለሁ፤ ፈልጉ/ፈልግ።

### ዋና ዓላማዎቹ

ምሕረት ለማይገባው ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቸርነት ማሳየት፤ እስራኤል በግፍ ከተሞላችበት ሁኔታ እንድትመለስ ማሳሰብ፤ በንስሐ ካልተመለሰች እስራኤልን ፍርድ እንደሚጠብቃት ማስጠንቀቅ፤ ወደፊት ስለሚሆነው ደህንነት ተስፋ መስጠት ናቸው።

### አስተዋጽኦ

I. በእስራኤል ጎረቤት አገሮች ላይ የሚመጣውን ፍርድ ማስታወቅ (ምዕ. 1-2)።

ሀ/ ነቢዩና የነበረበት ዘመኑ (1፥1-2)

ለ/ ፍርድ የሚመጣባቸው አገሮች (1፥3-2፥5)

1. ሶርያ የሰዎችን መብት ችላ በማለትዋ (1፥3-5)
2. ፍልስጥኤማውያን (ፍልስጥኤም) ሰዎችን ለገንዘብ በመሸጣቸው (1፥6-8)
3. ጢሮስ (ፊንቂ) የተሰፋን ቃል ማፍረስዋ (1፥9-10)
4. ኤዶምያስ ወንድሟን በመጥላትዋ (1፥11-12)
5. የአሞን ልጆች፤ መከላከል በማይቻል ሁኔታ ላይ ጭካኔ ስላሳዩ (1፥13-15)
6. ይሁዳ፤ ለአምላኳ ታማኝ አለመሆኗ (2፥4-5)

ሐ/ በእስራኤል ላይ ስለሚመጣ ፍርድ መነገሩ (2፥6-16)

II. በእስራኤል ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ መግለጽ (ምዕ. 3፥1-9፥10)

ሀ/ በኃጢአትዋ ምክንያት ያልተጠበቀ ፍርድ ይመጣባታል (ምዕ. 3-4)
ለ/ እስራኤል ንስሐ እንድትገባ መጠራቷ (ምዕፍ 5፥1-15)
ሐ/ ስለሚመጣው ፍርድ አስፈሪነት መግለጽ (ምዕ. 5፥16-9፥10)
- ክፉው ሕዝብ ፍርድ ይመጣበታል፣ ይማረካል፣ ይወድቃል።

III. የእስራኤል ሕዝብ የመታደስና የመባረክ ተስፋ (ምዕ. 9፥11-15)
- የወደፊት ተስፋቸው

## አሞጽ

### 1. ስሙና ቤተሰቡ

አሞጽ ማለት «ሸክም ተሸካሚ» ማለት ነው።
መኖሪያው፣ ተቁሔ የሚገኘው በይሁዳ ሲሆን ከቤተልሔም በስተደቡብ ወደሙት ባሕር አካባቢ ነው። ጌታ አሞጽን ላሞችንና በጐችን ከሚጠብቅበት ቦታ ለነቢይነት ጠራው (አሞ. 1፥1፣ 7፥14)። ስለቤተሰቡ የተነገረ ነገር የለም።

### 2. የነቢይነት አገልግሎቱ

ጌታ ዳዊትን ከበግ ጥበቃ እንደጠራው (1ኛ ሳሙ. 16፥11-13)፣ እንደዚሁ አሞጽንም ከበግ ጥበቃ ጠራው (7፥15)። ተወልዶ ያደገው በይሁዳ ሆኖ ሳለ ጌታ በእስራኤል (በሰሜኑ መንግሥት) እንዲሰብክ ላከው (አሞ. 1፥1-2፣ 7፥14፣ 15)። በተጨማሪም ይሁዳንና በጐረቤት ያሉ አገሮችንም በመልእክቱ አገልግሎአቸዋል። የነቢይነት አገልግሎት የሰጠው ለአሥር ዓመታት ነበር (765-755 ዓ.ዓ.)።

## የእስራኤል ሕዝብ ሁኔታ

## አሞጽ ያገለገላት እስራኤል በነቢዩ ዘመን

1. ሰላም የሰፈነባት ነበረች። ኃያልዋ አሦር በደካማ መሪዎች ትተዳደር ነበርና እስራኤል ሰብቻዋ ተተወች።

2. ንግድ እየጨመረ ሄደና እስራኤል ሀብታም እየሆነች ሄደች።

3. ዘመኑ የችግር ጊዜ ነበረ። የነበረው ሀብት ለሰው ሁሉ የደረሰ አልነበረም። ሀብታሞች ሀብት እየጨመሩ ሲሄዱ፣ ድሆች እያጡ መጡና በሀብታሞች እጅ ወደቁ። ለሕይወታቸው ሲሉ ጌታን መተው ጀመሩ። በውጭ ሲታዩ ሃይማኖተኞች ይመስላሉ፣ ውስጣቸው ግን ባዶ ነበር።



## የሥነጽሑፍ ይዘቱ

አሞጽ አድማጮቹን የሚያጽናና ሰው ሳይሆን አይቀርም፣ ለምን? ቢባል፣ መልእክቱ ቀጥተኛና ግልጽ በመሆኑ ነው። ነቢዩም እውነትን ከመግለጽ ወደኋላ አላለም (7፥17)። ትንቢቶቹ ስለፍርድና መከራ የሚገልጹ ናቸው። እግዚአብሔርንም በሚያገሳ አንበሳ አስመስሎ ይናገርና። መልእክቱን በተሰፋ ቃል ያጠቃልላል።

እንደሌሎቹ ነቢያት አሞጽ ስለሰዎች ኃጢአት፣ ስለሚመጣው ፍርድ፣ ስለእግዚአብሔር ጽድቅና ቅድስና እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ተናገረ።

## የመልዕክቱ ይዘት

1. እግዚአብሔር በኃጢአተኛ መንግሥታት ላይ እንደሚፈርድ በግልጽ ተናግሯል።
   - የመፍረድ ኃይልና ሥልጣን የእግዚአብሔር ነውና (1፥3-2፥3) የመረጣቸውን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ላይ ልክ እንደሥራቸው ይፈርዳል።

2. እግዚአብሔር ኅብረተሰቡ በቅንነት እንዲኖር ይፈልጋል።
   - በኃጢአት ላይ ይፈርዳል (3፥10፣ 15፥ 6፥4-6)፣ ድሆች እንዲጠቁ አይፈልግም (2፥7፣ 4፥1፣ 5፥11)
   - መልካም ባሕርይን ይጠብቃል (5፥14፣ 15፣ ክፉውን ጠልተው መልካሙን እንዲወዱ ይፈልጋል (5፥24)።

3. እግዚአብሔር ግብዝነት ያለውን ሃይማኖት አይፈልግም። እስራኤላውያን፦

ሀ/ ሐሰተኞች ሆነው ውል የሚያፈርሱ ነበሩ (2፥4-5፣ 3፥1-2)
ለ/ በቤተመቅደስም የማይከበሩ ነበሩ (2፥8)
ሐ/ ስላሰፈው ነገር የማያመሰግኑ ነበሩ (2፥9-12)
መ/ አምልኮአቸው የማስመሰል /የታይታ ዓይነት/ ነበር (4፥4፣ 5፥21-27፣ 8፥5)
ሠ/ ባላቸው ዝንባሌ በራሳቸው የረኩ ነበሩ (6፥1)
ረ/ ነቢዩን በስለላ መልክ ይከታተሉት ነበር (7፥10-17)

4. እግዚአብሔር እስራኤልን ወሰን በሌለው ፍቅር ይወድዳታል።
   - በአሞጽ በኩል የፍርድ መልእክት ቢያስተላልፍም ይወድዳቸዋል፣ ጌታ አምሳክም፦
     - በራሱ ውዴታ መርጦአቸዋል (3፥2)
     - በትዕግሥት ያስተምራቸዋል (4፥6-11)

- በቸርነት ይደግፋቸዋል (5÷6)
- በቸርነቱ ሲያድሳቸውና ሲባርካቸው ይፈልጋል (9÷11-15)

## ተጨማሪ ሃሣቦች

1. የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ፣ ዋና የኃጢአት ሥራ ነው (ምዕ. 1÷3፣ 6÷9፣ 11÷13፣ 2÷1፣ 4÷6)።
2. የእግዚአብሔርን ፍርድ መቀበል፣ ሕዝብ ኃጢአት ሲሠራ እግዚአብሔር ሳይቀጣ አያልፍም 1÷2፤1÷4፣ 6÷ 3÷13-15፣ 7÷1-6)።
3. የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት
   - እርሱ በሁኔታዎች በኩል ይናገራል - (4÷4-11)
   - እርሱ በነቢያት በኩል ይናገራል (7÷14÷15)

   እግዚአብሔር ሳይናገር ዝም ካለ፣ ለሰዎች እጅግ አስጊ የሆነ ጊዜ ያ ነው ማለት ነው (ምዕ. 8÷11÷12)።

## ስነ መለኮታዊ መልእክት

- እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ ለድሃውና ለባለጠጋው አሳቢ አምላክ እንደሆነ እናስታውስ፡፡
- ጥንቃቄ የጐደለው ምቾት አደገኛ ነገር ነው።
- የጌታ አገልጋይ፣ እንደአሞጽ ትሁትና ለተጠራበት አገልግሎቱ ታማኝ ሰው መሆን ይኖርበታል።
- አሞጽ 9÷11-12፣ በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶአል፡-

  የሐዋ 15÷16-17 መዳን ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም ጭምር መሆኑን በማስመልከት ተጠቀሰ።

## የአሞጽ አገልግሎት ከጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ጋር የሚመሳሰልባቸው ሰባት መንገዶች፡-

1. ስአገልግሎት መለየት - ለጌታ ሥራ ተለየ (አሞጽ 7÷14)
2. በትህትና - አሞጽ የተነሳበትን የቀድሞውን ቦታ አስመርሳቱ (አሞጽ 7÷15)
3. በምሳሌ አድርጐ የማስተማር ዘዴው (አሞጽ ምዕ. 7-8፣ ማቴ. 13)



4. መልእክቱን በቀጥታ ከእግዚአብሔር በመቀበል «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» ማለቱ (በዚህ መጽሐፍ ይህ ሐረግ 40 ጊዜ ተጠቅሷል)።
5. በአሞጽና በጌታ ኢየሱስ ላይ በአገልግሎታቸው ላይ ተቃውሞ መነሳቱ (አሞጽ 7÷10፣ ዮሐ. 19÷14)
6. አገልግሎታቸውን በፍጥነት ማከናወናቸው (መፈጸማቸው) (አሞጽ 3÷8፣ ዮሐ. 9÷4)
7. የባለጸጐችን ራስ ወዳድነት ማውገዛቸው (አሞጽ 6÷4-6፣ ሉቃ. 12÷15-21)።

**የአሞጽ መጽሐፍ ንድፍ**

| | | |
|---|---|---|
| በእስራኤል ጐረቤት አገሮች ላይ ስለሚመጣ ፍርድ የተነገረ ትንቢት ምዕ. 1-2 | በእስራኤል ላይ ስለሚመጣው ፍርድ የተነገረ ትንቢት ምዕ. 3÷1-9÷10 | የእስራኤል ሕዝብ የመታደስና የመባረክ ተስፋ ምዕ. 9÷11-15 |

## ማጠቃለያ

ከላሞች ጥበቃና ከበግ ጥበቃ እግዚአብሔር ነቢይ አድርጐ ያስነሳው አሞጽ ነቢይም ሆኖ እንደእረኛ (መጋቢ) ማገልገሉ ይነገርለታል። እግዚአብሔር የአይሁዶች ብቻ ሳይሆን የሰዎች ሁሉ አምላክ መሆኑን ተናገረ (ምዕ. 1÷3፣ 6÷9)። እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር ከገባው ቃል ኪዳን የተነሳ ከእነርሱ ብዙ ጠበቀ፣ ነገር ግን አይሁድ እንደተጠበቁት አልሆኑም። እንዲያውም ከጌታ ርቀው በክፋት ተሞሉ፣ በንስሐ ካልተመለሱ ፍርድ ይጠብቃቸዋል። ከእምነት ያልሆነ የሃይማኖት ሥርዓታቸው ከጌታ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው አሞጽ ይናገራል። እንዲያውም አይሁዳዊ ሁሉ ለላደረገው ኃጢአት በጌታ ቀን ተጠያቂ እንደሚሆን ይናገራል።

በመጨረሻም አሞጽ (9÷9-15) ወደፊት ለእስራኤል ደህንነት፣ ሰላምና የብልጽግና ዘመን እንደሚመጣ ተናግሯል።

# ትንቢተ ኢዩኤል

## (የጌታ ቀን) - ፍርድና ምሕረት

**ጸሐፊው:-** ኢዩኤል

**ዘመን:-** የኖረበ ዘመን በ ኖናል ሬይታወቅም::

**እርዕስት:-** የጌታ ቀን (1+15፣ 2+1፣ ፲፻፣ 31፣ 3+14)

**የመክፈቻ ጥቅሶች:-** 2+21፣ 32

**ዋና ዋና ክፍሎች:-** 2+1-11፣ 2+28-32፣ 3+18-21

**ቁልፍ ቃላት:-** አንበጣ፣ የጌታ ቀን (5 ጊዜ ተጠቅሷል)፣ መደሰት፣ መታደስ

## ዋና ዓላማዎች

1. ሕዝቡን ስለሚመጣው ፍርድ ማስጠንቀቅ፣
2. ወደጌታ በንስሐ እንዲመለሱ መጥራት፣
3. የይሁዳን የወደፊት ደህንነት ተስፋ አስረግጦ መናገር (ምዕ. 3+14-21)፣
4. ከመጨረሻው ዘመን አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ማስታወቅ፣
5. እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ በኃጢአተኞች ላይ እንደሚፈርድና የእርሱ ለሆኑ ካረፍ ንገ ሰላምንቹ በረሬትን እንደሚያመጣ መናገር::

## የኢዩኤል መጽሐፍ አስተዋጽኦ

I. **የአንበጣ መቅሠፍት (ምዕ. 1)**

ሀ/ እንዲጸልዩና እንዲያዝኑ መጥራት (1+1-14)

ለ/ ስለጌታ ቀን ማስታወቅ (1+15-20)

II. **የጌታ ቀን (ምዕ. 2)**

ሀ/ አንበጦች የጌታን ቀን መምጣት (2+1-11)

ለ/ ለጸሎትና ለንስሐ መጥራት (2+12-17)

ሐ/ እግዚአብሔር ምድሪቱን በበረከት ይሞላል (2+18-27)

መ/ ጌታ ምድሪቱን ያድሳል (2+28-32)

III. የእስራኤል እንደገና መቋቋም፣ የጌታ ቀን መምጣት (ምዕ. 3)

ሀ/ ጌታ በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል (ቁ. 1-16)

ለ/ የጌታ ሕዝብ ይባረካል ተነገረ (ቁ. 17-21)



## ኢዩኤል የተባለው ሰው

ኢዩኤል ማለት የስሙ ትርጉም «ያህዌ እግዚአብሔር ነው» ማለት ነው የነቢዩ ሳሙኤል በኩር ልጅ (1ኛ ሳሙ. 8+2) በዚህ ስም ተጠርቷል:: ነገር ግን ስለነቢዩ ኢዩኤል በራሱ ከሰጠው ቃል ውጪ ስለእርሱ የምናውቀው ነገር የለም፣ (ኢዩ. 1+1 የባቱኤል ልጅ፤ ወደ እርሱ የእግዚአብሔር ቃል መምጣቱ):: በአጠቃላይ እንደሚታሰበው ኢዩኤል በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ነቢያት ቀዳሚ እንደነበረ ይነገራል፣ ምናልባት ኤልያስንና ኤልሳዕን በወጣትነት ዘመኑ ደህና አድርጐ ሳያውቃቸው አልቀረም::

ትንቢቱን የተቼሬረው በደቡባዊው መንግሥት (በይሁዳ) ሲሆን ምናልባት በኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ተናግሮ ይሆናል ይባላል (2ኛ ነገሥ. 11-12፣ 2ኛ ዜና 24፤23-25)::

## የትንቢተ ኢዩኤል ታሪካዊ አቀማመጥ

ነቢዩ መልእክቱን ያቀረበው ለደቡባዊው መንግሥት ለይሁዳ ነበር ብለናል:: ከሰማርያ ውድቀት አስቀድሞ እንደተናገረ ይገመታል:: የሕዝቡን ኃጢአት አስመልክቶ ነበር ተናግሯል (2ኛ ነገ. 12)::

«የጌታ ቀን» ለኢዩኤል በዚያው ወቅት አገሪቱ በአንበጣ መንጋ መቅሰፍት መመታትዋን ያስታውሳል፣ ይህንንም በምሳሌ ሌላ መንፈሳዊ ትርጉም እንዳለው ያቀርበዋል:: አንበጣው በሕዝብ ኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የመጣ ፍርድ ነው:: ነገር ግን ትልቁ ፍርድ ቀርቦአል:: ይሁዳ በጠላት አገሮች ተከብባለች:: ተስፋ የሚኖራቸው ዘወም ጸሎት ንስሐ ሲገቡ ብቻ ነው:: መጽሐፉ ለኣለፈው ፍርድ (በአንበጦች)፣ ለሊሁኑ ፍርድ (ለሰከበቡአቸው አገሮች) የእግዚአብሔር ምሕረት እንዳለና እርሱ ንሰሐ እንዲገቡ እንደሚፈልግ ይገልጻል (ኢዮ. 1+13-20፣ 2+12-17) ::

## የኢዩኤል መልእክት ምንድነው?

ኢዮኤል የተስፋ መልፎና ሬስትሳሰፈ ነቢይ ነው:: እንደዚሁም ስለ መንፈሳዊ ተሐድሶ (መነቃቃት) ተናግሯል (ኢዩ. 2+18-32):: እርሱ ከተናገራቸው ተስፋዎች መካከል በበዓለ ሃምሣ ቀን መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ የተፈጸሙ አሉ፤ ገና ያልተፈጸሙም አሉ፤ (ኢዩ. 2+28፣ 29፣ የሐዋ. 2+16-21):: በተጨማሪም ይህ መጽሐፍ የአይሁድን ሕዝብ ወደአገራቸው መሰብሰብና በአሕዛብ አገሮች ላይ እግዚአብሔር እንደሚፈርድ ይናገራል (ኢዩ. 3+2-7፣ ማቴ. 25+32)::

እንግዲህ የኢዩኤል መልዕክት ዓላማው ጌታ በመጨረሻው ዘመን በዓለም እንደሚፈርድና ንጉሥ ሆኖ እንደሚገዛ ለማሳሰብ ነው (ከኢሳ. 2+6-22፣ አሞ. 5+18-20፣ ሶፎ. 1+2-18)።

«የጌታ ቀን» የሚለው ሐረግ ኢዩኤል አምስት ጊዜ ጠቅሶታል። የጠቀሰውም የፍርድንና የዘመቼ ን መሬረሻ ለማመልከት ነው። ሌሎችም የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይኸንኑ ቃል ጠቅሰዋል (ኢሳ. 2፡6-22፣ አሞ. 5+18-20፣ ሶፎ. 1+2-18)። ኢዩኤል ለጌታ ቀን መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ሲገልጽ ማስጠንቀቂያ ጭምር ነው የተናገረው (1+1-12፣ 2+1-11፣ ከአሞ. 7+1-3 ጋር አስተያይ)። እግዚአብሔር የሕዝቡን ንስሐ መግባት ስለሚፈልግ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይጋብዛቸዋል (ኢዮ. 2+13-20፣ 2+12-17፣ ሶፎን. 2+1-3)።

## የጌታ መልስ (ኢዩ. 2+18-3+21)

1. ለአገሮች የሚሆን በረከት (2፡18-27)
2. መንፈሱን እንደሚያፈስስ መነገሩ (2፡28-32)
3. በዙሪያ ባሉ አገሮች እንደሚፈርድ መነገሩ (3፡1-8)
4. ጌታ ለሕዝቡ ዕረፍት ሰጥቶ በሳያቸው ላይ እንደሚነግስ መነገሩ (3፡9-21)

የአዲስ ኪዳን ዘመን ጸሐፊዎችም ስለመጨረሻው የጌታ ቀን ተናግረዋል። ይህንንም ወደፊት እንደሚመጣ አድርገው ነው የተናገሩት (2ተሰሎ. 2፡2፣ 2ጴጥ. 3፡10)። ይህ ቀን ጌታ በኃጢአተኞች ላይ ፍርድን የሚያመጣበት ሲሆን ለጻድቃን ግን ከጌታ ጋር የሚነግሱበት ይሆናል። የሺህ ዓመት መንግሥትን ሁኔታ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ከዚያ ጋር ያያይዙታል (ራዕ. 20)።

## ስለጌታ ቀን አጀማመር ልዩ ልዩ አመለካከቶች

(መቼ እንደሚጀምር) ሦስት አሳቦች አሉ።

1. በመነጠቅ፣ ታላቁ የመከራ ዘመን ሲጀመር
2. ከመነጠቅ በኋላ በመከራው ዘመን
3. ከታላቁ መከራ በኋላ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሲመለስ፣ ጠላቶቹን በአርማጌዶን ጦርነት ሲደመስስ ሲመጣ የሚሉት ናቸው (ራዕይ 19+11-21)።

## ስነ መለኮታዊ መልእክቶች

1. ነገሮች ሲበላሹ በጾምና ጸሎት ወደጌታ መመለስ ይኖርብናል (2ኛ ዜና 7+14-16፣ ኢዩ. 1-2)። ያበላሸነውን ነገር በጌታ ፊት በንስሐ ማስተካከል አስፈላጊ ነው። ኢዩኤል እንዳደረገው ቤተክርስቲያን ለአባሉቿና ለዓለም የጌታን ቃል በታማኝነት



መስበክ ይኖርባታል። ጌታ ኢየሱስ የተበላሸ የሰውን ሕይወት ያድሳል (ማቴ. 11+28-30፣ 2ኛ ቆሮ. 5+17)።

### የኢዩኤል መጽሐፍ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| የአንበጣ መቅሰፍት፤ እንዲጸሙና እንዲጸልዩ ማሳሰብ ምዕ. 1 | የጌታ ቀን፣ ለጾምና ለንስሐ መጥራት የመንፈስ መፍሰስ ተስፋ ምዕ. 2 | የእስራኤል እንደገና መቋቋም፣ የጌታ ቀን መምጣት ምዕ. 3 |

## ማጠቃለያ

ነቢዩ ኢዩኤል ስለጌታ ቀን በምሳሌ አድርጐ በልዩ ልዩ መንገድ ተናግሯል። የእርሱ የሆኑ ሕዝብ ወደጌታ መመልከት ድምጹንም በመስማት ወደእርሱ መመለስ ይኖርባቸዋል። ጌታም ለሕዝቡ ተሐድሶንቼ በረሬትን ምላሽ አድርጐ ያመጣላቸዋል። በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ይፈርዳል። እርሱ አስቀድሞ የተናገረው ሁሉ እንደተፈጸመ፤ ገናም ወደፊትም እንደሚፈጽም በእምነት እንጠባበቅ።

# ትንቢተ አብድዩ

## « የሚወድቀው ዓለትና ስዘላለም የሚጸናው መንግሥት»

**ዘመን**:- በ6ኛው መቶ ዓመት ዓ.ዓ. (ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ ወደ 585 ዓ.ዓ. ገደማ)

**ርዕስ**:- ፍርድ በኤዶምያስ ላይ

**ቁልፍ ጥቅስ**:- ቁጥር 15

**ቁልፍ ቃላት**:- መውረስ፣ ኤዶምያስ

### የመጽሐፉ ዓላማ

ኤዶምያስ በይሁዳ ላይ ስለምትወስደው እርምጃ፤ ፍርድ እንደሚመጣባት ለመግለጽና ይሁዳ እንደምትከብር ለማሳየትናእግዚአብሔር በ ካቢቷ ምኖንሬት እንደሚያዋርዳት ለመግለጽ ነው (ቁጥር 1-4)።

### አስተዋጽኦ

I. አርዕስትና መግቢያ (ቁጥር 1)
II. በኤዶምያስ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ (ቁጥር 2-4)

ሀ/ የኤዶምያስ ጥፋት (ቁ. 2-9)
ለ/ የኤዶምያስ መጥፋት ምክንያቶች (ቁጥር 9-14)

III. አስፈሪው ታላቁ የጌታ ቀን (ቁጥር 15-21)
ሀ/ አስፈሪው ቀን (ቁ. 11-16)
ለ/ የእስራኤል መታደስ/የጌታ መንግሥት መቋቋም (ቁ. 17-21)

### ጸሐፊው

- የአብድዩ የስሙ ትርጉም «የጌታ አገልጋይ« ማለት ነው። መኖሪያ ቤቱ በይሁዳ ውስጥ እንደነበረ ይታመናል። የኖረውም በኢዮራም፣ በአካዝያስ፣ በአታልያና በኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ውስጥ ነበር።

- ይህ ሰው የጻፈው መጽሐፍ (ትንቢተ አብድዩ) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት መጻሕፍት መሐከል አጭሩ ነው።



### ታሪካዊ ዳራ

- ኤዶማውያን የያዕቆብ ወንድም የዔሳው ዘሮች ናቸው (ዘፍጥ. 25+19-34)

- ኤዶማውያን የሰፈሩት በሴይር ተራራ አጠገብ ነው (ዘፍጥ. 36)

- እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ሲመጡ፣ በመሃከላቸው እንዳያልፉ ከለከሉ (ዘኁል. 20+14-21)። ኢየሩሳሌም በጠላቶች በመያዝዋም ተደስተው ነበር (መዝ. 136(137)+7፣ ቁ. 1-6)።

- ያዕቆብና ዔሳው በመሠረቱ ወንድማማች ነበሩ (2ኛ ሳሙ. 8+14፣ 2ኛ ነገ. 14+1-7፣ 2ኛ ዜና 28+17)።

- ኤዶምያስ ከጌታ ኢየሱስ ልደት በፊት ተደመሰሰች፣ በመጨረሻም ከታሪክ እንደምንረዳው በ70 ዓ.ም. ሮማውያን ኢየሩሳሌምን ሲያጠፉ አንድ ላይ ጠፉች።

### የአብድዩ መጽሐፍ ዋና አሳብ

እግዚአብሔር በኤዶምያስ ላይ ፈራጅ ነው (ያዋርዳታል )ቁ. 2-4፣ 8)፣ ሌሎችን አገሮች በእርሷ ላይ ያስነሳል (ቁ. 1፣7)። እግዚአብሔር ከሚያመጣባት ፍርድ ልታመልጥ አትችልም (ቁ. 3፣ 4፣ 6፣ 8፣ 9)። እስራኤልን እጅግ በድላታለች፤በእርሷ ላይ ግፍ ሠርታለች (ቁ.11-15) እስራኤል ግን እንደገና ትነሳለች፣ ድንበሯም ይሰፋል ቁ.12፣ 13፣ 17-20።

እግዚአብሔር በሁሉ ላይ ታላቅ ይሆናል (ቁ. 15፣ 16፣ 21)።
ሁሉም አገሮች ፍርድ ያገኛሉ (ቁ. 15፣ 16)
እርሱ ብቻውን ሁሉን የሚያስተዳድር ንጉሥ ይሆናል (ቁ. 21)

### ስነ መለኮታዊ መልእክት

- የምንኖረው እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም ውስጥ ነው። በጥሩ ግብረገብ መኖር ይፈለግብናል።

- እግዚአብሔር አፍቃሪ እንደሆነ ሁሉ ቅዱስ አምላክም ነው። እግዚአብሔር ታሪክን ሁሉ የሚቆጣጠር አምላክ ነው። ትዕቢት (ኩራት) ምንጊዜም የሚመራው ወደ ውድቀት ነው። ግለሰብ ወይም አገር ከታበየ ውድቀት እሩቅ አይሆንም (ምሳ. 6+17፣ 11+2፣ 16+18፣ 29+23)። ስለዚህም እያንዳንዳችን በሌላው ላይ ስምናደርገው ነገር ሁሉ ተጠያቂዎች ነን፣ ስጌታም መልስ እንሰጣለን። የጌታ ሕዝብ ምንጊዜም ከመከራ ነፃ አይሆንም፣ ጌታ ግን በድል የወጣዋል።

## የመጽሐፉ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| በኤዶምያስ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ መነገሩ ቁ.14 | አስፈሪው ታላቁ የጌታ ቀን ቁ. 15፣ 16 | የእስራኤል መታደስና የጌታ መንግሥት መቋቋም ቁ. 17-21 |

### ማጠቃለያ

ነቢዩ አብድዩ ኤዶምያስ ከትዕቢት የተነሳ እንደምትወድቅ ይናገራል። የሚፈርድባት ራሱ እግዚአብሔር ነው። በእህቷ በይሁዳ ላይ ስላደረገችው ግፍ ትክኖለኛ የሆነውን ፍርድ ይሰጣታል፣ በመሆኑም ኤዶምያስ ትጠፋለች (ቁ. 1-4)። እንዴት እንደምትጠፋና ለምን እንደምትጠፋ በአብድዩ በኩል በዝርዝር ተነግሯል (ቁ. 5-14)። በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጹና ለእስራኤልም የመታደስ ዘመን እንደሚመጣ ተነገረ (ቁ. 15-21 ተመልከት)። በዙሪያ ያሉ አገሮችም በእስራኤል ላይ ካሳዩት መጥፎ ባሕርይ የተነሳ ይቀጣሉ። ባለፉት ዘመናት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ የተነሱ ቅጣታቸውን ከእርሱ ተቀብለዋል። ገና ወደፊትም የሚቀጡ ይኖራሉ (መዝ. 2)።



# ትንቢተ ዮናስ

## የእግዚአብሔር ታላቅ ምህረት

«ተነስተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፣ ክፋታቸውም ወደ ፊቴ ወጥቶአልና በእርስዋ ላይ ስበክ » (ዮና. 1÷2)

እግዚአብሔር ርኅራኄው ለሰው ሁሉ ነውን? እግዚአብሔር እርሱን የማይወዱትንና ለቃሉ የማይታዘዙትን እያወቀ ለእነርሱም የምሕረት እጁን መዘርጋት ይኖርበታልን? በምሥራቅ አገሮች ብዙዎችን ሕዝቦች ያጠፋች አሦር በእውነት ያን ክፋት ሁሉ እድርጋ እያለች፤ እግዚአብሔር ርኅራኄ ማሳየቱ ተገቢ ነበር? እግዚአብሔር ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ ሳይሆን፣ ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ ይፈልጋል (ሕዝ. 18÷23፣ 32 1ኛ ጢሞ. 2÷4)።

**ጸሐፊው፡-** ዮናስ

**ዘመን፡-** ወደ 780/770 ዓ.ዓ. ገደማ

**አርዕስት፡-** የእግዚአብሔር ታላቅ ምህረት

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-** 2÷9፤ 4÷2፤ 4÷11

**ቁልፍ ቃላት፡-** ትልቅ፣ አዘጋጀ፣ ንስሐ መግባት

### ዋና ዓላማዎቹ

የጌታ ልጆች በመጥፋት ላይ ላሉ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ቃል የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለባቸውና እግዚአብሔር በንስሐ ወደ እርሱ የሚመለሱትን በምህረት የሚቀበላቸው መሆኑን ያስገነዝባል (ኤር. 18÷7-10፣ 2ኛ ጴጥ. 3÷9)። ለሰው ዘር ሁሉ የደህንነትን ወንጌል መናገር፤ የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት መሆኑን ለማሳየት ነው (ሕዝ. 3÷16-18፤ 1ቆሮ. 9÷16)። የዮናስ በዓሣው ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ቆይቶ መውጣቱ፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ምሳሌ መሆኑን ያመለክታል (ማቴ. 12. 12÷40-41)።

### አስተዋጽኦ

I. የዮናስ አለመታዘዝ (ምዕ.1) - ኰብላዩን ዮናስ እግዚአብሔር እንደመለሰው
II. የዮናስ ጸሎት (ምዕ. 2) - ጸሎቱ ንስሐ መግባቱና ስዕለቱ (2÷10)
III. የዮናስ መታዘዝ (ምዕ. 3) - ስብከቱና የተገኘው ውጤት
IV. የዮናስ መቆጣት (ምዕ.4) - ለዮናስ የተሰጠው ትምህርት

**ጸሐፊው**

1. የስሙ ትርጉም፡- ዮናስ ማለት ርግብ ማለት ነው (1÷1)።

ስለቤተሰቡ፡- የአማቴ ልጅ እንደሆነ ተጠቅሶአል (2ኛ ነገ. 14÷25)
መኖሪያ ቤቱ፡- በሰሜን እስራኤል በገሊላ ክፍለ ሀገር ከናዝሬት በስተሰሜን ምሥራቅ ላይ እንደሚገኝ ይገመታል (ኤር.1÷1)

2. የነቢይነት አገልግሎቱ

- እንደሌሎቹ ነቢያት የነቢይነት ጥሪ ነበረው። በአሦራውያን ላይ የነበረው አመለካከት፣ ከአንድ የጌታ አገልጋይ የማይጠበቅ ዓይነት ከመሆኑ የተነሳ ለጌታ ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልነበረም። ጌታ የአይሁድ አምላክ ብቻ ሳይሆን የአሕዛብም አምላክ እንደሆነ ለዮናስ በሚገባ አስተምሮታል።

- በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት የነበረ ነቢይ ሲሆን የሰበከውና ያገለገለው በሰሜኑ መንግሥት በእስራኤል ነበር (2ኛ ነገ. 14÷25)።

3. የዮናስ መጽሐፍ

- የነቢዩን የሕይወት ታሪክ በከፊል በምስክርነት መልክ ስለሚያቀርብ ከሌሎች የትንቢት መጽሐፍ ለየት ያደርገዋል። እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝቦች ሁሉ አምላክ መሆኑን ይገልጻል። እርሱም ፍጥረትን ሁሉ ይወዳል፣ መሐሪ ስለሆነ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ የሚፈልግ አምላክ መሆኑን ይገልጻል (ዮሐ. 3÷16፣ ዮና. 4÷2፣ 11፣ 2÷5፣ 10፣ 3÷10)።

- ዮናስ በዓሣ ሆድ ለሦስት ቀንና ለሦስት ሌሊት መቆየቱን ይገልጻል፣ ይህም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በእርግጥ የተደረገ ታሪክ እንጂ የፈጠራ ታሪክ አለመሆኑን ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 12÷39-41 ላይ አረጋግጦአል።
እግዚአብሔር ሕዝቦችን ሁሉ የሚያስተዳድር እንደሆነ እንማራለን (ዮና. 1÷2፣ 3÷2፣ 9፣ 10)። ስለዮናስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሲሆን ለአሕዛብ አገር ሸክም ያልነበረው አገልጋይ እንደሆነ እንመለከታለን። እንደዚሁም እስራኤል የጌታ በመሆኗ ትታበይ ነበር። ዮናስም እስራኤልም አለመታዘዛቸው በጉልህ ይታያል (ዮና. 1÷3፣ 9፣ 2÷1-9፣ 4÷1-3፣9)። የአሕዛብ አገሮችም የወንጌል መልእክት ከደረሳቸው ወደጌታ ይመለሳሉ (ዮና. 1÷13፣ 14፣ 16፣ 3፣÷5-9)።

**ስነ መለኮታዊ መልእክት**



እግዚአብሔር በስሙ ለተጠራነው ብቻ ሳይሆን፣ ገና ወደ እርሱ ላልመጡም ያስባል። ወንጌል ለዓለም ሕዝብ ሁሉ መዳረስ አለበት (ማቴ. 28÷18-20፣ ማር. 16÷15)። የጌታን ጥሪና ትዕዛዝ አክብረን መቀጠል ይገባል፣ ይህም ከፍጹም ልብ፣ ከፍቅርና ጌታን ከመፍራት፣ ነፍሳትንም ከመውደድ የተነሳ መሆን ይኖርበታል።

ከእግዚአብሔር ሸሽተን ማምለጥ አንችልም (መዝ. 138 (139) ÷7-10)፣ ንስሐ መግባት/ራስን በጌታ ፊት ማዋረድ ዋጋ እንዳለው፣ ለጌታ አለመታዘዝ የሚያስከትለው ጦስ/ችግር፣ እግዚአብሔር ወደእርሱ ለሚመለሱ ምህረቱን እንደሚያሳይ፣ እንደጌታ ፈቃድ የሆነ ጸሎት መልስ እንዳለውና ጌታ የተአምራት አምላክ በመሆኑ እርሱ ሲፈቅድ፣ በራሱ ጊዜ እንደሚያደርግ ያስረዳል።

የዮናስ በዓሣው ሆድ ቆይቶ በሕይወት መውጣቱ፣ የክርስቶስ ከመቃብር የመውጣቱ ምሳሌው ነበር (ዮና. 2፣ ማቴ. 12÷39-41፣ ሉቃ.11÷30)።

**የዮናስ መጽሐፍ ንድፍ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| የዮናስ አለመታዘዝ ምዕ. 1 | የዮናስ ጸሎት ምዕ. 2 | የዮናስ መታዘዝ ምዕ. 3 | የዮናስ መቆጣት ምዕ.4 |

**ማጠቃለያ**

ዮናስ ከጌታ ፊት መኮብለሉ (ምዕ. 1) ንስሐ በመግባት ወደጌታ መጸለዩን (ምዕ.2) ከዚያም ለጌታ መታዘዙን (ምዕ. 3) ሆኖም ለአሦራውያን የጠነከረ ልብ እንደነበረው ጌታም ትምህርት እንደሰጠው (ምዕ. 4) ተመልክተናል።

እንደዚሁም ዛሬ ጌታ መልዕክተኞችን ወደጠፋ ነፍሳት መላክ ይፈልጋል፣ ምልጃን ይሰማል። ከአቅማችን በላይ በሆነ ነገር ላይ እርሱ ሥልጣን አለው፣ ተአምር ያሳየናል። ለነፍሳት ሁሉ ምህረቱን ማሳየት እንደሚወድ ሊያስተምረን ይፈልጋል። ለዮናስና ለነነዌ ሕዝቦች በተለያየ መንገድ ምህረቱን አሳይቶአል። ለእኛና ላልዳኑትም ምሕረቱን መግለጽ እንደሚፈልግ አውቀን ወደእርሱ እንጮህ ለእርሱም ለመታዘዝ ራሳችንን እንስጥ።

# ትንቢተ ናሆም

## «ለነነዌ ወዮላት»

### መግቢያ

**ጸሐፊው** :- ናሆም
**ዘመን** :- ከ663 ዓ.ዓ. በኋላ፣ ከ612 ዓ.ዓ. በፊት (ናሆ. 2÷6-8፤ 3÷8-10)
**ርዕስ** :- የነነዌ ውድቀት
**ቁልፍ ጥቅስ** :- ናሆ. 13÷7÷8
**ቁልፍ ቃላት** :- «በአንቺ ላይ ነኝ፣ ፍጻሜ፣ ነነዌ»

### የመጽሐፉ ዓላማዎች

- የነነዌን ሕዝብ መጥፋት ማስታወቅ፣
- የእግዚአብሔርን ቅን ፍርድ መግለጽ፣
- በዓለም ኃጢአተኛ ሕዝብ ላይ የሚመጣውን ፍርድ መግለጽና
- እግዚአብሔር ይሁዳን እንደማይተዋት መግለጽ ናቸው።

### አስተዋጽኦ

I. የነነዌ ፈራጅ (ምዕ.1)
«እግዚአብሔር በፍርድ አማካይነት የሚሰጠው ምሕረት»

II. የነነዌ መፈረድ (ምዕ. 2)
(የነነዌ መወረርና መውደቅ»

III. ነነዌ ፈጽሞ የምትጠፋበት ምክንያት (ምዕ. 3)
«ኃጢአትዋ ለፍርድ እንዳበቃት»

### ጸሐፊው

የናሆም የስሙ ትርጉም «አጽናኝ» ማለት ሲሆን ስለእርሱም ሆነ ስለቤተሰቡም በዝርዝር የተገለጸ ነገር የለም። ይኖርበት የነበረው ከተማ ከይሁዳ ከተሞች አንዱ ይመስላል። ስሙ ኤልቆሱ ይባል ነበር (1÷1)። ምናልባት ከኢየሩሴም በስተደቡብ ምዕራብ 20 ማይል ርቆ የነበረ ቦታ ሳይሆን እንዳልቀረ ይታሰባል።

መልእክቱን ከጌታ የተቀበለው በራዕይ መልክ ነበር። ነቢዩም ስለነነዌ ውድቀትና ይሁዳ በጌታ እንደምትጠበቅ ተናግሯል (1÷1 15÷2)።



### የመጽሐፉ ዋና ሃሣብ

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ፈራጅነት በግልጽ ያስቀምጣል (ናሆ. 1÷2-8)። ነነዌ ስትወድቅ፣ ይሁዳ እንደምትጠበቅ ይናገራል (ናሆ. 1÷9)። የናሆም ትንቢት በጽሑፍ ለፍሮ የነበረው በግጥም መልክ እንደነበረ፣ ይነገራል (ናሆ. 1÷2-11)። ይሁዳን ያስጨነቀች ነነዌ ሲፈረድባት፣ ለይሁዳ መዳንና ጥበቃ ይሆንላታል (ናሆ. 1÷12-15)። የቀሩት ምዕራፎች (ምዕ. 2 እና 3) የአሦር ከተማ ነነዌ ፈጽሞ እንደምትጠፋና የሚደርስባትን ፍርድ ይገልጻል።

ይህ መጽሐፍ በትምህርተ መለኮታዊ አቀራረቡ ከኢሳይያስና ኤርምያስ ይለያል (ናሆ. 1÷3-6)። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጠብቅ (1÷7) እና ጠላቶቹን የሚያጠፋ መሆኑ በግልጽ ተቀምጦአል (1÷2፣ 6)። የአሦር ወንጀልና ፍርድ በነነዌ ላይ እንደሚመጣባት በግልጽ ተነግሮአል። ይሁዳ መከራና ሐዘን ደርሶባት ነበር።

### ስነ መለኮታዊ መልእክት

እኛ የምንኖርባት ዓለም በግብረገብ (በሞራል) የተበላሸችና ለነፍስ ጭንቀት የሚያስከትሉ ነገሮች የበዛባት ናት። እግዚአብሔር ደግሞ አፍቃሪ ብቻ ሳይሆን ተበቃይ ፈራጅ አምላክ፣ እንዲሁም በእርሱ የሚታመኑትን ዐውቆ የሚጠብቃቸውም ነው። ትዕቢት ምንጊዜም ወደ ውድቀት ይመራል። እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን አስቀድሞ በታማኝ ባሪያዎቹ በኩል ይገልጻል። ጌታ አምላክ የሕዝቡን ጠላቶች ይጥላቸዋል (ይፈርዳል) (ናሆ. 1÷15)፣ ሮሜ 10÷15)።

### የናሆም መጽሐፍ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| የነነዌ ፈራጅ<br>ምዕ. 1 | ፍርድ በነነዌ ላይ እንደሚመጣ መነገሩ<br>ምዕ.2 | የነነዌ መጥፋት ምክንያት<br>ምዕ. 3 |

### ማጠቃለያ

በናሆም መጽሐፍ የእግዚአብሔር ባሕርይ በግልጽ ተቀምጦአል። ጠላቶቹን የሚበቀል፣ እርሱን አምነው ለሚከተሉት ሙሉ ጥበቃ የሚያደርግላቸው አምላክ መሆኑን ተመልክተናል (ናሆ. 1÷7፣ 15)። ጌታ ኢየሱስ መከራ ለሚያሳዩን በቀልን፣ መከራ ለምንቀበል ዕረፍትን ያመጣልናል (2ኛ ተሰ. 1÷5-10)። በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ ነው (የሐዋ. 10÷42-43)።

# ትንቢተ ዕንባቆም

## «ጻድቅ በእምነት በሕይወት ይኖራል»

### መግቢያ

ጸሐፊው :- ዕንባቆም
ዘመን :- በ7ኛው መቶ ዓ.ዓ.
ርዕስ :- ከጥርጣሬ ወደ እምነት
ቁልፍ ጥቅስ :- ዕንባ. 1÷3፣ 2÷2፣ 4÷20፣ 3÷2
ቁልፍ ቃላት :- ለምን? ወዮ!

### ዓላማዎቹ

1. ነቢዩ ዕንባቆም ወገኖቹ ካጠፉት ጥፋትና ግፍ የተነሳ ተረብሾ ጌታን መጠየቁን ማሳየት
2. ጌታ ለዕንባቆም የሰጠውን ጥያቄ መልሶች መግለጽ
3. «ጻድቅ በእምነት በሕይወት እንደሚኖር» መግለጽ፡፡

### አስተዋጽኦ

I. በባቢሎናውያን በኩል በይሁዳ ላይ የሚመጣ ፍርድ (ምዕ. 1)
II.. በባቢሎናውያን ላይ ስለሚመጣው ፍርድ መነገሩ (ምዕ. 2)
III. የዕንባቆም ጸሎት በመዝሙር (ምዕ. 3)

### ጸሐፊው

የስሙ ትርጉም ዕንባቆም ማለት «የሚያቅፍ» ማለት ነው፡፡
በጌታ ነቢይ ሆኖ የተጠራ ሲሆን፣

ነቢይነቱም ለይሁዳ ነበረ (ናሆ. 1÷1)፡፡ እስራኤል (የሰሜኑ መንግሥት) በአሦራውያን ተማርካ ተወስዳ ነበር (ዕንባ. 1÷6)፡፡ ባቢሎን ይሁዳን ለመውረር በመዛት ላይ ነበረች (በይሁዳ ከተናገሩት ነቢያት ዕንባቆም አንዱ ሲሆን እርሱም የመጨረሻው የይሁዳ ነቢይ እንደነበረ ይነገርለታል፡፡ ትንቢቱን የተናገረው ከ621-609 ዓ.ዓ. ወይም ከ609-598 ዓ.ዓ. እንደነበረ ይነገራል (2ኛ ነገ. 23÷1-24÷20፤ 2ኛ ዜና 36÷1-10)፡፡



### ዕንባቆም ያገለገለበት ዘመን

ከኢየሩሳሌም ውድቀት አስቀድሞ በንጉሥ ኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት ያገለገለ ይመስላል (ዕንባ. 1÷5-6)፡፡ በዘመኑ ባቢሎናውያን የገነኑ ነበሩ (ዕንባ. 1÷5-13)፡፡ በነቢዩ ዘመን በይሁዳ ሕዝብ መካከል የነበረው ግፍና በደል፣ በጌታ ፊት እንዲከራከር አደረገው (ዕንባ. 1÷1፣ 3÷1)፡፡ ዕንባቆም የጸለየው ጸሎት ስለእግዚአብሔር ሕግና ፍትሕ አሳቢ መሆኑን ያመለክታል (ዕንባ. 1÷3-4፣ 13)፡፡ ስለእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ባሕርይ እምነት ነበረው (ዕንባ. 1÷12-14)፡፡ የቤተ መቅደስ እምልኮ ልምምድ አልፏል (ዕንባ. 3÷1-19)፡፡ ዕንባቆም ምናልባት ከሌዋውያን ወገን ሳይሆን አይቀርም፣ በመቅደስ በመዝሙር አገልግሎአል (2ኛ ዜና 25÷1-8)፡፡ ዕንባቆም የይሁዳ ፖለቲካ መሪዎች በሕዝቡ ላይ ያደረሱት ግፍ እጅግ ቆጭቶት በጌታ ፊት ተከራክሮአል፣ አልቅሶአል፤ የወዮታ አሳቡን በጸሎት መዝሙር በጽሑፍ ለሕዝቡ አቅርቦአል (ዕንባ. 3÷1-19)፡፡

ይህ ነቢይ ለአገልግሎት የጠራውን ጌታ ያውቀዋል፣ በታማኝነት ያመልከዋል ያገለግለዋል፡፡ ከዚህም ጋር በእምነት ይጸልያል፣ ከጌታም መልስ ተጠባብቆ ያገኛል፡፡ በሁኔታዎች መበሳሸት የተረበሸ ቢመስልም ልቡ በአምላኩ ላይ የተደገፈ አገልጋይ ነበር፡፡

### የመጽሐፉ ጠቅላላ ገጽታ

ነቢዩ በምዕ. 1 ያቀረበው የመጀመሪያ ጥያቄ፤ «እግዚአብሔር ለምን በግፈኞች አይሁዶች ላይ ፍርዱን አያመጣም?» በማለት ይጠይቃል (ዕንባ. 1÷1-4)፡፡ ጌታም ባቢሎናውያንን በይሁዳ ሕዝብ ላይ በማምጣት እንደሚቀጣቸው ተናገረ (ዕንባ. 1÷5-11)፡፡ «ከለዳውያን» በኋላ ባቢሎናውያን ተብለዋል፡፡

የዕንባቆም ሁለተኛ ጥያቄ፤ «ኃጢአተኛው ለምን ጻድቁን ይቀጣል?» (ዕንባ. 1÷12-2÷1) እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ለመቅጣት ባቢሎናውያንን የመጠቀሙ ምሥጢር አልገባውም፡፡ ጌታ ግን ምሥጢሩን ያውቃል፣ የአሠራር ሥልጣኑ የእርሱ ነው፡፡

በምዕራፍ 2 ጌታ በባቢሎናውያን ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል፡፡ ጻድቃን ቅሬታዎች በሕይወት ለመኖር በእምነታቸው ጸንተው መኖር ነበረባቸው «ጻድቅ በዕምነቱ በሕይወት ይኖራል» (ዕንባ. 2÷1-5፣ ዘካ. 2÷4-5)፡፡ የዓለምን ሁኔታ ሁሉ የሚቆጣጠር አምላክ በላይ በሰማይ ይኖራል (ዕንባ. 2÷20)፡፡ ይህም ለነቢዩ ጥያቄ አስደናቂ የሆነ ምላሽ ነበር፡፡

**በምዕራፍ 3** ዕንባቆም ጸሎቱን በመዝሙር ያቀርባል፡፡ እግዚአብሔር ፍርዱን ሲያመጣ ምሕረት እንደሚደረግ ይለምናል (3÷1-2)፡፡ በመጀመሪያ ጌታን ስላየው ራዕይ ያመሰግነዋል (ዕንባ. 3÷1-2)፡፡ ጌታ ተዋጊና ፈራጅ ሆኖ ይመጣል እስ

(ዕንባ. 3÷3-15፤ ዘዳግ. 33÷2፤ ኢሳ. 63÷1-6፣ ራዕ. 6÷1-19÷16)። በመጨረሻም ነቢዩ በጌታ ደስ መሰኘቱን በመዝሙሩ ገለጸ (ዕንባ. 3÷16-19)።

### ስነ መለኮታዊ መልእክት

ጌታን እግዚአብሔር በእምነት፣ በእምልኮና በጸሎት ማወቅ አስፈላጊ ነው። ዕንባቆም ለዚህ ሕይወቱን ሰጥቶአል። በመሆኑም የአገልግሎትን ጌታ ዐውቆ በታማኝነት አገልግሎአል። ከእኛም የሚፈለገው ይኸው ነው። ያለንባት ዓለም በግፍና በደል የተሞላች ብትሆንም፣ ጌታ ከቤቱ ጀምሮ ኃጢአኞችን ይቀጣል፣ ዝም ብሎ አያልፍም (1ኛ ጴጥ. 4÷17-18)። ጻድቅ ሰው በሕይወት መኖር የሚችለው በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት ጸንቶ በመኖሩ ነው (ዕንባ. 2÷4፤ ሮሜ 1÷17፤ ገላ. 3÷11)። የጌታ ልጆች፣ በእምነታቸው ጸንተው ስለሚሆነው የውስጥና የውጭ ሁኔታ የጌታን ፊት በጸሎት ቢፈልጉ እርሱ በፈቀደ ጊዜ፣ በፈለገው ዓይነት መልሱን ይሰጣል (ዕንባ. 2÷2-3፣ ዕንባ. 3÷1-2)። እግዚአብሔርን ተማምኖ መጠበቅ ደስታን ያመጣል (ዕንባ. 3)። ክርስቲያን በመከራ ሲያልፍ እምላኩን በትዕግሥት መጠበቅ አለበት (ዕንባ. 3÷16-19)

<u>የዕንባቆም መጽሐፍ ሥዕላዊ መግለጫ (ንድፍ)</u>

| | | |
|---|---|---|
| በባቢሎናውያን በኩል፣ በይሁዳ ላይ የሚመጣ ፍርድ<br>ምዕ.1 | ስለሚመጣው ፍርድ መነገሩ<br>ምዕ. 2 | ምሕረት እንደሚደረግ በመዝሙር መጸለይ<br>ምዕ. 3 |

### ማጠቃለያ

የነቢዩ ዕንባቆም ሸክም ቀላል አልነበረም። የይሁዳ መሪዎችን ግፍ አይቶ ጌታን ጠየቀ። ጌታም መልስ ሲሰጠው ከለዳውያንን (ባቢሎናውያንን) በማምጣት እንደሚቀጣቸው ነገረው (ምዕ. 1)። ይሁዳን የሚያስጨንቁ ባቢሎናውያንንም ደግሞ ጌታ እንደሚፈርድባቸው ተናገረ (ምዕ. 2)። ዕንባቆም እግዚአብሔር በሁሉን ላይ ሆኖ ሁሉን እንደሚቆጣጠር፣ ኃጢአተኞችንም እንደሚቀጣ ተገነዘበ። ፍርዱን የሚያመጣ አምላክ በዘመናት መካከል የወደደውን ሲያደርግ ምሕረቱን እንዲያደርግ በመዝሙር መልክ በጸሎት አቀረበ። በእምላኩ ላይ እምነቱን በማጽናት ጌታ በሚሠራው ሥራ ሁሉ ጻድቅና እውነተኛ መሆኑን በመረዳት በደስታና በተስፋ ተሞላ (ምዕ. 3)።

ይህ መጽሐፍና የነቢዩ ሕይወት ለዛሬ ቤተክርስቲያንና አገልጋይ በዓለም ላለው እንቅስቃሴ የበላይ ተቆጣጣሪ አምላክ እንዳለ ያሳውቃል። እርሱም አዋቂ ፍርዱም እውነተኛ ነው። እንደ ዕንባቆም በጸሎትና በእምነት ጌታን መፈለግ ይኖርብናል።



# ትንቢተ ሶፎንያስ

## «ታላቁ የእግዚአብሔር ቁጣ ቀን ሳይደርስባችሁ... እግዚአብሔርን ፈልጉ፤ ጽድቅን ፈልጉ»

**ጸሐፊው** :- ሶፎንያስ (1÷1)

**የተጻፈበት ዘመን** :- ወደ 7ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ገደማ

**ርዕስ** :- የእግዚአብሔር ቀን መቅረብ (1÷7፣ 1÷14)

**ቁልፍ ጥቅሶች** :- 1÷15፤ 2÷3)

**ቁልፍ ቃላት** :- ሰው የማይኖርበት፣ የጌታ ቀን፣ በመሐከል

**የመከፈቻ ክፍሎች** :- ፍርድ (1÷14-18) መመለስ (3÷14-17)

### ዋና ዓላማዎቹ

1. በኃጢአቷ ምክንያት በይሁዳ ላይ ፍርድ እንደሚመጣ መነገሩና «ታላቁ የጌታ ቀን»
2. በመጨረሻው ዘመን በአይሁዶች ላይ የሚመጣውን ፍርድ
3. በአሕዛብ ላይ በመጨረሻው ዘመን የሚመጣውን ፍርድ መናገር ናቸው

### አስተዋጽኦ

**I. የጌታ ቀን መቅረብ (ምዕ 1)**
- **ሀ. መግቢያ፣ ፍርዱ ዓለም አቀፋዊነት (ቁ. 1-3)**
- **ለ. ፍርዱ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ማተኮሩ (ቁ. 4-13)**
- **ሐ. ከጌታ ቁጣ ቀን ማምለጥ እንደሚቻል (ቁ. 14-18)**

**II.. የእግዚአብሔር ፍርድ በአሕዛብ አገሮች (ምዕ. 2)**
- **ሀ. ንስሐ እንዲገቡ መጥራት (ቁ. 1-3)**
- **ለ. በፍልስጥኤማውያን (ቁ. 4-7)**
- **ሐ. በሞአብና በአሞን (8-11)**
- **መ. በኢትዮጵያውያን (ቁ. 12)**
- **ሠ. በአሦራውያን (ቁ.13-15)**

III በይሁዳ ላይ የሚመጣው ፍርድና የቅሬታው መዳን (ምዕ. 3)

ሀ. በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጣው ፍርድ (ቁ. 1-5)
ለ. ኢየሩሳሌም ንስሐ ለመግባት እምቢ ማለቷ (ቁ. 6-8)
ሐ. የቅሬታው መዳን፣ መጪው የበረከት ዘመን (ቁ. 9-20)
ንስሐ የመግባት ተስፋ (ቁ. 9-13)
የመመለስ ተስፋ (ቁ. 14-20)

## ሶፎንያስ

የስሙ ትርጉም፡- ሶፎንያስ ማለት በእግዚአብሔር የተጠበቀ፣ የተሰወረ ማለት ነው። ከይሁዳ ነገሥታት ዘር ሐረግ የሆነ አገልጋይ ነበር (1÷1)። ምክንያቱም የኖረውም በኢየሩሳሌም ከተማ እንደነበረ ይገመታል (1÷10-11) እነዚህን ቦታዎች እውቆ መጥቀሱ እንድንገምት ያደርጋል።

እንደ ኤርምያስ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት በ648 ዓ.ዓ. ገደማ በይሁዳ ተወለደ (2ኛ ነገ. 22÷1፣ ዕብ. 11÷37) ንጉሥ ሕዝቅያስ ለሶፎንያስ ቅድመ አያቱ ነው። አገልግሎቱን ከኤርምያስና ናሆም ቀደም ሲል ጀምሮ ይሆናል።

### የአገልግሎቱ ዘመንና የማሕበራዊ ኑሮው ሁኔታ

ታሪካዊ አቀማመጡ በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ዘመን ስብከት ሰበከ (ሶፎ. 1÷1)። የበዓል አምልኮና የጣዖታት አምልኮ በየኮረብታው ይደረግ ነበር (ሶፎ. 1÷4-5)። የሶፎንያስ ስብከት ንጉሥ ኢዮስያስ ላደረገው መነቃቃት ትልቅ አስተዋጽ አድርጉአል (2ኛ ዜና 34-35፡ 2 ነገ. 22-23)። የሶፎንያስና የኢዮስያስን ታሪካዊ አቀማመጥ የሚሳይ ሠንጠረዥ እንደሚከተሰው ቀርቧል።

| | |
|---|---|
| 640 ዓ.ዓ. | ኢይስያስ በይሁዳ ነገሠ |
| 632 ዓ.ዓ. | ኢዮስያስ እግዚአብሔርን ፈለገ |
| 628 ዓ.ዓ. | የኢዮስያስ የመጀመሪያ ተሃድሶ (መነቃቃት) 1÷4-5 ጣዖታትን ማፍረስ |
| 625 ዓ.ዓ. | የሶፎንያስ አገልግሎት |
| 621 ዓ.ዓ. | የኢዮስያስ ዋናው መታደስ (መነቃቃት) |
| 609 ዓ.ዓ. | የኢዮስያስ መሞት |

### የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታ

ሶፎንያስ ትንቢቱን ከማስተላለፉ በፊት በይሁዳ የፖለቲካ፣ የማሕበራዊ ኑሮና የኃይማኖት ለውጦች ተካሂደዋል። ሁለት ፖለቲካዊ አብዮቶች ተፈራርቀዋል። አንደኛው የምናሴና የልጁ መሞት፣ የይሁዳ ሕዝብ ከበዓልና ከከነዓናውያን ጣዖታት አምልኮ ወደ ጌታ ዘወር እንዲሉ አድርጉአቸዋል (2ኛ ነገ. 21÷1-18፣ 2ኛ ዜና 33÷1-9)፣ ኢዮስያስና ሶፎንያስ ሕዝቡ ወደ ጌታ እንዲመለሱ አደረጉ ማለት



ነው። ሁለተኛው የአሦር ንጉሥ በ627 ዓ.ዓ. አካባቢ ሞተና ኢዮስያስና ይሁዳ ለአሦር ከመገበር ነፃ ወጡ።

4. ነቢዩ ሶፎንያስ የተጫወተው የነቢይነት ሚና
በተለይ ከ633 ዓ.ዓ. እስከ 623 ዓ.ዓ. ድረስ ከፍተኛ አገልግሎተ ሰጥቷል ማለት ይቻላል። ሶፎንያስ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ መጽሐፉን ጽፎት ይሆናል (ሶፎ. 1÷3-6)።

5. ሶፎንያስ ይሁዳ በ586 ዓ.ዓ. እንደምትወድቅና በ536 ዓ.ዓ. እና በኋላ ከባቢሉን ስለሚመለሱበት ሁኔታም ተነበየ።

6. በመሢሑ በኩል ስለሚሆነው ስለመጨረሻው ፍርድም ሶፎንያስ ተናግሮአል።

## የሶፎንያስ መልእክት ይዘት

1. ይሁዳ ጌታን ረስታዋለች (1÷6-12፤ 3፤2)
2. ጌታ ጣዖት አምላኪዎችንና ኃጢአተኞችን ይፈርዳል (1÷4-6፣ 8÷12)
3. ጌታ ቁጣውን ይገልጻል፣ በዚያ ቀን ማንም አያመልጥም (1÷7፣ 14÷15-17÷18)
4. የእግዚአብሔር ፍርድ ዓለም አቀፋዊ መሆኑ (1÷18፣ 2÷4-15፣ 1÷2-3)
5. እግዚአብሔር ሁሉን የሚያስተዳድር የበላይ መሆኑ (2÷11፣ 3÷10÷9)።
6. ለእግዚአብሔር ቅሬታዎች ኖረው መዳናቸውን ያስረዳል (ምዕ. 3÷11-20)።

## ስነ መለኮታዊ መልእክት

- የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጌታ ተስፋ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የማስጠንቀቂያ መልእክትም ያስፈልገዋል።
- ከእግዚአብሔር መደበቅና የትም ማምለጥ አይቻልም። እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ መፈለግ አስፈላጊ ነው። ጌታ ፍርዱን የሚያመጣ ቢሆንም ንስሐ ስንገባ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ምሕረት ያደርግልንና በረከቱን ያፈስሳል።

## የሶፎንያስ መጽሐፍ ንድፍ

| የጌታ ቀን መቅረብ፣ ፍርድ በይሁዳ ላይ ምዕ. 1 | በአሕዛብ አገሮች ላይ የጌታ ፍርድ እንደሚመጣ መነገሩ ምዕ. 2 | ፍርድ በይሁዳ ላይ፣ የቅሬታው መዳን፣ መጪው የበረከት ዘመን ምዕ.3 |
|---|---|---|

### ማጠቃለያ

ነቢዩ ሶፎንያስ በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚመጣው የፍርድ ቀን መወሰኑን ተናግሯል። ምክንያቱም ሕዝቡ ጌታን ትቶና ረስቶ በእሊምንና ሌሎችን ጣዖታት በማምለኩ ነው (ምዕ. 1)። የአሕዛብ አገሮችም ንስሐ ካልገቡ ፍርድ እንደሚመጣባቸው ተንብዮአል (ምዕ. 2)። በመጨረሻም አይሁዶች ኃጢአት መሥራታቸውን ከቀጠሉ ፍርድ፤ ንስሐ ከገቡ ደግሞ የሕይወት መታደስና በረከት እንደሚመጣ በመናገር ትንቢቱን አጠቃልሎአል (ምዕ. 3)። ይህ ሁሉ ለቤተክርስቲያን ትልቅ ትምህርት ነው። ኃጢአት ፍርድን ያስከትላል፤ በንስሐ ወደ ጌታ መመለስ ግን በረከትንና የሕይወት መታደስን ያመጣል።



# ከምርኮ በኋላ የተናገሩ ነቢያት

## (ሐጌ፤ ዘካርያስና ሚልክያስ)

እነዚህ ትንቢታዊ መልእክቶቻቸውን በጽሑፍ ያሰፈሩት ከባቢሎን ምርኮ መልስ ነው። ከብሉይ ኪዳን የእስራኤል ነቢያት የመጨረሻዎቹም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ናቸው።

## ትንቢተ ሐጌ

## «ለየትኛው ነገር ቅድሚያ ትሰጣላችሁ?»

**ጸሐፊው** :- ነቢዩ ሐጌ
**ዘመን** :- ወደ 6ኛው መቶ ዓ.ዓ.
**ርዕስ** :- ቤተ መቅደሱን እንደገና መገንባት
**ቁልፍ ጥቅስ** :- 1÷14-15፤ 2÷4-5
**ቁልፍ ሐረጎች** :-

«የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ መጣ»
«ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር »
«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» (19 ጊዜ ተጠቅሶአል)።

### ዓላማዎቹ

የእግዚአብሔርን ቃል በመዘንጋት ቸልተኛ የሆነውን ሕዝብ በቃሉ ማነሳሳት (መቀስቀስ)፤ የቆመውን የቤተመቅደስ ግንባታ ሥራ እንዲሠሩ ማሳሰብ (ዕዝ. 5÷1-2)፤ ጌታ ቤተመቅደሱን በክብር እንደሚሞላው የተስፋ መልእክት ማስተላለፍ (ሐጌ 2÷1-9)፤ የረከሰው ሰው እንደሚነጻና እንደሚባረክ መልእክት ማስተላለፍና ለዘሩባቤል የተሰጠ ተስፋ፤ በክርስቶስ በኩል ስለሚሆነው በረከት መናገር ናቸው (ሐጌ 2÷20-23)።

### አስተዋጽኦ

I. ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ቀዳሚውን ቦታ (ቅድሚያ) እንዲሰጡ ማሳሰብ (1÷1-2፤ 9)

   ሀ. የራሳችሁን ወይስ የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ይኖርባችኋል? (1÷1-15)

ሰ. ምናምን የሆነውን (ትንሽ አነስተኛ፣ የተናቀውን) ቤተመቅደስ መሥራት ይኖርባችኋልን? (2÷1-9)

II ለቅድስና ቅድሚያ እንዲሰጡ ማሳሰብ (2÷10-19)

III. ለዳዊት ለተሰጠው ተስፋ ቅድሚያ መስጠት (2÷20-23)

## ጸሐፊው

ስለ ጸሐፊው ሐጌ የምናውቀው ነገር በጣም ትንሽ ነው (ዕዝ. 5÷1፣ 6÷14)። የስሙ ትርጉም፡- «በዓል» ወይም «የበዓል አከባበር» ማለት ነው። የተወለደው በምርኮ አገር በባቢሎን እንደነበር ይታሰባል።

ከዘሩባቤል ጋር መጀመሪያ ከባቢሎን በ536 ዓ.ዓ. ወደ ኢየሩሳሌም ሄዷል (ዕዝ. 2÷2)።

አገልግሎቱን አስመልክቶ የቃሉን መልዕክት አስተላልፎ ወዲያውኑ ጥሩ ምላሽ ያገኘ ነቢይ ቢኖር ሐጌ ነው (ምዕ. 1)። ዋና ስብከቱ ያተኮረው የቤተ መቅደሱ ግንባታ ሥራ እንዲጠናቀቅ ሕዝቡን በማነሳሳት ላይ ነበር። ሐጌና ዘካርያስ በነቢይነት አገልግሎታቸው ጓደኛሞች ነበሩ (ዕዝ. 5÷1፣ 6÷14፤ ማር. 6÷7)።

## ታሪካዊ አቀማመጥ

**586 ዓ.ዓ.** ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስዋም በባቢሎን ወራሪዎች ፈረሰች

**539 ዓ.ዓ.** ቂሮስ፥ ይገዛው የነበረ የፋርስ መንግሥት ኃያል መንግሥት ስለነበር። የባቢሎን መንግሥት ወደቀ።

**538 ዓ.ዓ.** እግዚአብሔር ቂሮስ አይሁዶችን ወደገዛ ምድራቸው እንዲመለሱ እንዲፈቅድ ቀሰቀሰው (ዕዝራ 1÷1-4)።

**536 ዓ.ዓ.** በዘሩባቤል አማካይነት አይሁዶች ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ይሁዳ ምድር ማለትም ወደ አገራቸው ተመለሱ (ዕዝ. 1÷5-2፤70፤ ነህ. 12)። የተመለሱት ሕዝብ ቁጥር 50000 ነበር (ዕዝ. 2÷64-67)።

**536-535 ዓ.ዓ.**

1. የቤተ መቅደሱ ሥራ በዘሩባቤል ተጀመረ



2. የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ በኢየሩሳሌም፣ በቤተመቅደሱ አንጻር ተሠራ። የማደሪያ ድንኳን በዓል ተከበረ። መሥዋዕቶችም ቀረቡ (ዕዝ. 3÷1-6)።

**535-534 ዓ.ዓ.** :- በዙሪያ በነበሩ ሳምራውያን የቤተመቅደሱ ግንባታ ሥራ ተቃውሞ ደረሰበት (ዕዝ. 4÷1-5)

**534 ዓ.ዓ.** - የቤተ መቅደሱ ሥራ ቆመ (ዕዝ. 4÷24)

**536 ዓ.ዓ.** - ዘሩባቤል የፋርስን ንጉሥ በመወከል፣ የእስራኤል ገዥ ሆኗል። ሊቀ ካህኑ ኢያሱ የሃይማኖታቸው መሪ ሆነ።

**520 ዓ.ዓ.** - ሐጌና ዘካርስያስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ለነበሩት አይሁዶች፣ በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢታዊ መልእክት አስተላልፈዋል (ዕዝ. 5÷1፤ ሐጌ 1÷1)።

**516 ዓ.ዓ.** - የቤተ መቅደሱ ግንባታ ሥራ ተጠናቀቀ (ዕዝ. 6÷14-15)።

**458 ዓ.ዓ.** - ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ የእግዚብሔርን ሕግ በማንበብ ለተሃድሶ ጌታ ተጠቀመበት።

**445 ዓ.ዓ.** - የፋርሱ ንጉሥ፣ ነህምያ ሄዶ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሥራ እንዲሠራ ፈቀደለት (ነህምያ 6÷15)፣ ሥራውም በ52 ቀናት ውስጥ ተጠናቀቀ።

## የቤተ መቅደስ አስፈላጊነት

ቤተ መቅደሱ ለሁለት ነገሮች አስፈላጊ ነበር። ይኸውም ጌታ በእነርሱ መካከል ስለሆነና ሕዝቡም እርሱን ማምለክ ስላለበት፣ና በቃሉ ማዕድ ዙሪያ ሕዝቡን ለማሰባሰብ፣ ሕዝቡም ባዳናቸው ጌታ እንዲደሰቱ ለማድረግ (ኢዩ. 3÷21፣ ዘዳ. 25÷8፤ የሐዋ. 7÷47-48፣ ኢሳ. 66÷1-2)።

## የስነመለኮታዊ መልእክቶች

እግዚአብሔር የሠራዊት ሁሉ ጌታ (1÷2፤ 7፣ 9፣ 14÷ 2÷6-9፣ 11፣ 23)፤ ትዕዛዝ ሰጪ፤ የሁሉም የበላይ ኃላፊ እርሱ ነውና (1÷2፣ 3፡ 2÷10-14)። እግዚአብሔር የኢኮኖሚ ገቢ ምንጭ ሁሉ የሚወስንና የሚቆጣጠር ጌታ ነው (1÷5-11)። እግዚአብሔር የምንደገፍበት ታማኝ አምላክ ነው (2፤5)።

እግዚአብሔር ሕዝቡን መባረክ ደስ ይሰኛል (ሐጌ 2፥10-19)። ለዘሩባቤል ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ ሰው የሚጠነቀቅ ጌታ ነው (2፥20-23)። ስለዚህም ሐጌ ከእኛ ፍላጐት ይልቅ ለእርሱ ፍላጐት ቀዳሚውን ሥፍራ መስጠት ይገባናል (ማቴ. 6፥33)።

ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ላይ ስንደርስ፣ ቀና ብለን ጌታን ማየት አለብን፤፤ እርሱ መታደስንና መከናወንን ያመጣልናል፤ ደግሞም ሁኔታዎችን ሁሉ ይቆጣጠራል።

## ስነ መለኮታዊ መልእክት

የእግዚአብሔርን ሥራ ቸል ልንል አይገባም፣ በሕይወትንና እኛ ባለን ነገር ላይ እርሱ ጌታ እንዲሆን እንፍቀድለት (1፥4)። መከናወን እንዲመጣ ለጌታ ቀዳሚውን ሥፍራ በመስጠት ጌታን በመፍራት እንኑር (ቁ፥5፣ 7)።

የገቢ ሁሉ ምንጩ (የብርና የወርቁ) ባለቤት እግዚአብሔር ነው (2፥8)። የእግዚአብሔር ሥራ ወደፊት የከበረ ይሆናል (2፥9)። ሰዎች በጌታ ተገስጸውም አለመመለሳቸው ጉዳትን ያመጣል (2፥17)። እግዚአብሔር ተስፋን የሚሰጥ የፍቅር አምላክ ነው (2፥19)።

### የሐጌ መጽሐፍ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| ለቤተ መቅደሱ ግንባታ ሥራ ቅድሚያ ስጡ<br>ምዕ. 1፥1-2፥9 | ለቅድስና ቅድሚያ ስጡ<br>ምዕ. 2፥10-19 | ለዳዊት ለለተጠሰው ተስፋ ቅድሚያ ስጡ<br>ምዕ. 2፥20-23 |

### ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በጊዜው ሐጌን ለሕዝቡ አስነስቶት የተጠቀመበት አገልጋይ ነው። አስደናቂ የሆኑ አራት መልእክቶችን አቅርቧል። በመጀመሪያው ስብከት፣ ሕዝቡ ተነስቶ በጅምር የቀረውን ቤተመቅደስ እንዲሠሩ ጠራቸው (ሐጌ 1፥1-11)። በሁለተኛው ስብከት የወደፊቱ ቤተመቀደስ በክብር እምንደሚሞላ በማጽናናት ተናገረ (ሐጌ 1፥12-15)። በሦስተኛው መልእክት፣ የረከሰው ሕዝብ ነጽቶ (ተቀድሶ) እንደሚባረኩ ተናገረ (ሐጌ 2፥10-19)። በአራተኛው መልእክቱ፣ ለዘሩባቤል የተሰጠውን ተስፋ አስተላለፈ (ሐጌ 2፥20-23)። ከላይ እንደተመለከትነው የሐጌ መጽሐፍ ለዛሬዋ ቤተክርስቲያን የሚሆኑ መልእክቶችን ይዟል።



# ትንቢተ ዘካርያስ

## «የእግዚአብሔር ዓላማ ምን ይሆን?»

**ጸሐፊው** - ዘካርያስ (ከምዕ. 1-8)፣ እንደዚሁም ሌላ ስሙ ያልተጠቀሰ ሰው (ከምዕ.9-14) እንደጻፈው ይታሰባል።

**ዘመን** - (520-518) ዓ.ዓ.

**አርዕስት** - የመሢሑ መምጣት (መገለጦች)

**ቁልፍ ጥቅስ** - 8፥3፤ 14፥9

**ቁልፍ ቃላት** - ቅርንጫፍ (ቁጥቋጦ)፤ ቅናት፤ ንጉሥ፤ እረኛ፤ ኢየሩሳሌም፤ አይቻለሁ፣ የሠራዊት ጌታ (52 ጊዜ)

### ዋና ዓላማዎቹ

1. እስራኤላውን ወደጌታ እንዲመለሱ መምከር (1፥3-4)፣
2. ስለቤተ መቅደሱ ግንባታ ሕዝቡን ማጽናናትና
3. ወደፊት በመሢሑ በኩል የሚመጡትን ተስፋና በረከት ለቅሬታዎቹ ማስታወቅ ነው።

### አስተዋጽኦ

I. ስምንት የማጽናናት ራዕዮች (ምዕ. 1-6)

II. አራት የተግሳጽ ራዕዮች (ምዕ. 7-8)

ሀ. የተግሳጽ መልእክት (ምዕ. 7)
ለ. የተስፋ መልዕክትት (ምዕ.8)

III. ሁለት የእግዚአብሔር ቃል ሸክሞች (ምዕ. 9-14)

ሀ. የመጀመሪያው ሸክም (9፥1-11፥17)
ለ. ሁለተኛው ሸክም (12፥1-14፥21)

### ጸሐፊው

1. የስሙ ትርጉም፡- ዘካርያስ ማለት «እግዚአብሔር ያስታውሳል» ማለት ነው።
2. ቤተሰብ፡- አባቱ ካህን በራክዩ ትርጉም «እግዚአብሔር ይባርካል» ማለት ነው። እያቱ፡- ካህን አዶ «የተወሰነው ጊዜ» ማለት ነው (ዘካ. 1፥1)። ቤተሰቦቹ ከዘሩባቤል ጋር በ536 ዓ.ዓ. ከባቢሎን ተመልሰዋል (ነህ 12፥4፥ 16)፣ ያኔ ዘካርያስ ገና ወጣት ነበረ። ትንቢት መናገር

የጀመረው በ520 ዓ.ዓ. ነበር፣ ይህም አገልግሎት የጀመረበት ጊዜ መሆኑ ነው።

**የዘካርያስ ዘመን ታሪካዊ አቀማመጥ**

**586 ዓ.ዓ. -** የኢየሩሳሌም መውደቅ
(ሕዝቡ በምርኮ ተወሰደ)

**539 ዓ.ዓ. -** የቂሮስ አዋጅ (አይሁዶች ወደአገራቸው እንዲመለሱ)

**536 ዓ.ዓ. -** የቤተመቅደሱ ሥራ ቆመ (ተጓጐለ)

**ዘካርያስ 1-6 - 520 ዓ.ዓ. -** የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጀመረ

**ዘካርስያስ 7-8 - 518 ዓ.ዓ.**

**516 ዓ.ዓ. -** የቤተመቅደሱ ሥራ ተፈጸመ

ዘካርያስ 9-14

**3. አገልግሎቱ**

በ520 ዓ.ዓ. አገልግሎት መጀመር ከሐጌ ጋር በመሆን ሕዝቡን የቤተ መቅድሱን ግንባታ ሥራ እንዲቀጥሉ አጽናንቶአቸዋል (ዕዝ. 6÷14-15)። ዘካርያስ ካህንም ነቢይም ነበር። ሐጌና ዘካርያስ ከምርኮው አገር የተመለሱትን 50000 ሰዎች ያጽናኗቸው ነበር።

**የአገልግሎቱ ዓላማዎች**

1. መንፈሳዊ ተሃድሶ እንዲመጣ ሕዝቡን ማነሳሳት (1÷2-3)
2. ሕዝቡ የመቅደሱን ሥራ እንዲጨርሱ ማበረታታት (1÷16፤ 4÷9)
3. በመከራ የነበረውን ሕዝብ መምከር/ማጽናናት
4. ስለሚመጣው መሢሕ የተነገረውን ትንቢት በመለኮታዊ ጽሑፍ ማስፈር ነበር።



ከኢሳይያስ ቀጥሎ ስለክርስቶስ አብዝቶ የተናገረ ነቢይ ቢኖር፣ ዘካርያስ ነው።

| ስለክርስቶስ የተነገረ ትንቢት | ፍጻሜው |
|---|---|
| ሱሌ (ባሪያ) 3÷8 | ማር 10÷45 |
| ቅርንጫፍ 3÷8፤ 6÷12 | ሉቃ. 1÷78 |
| ንጉሥ ካህን 6÷13 | ዕብ. 6÷20-7÷1 |
| ትሑት ንጉሥ 9÷9-10 | ማቴ. 21÷4-5፤ ዮሐ. 12÷14-16 |
| መሸጡ 11÷12÷ 13 | ዩሐ. 27÷9 |
| እጆቹን ተወጋ 12÷10 | ዮሐ. 19፣37 |
| የሚያነጻ ምንጭ 13÷1 | ራዕይ 1÷5 |
| ሰብዓዊ፣ መለኮታዊ 13÷7፤ 6÷12 | ዮሐ. 8÷40፤ 1÷1 ማቴ. 26÷31፤ ማር. 14÷27 |
| የተመታ እረኛ 13÷9 | ዮሐ. 10÷16፤ 11÷15፤ 21÷27 |
| ዳግም ምጽአቱ 14÷9 | |

***ለምዕራፎቹ የተሰጡ ማብራሪያዎች***

*ስምንት የማጽናት ራዕዩች (ምዕ. 1-6 )*

ይህ ክፍል ወደ ኢየሩሳሌም ከምርኮ አገር ስተመለሱት የሚሆን መልእክት ያቀርባል። ወደአገራቸው የተመለሱ ቢሆንም ሐዘን ውስጥ ስለነበሩ የሚያጽናና መልእክትት ስላስፈለጋቸው ጌታ አጽናንቶአቸዋል።

1. የመግቢያ ቃላት ለንስሐ መጥራት፣ ይህም የመጀመሪያው መልእክት ነው (ዘካ. 1÷6)።
2. የመጀመሪያው ራዕይ (ፈረሶቹ) 1÷7-17) ይህ ደግሞ ሁለተኛው መልእክት ነው። ዋናው መልእክትት «የቤተመቅደሱ ሥራ ተሠርቶ ይጠናቀቃል» የሚል ቢሆን፣ ሕዝቡ በንስሐ ወደጌታ ተመልሶ ጌታም ከእነርሱ ጋር ሆኖ እንደሚያጽናናቸው ሙሉ ተስፋ ይሰጣል (ዘካ. 1÷1-17)። በቁ. 11 «የእግዚአብሔር መልአክ» የተባለው በምሥጢር በመልአክ መልክ የተገለጸው መሢሕ (ክርስቶስ) ነው።
3. ሁለተኛው ራዕይ፡- አራት ቀንዶችና አራት ጠራቢዎች (ዘካ. 1÷18-21)።
   - አራት ቀንዶች፡- የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች (ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ግሪክና ሮም) ናቸው።
   - አራት ጠራቢዎች፡- ቀንዶቹን የሚጥሉና ስለእግዚአብሔር ልጆች የሚዋጉ ኃይላት ናቸው (2ኛ ነገ. 5÷8-23)

4. ሦስተኛው ራዕይ ከተማይቱ (2÷1-13)
   «ከተማይቱ ትገነባለች፣ ትታደሳለች» የሚል የተስፋ ቃል፤ ለዚያ ዘመንና ለወደፊት ጭምር ተነገረ።

5. አራተኛው ራዕይ፡- የካህኑ የኢያሱ መንጻት (3÷1-13)

6. አምስተኛው ራዕይ፡- መቅረዞቹ (4÷1-14)
   - ሁለቱ ዛፎች - የኢያሱና የዘሩባቤል ምሳሌዎች ናቸው።
   - የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። መክናወንን የሚያመጣው እርሱ ነውና። ከወይራው ዘይት ይወጣል፤ ዘይቱ ለብርሃንነት ያገለግላል ዘይቱ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑ ነው (ቁ. 7-9)። የተጀመረው የቤተ መቅደሱ ግንባታ በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ይፈጸማል።

7. ስድስተኛው ራዕይ፡- የመጽሐፍ ጥቅልል ይህ የእግዚአብሔርን ሕግ በሚጥሱ ሰዎች ላይ የሚመጣውን ፍርድ የሚያመላክት ነው (5÷1-4)።

8. ሰባተኛው ራዕይ፡- የኢፍ መስፈሪያ (መስኪያ) (5÷5-11) ጌታ የሕዝቡን በደል ያስወግዳል፣ ክፉት አያሸንፋቸውም።

9. ስምንተኛው ራዕይ፡- አራቱ ሰረገሎች (6÷1-15)
   - በዓለም ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ (ቁ. 1-8)
   - በኢያሱ በኩል የክርስቶስ ሥዕል ይታያል (ቁ. 9-15)
     የተግሳጽ ራዕዮች (ምዕ. 7-8)

   ሀ. የተግሳጽ መልእክት፤ ስለጾም የቀረበ ጥያቄ (ምዕ. 7)
   ለ. የተስፋ መልእክት፤ የኢየሩሳሌም ተስፋ (ምዕ. 8 )

   ከሁለት ዓመት በኋላ የንስሐ ጥሪ እንደገና ተደገመ (ምዕ. 7)፣ ኢየሩሳሌም ወደፊት ብሩህ ተስፋና ክብር ይጠብቃታል (ምዕ. 8÷ 1÷14፣ 16፣ 8÷14-23)። ይህ ሊሆን የሚችለው ከክፉ መንገዳቸው ወደጌታ ተመልሰው ፈቃዱን ሲያደርጉ ነው። የሚጠበቅባቸው እምነትና ለእርሱ መታዘዝ ነው።



## ሁለት የእግዚአብሔር ቃል ሸክሞች (ምዕ. 9-14)

ሀ. የመጀመሪያው ሸክም፡- በደማስቆና በሶርያ ላይ (9÷1-7)

ለ. ጌታ ለሰሕዝቡ ይዋጋል፣ ንጉሣቸውንም ይልክላቸዋል (9÷8-10) ክርስቶስን ይልካል ማለት ነው።

ሐ. የጌታ ሕዝብ በመጨረሻ እንደከበሩ ድንጋዮች ይሆናሉ (ቁ. 11-16)

መ. እንዲጸልዩ የተነገረ ማበረታቻ (ምዕ. 10)

እግዚአብሔር ፀሎትን ሰምቶ የሚመልስ ጌታ ነው።

መንጋው ከተበተነበት እንደገና ተመልሷል። ሕዝቡም መደገፍ ያለበት በጌታ ላይ ነው (ዘካ. 10÷1-2)። የሚያስፈልጋቸውን የሚሞላባቸው፣ የሚራራላቸውና የሚያበረታቸው እርሱ ነውና። መጥፎ መሪዎችን አስወግዶ ታማኝ መሪዎችን ይሰጣቸዋል። የቀሩትንም ወደገዛ ምድራቸው ያመጣቸዋል (10÷10፣ ኢሳ. 11÷11-15)። ትዕቢተኞቹን የውጭ ጨቋኝ መሪዎች አስወግዶ በጌታ መንገድ የሚሄዱትን ያበረታቸዋል (10÷11-11÷3)።

ሠ. አይሁድ መሢሐቸውን አለመቀበላቸው (ምዕ. 11)

እግዚአብሔር መንጋውን ያጠፉትን መጥፎ የፖለቲካ መሪዎች ይቀጣቸዋል (11÷3-17) ዘካርያስ ይህን የመልካሙን እረኛ ምሳሌያዊ ሚና በመጫወት በጌታ ሕዝብ መካከል አንድነት ለመጠበቅ ሞከሯል (ሕዝ. 37÷15-23)። ሕዝቡ ይህን መልካም ንጉሥ እምቢ ብለው መጥፎውን መሪ ተከተሉ (ዘካ. 11÷3-17)። መልካሙ እረኛ ሌላ ምንም ማድረግ አልቻለም፣ ከዚህ የተነሳ አንድነታቸው ጠፍቶአል (ዘካ. 11÷10-14)። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር የሚልክላቸውን ገዥ (ንጉሥ) እምቢ እንዳይሉ ለማስጠንቀቅ የተነገረ ነው። ወደ ወጉት (ወደ ክርስቶስ) በመመልከት ያለቅሱለታል (ቁ.10-14)።

ሰ. የሕዝቡና የምድሪቱ መንጻት (ምዕ. 13)
- የክርስቶስ ትንቢት፡- በእርሱ በኩል ከኃጢአት መንጻት ይቻላል፣ (ቁ. 1)
- ስለክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ የተነገረ (ቁ. 7)።
- ስለታላቁ የመከራ ዘመንና ስለሃሳዊ መሢሕ የተነገረ ትንቢት (ቁ. 8-9)

ሸ. የመጨረሻው ዘመን፣ ስለሺህ ዓመት መንግሥት መቋቋም የሚናገር ክፍል ነው (ምዕ. 14)።

አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን አመለካከት።

- የታላቁ መከራ ዘመን (ቁ. 1-2)

- ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ጠላቶቹን ያስወግዳል (ቁ.3-8)
- የሺህ ዓመተ መንግሥት ሁኔታ (መግስጫ) (ቁ. 9-11፣ 16-20)
  ይሁዳ ከዓለም መሪዎች ብዙ ጭቆና ደርሶባት ነበር (ዘካ. 12÷1-6፣ 14÷1-3)፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያድን ይገለጣል (ዘካ. 14÷3-5፤ 12-15):: በዓለም ላይ አዲስ ሥርዓት ይመሠረታል (ዘካ. 14÷6-11 ፤ 15-21)::

## ሦስቱ ዋና ገጸ ባሕርያት

ትንቢቱ በእነዚህ ሦስት ሰዎች ላይ ያተኩራል፦

- ዘካርያስ - የክርስቶስ ምሳሌ የሆነ መልካም እረኛ (ዘካ. 11፣ ማቴ. 26÷15፤ ዘዳ. 21÷32)
- ታላቁ ሊቀካህን ኢያሱ እርሱም የክርስቶስ ምሳሌ ነው (6÷12፤ ኢሳ. 11÷1፤ ኤር. 23÷5፤ 33÷15)::
- ዘሩባቤል ከባቢሎን በ537 ዓ.ዓ. መጀመሪያ ከመጣው ቡድን ጋር የመጣ መሪ:: እርሱም የቤተመቅደሱን ግንባታ ጀምሮ ፈጸመው (ሐጌ 2÷20-23)::

ዘሩባቤል፣ እግዚአብሔር ያስነሳው ንጉሥ ነበረ:: በተጨማሪ ስለነዚህ ሦስት ሰዎች የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመልከት (ዕዝ. 2÷1-2፤ 2÷1-9፣ 4÷1-3፣ ሐጌ. 2÷1-5፣ 20-23፣ ዘካ. 3÷1-10፤ 4÷6-10፤ 6÷9-15፤ 11÷7፤ ማቴ. 1÷12)::

## ስነ መለኮታዊ መልእክቶች

እግዚአብሔር ወደእርሱ በንስሐ ከተመለስን፣ በረከቱን ይዞ ወደእኛ ይመለሳል:: እግዚአብሔር ሕዝቡን በሚደርስበት ነገር ሁሉ ጣልቃ በመግባት ያጽናናል፣ ለክብሩም ማቆም ይፈልጋል::

እግዚአብሔር ሥራውን ሊፈጽም ታማኝ አገልጋዮችን ያነሳና ይጠቀምባቸዋል:: አገልጋዮቹም በታማኝነት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል:: የጌታ ሥራ የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነውና በእርሱ ሙላት ሆነን ማገልገል ይኖርብናል (ዘካ. 4÷6፤ ኤፌ. 5÷18):: እግዚአብሔር ምንጊዜም ቢሆን ለሕዝቡ ያለው እሳቡ መልካም ነው:: በጸጋው ሽፍና ሰዓላማው ማቆም ይፈልጋል:: ክርስቶስ ስለበጉቹ ሲል የተመታ እረኛ ነው (ምዕ. 13÷7-9)::

የትንቢተ ዘካርያስ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| የማጽናናት ራዕዮች ምዕ. 16 | የተግሳጽ ቃላት ምዕ. 7-8 | የእግዚአብሔር ቃል ሸክም ምዕ. 9-14 |

## ማጠቃለያ



በየጊዜው አገልጋዮችን የሚሰጥ ጌታ በዘካርያስ በኩል ሕዝቡን ማጽናናቱን (ዘካ. 1-6) የተግሳጽና የተስፋ መልእክት ሰጥቷል (ዘካ. 7-8):: የእግዚአብሔር ቃል ሸክሞች የእስራኤልን ጠላቶች እንደሚቀጣቸው፣ እስራኤል በንስሐ ወደጌታ ስትመለስ ከጌታ ዘንድ በረከት እንደሚጠብቃት ተናገረ (ዘካ. 9-14) ::

# ትንቢተ ሚልክያስ

## « የምታስብሩት ማንን ነው?» «ሰው እግዚአብሔርን ይሠርቃልን?»

**ጸሐፊው** - ሚልክያስ (1÷1)

**ዘመን** - 433 ዓ.ም. ነህ. 13÷6

**ርዕስ** - በሥነ ምግባር የተበላሸውን ሕዝብ ንስሐ እንዲገቡ ማሳሰብና ስለጌታ ፍርድ ቀን ማስታወቅ

**ቁልፍ ጥቅሶች** - ሚል. 3÷1 ፣ 3÷8

**ቁልፍ ቃላት** - (በየት? ትላላችሁ፣ የጌታ ቀን፣ መልእክተኛ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ)

### ዋና ዓላማዎቹ

የእስራኤልን ኃጢአትና ክህደት ማሳየት ስለሚመጣውም ፍርድ አስጠንቅቋል። ከመሢሑ መምጣት አስቀድሞ ሕዝቡን ለመጥራት ሌላ መልእክተኛ (መጥምቁ ዮሐንስን) እንደሚልክ ተናግሯል። በጌታ ስም የተጠሩ ሕዝቡ ጌታን እንደሚገባ እንዲወዱት፣ እንዲያመልኩት፣ እንዲፈሩትና እንዲያገለግሉት ማሳሰብ።

### አስተዋጽኦ

I. እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ፍቅር (1÷1-5)

II. ወቀሳ በካህናት ላይ (1÷6–2÷9)

III. ወቀሳ በሕዝቡ ላይ (2÷10-16)

IV. ወደፊት ሊመጡ ያሉ ነገሮች (2÷17-3-5)

V. ሕዝቡ በብሔር ደረጃ በጌታ ፊት (3÷6-15)

   ሀ. እግዚአብሔርን መስረቅ (3÷6-9)
   ለ. ለበረከት ቁልፍ (3÷10-12)
   ሐ. በጌታ ላይ በድፍረት መናገር (3÷13-15)



VI. እግዚአብሔርን የሚፈሩ ታማኞች ቅሬታዎች (3÷16-18)

VII. ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን (ምዕ. 4)

### ጸሐፊው

1. **የስሙ ትርጉም፡-** ሚልክያስ ማለትት «መልዕክተኛዬ» ማለት ነው። ምናልባትት ስለነቢዩ ቤተሰብም ሆነ ስለእርሱ በስፋት የምናውቀው ነገር የለም (1÷1)። ከምርኮ መልስ ከተነሱት ነቢያት አንዱ ሲሆን ምናልባት አገልግሎቱ ከ460-450 ዓ.ዓ. ወይም በነህምያ አማካይነት ተሃድሶ ከመደረጉ ከ5ኛው መቶ ዓ.ዓ. በፊት ሊሆን ይችላል። ብዙዎች እንደሚገምቱት በዕዝራና ነህምያ ዘመን በመንፈሳዊ ሕይወቱ የታደሰው ሕዝብ ከቆይታ ብዛት እየደከመ ሄደ። በዚህን ጊዜ ጌታ ሚልክያስን እንዳስነሳው ይታሰባል። እርሱም የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነቢይ ሆኖ ወደ አዲስ ኪዳን የመሸጋገሪያ ድልድይ ነው።

2. ሚልክያስ ይህን መጽሐፍ ለምን ጻፈው?

   ሕዝቡ በጠቅላላ በእምነቱ የቀዘቀዘና በማሕበራዊ ኑሮውም የተበላሸ በመሆኑ ወደ ንስሐ ለመጥራት የተጻፈ ነው። ይህ መጽሐፍ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለውን ቃል ኪዳን በግልጽ ይናገራል። ስለመጥምቁ ዮሐንስና ስለጌታ ኢየሱስ የመጀመሪያው መምጣት ይናገራል (ምዕ. 3÷1-2)። በተጨማሪም ለእግዚአብሔር መታዘዝ የተትረፈረፈ በረከት እንደሚያመጣ ይናገራል (3÷10)።

### የነቢዩ ሚልክያስ ታሪካዊ አቀማመጥ

586 ዓ.ዓ. - የኢየሩሳሌም መውደቅ (የሕዝቡ መማረክ)

539 ዓ.ዓ. - ቂሮስ የምርኮው ዘመን እንዲያበቃ አወጀ

536 ዓ.ዐ. - የቤተ መቅደሱ ሥራ ቆመ

516 ዱ.ዱ. - የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጠናቀቀ

458 ዓ.ዓ. - በዕዝራ አማካይነት የተደረገ ተሃድሶ

445 ዓ.ዓ. - ነህምያ የቅጥሩን ሥራ ፈጸመ

428 ዓ.ዓ. - ነህምያ ለሁለተኛ ጊዜ ኢየሩሳቢምን ጉበኘ

ሚልክያስ - 420 ዓ.ዓ.

## የሚልክያስ መጽሐፍ ዋና መልእክቶች

በጥያቄ መልክ ቀርበው ተብራርተዋል። እነዚህ የሕዝቡንና የካህናትን ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው።

1. እግዚአብሔር እንደሚወዳችሁ ታውቃላችሁ? (1፥1-5)

2. እግዚአብሔርን በእምልክ ታከብሩታላችሁ? (1፥6-2፥9)

3. በምታቀርቡአቸው መስዋዕቶች ታከብሩታላችሁ? (1፥6-14)

4. በጋብቻ ሕይወታችሁ ጌታን ታከብሩታላችሁ? (2፥10-16)

5. በእግዚአብሔር ጽድቅ (ፍትህ) ታምናላችሁ? (2፥17-3፥6)

6. በአስራታችሁ እግዚአብሔርን ታከብሩታላችሁ? (3፥13-4፥3)

7. በአገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን ታከብሩታላችሁ? (3፥13-4፥3)

እነዚህን ጥያቄዎች ካቀረበላቸው በኋላ እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ቅሬታዎች የመጨረሻ ምክር ይሰጣል (4፥4-6)።

## ስነ መለኮታዊ መልእክት

የእግዚአብሔርን ጽኑ ፍቅር እናስታውስ። እርሱ ሁልጊዜም ይወደናል። እርሱ በዓለማችን ላይ ከሚፈራረቁት ሁኔታዎች የተነሳ ለእኛ ያለውን የፍቅር ባሕርዩን አይለውጥም።

በሚልክያስ ዘመን አገልጋዮቹ የሆኑ (ካህናት) ጌታን እጅግ አሳዘኑት። በመሠዊያው ላይ የሚነቀፈውን ነገር በማቅረብ ስሙን አቃልለዋል። ከዚህ የተነሳ የተናቁና የተዋረዱ አደረጋቸው (ሚል. 1፥6-2፥9)። ጌታ ዛሬ በምንኖረው አገልጋዮች ያዘነብን ነገር ይኖር ይሆናል። እራሳችንን በመመርመር ወደእርሱ በንስሐ እንመለስ።

የክርስቲያን ጋብቻ መፋታትን ይቃወማል። ምክንያቱም ጌታ «መፋታትን እጠላለሁ» (ሚል. 2፥10-16፥16) ብሏል።

ለጌታ አገልግሎት መስጠት ያለበትን ለራስ ጥቅም ስንል እሥራት በኩራትን በየቤቶቻችን አናስቀር። ነገር ግን በታማኝነት እንስጥ። ይህን ብናደርግ ጌታ በረከቱን አትረፍርፎ ይሰጠናል (3፥7-12)። እግዚአብሔርን ማገልገል ትልቅ ዋጋ አለውና በፊቱ ሰድፍረት «እርሱን ማገልገል ከንቱ ነው» እንዳንል መጠንቀቅ ይኖርብናል



(3፥13-15)። ሁልጊዜም፣ በየትም ብንሆን እግዚአብሔርን በመውደድና በመፍራት የምንኖር፣ ከሆነ እርሱ ምሕረቱን ያበዛልናል (3፥16-18)። እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ሊያመጣው የወሰነው የፍርድ ቀን እንዳለ በማስታወስ፣ ያልዳኑት ከዚህ ፍርድ መዳን የሚችሉበትን የምሥራች ቃል እናስተላልፍ (ምዕ. 4)።

### የሚልክያስ መጽሐፍ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ፍቅር ምዕ. 1፥1-5 | ወቀሳ በካህናት ላይ ምዕ. 1፥6-2፥9 | ወቀሳ በሕዝቡ ላይ ምዕ. 2፥10-16 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወደፊት የሚሆኑ ነገሮች ምዕ. 2፥17-3፥5 | ሕዝቡ በጌታ ፊት ምን እንደሚመስል ምዕ.. 3፥6-15 | እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅሬታዎች ምዕ. 3፥16-18 | ታላቁ የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ምዕ. 4 |

## ማጠቃለያ

በየዘመናቱ የእግዚብሔር ሕዝብ፣ ጌታ እንደጠበቀው ዓይነት ሆኖ ያልተገኘበት ጊዜው ብዙ ነው። በነቢዩ ሚልክያስ ዘመን የነበሩ ካህናትና ሌላውም ሕዝብ በሥነ ምግባር የተበላሹ ነበሩ። ሚልክያስ ለዚህ መፍትሄው በንስሐ ወደጌታ መመለስ እንደሆነ ይናገራል። የእግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር አይለወጥም። እርሱ በሚወቅሰን ነገር ሁሉ ትክክል ነውና እርሱን መስማት ፣ ሰምቶም መታዘዝ አስፈላጊ ነው። ራሳችንና ያለንን ሁሉ ለእርሱ መስጠት ይጠበቅብናል።

# ትንቢተ ሚክያስ
## «የፍርድና የተስፋ መልእክቶች»

**ጸሐፊው፡-** ሚክያስ (1፥1)

**ዘመን፡-** ወደ ስምንተኛው መቶ ዓ.ዓ. አገልግሎት የሰጠው በ725 እና በ701 ዓ.ዓ. መሐከል እንደነበረ ይገመታል።

**አርዕስት፡-** ፍርድና መንግሥ

**ቁልፍ ጥቅስ፡-** 6፥8፣ 7፥18፣ 1፥2፣ 6፥2

**ቁልፍ ቃላት፡-** ያዕቆብ፣ ጽዮን፣ መሄድ፣ መስማት፣ ሕዝቦች፣ ቅሬታ፣ ጽድቅ።

### ዋና ዓላማዎች

1. የኢየሩሳሌምን መሪዎች ስለበደላቸው መውቀስ፣
2. ሐሰተኞችን ነቢያትን ማጋለጥ፣
3. የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ መናገር፣
4. ስለወደፊቱ የእግዚአብሔር ተስፋና በረከት መናገርና (ምዕ. 5-6)
5. ቢቃል ኪዳኑ መሠረት የተሰጡ ተስፋዎች እንደሚፈጸሙ አስረግጦ መግለጽ ናቸው (ምዕ. 7)።

### አስተዋጽኦ

I. በእስራኤልና ይሁዳ ስለሚመጣው ፍርድ የተነገረ ቃል (ምዕ. 1-3)

ሀ/ የእግዚአብሔር ክስ (ምዕ. 1)
ለ/ በሚክያስ ዘመን ሕዝቡ እንደተበላሸ (ምዕ. 2)
ሐ/ የመሪዎች መኰነን (ምዕ. 3)

II. ለእስራኤልና ይሁዳ የተነገረ ተስፋ (ምዕ. 4-5)

ሀ/ የሚመጣው መንግሥት (ምዕራፍ 4)
ለ/ የሚመጣው ንጉሥና የጌታ ሕዝብ የሚያገኘው ድል (ምዕ. 5)

III. እግዚአብሔር እስራኤልን መክሰሱ፣ ፍርድ እንደሚያመጣባትም መናገሩ (ምዕ. 6) እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለው ክርክር።

IV. ተግሳጽና ተስፋ የቃል ኪዳን ተስፋዎች እንደሚፈጸሙ መነገሩ (ምዕ. 7)

ሀ/ የእስራኤል ሕዝብ የሞራል ውድቀት (ቁ. 1-7)
ለ/ ደህንነት ከእግዚአብሔር (ቁ. 8-13)



ሐ/ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያሳየው ርኅራኄ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚያሸንፍ መነገሩ (ቁ.14-20)።

ሚክያስ የኖረው ኢሳይያስና ሆሴዕ በኖሩበት ዘመን ነው። የስሙ ትርጉም «እግዚአብሔርን የሚመስል ማን ነው?» ማለት ነው (ከምዕ. 7፥18 ጋር አስተያይ)። ሚክያስ ቤቱ ሞሬሼትጌት እንደሆነ ተጠቅሶአል (ምዕ. 1፥1፣ 14)። ይህ ቦታ በደቡባዊው ይሁዳ ክፍል በፍልስጥኤም ይገኛል። ቦታው ለም ለንግድም አመቺ የሆነ ገጠር ነበር። በገጠር ተወልዶ በገጠር ያደገ እንደመሆኑ መጠን ስለ ኢየሩሳሌምና ስለሰማርያ ከተማ ነዋሪዎች ሁኔታ መናገሩ እግዚአብሔር አስችሎት እንጂ ቀላል አልነበረም (ሚክ. 1፥5፣ 6፥9)። ሚክያስ ጥሪውን በሚገባ አውቆ በጌታ ጸንቶ የቆመ ታማኝ ነቢይ ነበር (ሚክ. 3፥8፣ 7፥7)። በመሆኑ በሰዎች አሳብ ከመመራት ይልቅ ከጌታ በተሰጠው አሳብ ብቻ ተመራ፣ ለሙንም አከበረ።

### በሚክያስ ዘመን የነበረው የሕዝቡ ሁኔታ፣

ሚክያስ የኖረው ሕዝቡ በብዙ ነገር በከሰረበት ዘመን ነው። ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ግብጽና አሦር ለታላቅነት ይዋጉ ነበር። የሚክያስ ሕዝብ ሲታይ ደህና ኑሮ የሚኖር ይመስላል (ቢተስይ በይሁዳው ንጉሥ በዖዝያን ዘመን (በ739 ዓ.ዓ.)። ነገር ግን ሁሉ ነገር ደህና አልነበረም። ሀብታሞቹም ድሆችን በማታለል ሀብት እየጨመሩ ሄዱ፤ ምድሪቱም በሙስና ተበላሸች። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ቸል በማለታቸው ጣዖታትን በየሥፍራው አስቀምጠው ያመልኩ ነበር። ይህን ሁሉ ጥፋት እየሠሩ እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው ያስቡ ነበር። ጌታ ለአሦራውያን አሳልፎ በመስጠት ቀጣቸውና በ722 ዓ.ዓ. እስራኤል በእነርሱ እጅ ወደቀች። ይሁዳ ከዚህ ትምህርት መውሰድ ነበረባት፣ ነገር ግን እሷም የእስራኤልን ፈለግ ተከተለች። ሚክያስ አገልግሎቱ ለይሁዳ ሕዝብ ቢሆንም እስራኤልንም እንዳገለገለ ይገመታል (1፥1፣ 3፥8)። በዘመኑ ስለነበረው የፖለቲካ ሁኔታ በ2ኛ ነገሥት 15፥17-20፥21፣ 2ኛ ዜና 26-30።

### የመጽሐፉ አበይት ትምህርቶች

1. እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል።
   ጭከና፣ ሙስና ቅጣትን የሚያስከትሉ ናቸው (ሚክ. 1፥2-5፣ 5፥10-15)።
2. እግዚአብሔር ሁሉን ታሪክንም ጭምር የሚቆጣጠር አምላክ ነው (ሚክ. 4፥8-13፣ 7፥8-10)።
3. እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚጠነቀቅ አምላክ ነው።

ሁልጊዜ ይወዳል፣ ቢቀጣም ተስፋን ይሰጣል፤ እርሱን ከፍጹም ልባቸው ለሚከተሉት ክቡር የሆነ አዲስ ሕይወት ይሰጣል (ሚክ. 2፥12፣ 13፣ 6፥3-5፣ 7፥14፣ 15)።

4. እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የዓለም ሕዝብ፣ ለአሕዛብ አገሮችም ጭምር ያስባል (ሚክ. 4+1-4፣ 7+16፣17)።

5. እግዚአብሔር አዳኝ ይልካል። የሚልከው መሲህ ትሁት ሆኖ በቤተልሔም ይወለዳል (ሚክ. 5+2-6)።

6. እግዚአብሔር ለወደፊት የሚሆን ተስፋ ሰጥቶአል (ሚክ. 4+1-5+15)

- ለኢየሩሌም (4+1-3፣ 8፣ 13)
- ለቅሬታው (2+12፣ 4+6፣ 7፣ 10)
- ለአገሮች ሁሉ (4+2-4)

እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው (7+18-20)።

በዚህ መጽሐፍ የሕዝቡ ኃጢአት በጉልህ ተጠቅሶአል።

- ጣዖት አምልኮ (1+5-7)
- ቅናት የሌላውን መመኘትት (2+2)
- የሌላውን ንብረት መቀማት (2+2)
- ዓመጽ ማካሄድ (2+2፣ 3+10፣ 6+12፣ 7+2 በደል ማድረስ)
- በሐሰተኞች ነቢያት መደገፍ (2+6፣ 11)
- የገዥዎች ሙስና (3+1-3)
- የነቢያት ሙስና (3+5-7)
- የካህናት ሙስና (3+11)
- ጉቦ መስጠትና መቀበል (3+9፣ 11፣ 7+3)
- ታማኝ አለመሆን (6+10-11)

## በሚክያስ ስለክርስቶስ የተነገሩ ክፍሎች

1. የሚወለድበት ቦታ በስም ተጠቀሰ (5+2) «ቤተልሔም»
2. ክርስቶስ ንጉሥ እንደሚሆን ተነገረ (2+12፣13)
3. ክርስቶስ በምድር ሁሉ ላይ እንደሚነግሥ ተነገረ (4+1፣ 7)።

## ሚክያስ በሌሎች መጻሕፍት መጠቀሱ

1. በይሁዳ ሽማግሌዎች (ኤር. 26+18፣ ሚክ. 3+12)
2. በሱብአስገል (ማቴ. 2+5፣ 6፣ ሚክ. 5+2)
3. በጌታ ኢየሱስ (ማቴ. 10+35፣ 36፣ ሚክ. 7+6)



## ስነ መለኮታዊ መልእክት

1. ክልብ ሳይሆን ላይ ላዩን የሆነ ሃይማኖት ዋጋቢስ ነው (3+11፣ 6፣ 8)። ለሕዝብ የምጋረው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማ መሆን ይኖርበታል (2+11፣ 3+5-8)። የእግዚአብሔር መልእክተኛ የተላከውን መልእክት በማድረስ ረገድ እንደሚክያስ ታማኝ መሆን ይኖርበታል። ዙሪያው ቢበላሽና ሰዎች መልእክቱን ለመስማት ባይፈልጉም እርሱ ለላከው ጌታ መታዘዝ ይኖርበታል (ሚክ. 7+7፣ 2+6፣ 3+8)።

### የሚክያስ መጽሐፍ ንድፍ

| | | | |
|---|---|---|---|
| በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ስለሚመጣ ፍርድ የተነገረ፤ ምዕ. 1-3 | ለእስራኤልና ይሁዳ የተነገረ ተስፋ ምዕ. 4-5 | እግዚአብሔር እስራኤልን መክሰሱ፤ ፍርድ እንደሚያመጣባትም መናገሩ | ተግሳጽና ተስፋ ምሕረት ይቅርታ ምዕ. 7 |

## ማጠቃለያ

ነቢዩ ሚክያስ ለይሁዳና ለእስራኤል (ኢየሩሳሌምና ለማርያ) የእግዚአብሔርን መልእክት አስተላለፈ። የመልዕክቱ ይዘት ፍርድና ተስፋ ነበር፣ ይህንንም በታማኝነት አስተላለፈ። ይህንን ሲያደርግ (በምዕራፍ 1-2 እስራኤልን ስለኃጢአትዋ በመውቀስ ተናገረ። በምዕ. 3-5 ስለሚመጣው መሲህ (ክርስቶስ) ያለውን መልዕክት ለመሪዎች አስተላለፈ። በምዕራፍ 6-7 እግዚአብሔር ከመረጠው ሕዝብ ጋር ስላለው ክርክር ተናግሯል። መጽሐፉ ስለኃጢአትና ፍርድ የሚናገር ቢሆንም ስለእግዚአብሔር ተስፋና ምሕረት በማሳወቅ ይደመድማል።

## የብሉይ ኪዳን አሰሳ ማጠቃለያ

ብሉይ ኪዳን በውስጡ 39 መጽሐፍትን የያዘ እያንዳንዱ መጽሐፍ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ የተጻፈ ቢሆንም ሁሉም በአንድነት አንድ መልዕክት አላቸው። ይኸውም እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን ያለውን ዕቅድ መግለጽ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን ያለውን ዕቅድ ያከናወነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነው።

«ኪዳን» የሚለው ቃል የሚያመለክተው «ቃል ኪዳን» ወይም «ስምምነት» የሚለውን ሃሣብ ለማመልከት ነው። ስለዚህ ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ያደረገውን ቃልኪዳን ወይም ስምምነት የሚናገር መጽሐፍ ነው። አዲስ ኪዳን ደግሞ በክርስቶስ አማካይነት በጸጋው እግዚአብሔር ዓለሙን ለማዳን ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሕግ ቃል ኪዳን

እናገኛለን። በአዲስ ኪዳን ደግሞ የፀጋ ቃል ኪዳን፣ ይህም በክርስቶስ አማካይነት የመጣ መሆኑን እናነባለን።

አንዱ (ብሉይ ኪዳን) ወደሌላው (አዲስ ኪዳን) የሚመራ (ገላ. 3፥17-25) ሲሆን በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜያቸውንና ትክክለኛ ትርጉም ያገኙት በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት ነው። ስለዚህም ጌታ ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 24፥44 ላይ ሲናገር «ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለእኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል» አላቸው። ይህ ማለት በብሉይ ኪዳን (በሕግ በነቢያትና፣ በመዝሙራት) ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ ያገኙት በክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

ስለመሲሁ የመጀመሪያው ምጽአት በብሉይ ኪዳን ከ300 በላይ ትንቢቶች ፍጻሜ ያገኙት በክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ከእነርሱም ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. በኢሳይያስ 11፥1 ላይ የተሰጠው ትንቢት መሲህ ከእሴይ ግንድ ከዳዊት ሐረግ የሚመጣ መሆኑን ሲሆን (1ኛ ሳሙ. 16፥19) ፍጻሜውን ያገኘው በሉቃስ 1፥31-33 በተገለጸው መሠረት ነው።
2. በሚልክያስ 5፥2 ላይ የተሰጠው ትንቢት መሲህ በቤተልሄም ከተማ እንደሚወለድ የሚገልጽ ሲሆን ፍጻሜውን ያገኘው በማቴዎስ ወንጌል 2፥1- መሠረት ነው።

በኢሳይያስ 7፥14 የተጻፈው ትንቢት መሲህ ከድንግል መወለዱን የሚያመለክት ሲሆን፣ የተፈጸመውም ከድንግል ማርያም በመወለዱ ነው (ማቴ. 1፥18-25)። በኢሳይያስ 40፥3 የተነገረ ትንቢት የክርስቶስ መምጣት በማንና እንዴት እንደሚታወጅ ሲሆን በመጥመቁ ዮሐንስ አስቀድሞ መምጣትና ስለክርስቶስ እርሱ በተናገራቸው ነገሮች መሠረት ፍጻሜ አግኝቷል (ማቴ. 3፥1-3)። በኢሳይያስ 53፥4-6 ላይ የተሰጠው ትንቢት ክርስቶስ የበደል ሥርየት ሆኖ መከራ እንደሚያይ የሚናገር ሲሆን በክርስቶስ ሞት ፍጻሜውን አገኘ (1ኛ ጴጥ. 2፥24-25)።

በዘካርያስ 9፥9 ላይ የተነገረው ትንቢት ክርስቶስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ንጉሥነቱን ለመግለጽ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ ሲሆን በማቴ. 21፥1-5 ባለው ክፍል በተጠቀሰው መሠረት ፍጻሜ አግኝቷል።
በመዝሙር 69፥21 የተነገረው ትንቢት ለመብሉ ሐሞት ለጥማቱ ሆምጣጤ እንደሚያጠጡት የሚያመለክት ሲሆን በማቴ. 27፥34 እና 48 መሠረት ተፈጽሟል። በመዝ. 34፥20 ላይ የተነገረው ትንቢት በሞቱ ጊዜ ከአጥንቱ አንድም የማይሰበር



መሆኑን ሲያመለክት፣ በዮሐንስ ወንጌል 19፥33 እና 36 መሠረት በኢየሱስ ሞት ጊዜ አጥንቱ ሳይሰበር በመሞቱ ተፈጽሟል። በመዝሙር 22፥18 የተነገረው ትንቢት ሰዎች የክርስቶስን ልብስ እንደሚከፋፈሉ የሚያመለክት ሲሆን፣ በማቴ. 27፥35 ክርስቶስን ከሰቀሉ በኋላ ልብሱን በመከፋፈላቸው ፍጻሜውን አግኝቷል።

በመዝ. 16፥9 እና 10 ቁጥሮች ላይ የተነገረው ትንቢት የክርስቶስ አካል በመቃብር ውስጥ እንዲበሰብስ የማይተው መሆኑን ስለሚያመለክት ኢየሱስ ክርስቶስ በአስደናቂ ሁኔታ በሦስተኛው ቀን ከሞት በመነሳቱ የተፈጸመ ትንቢት ነው። ሉቃ. 24፥1-47፣ በሐዋርያት ሥራ 2፥31 - 32 እና በ1ኛ ቆሮ. 15፥4-8 ባሉት ክፍሎች የትንቢቱ መፈጸም እውነተኝነት ተረጋግጧል።

እስካሁን ባለው ሃሣብ ውስጥ ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ዓለምን በልጁ በክርስቶስ አማካይነት የሚያድን መሆኑን የሚናገር መጽሐፍ በመሆኑ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ይህ የተነገረው ትንቢት ሙሉ በሙሉ ፍጻሜ አግኝቷል።

ለአብርሃም፣ በዘፍጥረት 12፥1-3 መሠረት ተስፋ በተገባለት ጊዜ «ዓለም ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ» የተባለው ትንቢት የተፈጸመው ክርስቶስ ከመጣ በኋላ የዓለም ሕዝብ በክርስቶስ በማመን በሚያገኘው ደህንነት ምክንያት ነው። አዳምና ሄዋን በኃጢአት በወደቁ ጊዜ በዘፍጥረት 3፥15 የተገባላቸው የተስፋ ቃል «ከሴቲቱ ዘር» የሚወለድ የእባብን (የዲያቢሎስን) ራስ እንደሚቀጠቅጥ የተነገረ ትንቢት ሲሆን ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የዓለምን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሞ በሞተ ጊዜ ከሞትም በድል ተነስቶ በሰይጣን እሥራት የነበሩትን ነፃ በመውጣት የእባቡን ጭንቅላት ቀጠቀጠ። የዲያብሎስንና የሞትን ሥልጣን ሻረው። እኛም የዚሁ ድል ፍሬዎች ነን።

ብሉይ ኪዳን የከበረ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል (ማቴ. 5፥18፣ ዮሐ. 10፥35)። ሰይጣን በምድረበዳ ፈተና ባቀረበለት ጊዜ «ተጽፏል» እያለ የመለሰው ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሰ እንደነበር ግልጽ ነው (ማቴ. 4፥1-11)። ከሞት ከተነሳም በኋላ ስለብሉይ ኪዳን የነበረው አመለካከት የከበረ ስለነበር ለኤማሁስ መንገደኞች በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለእርሱ የተነገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ግድ ነው እያለ ብሉይ ኪዳንን ይጠቅስላቸው ነበር።

በመጨረሻም ብሉይ ኪዳን ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ስለዓለም አዳኝ ክርስቶስ ኢየሱስ የሚገልጽ እና ዛሬም በአማኞች ሕይወት ውስጥ ለውጥ የሚያመጣ ቃል በመሆኑ በአክብሮት እናንብብና እንታዘዝ። ከዚህም የተነሳ በረከቱ ለእኛ፣ ምስክርነቱ ለዓለም ሕዝብ እና ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሆናል። አሜን!

## Bibliography/ዋቢ መጻሕፍት


Dillard, Raymond B. and Longman III, Tremper. An Introduction To The Old Testament. Leicester: Apollos, 1995.

Fleming, Don. Bridge Bible Commentary. Brisbane: Bridgeway Publications, 1994.

Greve, Fred J. Old Testament Surverry. Irving, Texas, ICI University Press, 1975.

Schultz, Samuel J. Broadening Your Biblical Horizones Wheaton, Illinoise: Evangelical Training Association, 1968.

Schultz, Samuel J. The Old Testament Speaks. San Francisco: Harper & Row, 1980 and 1990.


# ብሉይ ኪዳን አሰሳ

# የጥናት መመሪያ

# የብሉይ ኪዳን
# የጥናት መመሪያ
## ማውጫ


ምዕራፍ ገጽ

አጠቃላይ መግቢያ ............ i

I ፔንታቱክ ............ 1
- ዘፍረት
- ዘጸአት
- ዘሌዋውያን
- ዘኍልቁ
- ዘዳግም

II የታሪክ መጻሕፍት ............ 16
- ኢያሱ
- መሳፍንት
- ሩት
- 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል
- 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት
- 1ኛ እና 2ኛ ዜና
- ዕዝራ
- ነህምያ
- አስቴር

III የቅኔ መጻሕፍት ............ 52
- ኢዮብ
- ዳዊት
- ምሳሌ
- መክብብ
- መኃልዩ ዘሰሎሞን

ምዕራፍ ገጽ


IV ታላላቅ ነቢያት.......... 60
ኢሳያስ
ኤርምያስ
ሰቆቃወ ኤርምያስ
ሕዝቅኤል
ዳንኤል

V ደቂቀ ነቢያት.......... 72
ሆሴዕ
አሞጽ
ሚክያስ
ኢዩኤል
አብድዩ
ትንቢተ ዮናስ
ናሆም
ዕንባቆም
ሶፎንያስ
ሐጌ
ዘካርያስ
ሚልክያስ


# የብሉይ ኪዳን አሰሳ
# የጥናት መመሪያ

## አጠቃላይ መግቢያ

### የጥናት መመሪያው ዓላማ

በርቀት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በሚሰጠው ሥልጠና ከተጨማሪ ጽሑፎች ጋር እንደአስተማሪ ሆኖ በመተካት የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዲመራ ተዘጋጅቶ የቀረበ ጽሑፍ ነው።

### የኮርሱ መግቢያና መግለጫ

ይህ ኮርስ ስነመለኮታዊ እውነት የሆነውን የእግዚአብሔርን የደህንነት ታሪክ ከሕዝበ እስራኤል ጋር ባሰው ግንኙነቱና ከተሰያዩ ስነ ጽሑፋዊ ዕይታዎቹ አኳያ ያቀርባል። ብሉይ የአዲስ ኪዳን መሠረት እንደመሆኑ መጻሕቶቹን ማጥናታችን ለክርስቲያናዊ እምነታችን ጠቅላላ ግንዛቤን ያስጨብጠናል። የጸሐፊዎቹን ማንነት፣ ታሪኩ የተፈጸመበት መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ ዘመን፣ በጊዜው የነበረውን ቋንቋና ባሕል እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ያቀርባል። የተማሪውን የእውቀት አድማስ በማስፋትና የአተረጓጐም መመሪያ በመስጠት ሰተሻለ ክርስቲያናዊ መረዳትና ኑሮ ያዘጋጀዋል።

### የኮርሱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ኮርስ ሲያጠናቅቅ፡-

- የብሉይ ኪዳንን ታሪካዊ ዳራ ያውቃል፤
- የእግዚአብሔርን የደህንነት ታሪክ ይረዳል፤
- የስነ ጽሑፍ ዓይነቶቹን በማወቅ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በትክክል ይተረጉማል፤
- የእግዚአብሔርን መልካምነት ማሰትም የተስፋ ቃሉን በዘመናት ሁሉ እንደጠበቀ ስለሚገነዘብ ይህን እውነት ከሕይወቱ ጋር በማዋሃድ ሰተሻለ አገልግሎት ይዘጋጃል።

## ቁልፍ ቃላት

እንደ ትምህርቱ ዓይነትና የመጽሐፉ አጠቃቀም አንዳንድ ቁልፍ ቃላት ማብራሪያ ይሰጥባቸዋል።

## የጥናት ጊዜ

የኮርሱ ጠቅላላ የትምህርት ጊዜ 8 ሳምንታት ይሆናል። ተማሪውም የትምህርቱን ጊዜ በዕቅድና በፕሮግራም እንዲጠቀም ይበረታታል።

## የትምህርቱ ቅንጅትና የጥናት ቅደም ተከተል

እያንዳንዱ ትምህርት የሚያካትተው፦

1. የትምህርቱ ርዕስ
2. የትምህርቱ መግቢያ
3. የትምህርቱ አስተዋጽኦ
4. የትምህርቱ ዓላማዎች
5. የምንባብ ክፍሎች
6. ቁልፍ ቃላት
7. የጥናት ጥያቄዎች
8. መመዘኛ ፈተና
9. የጥያቄዎች መልሶች
10. የቃላት ፍቺ

## የፈተና ውጤት አሰጣጥ

90-100 - A
60-89 - B
70-79 - C
60-69 - D
< 60 - F
ያላሟላ - I

የጥናት ጥያቄዎች፣ የመመዘኛ፣ አጋማሽና አጠቃላይ ፈተና ዓላማ - ለማስተማርና ለመመዘን ነው።



በዚህ ትምህርት የብሉይ ኪዳንን በመረዳት በመተርጐም እውነቱን በኖርና ለሌሎች ይህን ህይወት በማካፈል እንዲባረኩ ጸሎታችን ነው።

## የመማሪያ መጻሕፍት

- የብሉይ ኪዳን እሰሳ 1994 ዓ.ም. የመጀመሪያ እትም (የመጽሐፉ የመጀመሪያ ክፍል)
- የብሉይ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 1
- የብሉይ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2
- የብሉይ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3 /ት.መ.ማ./ በቲም ፌሎስ፣ ትርጉም ጌቱ ግዛው
- ከመጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ ኪዳን ክፍልን ቅጥሶችን በ1954 ዓ.ም. ትርጉም አንብብ።

# I. ፔንታቱክ

## የሕግ መጻሕፍት (የሙሴ መጻሕፍት)

## ትምህርት 1 - ዘፍጥረት

### መግቢያ

በዘፍጥረት እግዚአብሔር የሰማይና የምድር በውስጥዋም ያሉ ነገሮች ሁሉ ጀማሪ መሆኑን ሰውንም በአምሳሉ ፈጥሮ የሰጠውን ድርሻና ኃላፊነት፣ እንዴት ሰው ለእግዚአብሔር መታዘዝ አቅቶት እንደወደቀ እናያለን። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን ደህንነት በተለያየ ሁኔታ ሕዝቡን በምህረቱ ሲያስብ ለሌሎች ቀጣይ መጻሕፍትም ሁሉ መሠረት የሆነ ትምህርት ከዘፍጥረት መጽሐፍ እንማራለን።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲጠናቀቅ፦

- የፍጥረትን አመጣጥ ቅደም ተከተል ይገነዘባል፣
- የሰው ልጆች ውድቀት ጀማሪ የአለመታዘዝ ውጤት ጥፋትና ሞት መሆኑን ያያል፣
- ዘፍጥረት የሌሎች መጻሕፍቶች መሠረት መሆኑን እንደሚገባ ለመረዳት ይችላል።

### አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- ጸሐፊ
- የተጻፈበት ጊዜና ቦታ
- የመጽሐፉ ዓላማዎች
- በዘፍጥረት ሰባቱ ታላላቅ ሰዎችና መልእክቶቻቸው
- በዘፍጥረት ቁልፍ ቦታዎች
- የትውልድ ሐረግ
- ዋና ሐሳቦች
- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ

### የምንባብ ክፍሎች

- ከብሉይ ኪዳን አሰሳ ገጽ 2-13 አንብብ
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 1፣ ከገጽ 77-173
- ከመጽሐፍ ቅዱስ የአሪት ዘፍጥረትን መጽሐፍ አንብብ።

## የጥያቄዎች መልሶች

1. አገልግሎቱ፣ በሚለው ነጥብ ሥር የተሰጡ አራት ዓለማዎችንና የመሳሰሉትን
2. ነቢዩ ኢሳይያስና ዘካርያስ
3. ዘካርያስ ምዕራፍ 14
4. ሀ. በእምነት የጸደቀ ሆኖ ለጌታ የተሰጠ
   ለ. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተደግፎ የሚሠራ

## ትምህርት 23.3

1. ስለመጥምቁ ዮሐንስ መምጣት ይናገራል።
2. . ፍቅሩን በመካድ
   - ለጌታ በሚቀርብ መሥዋዕት
   - በጌታ ፊት በድፍረት በመናገር
   - አሥራትንና በኩራትን ባለመስጠት (በመስረቅ)
   - «እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው» በማለት ወዘተ.

3. በዓለም መጨረሻ በጌታ ኢየሱስ በኩል በዓለም ላይ ሲመጣ ያለውን ታላቁን የፍርድ ቀን (ጊዜ)።

# ዘፍጥረት

## መግቢያ

ዘፍጥረት ከአምስቱ የሕግ መጻሕፍት የመጀመሪያው ሲሆን የስሙም ትርጓሜ በዕብራይስጥ በኩር፣ ቀዳሚ ወይም የመጀመሪያ የሚል ነው። የእግዚአብሔር ፈጣሪነትና እግዚአብሔር አልፋና ኦሜጋ ስለሆነ ጅማሬ እንደሌለው ሌሎች ነገሮች ግን ጅማሬአያቸውን በእርሱ እንዳገኙ ይተርካል። የሁሉን ነገር ማለትም የህያዋንን የፍጥረትን፣ የህዋን፣ ሕይወት ያለውን፣ የጋብቻን (የቤተሰብን) የትውልዶችን፣ የኃጢአትን፣ የመርገምን ጅማሬ ይዘግባል። እግዚአብሔር ሰውን ከውድቀት ለመቤዠት ያደረገውን የደህንነትን ታሪክ የሚተርክልን መጽሐፍ ነው። የግሪኩን ትርጉም ስንመለከት ጀነሲስ (Geneseos) ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን በሰብዓ ሊቃውንት ትርጓሜ ከእብራይስጡ ቃል የትውልድን/የፍጥረትን ጅማሬ የሚያሳይ ወይም ትውልድ (Toledot) ልደት ከሚለው የተወሰደ ነው። ቁልፍ ጥቅሱም «እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን ባደረገ ቀን በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው» የሚለው ነው (ዘፍጥ. 2፥4)። ከዚህ ቃል እንደምንረዳው የዘፍጥረት መጽሐፍ የትውልድ ዝርዝር የያዘ መሆኑን እንመለከታለን (ዘፍጥ. 2፥4፣ 5፥1፣ 6፥9፣ 10፥1፣ 11፥27፣ 25፥19፣ 36፥1፣ 37፥2)። ስለዚህም ከመጽሐፉ ይዘት እንደምናየው የሁለቱም የዕብራይስጡና የግሪኩ ትርጉም ለመጽሐፉ ርዕስ ተስማሚ መሆኑን ነው።

## ጸሐፊ

በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የሙሴን ስም ስለማናገኝና በዘዳግም 34 ስለሙሴ ሞት ስለሚናገር የፔንታቱክ ጸሐፊ ሙሴ አይደለም የሚሉ ክርክሮች ተነስተዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎችን ስናይ፣ ከታሪክና በጥንት ዘመን ከነበሩ ዕብራውያን ክርስቲያኖች ዝንባሌ ስንረዳ ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነና በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንደጻፈው እንረዳለን። ሙሴ እንደሚለው ከሚቀርቡት መረጃዎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የዘፍጥረት መጽሐፍ ታሪክ ሙሴ ከመወለዱ ሦስት መቶ ዓመታት ያህል ቀደም ብሎ እንደተከናወነ ግልጽ ነው። ሆኖም ሙሴ ይህን መረጃ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ተገልጦለት ወይም በቢያን ዘመን በግብጽና በፍልስጤም ይገኙ ከነበሩት የፅሑፍ መረጃዎች እንደጻፈው ይገመታል (ስሞ. 3፥7)። ሙሴ የጽሕፈትን ሥራ ይሠራ ነበር እናነባለን (ዘጸአ. 34፥27፣ ዘኁል. 17፥2፣ ዘዳግ. 6፥9፣ 24፥1፣ 3 ኢያ. 8፥32)።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የዘጸአት መጽሐፍና ሌሎችም የአሪት መጻሕፍት በአይሁዶች ዘንድ ለምን የሙሴ መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ?

2. የሙሴ ዕድሜ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፉን፣ ለጌታም የሚጠቅም ታማኝ ባሪያ መሆኑን ስትመለከት እግዚአብሔር ስለሰዎች ሕይወትና ስለሚያልፉበት ነገር ስለሚኖረው ዓላማ ምን ትማራለህ?

3. እግዚአብሔር በግብጽ መቅሰፍት ያወረደው ለምንድን ነው?

4. በዘጸአት 17 የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሲያጉረመርሙ በተለያየ ችግር ሲወድቁ፣ ሙሴ እጁን አንስቶ ሲፀልይ ሲያሸንፉ እናነባለን፣ ይህ ስለማጉረምረምና ስለፀሎት ውጤት ምን ያስተምረናል?

5. በዘጸአት 21-23 ስለተለያዩ ጉዳዮች የተሰጡ ሕጐችና ሥርዓቶች ስለእግዚአብሔር ምን ያሳዩናል?

6. የመገናኛው ድንኳን ለአዲስ ኪዳን አማኞች ምን ትርጉም እንደሚሰጥና ምን እንደሚያስተምረን ጻፍ።

7. ካህናት ከየትኛው ነገድና ቤተሰብ መሆን አለባቸው?

## የመመዘኛ ፈተና

1. እስራኤላውያን ያለካህን ሊያመልኩና ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ አይችሉም ነበር። በአዲስ ኪዳንስ በማን በኩል ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን? የሚያቀርቡን ካህናት ያስፈልጉናል?

2. በመገናኛው ድንኳን የነበረ መጋረጃ ምን ያሳየናል? ማር. 15 +37፣ 38፣ ዕብ. 10+19-20 ያለውን ክፍል አንብበህ ለምን መጋረጃው እንደተቀደደና ምን እንደሚያሳየን? እንዴት በአዲስ ኪዳን ወደ ጌታ መቅረብ እንደምንችል አብራራ።



# ትምህርት 3 - ዘሌዋውያን

## መግቢያ

ኦሪት ዘሌዋውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ በቅድስና መመላለስ ስለሚገባው እግዚአብሔር ሥርዓትንና ሕግን እንደሰጠና አገልጋዮቹም ይሆኑ ዘንድ ከእስራኤል ነገዶች የሆኑት የሲዊ ዘር ሲያገለግሉ እንደተመረጡ ሳይረክሱ መኖር እንደሚገባቸው ያስተምረናል።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፡-

- እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን መተዳደሪያ ደንብና ሕግ ያውቃል።
- እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ካህናቱም ተቀድሰው መቅረብ እንደነበረባቸው ይረዳል።
- የተለያዩ መስዋእቶችና ዓላማቸውን በመረዳት እግዚአብሔር ለሕዝቡ በዓላትን እንዲያከብሩ ለምን እንደፈቀደ ያውቃል።

## አስተዋጽኦ

ጸሐፊው
ቁልፍ ጥቅስ
የመጽሐፉ ዓላማ
የተጻፈበት ዘመን
የመስዋዕት ዓይነቶች
ማጠቃለያ

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ገጽ 24 እስከ 28
- የብሉይ ኪዳን ትመማ ክፍል 2 ከገጽ 1 እስከ 28
- የዘሌዋውያንን መጽሐፍ በማንበብ ለአዲስ ኪዳን ያለውን አስተዋጽኦ በማገናዘብ ተረዳ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የዘሌዋውያን መጽሐፍ ቁልፍ ቃል ምንድነው? ጥቅስ ስጥ።
2. የዘሌዋውያን መጽሐፍን ስታጠና በእያንዳንዱ ምዕራፍ ሕጎችን ታያስህ እነዚህን በ27ቱም መጻሕፍት የምታገኛቸውን ሕጎች በየምዕራፉ አስቀምጣቸው።
3. ስንት ዓይነት መስዋዕቶች አሉ? በስንት ይከፈላሉ? ዘርዝር።
4. በአዲስ ኪዳን የምናቀርበው መስዋእት ምን ዓይነት መስዋእት ነው?
5. የእስራኤላውያን ታላላቅ በዓላት ዋና ዓላማው ምንድን ነው?

## የመመዘኛ ፈተና

1. እግዚአብሔር ሕግን የሰጠበት ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. የሙሴ ሕግ ኃጢአተኝነታችንን እንድናውቅ ሲረዳን አዲስ ኪዳን ደግሞ አዳኙን እንድናገኝ ያሳዩናል፤ አንዱ ያለሌላው ሙሉ እንደማይሆን ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ሁለቱም አስፈላጊ መሆናቸውን ከዚህ አባባል እንዴት ትረዳለህ? ግለጽ።



# ትምህርት 4 - ዘሁልቁ

## መግቢያ

የእስራኤልን ሕዝብ ቆጠራ ሁለት ጊዜ እንደተደረገ (ከግብጽ ሲለቁና ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ሲዘጋጁ) የሚያሳየን መጽሐፍ ነው። በተጨማሪም ከግብጽ የወጣው ሕዝብ እግዚአብሔርን ባለማመን፣ ባለመታዘዝና፣ በማጉረምረም በምድረበዳ መቅረቱንና፣ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም ታማኝ ስለሆነ የታመኑትን ሁለትና (ኢያሱና ካሌብ) ከ20 ዓመት በታች ያሉትን ይዞ ወደተስፋይቱ ምድር ዳርቻ ስለመድረሱ ታሪክ የሚያብራራ መጽሐፍ ነው።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፡-

- የእግዚአብሔርን የተለያዩ ባሕርያት ለምሳሌ ታጋሽነቱን፣ ቅድስናውን ለሕዝቡ ቀናተኛ መሆኑን ፀሎትን የሚሰማ መሆኑን፣ ቃልኪዳን ጠባቂነቱን (ታማኝነቱንና) በዓመጽ ላይ መፍረዱን መረዳት ይችላል።
- በእምነት የመራመድን ውጤትና ያለማመንን ጠንቅ በማወቅ በረከትን ለመውረስ መታዘዝ እንደሚያስፈልግ ይገነዘባል።
- እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ መሆኑን ይረዳል።

## አስተዋጽኦ

የመጽሐፉ ዓላማ
ጸሐፊው
የቦታው አቀማመጥ
ቁልፍ ጥቅስ
የመጽሐፉ አስተዋጽኦ
ዋና ትምህርቶች

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ገጽ 29 እስከ 32
- የብሉይ ኪዳን ትመማ ክፍል 2 ከገጽ 29 እስከ 61
- የዘሁልቁን መጽሐፍ ሙሉውን በማስተዋል አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. ሀ. የዚህ መጽሐፍ ርዕስ ዘሁልቁ የተባለበት ምክንያት ምንድነው?
   ለ. ታሪኩስ የሚነግረን ስለምንድን ነው?

2. የዘሁልቁ መጽሐፍ ዋና መልእክት ምንድን ነው?

3. ኢያሱና ካሌብ ከሌሎች የሚለዩት በምንድን ነው?

4. እግዚአብሔር አሮንና ማርያም በሙሴ ላይ ሲያጉረመርሙ የተቆጣበትን ምክንያት ስታይ መሪዎችን ስለማክበርና ቅናትን ከሕይወትህ ስለማስወገድ ምን ያስተምርሃል? (ዘኁል. 12፥1-16)

## የመመዘኛ ፈተና

1. ዘኁልቁ 22፥4-5 አንብበህ የሞአብ ንጉሥ ነቢዩ በለዓምን ምን እንዲያደርግለት እንደፈለገ ግለጽ።

2. ከዘኁልቁ 22 (የበለዓም ታሪክና) በአጠቃላይ ከዘሁልቁ መጽሐፍ ታሪክ እንደምንረዳው እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ በራስ (በሌሎች) መደገፍን የተለያዩ ጥቅሞች በመፈለግ ለመከበር መመኘትን ሰይጣን እንዴት መጠቀሚያ እንደሚያደረግ ከበረከትም እንደሚያጉድል ያገኘኸውን መረዳት ግለጽ።



# ትምህርት 5 - ዘዳግም

## መግቢያ

የዘዳግም መጽሐፍ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ሲያወጣቸው የሰጣቸውን ሕግ የማያውቀው አዲሱ ትውልድ በተስፋይቱ ምድር መግቢያ ላይ ሆኖ ከሙሴ ሕጉን ሲቀበልና ወደተስፋይቱ ምድርም ሲገባ መፈጸም የሚገባቸውን ሥርዓትና ደንብ ለመረዳት የሚያስችል መጽሐፍ ነው።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ:-

- ሙሴ በዘመኑ መጨረሻ ሲመራው ለቆየው ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሰጠውን ንግግር ይረዳል፣
- ሕጉ ለአዲስ ኪዳን አማኞች ያለውን አስተዋጽኦ ያስተውላል፣
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ በቃልኪዳኑ የፀና ታማኝ አምላክ መሆኑን ይረዳል፣
- የእግዚአብሔር ሕዝብ በጌታ ኃይል ያገኙትን ታላላቅ ድሎች በማወቅ እምነቱ እንዲጉለብት ያስችለዋል።

## አስተዋጽኦ

- ርዕሱ
- ዓላማው
- ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
- የመልክአምድር አቀማመጡ
- ቁልፍ ጥቅስ
- ዋና ገጸ ባሕርያት
- ቁልፍ ቃላቶች

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ገጽ 33 እስከ 36
- የብሉይ ኪዳን ትመማ ክፍል 2 ከገጽ 62 እስከ ገጽ 88
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ የዘዳግምን መጽሐፍ በሙሉ በማስተዋልና ከሕይወትህ ጋር በማዛመድ አንብበው።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. ዘዳግም ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ተጻፈ?
2. ሰይጣን ለሚያዘጋጀው ለብዙ ጥያቄዎች መልስ እንዴት እንደምናገኝ ከኢየሱስ ሕይወትና ከዘዳግም መጽሐፍ ምን እንረዳለን?
3. ሙሴ ሕጉን እንዲያስታውሱ የሚነግራቸውና (ዘዳ. 8+3) ያለቃሉ መኖር እንደማይችሉ መናገሩ ምን ያስገነዝበናል?
4. ሙሴ ጠንካራ መሪ ነው የምንለው ለምንድነው?

## የመመዘኛ ፈተና

ሙሴ በዘዳግም 27-30 ከሕይወትና ከሞት እንዲመርጡ ለእስራል ሕዝብ ምርጫን ያስቀምጥላቸዋል:: ይህ መልእክት ለአዲስ ኪዳን አማኞች የሚያስተላልፈው ትምህርት ምንድነው? ጌታ በልባቸው የጻፈውን መልእክት በመታዘዝ ዕለት በዕለት መኖር በሕይወት ለመኖር እንደሚረዳ በማነጻጸር ተመሳሳይነቱንና ልዩነቱን አብራራ (ከ1ኛ ዮሐ. 5+12፣ ዮሐ. 1+12፣ 3+36፣ 5+22፣ 10+10፣ 14+6፣ 23፣ 24)::



## የጥያቄዎች መልስ /ምዕራፍ 1/

### ትምህርት 1 - ዘፍጥረት

1. የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም እምስቱ ጥቅል መጻሕፍት ማለት ነው::
   ዘፍጥረት፣ ዘጸእት፣ ዘኍልቁ፣ ዘሌዋውያንና ዘዳግም ናቸው::

3. ዘፍጥረት 3+15

4. አብርሃም ከጣኦት አምላኪ ሕዝብ ውጣ እኔ ወደማሳይህ ሂድ ሲባል የሚሄድበትን ሳያውቅ በእምነት ታዘዘ፣ ዘፍጥ. 15+6 «አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት»::

5. አስቀድሞ አዳምና ሄዋን በእግዚአብሔር ላይ አመፁ ይህም አስጨናቂ ውጤቶችን አስከተለ:: የጥፋት ተጽዕኖ በሔዋን፣ በአባቡ በአዳምና ላይና በፍጥረት ላይ ከዚያም እየተስፋፋና እያደገ በመሄዱ ከልጃቸው ቃየል ጀምሮ አመጽ እየጨመሩ በዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ ተደጋጋሚ አመጽና ጥፋት እስከዛሬ ድረስ ማደጉን እናያለን::

## ትምህርት 2 - ዘፀአት

1. ሙሴ ስለጻፋቸው

   ሙሴ ዋናው የመጽሐፉ ገጸ ባህርይ ስለሆነ

2. እግዚአብሔር ሕዝቡን አስቀድሞ በዕቅድ እንደሚመራ «ብሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማህፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ» ኤር. 1፥5 ተብሎ እንደተጻፈ ጌታ በሕዝቡ ላይ የከበረ ዓላማ አለው:: (የግል መልስ)

3. የሕግ መጻሕፍ ይባላሉ:: የተሰጡትም ስዎች ጠቃሚ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ አውቀው እንዲኖሩበትና ጌታን እንዲያከብሩ እርስ በርሳቸውም በሰላም እንዲኖሩ ነው::

4. ማጉረምረም ጌታን እንደሚያሳዝንና ተጨማሪ ችግር እንደሚያስከትል መፀሰይና ጌታ የሚለውን ማድረግ ግን ለችግር መፍትሄና ድልን የሚያጐናጽፍ ነው::

5. እግዚአብሔር ስለእያንዳንዱ የሕይወታችን ጉዳይ እንደሚገደውና፣ ደስተኞችና ሥርዓት ያለን እንድንሆን፣ ከሌሎች ጋርም ባለን ሕብረት ጤናማ ግንኙነት እንዲኖረን ይፈልጋል::

6. እግዚአብሔር ለሙሴ በመካከላቸው ለማደር ይህን የማደሪያ ድንኳን እንዲሰራለት ትዕዛዝ ሰጠው:: በአዲስ ኪዳን ግን ሕዝቡ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ስለሆነ በልጆቹ ውስጥ ማደሪያ አድርጓል (1ኛ ቆሮ. 6፥19)::

7. ከሌዊ ነገድ ከአሮን ቤተሰብ መሆን ነበረባቸው:: ሌዊ ከ12ቱ የያዕቆብ ነገዶች አንዱ ነው::

## ትምህርት 3 - ዘሌዋውያን

1. ቅድስና ነው:: ዘሌዋ. 19፥2 «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ» (ዘሌዋ. 11፥44-45)

2. ከምዕራፍ 1-7 ስለመስዋእት ሕጐች
   ከምዕራፍ 8-10 ስለካሕናት
   ከምዕራፍ 11-15 ስለአለመንጻት
   ከምዕብፍ 16-17 የተለያዩ ሕጐች



3. እምስት ዓይነት መስዋእቶች አሉ:: በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ::

| | |
|---|---|
| 1. የሚቃጠል መስዋእት | በፈቃደኝነት (በውዴታ) መስዋእቶች |
| 2. የእህል ቁርባን መስዋእት | ለምሥጋናና አምልኮ የሚቀርቡ:: |
| 3. የደህንነት (የሰላም) መስዋእት | |
| 4. የኃጢአት መስዋእት | የግዴታ መስዋዕቶች ለኃጢአትና |
| 5. የበደል መስዋእት | በደል ምህረት ለመግኘት የሚቀርቡ:: |

4. ክርስቶስ ለኃጢአታችን ይቅርታ ሞቶልናል፣ እንዴና ለዘለዓለም ኃጢአታችንን ያስወገደውን ጌታ ይዘን ወደአብ እንቀርባለን እንጂ ሌላ መስዋእት አያስፈልገንም:: (ዕብ. 9፥9-12፣ 1ኛ ቆሮ. 5፥7):: ይህ ሲባል ራሳችንን ህያው መስዋእት አድርገን እንድናቀርብ (ሮሜ 12፥1-2፣ 1ኛ ጴጥ. 2፥5) ለሌሎች ማካፈልን መልካም መስራትንና፣ የምስጋና መስዋእትን ልናቀርብ እንደሚገባን፣ ለጌታ የተሰጠን እንድንሆን የጌታን ሥራ ለመስራት፣ ሕብረትን ለማድረግ የጌታ ቃል ይመክረናል::

## ትምህርት 4 - ዘሁልቁ

1. የእስራኤል ሕዝብ ቆጠራ ሁለት ጊዜ ስለተካሄደበት ነው::

   ሀ. በሲና (ዘኁል. 1+46 - 603.550)
   ለ. በከነዓን ዳር ሆነው:: ዘኁ. 26+51 - 601:730

2. የዘኁልቁ መልእክቶች እነዚህና የመሳሰሉት ናቸው

   - እግዚአብሔር የስርዓት አምላክ እንደሆነና ነገሮች በሥርዓት እንዲሄዱ መፈለጉን ለሕዝቡ መመሪያ ስርዓት ሰጣቸው (1ኛ ቆሮ. 14+33፣ 40)

   - ማጉረምረም ከሕዝቡ ሕይወት እንዲወገድ መፈለጉ (ዘኁል. 11+1-6፣ 12+1-2)

   - ዓለምን መውደድ ከእግዚአብሔር ጋር ጠብ መሆኑ (1ኛ ዮሐ. 2+15)

   - አለመታዘዝ እግዚአብሔር ካሰበልን በረከት ማጉደሉን በጠላት ፊት ተሸናፊ እንደሚያደርግ (ዘኁል. 14+40-42)

   - አለማመን ውድቀትን እንደሚስከትል (ዘኁል. 13+27-28)

   - እግዚአብሔር ኃጢአትን መቅጣቱን 40 ዓመት ተቅበዘበዙ በምድረበዳ አለቁ (1ኛ ቆሮ. 10+1-6)::

3. ከችግሮቹ በላይ ጌታን ማየት የቻሉ እምነት ያላቸው መሆናቸው (ዘኁል. 13+31)::

4. በዘሁልቁ 12+2 ማርያምና አሮን እግዚአብሔር በሙሴ በመጠቀሙ ደስተኞች አልነበሩም ለራሳቸው የእርሱን ሥፍራ መመኘታቸውን ያሳየናል:: ቅናት የእግአብሔር ሥራ እንዳይሠራ እንቅፋት የሚያመጣ ክፉ ኃጢአት ነው:: በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ማጉረምረምና፣ ሃሜት፣ የጌታን ሥራ ማዘግየት ጌታን ያስቆጣዋል:: (ዘሁል. 12+8-10)

   ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ሲከስ አናየውም ነገር ግን እግዚአብሔር ቀጣለት:: በዚህም በፍቅርና በትህትና እግዚአብሔር ማርያምን እንዲምራት ወደ እግዚአብሔር መጮሁን ከመሪ ሕይወት ፍቅር ትህትናና ወደ እግዚአብሔር ልመና ማድረግ ራዕይን መቀበል እንደሚያስፈልግ እንማራለን (ዘኁል. 12+3፣ 8፣ 13)



## ትምህርት 5 - ዘዳግም

1. «ሁለተኛ ሕግ» ወይም «ዳግማዊ ሕግ» ማለት ነው::
   አዲሱ ትውልድ የእግዚአብሔርን ታላቅነት እንዲያውቅ ተዓምራቱንና ምሪቱን ሕጉንና ደንቡን እንዲረዳ፣ ውለታውን እንዳይረሳ ለማስተላለፍ ተጻፈ::

2. የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ሲኖርብን ድልን የሚሰጠን እንደሆነ ከዘዳግም መጽሐፍ ጌታ ኢየሱስም ለሰይጣን በመጥቀስ ጠላትን እንዳሸነፈ እንመለከታለን:: (ዘዳግ. 8+3፣ 6፣ 16፣ 6+13፣ 10-20፣ ማቴ. 4+1-11፣ ሉቃ. 4+1-13::

3. የተለያዩ ፈተናዎችን ለመቋቋምና ዓለምን ለማሸነፍ የጌታን ቃል በመማር መዘጋጀት እንደሚስፈልግና ቃሉን ከተመገብን እንደምንጠነክር ለማሳየት ነው::

4. ሀ. እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ትሁት ሰው ነበር (ዘኁል. 14+26፣ 27፣ 24+12፣ 15)::

   ለ. የሚተካውን መሪ ማሰልጠን በጊዜ ሲጀምር በፍጻሜውም ፀልዮ ኃላፊነትን ሲሰጥ እንመለከታለን (ዘጸአ. 17+9፣ 24+13፣ 34+9)::

# II. የታሪክ መጻሕፍት

## ትምህርት 6 ኢያሱ

### መግቢያ

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ እስራኤል ሕዝብና ስለተስፋይቱ ምድር የሚያትት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው መጽሐፍ ነው። በዚህኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ስለፀሐፊው ማለትም ስለኢያሱ ማንነት፣ ስለእስራኤል ሕዝብ፣ ስለከንዓን ምድር፣ እና ስተለካሄዱት ጦርነቶች በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስለእግዚአብሔር አዳኝነት፣ ቅን ፈራጅነትና ኃያልነት መጽሐፉ የሚለውን ለመዳሰስ እንሞክራለን።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፡-

- በስመጽሐፈ ኢያሱ ዋና ዓላማ በቂ ግንዛቤ በመጨበጥ ሃሣቡን ለሌሎች ማካፈል ይችላል።
- መጽሐፉ በብሉይ ኪዳን ላይ ተመዝግቦ ባለው የእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ይረዳል።
- እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል እንደሚጠብቅና የተስፋ ቃሉን ለማስጨበጥ የሚያስፈልገውን ዕርዳታ ሁሉ እንደሚሰጥ በመረዳት በሕይወቱ ከበፊቱ በተሻለ መስጠት በእግዚአብሔር ይታመናል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- ፀሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
  - የመጽሐፉ ርዕስ
  - ኢያሱ
    - የሕይወቱና የአገልግሎቱ ጅማሬ
    - የሙሴ ረዳት
    - የሙሴ ምትክ
    - ሕይወቱ
- አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት
- የምድሪቷ አጭር ታሪክ
- መጽሐፉ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለው ሥፍራ።



### የመጽሐፉ ቁልፍ ጥቅሶች

ኢያሱ 11+23፣ 21+43-45 (እንደዚሁም ኢያሱ 1+11)

### ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት

ኢያሱ፣ ረሃብ፣ አክዓን፣ ፊንሐስ፣ እና አልዓዛር

### የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራዎች (ቦታዎች)

- ሰጢም 1+1-18
- የዮርዳኖስ ወንዝ 2+1-4+24
- ጌልገላ 5+1-15
- ኢያሪኮ 6+-27
- ጋይ 7+1-8+29
- የገሪዛን እና የኤባል ተራሮች 8+30-5
- ገባኦን 9+1-27
- የኤሎን ሸለቆ 10+1-43
- አሶር 11+1-23
- ሴሎ 18+1-19+51
- ሴኬም 24+1-33

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ትምህርት 11
- «የታሪካዊ መጻሕፍት መግቢያ» የሚለውን ከገጽ 89-128
- የብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 37-43
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ በተሰጠው የመጽሐፉ አስተዋጽኦ ላይ በመመርኮዝ መጽሐፈ ኢያሱን በሙሉ በጥንቃቄ አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. መጽሐፈ ኢያሱን የእስራኤል ሕዝብ የአንድ የታሪክ ምዕራፍ ታላቅ ፍጻሜ እና የአዲስ ልምምድ ጅማሬ ነው ብለን የምንልበት ምክንያት አስረዳ።
2. የኢያሱ መጽሐፍ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፋፍሎ ማጥናት እንደሚቻል ተመልክተናል። በእነዚህ አራት ዓበይት ነጥቦች ላይ ያለህን መረዳት በአጭሩ ግለጽ።
3. በመጽሐፈ ኢያሱ ታሪክ ውስጥ የከንዓን ምድር ቁልፍ ሚና ይጫወታል የምንልበት ምክንያት ምንድነው?
4. በጥናት መመሪያው ከተጠቀሱት ቁልፍ ሰዎች ውስጥ ሁለቱን በመምረጥ ስለሕይወታቸውና ስለአገልግሎታቸው አጠር ያለ ማብራሪያ ስጥ።
5. በጥናት መመሪያው ከተጠቀሱት ቁልፍ ሥፍራዎች ውስጥ አራቱን በመምረጥ በሥፍራዎቹ ላይ ስለተከናወኑት ነገሮች ማብራሪያ ስጥ።

## የመመዘኛ ፈተና

1. ኢያሱ 5+13-15ን በጥንቃቄ አንብብ። ከዚህ ክፍል ውስጥ በመጽሐፈ ኢያሱ ስለተካሄዱት ጦርነቶች ምን ትማራለህ?

2. ከግብጽ ምድር ውስጥ ከወጡት በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩት ሕዝቦች መካከል ኢያሱና ካሌብ ብቻ ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባታቸው ለአንተ ምን ትርጉም ይሰጥሃል?



## የጥያቄዎች መልስ

1. መጽሐፈ ኢያሱ ከንዓንን ለመያዝ የተደረጉትን ውጊያዎችና የእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ታሪክ የሚዘግብ ስለሆነ በተጨማሪም ከ40 ዓመታት የምድረበዳ ጉዞ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ሥፍራ ተቀምጠው የምድሪቱን ፍሬ መብላት የጀመሩበት ጊዜ ነበር። (ለተጨማሪ ሃሣብ ገጽ 1 ላይ ተመልከት)

2. . ወደምድሪቷ መግባት የጦርነት ዝግጅት 1+1-5
   - ምድሪቷን ለመውረስ የሚደረግ ጦርነት ጦርነትና ድሉ 6+1-12
   - ምድሪቷን መከፋፈልና መውረስ የርስቱ መወረስ 13+1-21
   - በምድሪቷ ውስጥ መኖር መጀመር መቀደስ (መለየት) 22+10-24+33 (ለተጨማሪ ሃሣብ ገጽ 5፣ 6 ላይ ተመልከት)

3. ምድሪቷ ለእስራኤል ሕዝብ ርስት እንድትሆን በተስፋ ቃሉ መሠረት የተሰጠች፣ አስቀድሞም እግዚአብሔር ለእስራኤል አባቶች ተስፋ የገባላቸው ምድር ስለሆነች ነው (ዘፍጥ. 12+7፣ 15+18-21፣ ኢያ. 1+6)።

4. የግል መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።

5. የግል መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።

# ትምህርት 7 መሳፍንት

## መግቢያ

በመጽሐፉ እስራኤላውያን ደጋግመው እግዚአብሔርን ሲበድሉና እግዚአብሔርም በቅን ፈራጅነቱ በመቅጣትና መልሶ ምሕረት በማድረግ በተለያዩ መሳፍንት እጅ ሲታደጋቸው እንመለከታለን:: መጽሐፈ መሳፍንት የእግዚአብሔርን መሐሪነትና ቤዛነት በግልጽ የምናይበት መጽሐፍ ነው:: በንስሐ የሚመለሱትን የሕዝቦቹን ሕይወት በማደስ ሰላምንና ዕረፍትን ይሰጣል። በአንጻሩም ደግሞ ቃል ኪዳኑን በማይጠብቁት ላይ ቁጣውን ያመጣል ለጠላቶቻቸውም አሳልፎ ይሰጣቸዋል:: በመሆኑም እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ተጽዕኖ ነጻ እንዲያወጣቸው በሾማቸውና ባስነሳቸው መሳፍንት መሪነት ሥር የቃል ኪዳኑን ቃል መጠበቅ እንዳልቻሉና በተደጋጋሚ እንደበደሉ እንማራለን::

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ:-

- የመጽሐፈ መሳፍንትን ዋና ይዘትና ዓላማ በማግኘት በሕይወቱና በአገልግሎቱ ሁሉ በተሻለ ሁኔታ እግዚአብሔርን መፍራት ይለማመዳል::
- እግዚአብሔር መስራት ሲፈልግ በሰው ማንነትና ብርታት ላይ ሳይሆን በራሱ ኃይል ብቻ በመተማመን በደካሞች ውስጥ አልፎ ታላላቅ ሥራዎችን እንደሚሠራ ስለሚገነዘብ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ራሱን ለእግዚአብሔር ሥራ ዝግጁ ያደርጋል::

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- የመጽሐፉ ፀሐፊና የተጻፈበት ዘመን
- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት
- የመጽሐፉ ዋና ዓላማ
- መደምደሚያ



## ቁልፍ ጥቅስ

17+6 «በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፣ ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር::»

## ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት

- ጐቶልያ
- ናዖድ
- ዲቦራ
- ጌዴዎን
- አቢሜሌክ
- ዮፍታሄ
- ሳምሶን
- ደሊላ

## የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራዎች

- ቦኪም 1+1-3+11
- ኢያሪኮ 3+12-31
- እሶር 4+1-5+31
- የሞሬ ኮረብታ 6+1-7+25
- ሴኬም 8+28-9+57
- የአሞን ምድር 10+1-12+15
- ተምና 13+1-14+20
- የሶሬቅ ሸለቆ 15+1-16+20
- ጋዛ 16+21-31
- ተራራማው የኤፍሬም አገር 17+1-13
- ዳን 18+1-37
- ጊብዓ 19+1-30
- ምጽጳ 20+1-21+25

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 44-48
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ትምህርት 12 ከገጽ 129-160
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ መጽሐፈ መሳፍንትን በሙሉ አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የመጽሐፈ መሳፍንት ዋና ዓላማና ይዘት ምንድን ነው ትላለህ?
2. መሳፍንት 21+25 በጥንቃቄ አንብብ። ከዚህ ክፍል ውስጥ የምታገኘው መልዕክት ምንድን ነው? ጥቅሱ የመጽሐፈ መሳፍንትን ዋና ዓላማ ከማወቅ ረገድ እንዴት ሊረዳህ ይችላል?
3. በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምን ይመስላል?
4. በጥናት መመሪያው ከተሰጡት ቁልፍ ሰዎች ውስጥ ሦስቱን በመምረጥ ከሕይወታቸውና ከአገልግሎታቸው ለራስህ የምታገኘውን ትምህርት ካለ በዝርዝር አስረዳ።
5. በጥናት መመሪያው ከቀረቡት ቁልፍ ሥፍራዎች ውስጥ አምስቱን በመምረጥ በሥፍራዎቹ ላይ የተፈጸሙትን ዓበይት ክንውኖች በአጭሩ ግለጽ።

## የመመዘኛ ፈተና

1. በመጽሐፉ ውስጥ እንዳየነው እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው መሳፍንት እንደማናቸውም ሰው ደካሞች ነበሩ። እግዚአብሔር በደካሞች የሚጠቀመው ለምን ይመስልሃል?
2. በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረበው ታሪክ ውስጥ የሳምሶንንና የጌዴዎንን ሕይወት አነጻጽር። ከዚህ ምን ትማራለህ?
3. በአዲስ ኪዳን ዘመን ላይ የክርስቲያኑ ውጊያ ከማን ጋር ነው? እንዴት ይከናወናል?



## የጥያቄዎች መልስ

1. መልስህን ከጥናት መመሪያው መግቢያ እና ከማስታወሻው ጋር አስተያየው።
2. የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች አልፎ ታላላቅ ሥራዎችን ሠርቷል። የተነሱት መሳፍንት እንደማናቸውም ሰው ደካሞች ሆነው እያሉ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው ታላላቅ ውጊያዎችን አድርገዋል፤ መርተዋል ሕዝቡን አስተዳድረዋል፤ (ፈርደዋል) ጠላቶቻቸውንም ድል ነስተዋል። የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት (መሳ. 3+10፤ 6+34፤ 11+29፤ 13+25፤ 14+6፤ 19፤ 15+14)።
3. የግል መልስ
4. የግል መልስ

# ትምህርት 7 - ሩት

## መግቢያ

መጽሐፈ ሩት በዘመነ መሳፍንት ውስጥ ስለነበረው እግዚአብሔርን የሚፈራ አንድ ቤተሰብ የሚያወራ የታሪክ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ ስለ ሩት፣ ኑኃሚንና ቦኤዝ ጽናት ያትታል። እነዚህ ሰዎች በዙሪያቸው በነበረው የሰዎች ውድቀትና ጥፋት ሳይወናበዱ ልባቸውን ጠብቀው አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ ሰዎች ነበሩ። መጽሐፈ ሩት ለዘመኑ ክርስቲያን ትልቅ መልዕክት አለው። ዓመጻና እርኩሰት በበዛበት ዘመንና ሰው እግዚአብሔርን በተወበት ዘመንም እርሱን በሚፈራ ማናቸውም ታናሽ ሰው ውስጥ እልፍ እንደሚሠራ ያሳያል። እንደዚሁም እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚመጣው ስለመሲሁ የትውልድ ሐረግ ቀጣይነት ሲጠነቀቅ እንመለከታለን (ማቴ. 1፥5፣ 6)።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፦

- እግዚአብሔር የሰዎችን እምነት እንደሚያከብር በሰዎችም ዕለታዊ ኑሮ ግድ እንደሚለው መረዳት ይችላል።
- ለሌሎች ለናስብ በእግዚአብሔር እንደምንታሰብ በመረዳት ለሌሎች ማሰብን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በሕይወቱ ለመለማመድ ቆርጦ ይነሳል።
- ከማጉረምረም ይልቅ እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም እንደሆነ ይረዳል። ጌታ በችግሮችም ውስጥ ክንዱን እንደሚገልጽ ይማራል።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

መጽሐፈ ሩት

- ጸሐፊው
- የተጻፈበት ዘመን
- ታሪካዊ አቀማመጡ (ዓውድ)
- ቁልፍ ጥቅስ
- ቁልፍ ቦታዎች



- ቁልፍ ቃላት
- ዓላማ
- የመጽሐፉ ልዩ ባሕርይ
- የመጽሐፈ ሩት ዋና ዋና ትምህርቶች

## ቁልፍ ጥቅስ

ሩት 1፥16

## ዋና ገጸ ባሕርያት

ሩት፣ ኑኃሚንና ቦኤዝ

## የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራዎች

- ሞአብ
- ቤተልሄም

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 49-51
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 1 ከገጽ 159-169
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ የመጽሐፈ ሩትን በጥንቃቄ አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የሩት መጽሐፍን ስታጠና ታማኝነት ስለተሞላበት ፍቅር ምን አስተዋልክ?
2. ከሌሎች መልካም ምክርን ስለመቀበል፣ ስለመስገስ፣ ስነሥርዓትንም ስለመጠበቅ ከሩት መጽሐፍ ምን ተማርክ?
3. በሮሜ 8፥28 የተጻፈውን ቃል በሩት መጽሐፍ ውስጥ እንዴት ተገልጾ ታገኘዋለህ?
4. በጥናት መመሪያው በተሰጡት ቁልፍ ሰዎች ላይ ተመርኩዘህ ስለማንነታቸው፣ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው የተማርከውን ያህል በአጭሩ አስረዳ።

5. በጥናት መመሪያው በተሰጡት ሁለት ቁልፍ ሥፍራዎች ላይ የተከናወኑትን ዓበይት ክንውኖች በአጭሩ አስቀምጥ::

## የመመዘኛ ፈተና

1. የቦኤዝ መቤዠት ለክርስቶስ መቤዠት ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው?

2. ሞአባዊቷ ሩት በክርስቶስ የዘር ግንድ ታሪክ ውስጥ ገባች ስንል ምን ማለታችን ነው?



## ጥያቄዎች መልስ

ኑሐሚን ምንም እንኳ ብትቸገር ሩትን በአገርዋ (ከዘመዶችዋ ጋር) እንድትሆን ስታስብላትና ስትጠነቀቅላት፤ ሩት ከራስዋ ይልቅ ኑሐሚንን ለመረዳት በማይመች ሁኔታ ውስጥ ቆርጣ ስትወጣ፣ ከታሪኩ ውስጥ የምናየው ፍቅርንና ታማኝነትን የሚገልጽ ተግባር ነው::

ከኑሃሚን ሕይወት-መልካም ምክርን መስገሥ፣ ከሩት-መስማትንና መታዘዝን፣ ቦኤዝ-ሥርዓትን ተከትሎ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማድረግን ከታሪኩ እናያለን::

እግዚአብሔር ለሚታመኑበት ጋሻ እንደሆነ ሁሉን ለበጐ እንደሚሰውጥ የኑሃሚንና የሩት ችግር ወደ ታላቅ በረከት የመለወጡ ታሪክ ሮሜ 8+28ን ጥቅስ ያብራራልናል::

መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህና ከማስታወሻው ጋር አስተያየው::

መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው::

# ትምህርት 8
# 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል

## መግቢያ

1ኛና 2ኛ ሳሙኤል በመጀመሪያው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ መጽሐፍነቱ የሚታወቅ ሲሆን በሂደት ግን በሁለት የመከፈሉ ድርጊት ተከናውኗል፡፡ በዚህ ትምህርት ግን እንደ አንድ መጽሐፍ ቀርቧል፡፡ በዚህ መጽሐፍም በመጀመሪያ የምናገኘው የዔሊንና የሳሙኤልን ታሪክ ሲሆን በቀጣዮቹ ምዕራፎች ግን የሳኦልንና የዳዊትን ሕይወት እንዲሁም ደግሞ በእስራኤል ላይ የአገዛዛቸውን ታሪክና ድምዳሜአቸውን የሚያስረዳን ይሆናል፡፡ መጽሐፉ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ አስከፊ ውጤት እንዳለው ከዔሊና ከሳኦል ፍጻሜ የሚያስጨብጠን ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ሳሙኤልና ዳዊት እግዚአብሔርን በመታዘዛቸው መጨረሻቸው መልካም እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፡-

- የመጽሐፉን መሠረታዊ አንድነትና የክፍፍሉን ሂደት ያውቃል፡፡
- በእስራኤል የንጉሥ አገዛዝ ታሪካዊ አጀማመሩን ይመለከታል፡፡
- ከሁለቱ ካህናትና (ዔሊና ሳሙኤል) ነገሥታት (ሳኦልና ዳዊት) ታሪክ ግንዛቤን ለማስጨበጥና የድል ፍጻሜ ምስጢር ለእግዚአብሔር መታዘዝ መሆኑን ለማስረገጥ ነው፡፡
- መታዘዝ ከሌለ መቀባት ብቻውን ከውድቀት ለመዳን ዋስትና እንደማይሆን ለመጠቆም ያመቻል፡፡
- እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ኪዳን ለማሳየትና ይህም ኪዳን በመጨረሻ በክርስቶስ ኢየሱስ እንደተፈጸመ ያረዳል፡፡

## አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- የመጽሐፉ አከፋፈል ታሪክ



- ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
- የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል አስተዋጽኦ
- ሥነ መለኮታዊ መልእክት

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 52-58
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 170-243
- ከመጽሐፍ ቅዱስ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤልን አንብብ፡፡

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የሳሙኤል መጽሐፍ እንዴት ለሁለት እንደተከፈለ የአከፋፈሉን ሂደት አብራራ፡፡
2. መጽሐፉን ሳሙኤል ስለመጻፉ ለምን የተለያዩ አመለካከቶች እንደተሰጡ ምክንያቱን ግለጽ፡፡
3. የሳኦል ውድቀት ዋና ምክንያት ምንድንነበር?
4. የዳዊትስ የድል ሕይወት ምስጢሩ ምንድን ነበር?
5. ሳኦል ከዳዊት የበለጠ ኃጢአት ሠርቷል ብለህ ታምናለህ? ካላመንክ ውድቀቱ ለምን አሳዛኝ እንደሆነ ግለጥ፡፡ ዳዊትስ ኃጢአቱ እንደዚያ ታላቅ ኃጢአተኛ ሆኖ ሳለ ፍጻሜው እንዴት ሊያምር ቻለ? ምክንያቱን ግለጥ፡፡

## የመመዘኛ ፈተና

1. ዳዊት በጐልያድ ላይ ድል ከመቀዳጀቱ አኳያ የምትማረውን ፍሬ ነገር በማብራራት ጻፍ፡፡
2. ሐና በመካንነት ቆይታ ሳሙኤልን የመውለዷን ጉዳይ ስታስብ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አንጻር ምን የሚገባህ ነገር አለህ?
3. ሳሙኤል ወደ እሴይ ቤት በተላከ ጊዜ ኤልያብን እግዚአብሔር የመረጠው መስሎት ሊሳሳት እንደነበር በሳሙ.16፥6-7 ላይ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ለምን ይመስልሃል? ከአገልግሎትህስ አንጻር ምን ዓይነት ጥንቃቄ መውሰድ ያለብህ ይመስልሃል?

## የጥያቄዎች መልስ

1. እንድታጠናው ከተሰጠህ ከ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ያለውን አንብብ።
2. አሁንም ከ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ጥናት ብታነብ ሳሙኤል መጽሐፉን ስለመጻፉ ለምን የተለያዩ አመለካከቶች እንደተፈጠሩ ምክንያቱን እንድትረዳ ይረዳሃል። በተጨማሪ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 172-173 ያለውን ክፍል አንብብ።
3. የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ያለመፈጸሙና ያለመታዘዙ ነው። 1ኛ ሳሙ. 13÷5-14፤ 15÷1-29፤ 16÷1፤ 14፤ እነዚህን ክፍሎች በማንበብ ለመልሱ እርግጠኛ ትሆናለህ። በተጨማሪም የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 179-180 አንብብ።
4. ፈጥኖ ንስሃ መግባቱ ነው (የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 177-178 አንብብ)።
5. የብሉይ ኪዳን ትመማ ከገጽ 177-180 ያለውን አንብብ።



1. በመሳፍንት አገዛዝ ዘመን እግዚአብሔር በመጨረሻ ቀብቶ ያስነሳው መስፍን ማን ይባላል?

2. ስለ መጽሐፉ በተሰጠህ ማስታወሻ መሠረት የሳሙኤል መጽሐፍ የተጻፈው፡-
   ሀ. በ850 ዓ.ዓ.
   ለ. በ950 ዓ.ዓ.
   ሐ. በ930 ዓ.ዓ.
   መ. መልሱ የለም።

እውነት/ውሸት በማለት መልስ

3. ሳኦል መሞቱን የሚነግረን 1ኛ ሳሙኤል ነው።

## የጥያቄዎቹ መልስ

1. ሳሙኤል
2. ሐ. በ930 ዓ.ዓ.
3. እውነት

# ትምህርት 9

# መጽሐፈ ነገሥት (1ኛ እና 2ኛ)

## መግቢያ

የመጽሐፈ ነገሥት መጻሕፍት ስለ እስራኤልና ይሁዳ ነገሥታት ማንነት እና የግዛት ዘመን ያትታሉ። በተለይ ለእግዚአብሔር የሚገዙትና የማይገዙት ነገሥታት ሕይወትና የግዛት ዘመን በማነጻጸር ያቀርባል። ከዚህም በተጨማሪ በእስራኤልና በይሁዳ የነገሡት ነገሥታት በወሰዷቸው እርምጃዎች ማለትም እግዚአብሔርን መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ ምን ያህል በምድራቱና በሕዝቡ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳረፈ ማየት እንችላለን።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፦

- የመጽሐፉን ዋና ዓላማ በመረዳት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር ብቻ መኖር እንዳለበት ይገነዘባል። ከመጀመር ይልቅ መጨረስ ትልቅ ነገር መሆኑን ስለሚረዳ ዕለት ዕለት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ይተጋል።
- ከእስራኤልና ከይሁዳ ነገሥታት የአመራር ልምምድ በመነሳት በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለው ኃላፊነት የተሻሉ የአመራር መርሆዎችን ያገኛል።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- ፀሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ (የ1ኛና 2ኛ ነገሥት)
- የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት
- እግዚአብሔር
  - የእግዚአብሔር የታሪክ ባለቤትነት
  - የእግዚአብሔር አዳኝነት
  - የእግዚአብሔር ድምጽ በነቢያት ተሰተጋብቷል
  - የእግዚአብሔር ቅን ፈራጅነት ይታያል።



## ቁልፍ ጥቅሶች

1ኛ ነገሥት 9+4፣ 5
2ኛ ነገሥት 17+13፣ 14

## ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት

### 1ኛ ነገሥት

- ዳዊት
- ሰለሞን
- ሮብዓም
- ኢዮርብዓም
- ኤልያስ
- አክዓብ
- ኤልዛቤል

### 2ኛ ነገሥት

- ኤልያስ
- ኤልሳዕ
- ሱናማይቷ ሴት
- ንዕማን
- ኤልዛቤል
- ኢዩ
- ኢዮአስ
- ሕዝቅያስ
- ሰናክሬም
- ኢሳይያስ
- ምናሴ
- ኢዮስያስ
- ኢዮአቄም
- ሰደቅያስ
- ናቡከደነጾር

## የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራዎች

### 1ኛ ነገሥት

- ሴኬም 1+1-11+25
- እስራኤል 12+20፣25
- ይሁዳ 12+21-24
- ኢየሩሳሌም 12+26፣ 27
- ዳን. 12+28፣ 29
- ቤቴል 12+2?-15+26
- ቴርሳ 15+27-16+22
- ሰማርያ 16+23-34
- የቀርሜሎስ ተራራ 17+1-18+46
- ዜማት ዘገለዓድ 20+1-22+53

### 2ኛ ነገሥት

- ኢያሪኮ 1+1-2+25
- የኤዶም ምድረበዳ 3+1-27
- ሱነም 4+1-37
- ጌልጌላ 4+38-6+7
- ዶታይን 6+8-23
- ሰማርያ 6+24-7+20
- ደማስቆ 8+1-29
- ሬማት ዘገለዓድ 9+1-11+1
- ኢየሩሳሌም 11+2-13፣ 19፣ 18+1-25+30

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን እሰሳ ከገጽ 59-65
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3 ከገጽ 1-74
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥትን በጥንቃቄ አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የ1ኛና 2ኛ ነገሥት መጽሐፍን ዋና ሃሣብ እንዴት ትረዳዋለህ?
2. በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የመጽሐፉ ስም «ነገሥት» ተብሎ መተርጎሙ ስለመጽሐፉ ይዘት ምን ሊያመለክት ይችላል ትላለህ?
3. በ1ኛ ነገሥት ላይ እንደምንመለከተው የእስራኤል ግዛት ለሁለት ተከፍሏል፣ /የሰሜኑ ክፍለ ግዛት እስራኤል እና የደቡቡ ክፍለ ግዛት ይሁዳ/ ከዚህ ምን ትማራለህ?
4. በ2ኛ ነገሥት ውስጥ ከተጠቀሱት ነቢያት ትልቁን ሥፍራ የሚይዘው ነቢዩ ኤርሚያስ ነው። በተከፈለው የደቡቡ የይሁዳ ግዛት እስከ ባቢሎን ምርኮ ባሉት ዘመናት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን አገልግሏል። ከዚህ ነብይ ሕይወትና አገልግሎት ምን ትማራለህ?
5. በጥናት መመሪያው ከተሰጡት ቁልፍ ሰዎች ውስጥ ሶስቱን (ሁለቱን ከ1ኛ ነገሥት አንዱን ከ2ኛ ነገሥት) በመምረጥ ከሕይወታቸውና ከአገልግሎታቸው ለራስህ የምታገኘው ትምህርት ካለ በዝርዝር አስረዳ።
6. በጥናት መመሪያው ከተሰጡት ቁልፍ ሥፍራዎች ውስጥ አራቱን (ሁለቱን ከ1ኛ ነገሥት ሁለቱን ከ2ኛ ነገሥት) በመምረጥ በሥፍራዎቹ ላይ የተከናውኑትን ዓበይት ፍጻሜዎች በአጭሩ ግለጽ።

## የመመዘኛ ፈተና

1. አንድ የነበረው መንግሥት ለሁለት የተከፈለበትን ምክንያት ስትመለከትና የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ምርኮ መወሰድ ስታይ አሁን ላለችው ቤተክርስቲያን ምን መልዕክት ይኖረዋል ብለህ ታስባለህ?



2. ሁለቱ የይሁዳ ነገሥታት ሕዝቅያስና ኢዮስያስ ያካሄዱት መንፈሳዊ ተሐድሶ በ2ኛ ነገሥት ከሰፈረው ታሪክ ውስጥ አንዱ ነው። ከዚህ መንፈሳዊ ተሃድሶ እንቅስቃሴ ምን ትማራለህ? ሁለቱ ነገሥታት የወሰዱት እርምጃ ምን ነበር? እርምጃው ለአሁኗ ቤተክርስቲያን የሚያስተላልፈው መልዕክት ይኖራል? (2ኛ ነገሥት 18+1-8 እና 22+1-23+30)

## የጥያቄዎች መልስ

1. የመጽሐፈ ነገሥት መጽሐፍ የእስራኤልንና የይሁዳን ነገሥታት ሕይወትና የግዛት ዘመን በሰፊው ይዘግባሉ::
2. የመጽሐፉ ስያሜ ስለ ጠቅላላ ይዘቱ ፍንጭ የሚሰጥ ነው:: ይኸውም ስለ እስራኤልና ይሁዳ ነገሥታት የግዛት ዘመንና ሕይወት በሰፊው እንደሚተርክ ያሳያል::
3. ይህ የሆነው ከንጉሥ ሰለሞን ውድቀት በኋላ ነው:: ስለዚህም ግዛቱ የተከፋፈለው ከኃጢአት የተነሳ እንደሆነ እንረዳለን::
4. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው (በተለይ በ2ኛ ነገሥት ላይ አትኩር)::
5. መልስህን ከጥናት መመሪያውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው::
6. መልስህን ከጥናት መመሪያውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አሰተያየው::



# ትምህርት 10
# ዜና መዋዕል (1ኛ እና 2ኛ)

## መግቢያ

ምንም እንኳ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል የተጻፈው ታሪክ በሌሎች (ለምሳሌ በ1ኛና 2ኛ ነገሥት፣ በ2ኛ ሳሙኤል) የታሪክ መጻሕፍት ተጽፎ ቢገኝም፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ይህ መጽሐፍ ከአዲስ ዕይታ አንጻር እንዲጻፍ ማድረጉ ከመጽሐፉ ይዘት መረዳት እንችላለን:: መጽሐፉ ከምርኮ ዘመን መልስ በኋላ የተጻፈ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደገና በእውነተኛ አምልኮ ዙሪያ አንድ በማድረጉ ላይ ያተኩራል:: በመሆኑም 1ኛ ዜና መዋዕል በይሁዳና በእስራኤል አገሮች መንፈሳዊ የታሪክ ዓውድ ላይ ሲያተኩር 2ኛ ዜና መዋዕል ደግሞ በክህነት አገልግሎት፣ በቤተመቅደሱ አገልግሎትና በይሁዳ ምድር በተካሄዱት መንፈሳዊ መነቃቃቶች (መታደስ) ላይ ያተኩራል:: እንደዚሁም በ2ኛ ዜና መዋዕል ላይ በይሁዳ ምድር ስለነገሱት ነገሥታትና በእግዚአብሔር የሕግ ሚዛን ተመዝነው የተገኙበት ሁኔታን በሰፊው ተዘግቦ እናገኛለን:: እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለኖሩት ነገሥታትና በዘመናቸው ስላካሄዷቸው መንፈሳዊ መነቃቃቶችም በስፋት ተዳሷል:: (በ2ኛ ዜና መዋዕል የሰሜኑ ክፍለ ግዛት ማለትም የእስራኤል አገር ብዙ ትኩረት አልተሰጠውም)::

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ:-

- የ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ዋና ዓላማን ይረዳል:: በተለይ መጽሐፉ ከመጽሐፈ ነገሥትና ከመጽሐፈ ሳሙኤል ጋር ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ስለሚገነዘብ በእነዚህ የታሪክ መጻሕፍት ላይ ያለው መረዳት ይጨምራል::
- ስለትክክለኛ አምልኮና መንፈሳዊ መነቃቃት ምንነት ከታሪኩ ስለሚማር በሕይወቱ አወንታዊ ለውጥ ያያል::
- በተለያየ የአመራር ኃላፊነት ላይ ያሉት ሰዎች (የሚያምኑትም የማያምኑትም) ለሚወስዷቸው እርምጃዎች በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ መሆናቸውን ስለሚገነዘብ በአገልግሎት ውስጥ ባለው የአመራር ኃላፊነቱ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ማስተዋልና መጠንቀቅ እንዳለበት ይረዳል::

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- ጸሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
- አስተዋጽኦ (የ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል)
- የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት
    - የዳዊት ንግሥና
    - የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
    - የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ
    - አሕዛብ
- የመጽሐፉ ዋና ዓላማ
- ማጠቃለያ

## ቁልፍ ጥቅሶች

1ኛ ዜና መዋዕል 14፥2 «ስለ ሕዝቡም ስለ እስራኤል መንግሥቱ ከፍ ብሎአልና እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጐ እንዳጸናው ዳዊት አወቀ።»

2ኛ ዜና መዋዕል 7፥14 «... በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢፀልዩ ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።»

## ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት

### 1ኛ ዜና መዋዕል

- ዳዊት
- ሰለሞን

### 2ኛ ዜና መዋዕል

- ሰሎሞን
- የሳባ ንግሥት
- ሮብዓም
- አሳ
- ኢዮሳፍጥ
- ኢዮራም
- ኢዩአስ
- ያዝያን
- ሕዝቅያስ
- ምናሴ
- ኢሳይያስ



## የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራዎች

### 1ኛ ዜና መዋዕል

- ኢየሩሳሌም (ቤተመቅደሱ) 11፥4-12፥40
- ቁርያት ይዓሪም 13፥1-14
- ጢሮስ 14፥1-17፥27
- በአልፐራሲም 14፥11-17፤ 15፥1-17፥27፤ 18፥1-29፥30

### 2ኛ ዜና መዋዕል

- ገባዖን 1፥፥1-12
- ኢየሩሳሌም 1፥13-9፥31 (ቤተመቅደሱ)
- ሴኬም 10፥1-12፥16
- ተራራማው የኤፍሬም አገር 13፥1-22
- ሰማርያ 17፥1-18፥27
- ሬማት ዘገለዓድ 18፥28-22፥9

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 66-69
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3 ከገጽ 75-95 ያለውን ክፍል በጥንቃቄ አንብብ።
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ የ1ኛና 2ኛ ዜና መጻሕፍትን በጥንቃቄ አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. የ1ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍን ከ2ኛ ሳሙኤል መጽሐፍ ጋር ለማስተያየት ሞክር። ያስተዋልከውን ነገር በአጭሩ አስረዳ።
2. የ1ኛና የ2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ጠቅላላ ይዘት በአራት ዓበይት ነጥቦች ዙሪያ ለመዳሰስ ሞክረናል። በእነዚህ በተሰጡት አራት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ያለህን የራስህን መረዳት በአጭሩ አብራራ።
3. የ2ኛ ዜና መዋዕል ቁልፍ ጥቅስ 7፥14ትን በጥንቃቄ ካነበብክ በኋላ በቤተክርስቲያንህ ካሉት ከሌሎች ወገኖች ጋር አንድ ላይ ስለቃሉ ምንነትና አሁን ላለችው ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊኖረው ስለሚችለው መልዕክት ተነጋገሩበት።
4. በጥናት መመሪያው ላይ ከተሰጡት ቁልፍ ሰዎች ሦስቱን በመምረጥ ስለአገልግሎታቸውና ስለሕይወታቸው ከታሪኩ ውስጥ የምታገኘው ትምህርት ከራስህ ሕይወትና አገልግሎት ጋር በማዛመድ በአጭሩ አስረዳ።
5. በጥናት መመሪያው ላይ ከተጠቀሱት ቁልፍ ሥፍራዎች ውስጥ ሦስቱን በመምረጥ በሥፍራዎቹ ላይ ስለተከናወኑት ዓበይት ፍጻሜዎች በአጭሩ አስረዳ።

## የመመዘኛ ፈተና

1. በ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን፤ ስለቤተመቅደሱና ስለአምልኮ፤ እንደዚሁም ስለዳዊት ቤት ስርወ መንግሥት (ዘውዳዊ አገዛዝ) ምን ትገነዘባለህ? በእነዚህ ሦስት ዓበይት ነጥቦች መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?

2. በ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ላይ ስለ እውነተኛ አምልኮ ምን ትማራለህ?



## ጥያቄዎች መልስ

1. 1ኛ ዜና መዋዕል ከ2ኛ ሳሙኤል መጽሐፍ ይዘት ጋር በአመዛኙ ይመሳሰላል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ዜና መዋዕል ከምርኮ ዘመን በኋላ የተጻፈ በመሆኑ የ2ኛ ሳሙኤል መጽሐፍ ታሪክን ይበልጥ በማብራራት ይገልጸዋል፡፡ (በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስህን ተመልከት)

2. መልስህን ከ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ማስታወሻ ጋር አስተያየው፡፡

3. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው ፡፡

4. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው፡፡

# ትምህርት 11

## መጽሐፈ ዕዝራ

### መግቢያ

በመጽሐፈ ዕዝራ ላይ ተጽፎ የምናነብበው ታሪክ ወጥ የሆነ ተከታታይነት ያለው ታሪክ ሳይሆን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ከተከሰቱት ጉዳዮች መካከል ጸሐፊው ዐበይት ናቸው ያላቸውን መርጦ ያሰፈራቸው ታሪኮች ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ሲኖሩ እነርሱም የአይሁድ ወደምድራቸው ተመልሶ መግባትና የመንፈሳዊ ሕይወታቸው መታደስ ናቸው።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፦

- የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የታሪክ ባለቤትነትን ስለሚገነዘብ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ለሚገጥሙት ተግዳሮቶች ሳይንበረከክ በእግዚአብሔር መደገፍን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ በሕይወቱ ይለማመዳል።
- እውነተኛ መንፈሳዊ መታደስ (መነቃቃት) በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት እንደሚመጣ ስለሚረዳ ለእግዚአብሔር ቃል በሕይወቱና በአገልግሎቱ ቅድሚያ እንዲኖረው ከበፊቱ ይበልጥ ይተጋል።
- የመጽሐፈ ዕዝራን ዋና ዓላማ ስለሚረዳ ለሌሎች በተሻለ መንገድ የመጽሐፉን መልዕክት ለማስተላለፍ ይችላል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- ፀሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
- አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘት
- ማጠቃለያ



### የመጽሐፉ ቁልፍ ጥቅስ

ዕዝራ 6፥21፣ 22

### ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት

ቂሮስ፣ ዘሩባቤል፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ዳርዮስ፣ አርቴክሲስና ዕዝራ

### የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራዎች

- ባቢሎን
- ኢየሩሳሌም

### የምንባቡ ክፍሎች

- ከብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 70-72
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3 ከገጽ 96-120
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ በማስታወሻው በተሰጠው የመጽሐፉ አስተዋጽኦ ላይ በመመርኮዝ መጽሐፈ ዕዝራን በጥንቃቄ አንብብ።

### የጥናት ጥያቄዎች

1. መጽሐፈ ዕዝራ ውስጥ ከምዕራፍ 1-6 ያለው ክፍል በዘሩባቤል መሪነት ስለተደረገው ስለመጀመሪያው ዙር ከምርኮ አገር መመለስ ሲናገር ከምዕራፍ 7-10 ያለው ክፍል ደግሞ በዕዝራ መሪነት ስለተደረገው ስለሁለተኛው ዙር ከምርኮ አገር መልስ ይናገራል። በእነዚህ ሁለት የታሪክ ምዕራፎች ላይ የተከናወኑት ዓበይት ክንውኖች ምን ነበሩ?
2. ዕዝራ ለአይሁድ መንፈሳዊ ሕይወት መታደስ የተጠቀመበት ዋነኛ ዘዴ ምንድነበር?
3. የቤተክርስቲያን መሪዎች ከመጽሐፈ ዕዝራ ስለመሪነት ምን ሊማሩ እንደሚችሉ ከጓደኛህ ጋር ተወያዩበት።

4. በጥናት መመሪያው ከተሰጡት ቁልፍ ሰዎች ውስጥ የሦስቱን በመምረጥ ስለሕይወታቸውና ስለአገልግሎታቸው የተገነዘብከው ጠቃሚ ነገር ከራስህ ሕይወትና አገልግሎት ጋር በማዛመድ በአጭሩ አስረዳ::

5. በጥናት መመሪያው በተሰጡት ሁለት ቁልፍ ሥፍራዎች ማለትም ባቢሎንና ኢየሩሳሌም ላይ የተከናወኑትን ዓበይት ፍጻሜዎች በአጭሩ ግለጽ::

## የመመዘኛ ፈተና

1. እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል እንደሚፈጽም ግልጽ ነው:: ከመጽሐፈ ዕዝራ ውስጥ ይህንን አስመልክቶ ምን ተምረሃል?

2. ከዕዝራ ሕይወት በመነሳት ለዛሬዋ ቤተክርስቲያን ሊጠቅሙ የሚችሉ ሦስት የአገልጋይ ባህሪያትን ዘርዝር::



## የጥያቄዎች መልስ

1. በመጀመሪያው መመለስ የተሰራው ትልቅ ነገር የቤተመቅደሱ ዳግም-ግንባታ ይኸውም በዘሩባቤል መሪነት ሲሆን፤ ከሁለተኛው የምርኮ አገር መልስ በኋላ ደግሞ ሕዝቡን ወደ ንስሐና መታደስ የመመለሱ እንቅስቃሴ ይኸውም በዕዝራ አማካኝነት የተካሄደው ትልቅ ክንዋኔ ነበር::

2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጽሐፈ ዕዝራ ምዕራፍ 9 እና 10ን ተመልከት::

3. የግል ውይይት

4. መልስህን ከማስታወሻውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው::

5. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው::

# ትምህርት 11

## ነህምያ

### መግቢያ

በመጽሐፈ ነህምያ ላይ በዋነኛነት የምንመለከተው ሃሣብ የኢየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ መገንባት ሲሆን ነህምያም ይህንን ሥራ በኃላፊነት እንደመራው ያሳየናል። በተጨማሪም ይህ የነህምያና የዕዝራ መጽሐፍት እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ አፍ እንደተናገረው (ኤር. 29፥10-14) የምርኮውን ዘመን ፍጻሜ ታሪክ የሚያስገነዝቡን መጽሐፍት ናቸው። በሁለቱም መጻሕፍት ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የምናገኘው ሌላው ታሪክ ደግሞ የአይሁድን መንፈሳዊ ኑሮና ሕይወት መታደስ ይሆናል።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፡-

- በመጽሐፈ ነህምያ ላይ የተጻፈውን ታሪክ እና የታሪኩን ዓላማ በሚገባ ይረዳል። በተጨማሪም የመጽሐፉን ታሪካዊ ይዘትና አገባብ ስለሚገነዘብ መጽሐፉን እንደሚገባ ለመተርጎም ይችላል።

- አንድ መሪ አገልጋይ ምን ዓይነት ሕይወት ሊኖረው እንደሚገባ ይገነዘባል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መግቢያ
- የጻሐፊውና የተጻፈበት ዘመን
- አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት
- ማጠቃለያ

### ቁልፍ ጥቅስ

ነህ. 6፥15፤ 16፤ 2፥17



### ዋና ገጸ ባሕርያት

- ነህምያ፤ ዕዝራ፤ ሰንበላጥና ጦቢያ

### የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራ

- ኢየሩሳሌም

### የምንባብ ክፍሎች

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጽሐፈ ነህምያን
- ከብሉይ ኪዳን እስሳ ከገጽ 73-77
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3ን ከገጽ 121-137 አንብብ።

### የጥናት ጥያቄዎች

1. ነህምያ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ምን እንዳደረገና በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ዋና ዋና ጉዳዮች ምን እንደሆኑ አስረዳ?

2. ከጠላቶቹ የገጠሙት ተግዳሮቶች ነህምያን ጠቅመውታል ወይስ ጎድተውታል? ምክንያቱ ይገለጽ።

3. በመጽሐፈ ነህምያ ኋለኛ ምዕራፎች ላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ለማስፈጸም (የሰዎችን ሕይወት ለማበርታት) ነህምያ የተጠቀመውን ዘዴ አስረዳ።

4. በጥናት መመሪያው ከተሰጡት ቁልፍ ሰዎች ውስጥ ሁለቱን በመምረጥ ከሕይወታቸውና ከአገልግሎታቸው (ወይም በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላትነታቸው) የምትማረው ትምህርት ምንድነው?

5. በጥናት መመሪያው ስለተሰጠው ብቸኛ ቁልፍ ሥፍራ ኢየሩሳሌም ከመጽሐፉ ምን ትማራለህ? በኢየሩሳሌም የተከናወኑት ዓበይት ፍጻሜዎች ምን ምን ነበሩ?

### የመመዘኛ ፈተና

1. ጠቅለል ባለ መልኩ የመጽሐፈ ነህምያን ዋና ዋና ሃሣቦች አስቀምጥ

## የጥያቄዎች መልስ

1. በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ1 በተጨማሪ መልስህ ከመጽሐፍቶቹ ጋር አስተያየው።
2. ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።
3. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር አዛምደው።
4. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።
5. መልስህን ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።



# ትምህርት 12

# መጽሐፈ አስቴር

### መግቢያ

ይህን መጽሐፍ ለመረዳት ንግሥቲቱ አስቴርን የቤተክርስቲያን አምሳያ፣ ንጉሡ አርጤክስስን ደግሞ የክርስቶስ አምሳያ በማድረግ መተርጐሙ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን እነዚህ ሰዎች አምሳያ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ጥቅስም ሆነ ሃሣብ የለም። ስለዚህ ጽሑፉ የያዘውን መልዕክት ሳናሳንስ ወይም ሳናሳድግ በማስተዋል የእግዚአብሔርን ታዳጊነትንና ከሰዎቹም ታሪክ የምንማረው መታመንን ሊሆን ይገባል።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይኸን ክፍል ሲያጠናቅቅ፡-

- መጽሐፈ አስቴር የተጻፈበትን ሁኔታና ታሪክ ይረዳል።
- ስለእግዚአብሔር ታዳጊነት ከታሪኩ ውስጥ ስለሚማር በሚገጥመው ፈተናና መከራ ሁሉ ፀንቶ መቆምን በሕይወቱ ይለማመዳል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መልዕክቱ
- ቁልፍ ጥቅስ
- ፀሐፊው
- የመጽሐፉ ዓላማ
- አስተዋጽኦ
- የስነ መለኮታዊ መልእክት
- ዋና ገጸ ባሕርያት

### ዋና ገጸ ባሕርያት

- አስቴር
- መርዶክዮስ

- ንጉሥ አርጤክሲስ
- ሐማ

## የመጽሐፉ ቁልፍ ሥፍራ

በሱሳ (በፋርስ) የነበረው የንጉሱ ቤተመንግሥት

## የምንባብ ክፍሎች

- ከብሉይ ኪዳን ትመማ 1ኛ መጽሐፍ ክፍል 3 ከገጽ 138-154
- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 78-79
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ የመጽሐፈ አስቴርን ክፍል በጥንቃቄ አንብብ::

## የጥናት ጥያቄዎች

1. መጽሐፈ አስቴር ከአይሁድ ውጭ ሌላ የየትኛውን መንግሥት ታሪክ ዘግቧል?
2. በጥናታችን መሠረት ስለአስቴር መጽሐፍ ፀሐፊ የሚታወቀው ምንድን ነው?
3. በመጽሐፈ አስቴር የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም ታዲያ ይህ ሁኔታ አምላክ ለሕዝቡ ያደረገውን መልካም ጥበቃ ያስከዳል?
4. በጥናት መመሪያው ላይ ከተጠቀሱት የታሪኩ ቁልፍ ሰዎች ውስጥ ሁለቱን በመምረጥ ከሕይወቸውና ከሠሩት ነገር ለራስህ የምታገኘውን ትምህርት አስረዳ::

## የመመዘኛ ፈተና

1. ንግሥት አስቴር ለምን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አምሳያ መሆን እንደማትችል ማብራሪያ ስጥበት::



## የጥያቄዎች መልስ

1. የፋርስ መንግሥትን
2. ፀሐፊው ማን እንደሆነ ባይታወቅም የፋርስን መንግሥት ባሕል በሚገባ የሚያውቅ አይሁዳዊ ሰው እንደሆነ ይገመታል::
3. አያስከድም፤ እንዲያውም በታሪኩ በጉልህ ሰፍሮ እንደምናየው እግዚአብሔር ሕዝቡን ታድጓል::
4. የግል መልስ

# III. የቅኔ መጻሕፍት

## ትምህርት 13 - ኢዮብ

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት የኢዮብ መጽሐፍ ከሌሎች ጽሑፎች ለየት የሚያደረገው ነጥብ፣ የምልልሶቹ ምንነትና አስፈላጊነት፣ የአተረጓጐም መመሪያ፣ ቁልፍ ጥቅሶች፣ አስተዋጽኦ፣ የመጽሐፉ ዓላማ በበቂ ሁኔታ፣ ሰፍሯል። ደግሞም ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጻድቅ ሰው ስለነበር በመከራ ወቅት በትዕግሥት ፀንቶ መባረክን ያስገነዝባል።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ:-

- የኢዮብን መጽሐፍ ዋና ዓለማ ይገነዘባል።
- ለምን መጽሐፉ ኢዮብን ከፔንታቱክ ጋር እንደደምናጠና ይረዳል።
- ለመከራ ተገቢውን ትርጉም መስጠት ይችላል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- መጽሐፈ ኢዮብ
- መቼና በማን ተጻፈ?
- ቁልፍ ጥቅሶች
- አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ ዓላማ

### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 80-83
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 1 ከገጽ 31-59፣
- ከመጽሐፍ ቅዱስ የኢዮብን መጽሐፍ በሙሉ አንብብ።

### የጥናት ጥያቄዎች

1. የኢዮብን መጽሐፍ ከሌሎች የጥበብ መጽሐፍት ለየት የሚያደርገው ነጥብ ምንድን ነው?



2 ለምን መጽሐፈ ኢዮብን ከፔንታቱክ ጋር እናጠናዋለን?

3. የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብ ላይ የደረሰው መከራ መንስዔ እንዴት ተረድተውታል?

### የመመዘኛ ፈተና

1. በዚህ ዘመን «ክርስቲያንና መከራን» በተመለከተ የሚሰነዘሩ አስተሳሰቦችን በዝርዝር ጻፍ። ቀጥሎም ጠንካራና ደካማ ጐናቸውን በማውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ስጥባቸው።

2. ለምን የኢዮብ መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ የቅኔ መጽሐፍ አይደለም ተባለ?

### የጥያቄዎች መልስ

1. የተጻፈበት ዘመን
2. ታሪኩ የተፈጸመው በጥንት አባቶች ዘመን ስለሆነ ነው።
3. በኢዮብ ኃጢአት ምክንያት የደረሰ ውጤት ነው ብለው ስለተረዱ ነው።



# ትምህርት 14

## መዝሙረ ዳዊት

### መግቢያ

በተለያዩ ጸሐፊዎች የተጻፉት መዝሙራት በእግዚአብሔር ላይ መታመንን ያስተምሩናል። መዝሙራት የሰውን ድካምና የእግዚአብሔርን ብርታት ያሳዩናል። በዘመናት የማይቀያየረውን ዓለም አቀፋዊ የሰው ባሕርይ ያመለክታሉ። በው ኃጢአተኛና ክፋት የሞላበት ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ከፍጥረት ሁሉ በላይ አከብሮታል።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ:-

- መዝሙረ ዳዊት በእነማንና እንዴት እንደተጻፈ ማወቅ
- የመዝሙረ ዳዊትን የስነጽሑ ይዘት በመረዳት መተርጉም ይችላል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- የጽሑፍ ይዘት
- የመዝሙራት ዓይነቶች
- ጸሐፊ
- አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ ዓላማና ዋና አሳብ

### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን ት.መ.ማ. 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 1፣ ከገጽ 60-79

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 84-86

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በድሮው ትርጉም መዝሙረ ዳዊትን ተመልከት።

### የጥናት ጥያቄዎች

1. በመዝሙረ ዳዊት ከተካተቱት መዝሙሮች ምን ያህሉ በዳዊት ተጻፉ?

2. በመዝሙረ ዳዊት ስንት ምዕራፎች አሉ?

3. በመዝሙረ ዳዊት ያሉትን የመዝሙሮች ይዘት ዓይነት ዘርዝሩ

4. በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ምን ያህሉ ከመዝሙረ ዳዊት ናቸው?

5. ይህን የመዝሙር መጽሐፍ በአንድ ላይ ለመጠረዝ ምን ያህል ዓመታት ፈጀ?

## የመመዘኛ ፈተና

1. በአሁኑ ዘመን መዝሙር በቤተክርስቲያን ያለውን ሥፍራ በሰዎችም ሕይወት ያለውን መልካም ተጽዕኖ በመገምገምና ከመዝሙረ ዳዊት ጋር በማነጻጸር ሊደረጉ የሚገቡ ነጥቦችን ጻፍ።

## የጥያቄዎች መልስ

1. 73 ምዕራፎች በዳዊት ተጻፉ
2. 150
3. የታሪክ፣ የህግ፣ የምሥጋና፣ የልመና እና የመመሳሰሉት ናቸው
4. 116
5. 1000 ዓመታት ፈጅቷል።



# ትምህርት 15

## ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልዩ

### መግቢያ

እነዚህን ሦስት የጥበብና የቅኔ መጻሕፍት ንጉሥ ሰለሞን በተለያዩ የዕድሜ ዘመኑ ማለትም በወጣትነቱ፣ በጉልማሳነቱና በእርጅናው ዘመኑ የጻፋቸው ናቸው። ይህንን ትምህርት በማጥናት ተግባራዊ በሆነው ዕለታዊ ሕይወት ጠቃሚ ምክርና መመሪያን ማግኘት የአንባቢው ድርሻ ነው።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፦

- ሦስቱ መጻሕፍት እንዴት፣ መቼና በማን እንደተጻፉ ይረዳል፣
- የጸሐፊዎቹን ታሪካዊ አውድ ያስገነዝባል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

ምሳሌ
- በማንና መቼ ተጻፉ
- የመጽሐፉ ዓላማዎች
- ተደራሲያን
- የጽሑፉ ይዘት
- አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ አጠናን ዘዴ

መክብብ
- ማን ጻፈው
- ቁልፍ ጥቅስ
- የመጽሐፉ ዋና ዓላማ
- አስተዋጽኦ

መኃልዩ መኃልዩ
- በማንና መቼ ተጻፈ?
- የመጽሐፉ ዓላማ
- አስተዋጽኦ

### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን ት.መ.ማ. 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 1ን ከገጽ 80-104

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 87-94
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ከምሳሌ መክብብና መኃልዩ ዘሰሎሞን መጽሐፍት አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. መጽሐፈ ምሳሌ ስለዕውቀትና ስለጥበብ ሲናገር የሁሉም ጌታና ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን የገለፀበት ጥቅስ ምን የሚለው ነው?

2. በመጽሐፈ ምሳሌ ፀሐፊው መልዕክቱን፤ምክሩን/ ሲጽፍ አንባቢዎቹን ምን ብሉ ይጠራቸዋል?

3. የመክብብ መጽሐፍ ዋና መልዕክቱ ምንድን ነው?

4. ንጉሥ ሰለሞን የመክብብን መጽሐፍ የጻፈው በየትኛው የሕይወቱ ዘመን ነው?

5. ስለመኃልየ መኃልዩ መልዕክት ከሦስት በላይ የተሰያዩ አስተያየቶች አሉ፡፡ እነዚህም:-

## የመመዘኛ ፈተና

1. የመጽሐፈ ምሳሌ አጻጻፍ ይዘትን ዘርዝር
2. የመክብብን መጽሐፍ ንጉሥ ሰለሞን ጻፈው ቢባልም፤ ሰለሞን አልጻፈም የሚሉ ሰዎች ምክንያታቸው ምንድን ነው?



## የጥያቄዎች መልስ

1. ጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ምሣ. 1፥7
2. ልጆቼ
3. እግዚአብሔር በሰጠህ ሕይወት ተደሰትበት
4. በእርጅና ዘመኑ ነው
5. ሀ. ስለእግዚአብሔርና እስራኤል
   ለ. ስለክርስቶስና ቤተክርስቲያን
   ሐ. ስለሁለት ፍቅረኛሞች

# IV. ታላላቅ ነቢያት

## ትምህርት 16

## ኢሳይያስ

### መግቢያ

ትንቢተ ኢሳይያስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ8ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ (740-681) ነቢይ ሆኖ ባገለገለ የዓሞጽ ልጅ ኢሳይያስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው:: መጽሐፉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደብ ይችላል:: ከም. 1-39 ያለው ክፍል የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእርሱ ባለመታዘዛቸው ምክንያት ፍርድ እንደሚመጣ የሚናገር ክፍል ነው:: ከምዕራፍ 40-66 ያለው ክፍል ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን በምሕረት የሚጐበኝበት ዘመን እንደሚመጣ፣ ሰላም የሚሰፍንበትና በፍጹምነት የሚያስተዳድር ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ የሚመጣበት ጊዜን የሚያመለክት ነው:: እግዚአብሔር በቅድስናው የከበረ አምላክ መሆኑም የተገለጠበት መጽሐፍ ነው::

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ:-

- ስለኢሳይያስ መጽሐፍ መልእክት አጠቃላይ ግንዛቤ ያገኛል::
- የእግዚአብሔር ቅድስና በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያመጣውን ለውጥ ይረዳል::
- ስለመሲሁ የተሰጡትን የትንቢት ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ካለው ከትንቢት ፍጻሜ ጋር በማገናዘብ ያስተምራል::
- በእግዚአብሔር ላይ መታመን ደህንነትን የሚያስገኝ መሆኑን ያብራራል::

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- ፍርድና መቤዠትን ያመጣው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው
- የኢሳይያስ አስተዋጽኦ
- የመጽሐፉ ቁልፍ ቃላትና ጥቅሶች



- ሥነ መለኮታዊ መልእክት

### ቁልፍ ጥቅሶችና ሐረጉች

ኢሳ. 6፥3፤ 53፥5፤ 61፥1-3 «የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር» ተደጋጋሚ ሐረግ ነው::

### ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት

ኢሳይያስ እና ሁለቱ ልጆቹ

### የምንባብ ክፍሎች

- መጽሐፍ ቅዱስ፣ ትንቢተ ኢሳይያስን
- ብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 1 ገጽ 164 እስከ 217
- ከብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 95 እስከ 103 አንብብ::

### የጥናት ጥያቄዎች

1. ኢሳይያስ ምዕ. 1-5 በተለይ ምዕራፍ ስድስትን 6ን በማስተዋል አንብብ:: ከዚያም በኋላ ኢሳይያስ በምዕ1-5 ባለው ክፍልና በምዕራፍ 6 ስለራሱ ምን የተለየ አመለካከት እንዳለው አመዛዝነህ ጻፍ::
2. ኢሳ. 19፣ 45፣ 49፣ 60 እና 66 ውስጥ ስለእግዚአብሔር ሚሲዮናዊ ዓላማው ላይ ሁሉን ሕዝብ ወደ መንግሥቱ ለማምጣት ስላለው ዕቅዱ ምን የማበረጃ አሳብ ትመለከታለህ?
3. በኢሳ. 7፥14፤ 9፥1-7፤ 49፥6፤ 52፥13-53፥12፤ 61፥1-3 የተሰጡትን የኢሳይያስን ትንቢቶች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በምን መልኩ ከኢየሱስ ሕይወት ጋር ያገናኛሉ?
4. ኢሳይያስ 48፥17 በቃልህ አጥናና በማስታወሻህ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሳትመለከት ጻፍ::
5. ኢሳይያስ 58-59 በማንበብ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚፈልግባቸውን ነገሮች ጻፍ::
6. እውነት ወይም ውሸት በማለት መልስ::
7. የኢሳይያስ ሚስት ነቢይት ነበረች::

### የመመዘኛ ፈተና

1. ኢሳይያስ ምዕራፍ 25-26 ሰቤተ ክርስቲያን በምትሰብክበት ሁኔታ መልእክት አዘጋጅ::
2. ኢሳይያስ 7+14 የተሰጠው ትንቢት ሁለት ዓይነት ፍጻሜ አግኝቷል:: ሁለተኛው ጌታ ኢየሱስን የሚመለከት ሲሆን የመጀመሪያው ፍጻሜ እንዴት እንደተከናወነ ኢሳይያስ ምዕራፍ 8 አንብበህ አብራራ::



# ትምህርት 17
# ኤርምያስና ሰቆቃወ ኤርምያስ

### መግቢያ

ኤርምያስ ከነቢያት ሁሉ በአስቸጋሪ ወቅትና ሁኔታ ውስጥ ለአገልግሎት የተጠራ ነቢይ ነበር:: ብዙ ስደትና መከራ ከሕዝቡም ሆነ ከነገሥታት እየደረሰበት በድፍረት የእግዚአብሔርን ቃል ተናግሯል:: የመጽሐፉ ዋና መልዕክት «ንስሐ ግቡና ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፣ ይህ ካልሆነ እግዚአብሔር ይቀጣችኋል» የሚል ነበር:: ሕዝቡ ለዚህ ጥሪ ምላሽ መስጠት እምቢ ባሉ ጊዜ ኢየሩሳሌም የምትደመሰስ ከተማ መሆኗን ተናግሯል:: ኤርምያስ የሐሰት ነቢያትንም የተቋቋመ ነቢይ ነበር:: ከሁሉም ነቢያት በበለጠ ሁኔታ የተነበየው ነገር በሕይወቱ ዘመን የተፈፀመ ነቢይ ቢኖር ኤርምያስ ነበር:: በዚህ ትምህርት ስለኤርምያስ መጽሐፍት ማለትም ትንቢተ ኤርምያስና ሰቆቃ ኤርምያስ እንማራለን::

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ:-

- የኤርምያስንና ሰቆቃወ ኤርምያስን መጻሕፍት ዋና ሃሣብ ይገነዘባል::
- ለኢየሩሳሌም መደምሰስ ዋናው ምክንያት የባቢሎናውያን ብርታት ሳይሆን ሕዝቡ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ መሆኑን ያስተምራል::
- ኤርምያስ ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን በድፍረት ቃሉን የተናገረ ነቢይ መሆኑን ይረዳል፣ በአገልግሎቱ ለጥሪው ታማኝ ለመሆን ይችላል::
- እግዚአብሔርን አለመስማት ጥፋትን ወደሕይወት መጋበዝ መሆኑን ከሰቆቃው ኤርምያስ መጽሐፍ በማብራራት የመጽሐፉን መልዕክት ይተንትናል::

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

**ትንቢተ ኤርምያስ**

- መግቢያ
- አታላይነትንና ስደትን ማሸነፍ
- አስተዋጽኦ
- ሥነ መለኮታዊ መልእክት

**ሰቆቃወ ኤርምያስ**

- መግቢያ
- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ
- ሥነ መለኮታዊ መልእክት

**ቁልፍ ጥቅስ**

ኤርምያስ 2፥19 «ክፋትሽ ይገሥጽሻል፣ ክዳትሽም ይዘልፍሻል፤ አምላክሽንም እግዚአብሔርን የተወሽ እኔንም መፍራት የሌለብሽ ክፉና መራራ ነገር እንደሆነ እወቂ፤ ተመልከቺ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።»

**ቁልፍ ሥፍራዎች**

አናቶት፣ ኢየሩሳሌም፣ ራማ፣ ግብጽ

**ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት** - የይሁዳ ነገሥታት (ኢዮስያስ፣ ኢዮአካዝ፣ ኢዮአቄም፣ ዮአኪን፣ እና ሴዴቅያስ)፣ ባሮክ፣ ኢቤድ-ሜሌክ፣ ንጉሥ ናቡከደነፆር እና ሬካባውያን።

## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 104 እስከ 112
- የብሉይ ኪይን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 1 ከገጽ 218 እስከ
- መጽሐፍ ቅዱስ የኤርምያስን መጽሐፍ በሙሉ አንብብ።



## የጥናት ጥያቄዎች

1. ኤርምያስ ምዕራፍ አንድን (1) አንብበህ ለኤርምያስ እግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋዎች ምን ምን እንደሆኑ ጥቀስ። ተቃውሞ እንደሚገጥመው ኤርምያስ ያውቅ ነበር?

2. በምን ዓይነት መንገዶች ነበር የይሁዳ ሕዝቦች የተታለሉት? ኤርምያስ ይህን ግንዛቤአቸውን ለመለወጥ ምን ሙከራ አደረገ? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከምዕራፍ 2-20 በማስተዋል አንብብ።

3. ኤርምያስ 11፥18-23፤ 15፥15-21፤ 26፥1-19፤ 38፥1-23 ያሉትን ክፍሎች አንብበህ ኤርምያስ ሳጋጠመው ስደት ምላሽ የሰጠባቸውን መንገዶች ጥቀስ።

4. በኤርምያስ 31፥31-37 ባለው ክፍል በተሰጠው አዲስ ኪዳንና በብሉይ (በሙሴ ጊዜ በተሰጠው አሮጌ) ኪዳን መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት የሚያሳዩአቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

5. በሰቆቃወ ኤርምያስ ምዕራፍ 3 መሠረት የእግዚአብሔር ታማኝነት እንዴት ባለ መልኩ በታላቅ ሐዘን ውስጥ መጽናናትን ይሰጣል?

## የመመዘኛ ፈተና

1. ኤርምያስ ነ፡ሰ. 36-45 ያለውን አንብበህ የአሁኑ አገር መሪዎችና ባለሥልጣናት ለእግዚአብሔ... ቃል ያላቸውን አመለካከት ከንጉሥ ኢዮአቄም (ም. 36) ሁኔታ ጋር ስታስተያይ ምን ልዩነት ወይም አንድነት ትመለከታለህ?

# ትምህርት 18
# ትንቢተ ሕዝቅኤል

## መግቢያ

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለኃጢአታቸው ቅጣት ይሆን ዘንድ ወደ ምርኮ አገር ቢሰድዳቸውም መናገሩን ቀጥሏል:: ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ሲያነጻ የሚችለውን፣ የመጀመሪያ ልባቸውን አደነደነው፣ አምቢ ያሉትን ቃሉን በድጋሚ መስማት ነበረባቸው:: ናቡከደነፆር ለሁለተኛ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ወደ ባቢሎን በ597 ዓ.ዓ. በምርኮ ሲወስድ ነቢዩ ሕዝቅኤልም ነበረ:: ሕዝቅኤል በምርኮ አገር ላሉት ሰዎች ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው:: በዚህ ትምህርታችን ስለሕዝቅኤል መጽሐፍ ይዘትና አቀራረብ በተወሰነ ደረጃ እንማራለን::

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ:-

- የሕዝቅኤልን መጽሐፍ ዋና ዓላማ ይገልጻል
- ኃጢአት ሕዝቡን ወደምርኮ እንዳስገባቸው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብም በንስሐና ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ደህንነት እንደሚያገኝ ያብራራል::
- የሐሰት መምህራን (በኤር. 28 እና 29 መሠረት) «እግዚአብሔር ሕዝቡን አይፈርድባቸውም» ብለው ቢያስተምሩም ምርኮው 70 ዓመት እንደቆየ እግዚአብሔር ለተናገረው ቃል ታማኝ መሆኑን ይገልጻል::
- ለታመኑ የአይሁድ ቅሬታዎች ወደፊት መመለስና መታደስ እንደነበር ይገነዘባል::
- ኃጢአት የእግዚአብሔርን ክብር ከሕዝቡ ዘንድ የሚያርቅ መሆኑን በቤተክርስቲያን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሥፍራ እና በተለያዩ ፕሮግራሞች ማስተማር ይችላል::



## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

የዘመኑ ምርኮ ነቢይ

- የአገልግሎቱ ዘመን
- አስተዋጽኦ
- ሥነ መለኮታዊ መልእክት

## ቁልፍ ጥቅስና ሐረጐች

- ሕዝቅኤል 36፥24-26
- «የሰው ልጅ ሆይ» 93 ጊዜ
- «የእግዚአብሔርም እጅ በእኔ ላይ ሆነች» 7 ጊዜ
- «የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔረ ክብር» ወይም «የጌታ ክብር» 11 ጊዜ
- «ጌታ እግዚአብሔር» 200 ጊዜ ተደግሟል::

## ዋና ገጸ ባሕርያት

- ሕዝቅኤልና ሚስቱ፣ የእስራኤል መሪዎች፣ ናቡከደነፆር

## ዋና ዋና ሥፍራዎች

- ኢየሩሳሌም፣ ባቢሎን፣ ግብጽ

## የምንባብ ክፍሎች

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ሕዝቅኤል
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ገጽ 1 እስከ 54
- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 113 እስከ 119

## የጥናት ጥያቄዎች

1. ሕዝቅኤል ምዕ. 4-24 ያለውን ክፍል አንብበህ ሕዝቅኤል የእሥራኤልንና የይሁዳን ሕዝብ ሠርተዋል ብሎ የሚከሳቸው ምን ዓይነት ምንዝርና ኃጢአት ነበር? ሥጋዊ ምንዝርና ከመንፈሳዊ ምንዝርና ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
2. ሕዝቅኤል ምዕራፍ 8-11 ያለውን ክፍል አንብበህ የእግዚአብሔር ክብር ቤተመቅደሱን ለቆ የሄደበትን ምክንያቶች ዘርዝር::
3. እግዚአብሔር በምን መልኩ ሁሉን ቻይ፣ ቅዱስ፣ የዓለም ገዢና ለሚወዳቸው ሁሉ አባት እንደሚሆን ከሕዝቅኤል መጽሐፍ ምዕ. 25-32 ያለውንና ከ33-48 ያለውን ክፍል በማንበብ አብራራ::
4. ሕዝቅኤል ምዕ. 18ን አንብብና ሕዝቅኤል በምን መልኩ ሕዝቡ በቅጣት ውስጥ ያሉት ከአባቶቻቸው ኃጢአት የተነሳ እንደሆነ አድርገው በተሳሳተ መንገድ የሚያስቡትን እንዴት እንዳስተካከለ አብራራ::

## የመመዘኛ ፈተና

1. ሕዝቅኤል 40-48 ያለውን ክፍል አንብበህ ስለቤተመቅደስ መታደስና ስለእግዚአብሔር ክብር መመለስ ሕዝቡ ነበረው ብለህ የምታስበው ግንዛቤአቸው ምን አብራራ::



# ትምህርት 19

# ዳንኤል

## መግቢያ

ዳንኤል፣ በስሙ «እግዚአብሔር ፈራጄ ነው» የተባለው ሰው በልጅነቱ ወደ ምርኮ አገር በ605/606 ዓ.ዓ. ተወሰደ:: በሄደበትም ሥፍራ እግዚአብሔርን በማይፈሩት የአሕዛብ ነገሥታት ዘንድ በታማኝነቱ ተመስክሯል:: ወደ እግዚአብሔር በመፀለዩ በሐሰት ተከሰሶ በአናብስት ጉድጓድ መጣሉ፣ ሦስቱ ጓደኞቹ በእሳት መጣላቸው እግዚአብሔር ግን በእርሱ የታመኑትን የአናብስትን አፍ ዘግቶ የእሳትን ኃይል አጥፍቶ አዳናቸው:: በዚህም፣ የሁሉ የበላይና ተቆጣጣሪ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን አስመሰከረ:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለወደፊቱ የተተነበዩ ትንቢቶችና ለመተርጐም ከባድ የሆኑ ራዕዮችም ይገኙበታል:: ዳንኤል በጥበቡ ስለተረጐማቸው ራዕዮች፣ ሕልሞች እና ስለሌሎችም ነገሮች እንማራለን::

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ:-

- ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ በምርኮ አገር ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ያሳለፉትን አይሁዶች ይዘረዝራል::
- እግዚአብሔር የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ የበላይ፣ የሕዝብን ሁሉ ፍጻሜያቸውን የሚያውቅ ትገዛ ሕዝቡ ጥንቃቄ የሚያደርግና ሁሉን የሚቆጣጠር መሆኑን ይገልጻል::
- እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ሁሉ የሚያዋርድ፣ ትሁታንን የሚያከብር አምላክ መሆኑን በቤተክርስቲያን ያስተምራል::

## ቁልፍ ጥቅሶች

«የጠለቀውንና የተሰወረውን ይገልጣል፣ በጨለማ ያለውን ያውቃል፣ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው» (ዳን. 2፥22)::

«ልዑል በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሰለነጥን ለወደደውም እንዲሰጠው፣ ከሰውም የተዋረደውን እንዲሾምበት ሕያዋን ያውቁ ዘንድ ይህ ነገር የጠባቂዎች ትዕዛዝ፣ ይህም ፍርድ የቅዱሳን ቃል ነው» (ዳን. 4፥17)።

## ቁልፍ ቃላት

«ራዕይ» «ሕልም» 4፥17

## ቁልፍ ሥፍራዎች

የናቡከደናፆር ቤተመንግሥት፣ የእቶኑ እሳት ሥፍራ፣ የብልጣሶር ግብዣ ሥፍራ እና የአናብስት ጉድጓድ።

## ዋና ገጸ ባሕርያት

ዳንኤል፣ ናቡከደነፆር፣ ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብድናጐ፣ ብልጣሶር፣ ዳርዮስ

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- የአገልግሎት ዘመኑ
- ዘመኑ
- ሥነ መለኮታዊ መልእክት

## የምንባብ ክፍሎች

- ከመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ገጽ 56-88
- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 120-127 አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. ከዳንኤልና ከጓደኞቹ ታሪክ ለዛሬ ቤተክርስቲያንና ክርስቲያኖች የሚሆን ምን ትምህርት እንማራለን?

2. የዳንኤልን መጽሐፍ በሙሉ እንብበህ መጽሐፉ ስለውጤታማ ጸሎት ምን እንደሚያስተምር ጻፍ።



3. እግዚአብሔር የታሪክ ሁሉ የበላይና ባለቤት ጌታም ነው። መጽሐፉ ይህን ሃሣብ በምን መልኩ ይገልጻል?

4. በምዕራፍ 4 እና 5 መሠረት የናቡከደነፆርና የብልጣሶር ዋና ኃጢአታቸው ምን ነበር? እግዚአብሔርስ እነርሱን ለማስተማር የፈለገው ነገር ምን ነበር?

5. በዳንኤል 9 ላይ የሚገኘው ጸሎቱ በምን መልኩ ዳንኤል ዘሌዋውያን 26፣ 1ኛ ነገሥት 8 እና ኤርምያስ 25 የሚያውቅ መሆኑን ያመለክታል? ይህን ጥያቄ ለመመለስ የተሰጡትን ክፍሎች በጥንቃቄ አንብብ።

## የመመዘኛ ፈተና

1. በዮሐንስ 17 ቁ.11 እና ቁ. 16 ላይ «በዓለም ናችሁ ግን ከዓለም አይደላችሁም» የሚለውን ሃሣብ ከነዳንኤል ሕይወት ጋር በማስተያየት አብራራ።

2. ዳንኤልና (ምዕራፍ 6) ሦስቱ ጓደኞቹ (ምዕራፍ 3) ወደፊት ጠንካራ መከራ ለሚያዩ ቅዱሳን በምን መንገድ ምሳሌ መሆን ይችላሉ?

# V. ደቂቀ ነቢያት

## ትምህርት 20

## ሆሴዕና አሞጽ

### 20.1 ትንቢተ ሆሴዕ

#### መግቢያ

የሆሴዕ መጽሐፍ አቀራረብ እስራኤል እግዚአብሔርን ትታ ሌሎችን አማልክት እንዳትመለከት (በምሳሌያዊ አነጋገር እንዳመነዘረች)፣ በተደጋጋሚ በማመጽ አምላኳ እንዳሳዘነች ይገልጻል። ጌታም ሊተዋት በማይችል ፍቅር እስራኤልን ስለወደዳት ደጋግሞ ንስሐ በመግባት እንድትታደስ ይጠራታል። በክፉ ሥራቸው የተጠመዱትን መቅጣቱን ያስገነዝበናል።

#### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲስጠናቅቅ:-

- እግዚአብሔር ለኃጢአተኛና ደጋግሞ ላመጸው ሕዝቡ ፍቅሩ የማይለወጥ መሆኑን ይረዳል።

- እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ኃጢአትን ግን እንደሚጸየፍና/እንደሚቀጣም ማየት ይችላል።

- ሰፊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ትዕግሥትና ምህረት እንዲሁም አስደናቂ የሆነውን የማይለወጥ ፍቅሩን ይገነዘባል።

- እግዚአብሔር ታማኝና ቃልኪዳን አክባሪ እንደመሆኑ ኃጢአት የሚያስከትለውን ጥፋትና ወደጌታ መመለስ ውጤቱ በረከት መሆኑን ያውቃል።

#### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- ዋና ዓላማዎች
- አስተዋጽኦ



- ዋና መልእክት
- ስነ መለኮታዊ መልእክት
- ማጠቃለያ

#### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 128 እስከ 134
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ ሁስተኛ መጽሐፍ የትንቢተ ሆሴዕን ክፍል
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ የሆሴዕን መጽሐፍ ክፍል በሙሉ አንብብ።

#### የጥያቄዎች መልስ

1. ጌታ ኃጢአትን እንደቀጣ፣ ቅዱስ እንደሆነና ከኃጢአት ጋር ሕብረት እንደማያደርግ፣ ጻድቅ እንደሆነና ኃጢአትን እንደሚፈርድ፣ መልሶ የሚያቅፍ መሆኑን።

2. ንስሐና አምልኮ እንደማይነጣጠሉ የሆሴዕ መጽሐፍ በእምነት በመታዘዝ ራስን ለጌታ ሳይሰጡ መስዋዕት ማቅረብ ጌታን ማምለክ፣ በጌታ ዘንድ ፍጹም ተቀባይነት የለውም (6፥1-6)።

3. ኃጢአት ሁሉን ነገር የሚነካና የሚያበላሽ እንደሆነ ታማኝነት ማጉደሏ በኃይማኖት፣ በፖለቲካና በግብረገብ በኢኮኖሚዋም ጭምር ውድቀትንና ጥፋትን አስከትሎባታል።

4. ባል፣ አረኛ፣ አባት

#### የጥናት ጥያቄዎች - ትንቢተ ሆሴዕ

1. እግዚአብሔር እስራኤልን መቅጣቱ ምን ያስተምርሃል?
2. ንስሐና አምልኮ እንደማይነጣጠሉ ከሆሴዕ መጽሐፍ ምን ተረዳህ?
3. እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ታማኝ አለመሆንዋ ምን ችግር አስከተለባት?
4. እግዚአብሔር ለመረጠው ሕዝቡ እንደ ምንድን ነው?

#### የመመዘኛ ፈተና

1. ኃጢአት በሰራህ ጊዜ ወይም በተለያየ ችግር ውስጥ ሆነህ እግዚአብሔር የተወህ ሲመስልህ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም እንደሆነና በሁኔታዎች እንደማይለዋወጥ

ለመረዳት የሆሴዕ መጽሐፍ ምን እንደረዳህ ለወደፊቱ ሕይወትህ መጽናናትና ተስፋ የሚሆን ትምህርት ያገኘኸውን በአጭሩ ጻፍ::

2. የሆሴዕን መጽሐፍ ከዘዳግም መጽሐፍ ጋር በማገናዘብ እግዚአብሔር ለገባው ቃልኪዳን ታማኝ መሆኑንና ሕዝቡም የቃል ኪዳን ግዴታዎቹን የመፈጸም ኃላፊነት እንደሚጠበቅበት ምን አስተዋልክ?

## 20.2 ትንቢተ አሞጽ

### መግቢያ

እግዚአብሔር ለነቢዩ አሞጽ የቃል ኪዳን ግዴታዎችዋን ባልፈጸመችው በእስራኤል ላይ እንደሚፈርድባት አስጠንቅቋል:: ግን በግፍ ከተሞላችበት ሁኔታ መመለስ አለባት:: ሁሉን የሚገዛ አምላክ በእርሱ ስልጣን ላይ የተነሱትን ሕዝብ ሁሉ እንደሚቀጣ ለእስራኤል ግን ወደ እግዚአብሔር በሚመለሱት ቅሬታዎች አማካይነት በፍጻሜ የመባረክና የማደስ ተስፋ እንዳላት ያሳየናል::

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲጠናቅቅ:-

- ሰላምና ብልጽግና ሁልጊዜ የበረከት ምልክት እንዳይደለ ያውቃል፣
- እግዚአብሔር ተመለሱ ሲል በእመጽ መግፋት ፍርድን እንደሚያመጣ ይገነዘባል፤
- እግዚአብሔር እስራኤልን ብቻ ሳይሆን ሰውን ሁሉ የሚያስተዳድርና፣ የሚዳኝ እንደሆነ ይረዳል::
- እግዚአብሔር የፍርድ አምላክ ብቻ ሳይሆን ተመልሶ እንደሚምርና ተስፋን የሚያድስ አምላክ መሆኑን ለማሳሰብ ይችላል::

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- ዋና ዓላማዎች
- አስተዋጽኦ



- አሞጽ
- የስነ ጽሑፍ ይዘቱ
- ማጠቃለያ

### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 135-139
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ ሁለተኛ መጽሐፍ ስለ ትንቢተ አሞጽ የተሰጠውን ማብራሪያ አንብብ::
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ የትንቢተ አሞጽን መጽሐፍ አንብብ::

### የጥናት ጥያቄዎች

1. አሞጽ ማለት ምን ማለት ነው? ከየት ተጠራ? ይህ ጥሪ ምን ያስተምርሃል?
2. ምቾትና ኃብት ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት ምልክት ይመስልሃል?
3. ግብዝነት ስለሞላበት ሃይማኖት የአሞጽ መጽሐፍ የሚያሳየውን ጥቂት ነጥቦችን ዘርዝር::
4. የአሞጽ አገልግሎት ከጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ጋር ይመሳሰላል የተባለው ለምንድን ነው?

### የመመዘኛ ፈተና

1. የዘመናችንን እምልኮ ከአሞጽ ዘመን ጋር በማመሳከር አምልኮአችንን እንዴት ማስተካከል እንደሚገባን ጥቂት ሃሣቦችን ከተረዳኸው ግለጽ::

2. የአሞጽ መጽሐፍ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳን ብቻ ሳይሆን፣ እስራኤልም ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን የቃል ኪዳን ግዴታዎች ማስታወስ እንደሚገባት ሲያሳስበን በራሳችን ሕይወትና በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ይህን እውነት እንዴት እናየዋለን?

3. እግዚአብሔር እስራኤልን ከአመጽ የተነሳ ሊያጠፋ ቢነሳም በንስሐ የሚመለሱትን ጥቂት ቅሬታዎች አድሶ በእነርሱ በኩል ሕዝቡን ሁሉ ወደ ራሱ ስም ይሰባል። ከአሞጽ መጽሐፍ ስታጠና እግዚአብሔር ለልጆቹ ኪዳን ያለውን አክብሮት እንዴት ትረዳለህ?



## የጥያቄዎች መልስ

1. አሞጽ ማለት ሸክም ተሸካሚ ማለት ነው። ላሞችንና በጐችን ከሚጠብቅበት ቦታ ተጠራ እግዚአብሔር በማንም ሰው ሊጠቀም እንደሚችልና ሁልጊዜ ለእርሱ ጥሪ በየተሰማራንበት ሥራ ላይ ሆነን ንቁዎችና ምላሽ የምንሰጥ መሆን እንደሚገባን ያስረዳል።

2. ምቾትና ኃብት ሁሉ ከእግዚአብሔር በረከት ምልክት እንዳልሆነ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንዳመጣና በእርስ በርስ አመጽንና መለያየትን እንዳስከተለ ያለሕግና ያለ እግዚአብሔር ቸርነት በዝርፊያ በአመጽም እንደሚገኝ ከታሪኩ እንረዳለን።

3. ግብዝነት የተሞላበት ሃይማኖት ከአሞጽ መጽሐፍ የምናገኛቸው ነጥቦች ተዘርዝረዋል።

4. የአሞጽ አገልግሎት ከጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ጋር የሚመሳሰልባቸውን መንገዶች ተመልከት።

# ትምህርት 21

## ሚክያስ፣ ኢዩኤል፣ አብድዩና ዮናስ

### መግቢያ

ከእነዚህ ታናናሽ ነቢያት ታሪክ የምንረዳው ሰዎች በሚያጠፉት ጥፋት ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ እንደሚመጣ ነው:: እግዚአብሔር ከመልካምነቱ የተነሳ፣ ንስሐ ለሚገቡ ምሕረትንና ይቅርታን ማዘጋጀቱን እንማራለን:: ደግሞም እግዚአብሔር የተስፋና የበረከት አምላክ በመሆኑ የበለጠ ለጌታ መኖር ይገባናል::

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ክፍል ሲጠናቀቅ:-

- የተጠቀሱትን መጻሕፍት በሚገባ ያውቃቸዋል፣
- መጻሕፍቱ ለክርስትና ኑሮ የሚሆኑ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል::
- ያገኛቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች በተግባር ላይ ማዋል ይችላል::

### አስተዋጽኦ

### ትንቢተ ሚክያስ

«የፍርድና የተስፋ መልእክት»

- መግቢያ
- ዓላማዎቹ
- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ
- በሚክያስ ዘመን የነበረው የሕዝቡ ሁኔታ
- ማጠቃለያ

### ትንቢተ ኢዩኤል

«(የጌታ ቀን) ፍርድና ምሕረት»

- ዋና ዓላማዎች



- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ
- የስነ መለኮታዊ መልእክት
- ማጠቃለያ

### ትንቢተ አብድዩ

«የሚወድቀው ዓለትና ለዘላለም የሚጸናው መንግሥት»

- መግቢያ
- ፀሐፊው
- ዘመን
- ርዕስ
- የመክፈቻ ጥቅስ
- የመክፈቻ ቃል
- የመጽሐፉ ዓላማ
- አስተዋጽኦ
- ታሪካዊ መነሻ
- ከአብድዩ መጽሐፍ ለሕይወታችን የምናዛምዳቸው ትምህርቶች
- ማጠቃለያ

### 21.4 ትንቢተ ዮናስ

- ዋና ዓላማዎች
- ጸሐፊው
- የመጽሐፉ አስተዋጽኦ
- ስነ መለኮታዊ መልእክት
- ማጠቃለያ

### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን እስሳ ከገጽ 147 እስከ 149
- የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2ትን ከገጽ 126-169

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ሚክያስ፣ ኢዩኤል፣ አብድዩና ዮናስን አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. በትንቢተ ኢዩኤል ከተጠቀሱት የተስፋ ቃሎች አንዱ ስለመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የተነገረ ነው። የአዲስ ኪዳን ስለዚህ ምን ይላል? መቼስ ተፈጸመ?
2. ለኢዩኤል መልእክት የመጀመሪያ ሰሚዎች (አንባቢዎች) እነማን ናቸው?
3. ነቢዩ ሚክያስ የኖረበት ዘመን ከሌሎች ነቢያት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ስማቸውን ጻፍ።
4. የሚክያስ ስም ትርጓሜ ምንድን ነው?
5. ትንቢተ አብድዩን ከሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው?
6. በትንቢተ ሚክያስ ስለክርስቶስ ከተነገሩት ትንቢቶች ሁለቱ ምንን በተመለከተ ነው?

## የመመዘኛ ፈተና

1. ዮናስ ነቢዩ በአሳ ሆድ 3 ቀን አደረ ይላል፣ ለአንድ የማያምን ሰው ይህን እውነት እንዴት ትገልጽታለህ?
2. ስለትዕቢት መንስኤና ውጤት ትንቢተ አብድዩን ደጋግመህ በማንበብ ነጥቦችን ዘርዝርና ማብራሪያ ስጥ።
3. የዮናስ መጽሐፍ ሚሲዮናዊ (ወንጌልን ለሌሎች የማድረስ) ሃሣብ አለው። ዛሬስ የእኛ ቤተክርስቲያን ምን ዓይነት ዕርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባታል?



## የጥያቄዎች መልሶች

1. «መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ» (ምዕ. 2) ይህም የተፈጸመው በኢየሩሳሌም በበዓለ ሃምሣ ዕለት ነው (የሐዋ. 2)
2. ለይሁዳ (ደቡባዊ የእስራኤል መንግሥት) ነው።
3. ከእነኢሳይያስና ሆሴዕ ጋር ነው።
4. «እግዚአብሔርን የሚመስል ማነው?»
5. አጭሩ (ትንሹ) መጽሐፍ ስለሆነ ነው።
6. . በቤተልሄም ስለመወለዱ (5፥2)
   - ክርስቶስ እንደሚነግስ (2፥12-13፤ 4፥1፤ 7)

# ትምህርት 22

## ናሆም፣ ዕንባቆምና ሶፎንያስ

| 22.1 ትንቢተ ናሆም | 22.2 ትንቢተ ዕንባቆም | 22.3 ትንቢተ ሶፎንያስ |
|---|---|---|
| መግቢያ፦ የመጽሐፉ ዋና ይዘት በአሶር ላይ የፍርድን ቃል ለማወጅና በዚህም ይሁዳን ለማጽናናት ያቀደ ይመስላል። ስለ ነነዌ (የአሶር ዋና ከተማ) መመታትም በሰፋት ተጽፏል። በዚያን ወቅት የአሶር መንግሥት እሱ ከሚባሉት ኃያላን መንግሥታት አንዷ ብትሆንም የኃያላን ኃያል የታሪክ ባለቤት የሆነው አምላክ ይፈርዳታል። እግዚአብሔር ዓመጸን የሚበቀል መሆኑን ከመጽሐፉ እንማራለን። | መግቢያ፦ መጽሐፉ የሚያተኩረው በደቡባዊው የይሁዳ ግዛት ላይ ሆኖ የእግዚአብሔር ፍጹም የታሪክ ባለቤትነት<br>ን የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። ምንም እንኳ ኃጢአትና ዓመጻ በምድር ቢበዛ እግዚአብሔር ምን ጊዜም ቢሆን የበላይ ገዥና ሉዓላዊ አምላክ መሆኑን ከመጽሐፉ እንረዳለን። ዕንባቆም የከበደውንና ያልገባውን ነገር በፀሎት በእግዚአብሔር ፊት ሲያቀርበው እናያለን። ነቢዩ ዕንባቆም «እግዚአብሔር ጻድቅ ሆኖ እያለ ለምን ዓመጻ ሲበዛ ዝም ይላል?» ሲል ያቀረበው ጥያቄ፤ ከብዙ ሰዎች ጥያቄ ጋር ይመሳሰላል። | መግቢያ፦ መጽሐፉ ስለይሁዳ ኃጢአትና ድፍረት ያትታል። በመጽሐፉ ውስጥ የይሁዳው ንጉሥ ኢዮስያስ በቀደሙት ዓመጸኞች ነገሥታት ምናሴና አሞን የተደረጉትን ጥፋቶች ለማረም እንደሞከረ እንመለከታለን። የነቢዩ ሶፎንያስ አገልግሎት (ያስተላለፋቸው ትንቢቶቹ) የንጉስ ኢዮስያስ የማደስ እርምጃዎችን በእጅጉ እንዳገዘ ይታመናል። |

የትምህርቶቹ ዓላማዎች፦

ተማሪው ይህን ክፍል ሲያጠናቅቅ፦

| 22.1 | 22.2 | 22.3 |
|---|---|---|
| 1. የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ በኃጢአተኛው ዓለም ላይ እንደሚመጣ ከበፊቱ ይልቅ በመረዳት የሚጠፉትን ሰዎች ለመድረስ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ይፀልያል፤ ይተጋል፤ ወንጌልን ይመሰክራል።<br><br>2. እግዚአብሔር ለሕዝቡ (ለቤተክርስቲያን) ተሟጋች እንደሆነ ስለሚረዳ በቀልን ለእግዚአብሔር መተው ይማራል። | 1. እግዚአብሔር የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኖ በሉዓላዊነቱ ዓለም<br>2. ን ሁሉ እንደያዘ ስለሚገነዘብ በዙሪያው በሚያየው ዓመጻና እርኩሰት አይደናገጥም።<br><br>3. ዘሕይወቱ፣ በአገልግሎቱ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በምድሪቷ፣ ወዘተ. በሚገጥመውና በሚያያቸው<br><br>ተግዳሮቶች የተነሳ በእግዚአብሔር ላይ ያለው መታመን ይበልጥ ሥር እየሰደደ መሄድ እንጂ መናድ እንደሌለበት ይረዳል። | 1. ዓመጸና ኃጢአት በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ካለ የእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ ደግሞ እንደማይቀር ስለሚረዳ ስለሕይወቱ፣ ስለቤተሰቡ፣ ስለቤተክርስቲያንንና በአጠቃላይ ስለምድሪቷ መንፈሳዊ ጤንነት በእግዚአብሔር ፊት ሁሉ መቅረብ እንደሰበት ይማራል።<br>2. እግዚአብሔር የሚቀጣቸው የሚወዳቸውን እንደሆነ ይረዳል።<br>• እግዚአብሔር ፍቅር ነው = እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው በሚሉት አባባሎች ላይ ያሰው መረዳት ይጨምራል። |

የትምህርቱ አስተዋጽኦ

| 22.1 | 22.2 | 22.3 |
|---|---|---|
| • መግቢያ<br>• ዓላማዎቹ<br>• የናሆም አስተዋጽኦ<br>• ናሆም<br>• የስሙ ትርጉም<br>• የመጽሐፉ ማዕከላዊ ሃሣብ<br>• የናሆም መጽሐፍ ንድፍ<br>• ማጠቃለያ | • መግቢያ<br>• ዓላማዎቹ<br>• የዕንባቆም አስታዋጽኦ<br>• ስለዕ<br>• ንባቆም<br>• ዕ<br>• ንባቆም ያገለገለበት ዘመን<br>• ስለመጸሐፉ የተሰጠ ጠቅሰል ያለ | • መግቢያ<br>• ዓለማዎቹ<br>• የሶፎንያስ (አስተዋጽኦ)<br>• ሶፎ<br>• ንያስ የተባለው ሰው<br>• የሶፎንያስ መልዕክት ይዘት<br>• ከሶፎንያስ መጽሐፍ ወደ ወደሕይወታችን የምናዛምዳቸው |



| 22.1 ትንቢተ ናሆም | 22.2 ትንቢተ ዕንባቆም | 22.3 ትንቢተ ሶፎንያስ |
|---|---|---|
| | ማብራሪያ<br>• የዕንባቆም መጽሐፍ ሥዕላዊ መግለጫ (ንድፍ)<br>• ማጠቃለያ<br>የመጻሕፍቱ ቁልፍ ጥቅሶች | ትምህርቶች፦<br><br>• የሶፎንያስ መጽሐፍ ንድፍ<br>• ማጠቃለያ |
| 1+7-9<br>• ናሆም | 3+2<br>• ዕንባቆም<br>• ባቢሎናውያን | 2+3<br>• ሶፎንያስ<br>• ኢዮስያስ |

የመጻሕፍቱ ቁልፍ ሥፍራዎች

| | | |
|---|---|---|
| • ነነዌ | • ይሁዳ | • ኢየሩሳሌም |

## የምንባብ ክፍሎች

### 22.1 - ትንቢተ ናሆም

- የብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 150 እስከ 151
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 170-177
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ የትንቢተ ናሆምን ክፍል በጥንቃቄ አንብብ።

### 22.2 - ትንቢተ ዕንባቆም

- ከብሉይ ኪዳን ቅሰሳ ከገጽ 152 እስከ 154
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 178-190
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ የትንቢተ ዕንባቆምን ክፍል በጥንቃቄ አንብብ።

### 22.3 - ትንቢተ ሶፎንያስ

- ከብሉይ ኪዳን አስሳ ከገጽ 155 እስከ 158
- ከብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2 ከገጽ 190-201
- ከመጽሐፍ ቅዱስህ የትንቢተ ሶፎንያስን ክፍል በጥንቃቄ አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር የነነዌን ከተማ ለመቅጣት የተነሳበትን ምክንያቶች አስረዳ።

2. በትንቢተ ዕንባቆም ላይ እንደምትመለከተው እዚአብሔር ባቢሎናውያንን ተጠቅሞ ይሁዳን ቀጥቷል፤ የዕንባቆምም ጥያቄ ለምን እግዚአበሔር በአሕዛብ ይጠቀማል? የሚል ነበር። ለዚህ ጥያቄ ከመጽሐፉ ጋር እያስተያየህ የራስህን መረዳት ስጥ።

3. በትንቢተ ሶፎንያስ ላይ እንደምናነበው የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳ ላይ እንደሚመጣ ተነግሯል። ቁጣው በይሁዳ ላይ የሚመጣበትን ምክንያት/ቶች በዝርዝር አስረዳ።

4. በትምህርት 22 ውስጥ ባሉት ሦስት የትንቢት መጻሕፍት ማለትም ትንቢተ ናሆም፣ ዕንባቆምና ሶፎንያስ ላይ የተሰጡትን ቁልፍ ጥቅሶች በጥንቃቄ አንብብ። ከእነዚህ ጥቅሶች ስለእግዚአብሔር ማንነት (ባሕርይ) የምታገኘውን ትምህርት በዝርዝር አስረዳ።

5. ከነብዩ ናሆም፣ ዕንቆባምና፣ ሶፎንያስ ሕይወትና አገልግሎት የምታገኘው ትምህርት ከራስህ ጋር እያዛመድክ አብራራ።

## የመመዘኛ ፈተና

1. አሁን በዓለም ላይ ሐጢአት፣ ዓመጻና እርኩሰት ሲስፋፋ ስትመለከት ስለእግዚአብሔር ማንነት፣ ስለሰው ማንነት፣ እና ስለእግዚአብሔር ፍርድ ምን ትገነዘባለህ?

2. ከነቢዩ ዕንባቆም የምትማረው አንድ ልዩ ትምህርት ምንድነው?

3. የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ የሚመጣበት ዋና ዋና ምክንያቶች በራስህ አባበል ግለጽ። በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ከመጣ በኋላ የሚገኘው/የሚታየው/ ውጤት ምንድነው?



## የጥያቄዎች መልስ

1. በነነዌ ከተማ ከተስፋፉት ዓመጻዎች ዋና ዋናዎቹ፦

   ደካማውን መበዝበዝ፣ እርኩሰት፣ አለመታዘዝ፣ ግድያ፣ ጭካኔ ወዘተ. (3፥1፣ 3፥19፣ ተመልከት)

   - የአሦራውያን ኃጢአት በተመለከተ ናሆም 1፥11፣ 1፥14፣ 3፥1-19 ላይ ተመልከት።

2. መልስህን ከማስታወሻውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።

3. መልስህን ከማስታወሻውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።

4. መልስህን ከማስታወሻውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።

5. መልስህን ከማስታወሻውና ከመጽሐፍ ቅዱስህ ጋር አስተያየው።

# ትምህርት 23.1 ሐጌ

«ለየትኛው ነገር ቅድሚያ ትሰጣላችሁ?»

«...ቤቱንም ሥሩ፤ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል፤ እኔም እመሰገናለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር (1+8)»

## መግቢያ

ሐጌ ከባቢሉን ምርኮ መልስ ከተናገሩት ነቢያት አንዱ ነው። እግዚአብሔር ዕረፍት ከሰጠ በኋላ የግልን ጉዳይ በማስቀደም የእርሱን ሥራ ቸል ማለት በሰዎች ዘንድ የተለመደ ነው። በሐጌ ዘመን የነበሩትን ሕዝብ የተፈታተናቸው ነገር ቢኖር ይኸው ነበር። የጌታን ቤት ግንባታ ሥራ ቸል በማለታቸው በልዩ ልዩ መንገድ ቀጣቸው፤ ነገር ግን አላስተዋሉም፤ ንስሐም አልገቡም። ለጌታ ሥራ ቀዳሚውን ሥፍራ መስጠት በረከትን ያመጣል፤ ጌታም ይከብርበታል።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ትምህርት ሲያጠናቅቅ:-

- ለእግዚአብሔር ሥራ ቀዳሚውን ቦታ አለመስጠት ቅጣት ማስከተሉን።
- ጌታ በመንፈሱ የሕዝብ መሪዎችንና ሕዝብን ለዓላማው እንደሚያነሳሳቸው፤ እርሱ መስራት ሲጀምር ሁሉም ለእርሱ፤ ለቅድስና ሕይወት ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ።
- በክርስቶስ በኩል ሊመጣ ያለውን ክብር ለማየት መመኘት እንዳለብን ይገባል።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

- ዓላማዎች
- አስተዋጽኦ
- ጸሐፊው
- ሥነ መለኮታዊ መልእክቶች
- ማጠቃለያ



## የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 21 ገጽ 202-215
- ትንቢተ ሐጌ ምዕ. 1 እና 2
- የብሉይ ኪዳን እሰሳ ከገጽ 159 እስከ 162 አንብብ።

## የጥናት ጥያቄዎች

ሀ. ሐጌ ከባቢሉን ወደ ኢየሩሳሌም መጀመሪያ የሄደው መቼ ነበር?

ለ. አይሁዶች ወደገዛ አገራቸው እንዲመለሱ ያወጀው የአሕዛብ ንጉሥ ማን ይባላል?

ሐ. ሐጌና ዘካርያስ በኢየሩሳሌም ለነበሩት አይሁድ ምን እንዳደረጉ ግለጽ።

መ. መሠራት የተጀመረው የቤተመቅደስ ሥራ መንገድ ላይ የቆመው በምን ምክንያት ነበር?

## የመመዘኛ ፈተና

1. በአካባቢህ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔር ሥራ ቸል የተባለበት ሁኔታ ካለ ዘርዝር (ጥቀስ)
2. ለዚህ ቸልተኝነት መፍትሄ ይሰጣሉ ብለህ የምትገምታቸውን ነገሮች ጥቀስ።
3. የእግዚአብሔር መንፈስና ቃሉ ማድረግ የሚችልባቸውን ዋና ዋና ነገሮች ግለጽ።
4. በሐጌ መጽሐፍ ጥናትህ ውስጥ ጌታ ለልብህ በይበልጥ የተናገረህ ነገር አለ? እንዴት?
5. መልሶቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሣብ ጋር የሚስማሙ መሆን ይኖርባቸዋል።

## የጥያቄዎች መልሶች

1. በ536 ዓ.ዓ.
2. ቂሮስ
3. በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢታዊ መልዕክት አስተላልፈዋል።

4. በሳምራውን በኩል ከተነሳው ተቃውሞ የተነሳ (ዕዝራ 4፥24)

## ከትምህርት 23.1

1. በ536 ዓ.ዓ.
2. ቂሮስ
3. በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢታዊ መልዕክት አስተላልፈዋል።
4. በሳምራውን በኩል ከተነሳው ተቃውሞ የተነሳ (ዕዝራ 4፥24)

# ዘካርያስና ሚልክያስ

## መግቢያ

በእነዚህ ሁለት መጻሕፍት አስደናቂ የሆኑ ትምህርቶችን እናገኛለን። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ዓላማው ምንድን ነው? ሕዝቡስ በፊቱ ምን ይመስላል? ጠቅላላ የእምነት ሕይወቱ (ኑሮው) እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ነው? ወይስ መስተካከል ያለበት ነገር አለ? ጌታ የሚያጽናና ምክርና ተስፋ ካስፈለገም የተግሳጽ መልእክቶች አሉት። እነዚህን አሳቦች በሚያካትት መልኩ ትንቢተ ዘካርስያስንና ሚልክያስን እናጠናለን።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ትምህርት ሲያጠናቅቅ፡-

- የትንቢተ ዘካርያስንና ሚልክያስን መጽሐፍ በሚገባ ይረዳል።
- በዘመናችን ላሉ አገልጋዮችና ክርስቲያኖች የሚሆኑ ትምህርቶችን ከእነዚህ መጽሐፎች ማዘጋጀት ይችላል።



# 23.2 - ዘካርያስ

## መግቢያ

የእግዚአብሔር ዓይኖች ዘወትር በሕዝቡ ላይ ናቸው። እኛ ለእርሱ ሙሉ በሙሉ ተሰጥተን ሥራውን የምንሠራ ከሆንን፣ እርሱ በሚያስፈልገን ሁኔታ ይመክረናል፣ መጽናትንም ይሰጠናል። ከዚያም አልፎ የዘላለም ተስፋውን ሲያስጨብጠን የልቡን ይነግረናል። እነዚህን በመሳሰሉ ሃሣቦች ትንቢተ ዘካርያስ ሰፊ ትምህርቶች አሉት።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ትምህርት ሲያጠናቅቅ፡-

- የትንቢተ ዘካርያስን ዋና ዋና መልእክቶች ይረዳል፣
- ስለክርስቶስ በዚህ መጽሐፍ የተነገሩትን ትንቢቶች ይገነዘባል፣
- እግዚአብሔር ሕዝቡ ወደእርሱ ሲመለሱ፣ እርሱም ወደእነርሱ በመመለስ እንደሚያጽናናቸው ይገነዘባል፣
- እግዚአብሔር ለሚጠቀምባቸው ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቅላቸውና የሰይጣንን ተቃውሞና ክስ እንደሚመታ ይረዳል (ምዕ. 3)።
- ስለመንፈስ ቅዱስና ስለጌታ ሥራ ሲያስብ ዘወትር በእርሱ ላይ መደገፍ እንዳለበት ይገነዘባል (ዘካ. 4፥6፣ ኤፌ. 5፥18)።
- እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል አስቀድሞ የተናገራቸውን ተስፋዎች እንደፈጸመ፣ የቀሩትንም ወደፊት እንደሚፈጽም በማመን በተስፋ መኖር እንዳለበት ይረዳል።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦ

አስተዋጽኦ
ጸሐፊው
ታሪካዊ አቀማመጥ
ስነ መለኮታዊ መልእክቶች
ማጠቃለያ

### የምንባብ ክፍሎች

1. የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ ክፍል 2፤ ከገጽ 215-239
2. የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ ገጽ 163 እስከ 169

### ከትምህርት 23.2 የቀረቡ ጥያቄዎች

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ፦**

ሀ. የነቢዩ ዘካርያስ ዋና አገልግሎት ምን እንደነበረ በአጭሩ ግለጽ።

ለ. በብሉይ ኪዳን በብዛት ስለክርስቶስ ትንቢት የተናገሩትን ሁለት ነቢያት ስም ጥቀስ።

ሐ. ከትንቢተ ዘካርያስ ገና ያልተፈጸመ፤ ግን በክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት ጊዜ ይፈጸማል ብለህ የምታስበውን ምዕራፍ ጥቀስ።

መ. እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ የሚጠቀምበት ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው (ዘካ. 3-4)?

## 23.3 - ሚልክያስ

### መግቢያ

የጌታ ሕዝብ ብዙ ምክርና ተግሳጽ ተቀብሎ ንስሐ በመግባት ከታደሰ በኋላ በእምነቱ መጽናት ሲገባው መድከም ጀመረ። የሃይማኖት መሪዎችም ራዕያቸው ይጠፋና ጌታን መፍራት ሁሉ ይረሳሉ። አገልጋዮችና ተገልጋዮች ሁሉም እምላካቸውን ወደሚያሳዝን ሁኔታ ይደርሳሉ። ይህን ዓይነት ሕይወት የኖሩ የሚልክያስ ዘመን ሰዎች ናቸው። ሕዝቡ ሲጠፋ ዝም ብሎ ማየት የማይፈቅድ ጌታ፤ በፍቅር ድምጹ በቃሉ በኩል ንስሐ እንዲገቡ ይጋብዛል። ድምጹን ሰምተው ለሚመለሱ የዘላለም ተስፋ ይሰጣቸዋል።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ተማሪው ይህን ትምህርት ሲያጠናቅቅ፦

1. የትንቢተ ሚልክያስን መጽሐፍ ዋና መልእክት ይረዳል።
2. ኃጢአትና ክህደት ፍርድ እንደሚያስከትሉ ይገነዘባል።



3. በጌታ የተጠሩት ሕዝቡ ጌታን በመፍራት፤ በመውደድ፤ በቅድስና ኑሮ ማምለክ እንደሚገባቸው ይረዳል።
4. ወደፊት ለጻድቃን የዕረፍት፤ ለኃጢአን ደግሞ የፍርድ ቀን እንደሚመጣ ይገነዘባል።

### የትምህርቱ አስተዋጽኦ

ዋና ዓላማዎቹ
አስተዋጽኦ
ጸሐፊው
ስነ መለኮታዊ መልእክት
ማጠቃለያ

### የምንባብ ክፍሎች

- የብሉይ ኪዳን ትመማ 2ኛ መጽሐፍ፤ ክፍል 2፤ ገጽ 242-261
- መጽሐፈ ሚልክያንስን በሙሉ
- የብሉይ ኪዳን አሰሳ ከገጽ 170 እስከ 173 አንብብ።

### የጥናት ጥያቄዎች

1. በሚልክያስ ምዕ. 4 «መልእክተኛዬን» እንደዚሁም «ኤልያስን እልካለሁ» ሲል ምን ማለቱ ነው (ማንን ይልካል)?

2. የሚልክያስ ዘመን ሕዝቦችና ካህናት ጌታን በምን በምን እንደበደሉት ከ3 ያላነሱ ነጥቦችን ጥቀስ፡

3. «ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን» የሚለው ሐረግ ወደ ምን ያመለክታል?

### የመመዘኛ ፈተና

1. ከትንቢተ ዘካርያስ ለዛሬዋ ቤተክርስቲያን የሚሆኑ ሦስት ነገሮችን በመጥቀስ ችግሩንና የመፍትሄውን አሳብ በተማርነው መሠረት ግለጽ።

2. ስለክርስቶስ በዘካርያስ ተጠቅሰው፤ በአዲስ ኪዳን ተፈጸሚነት ያገኙ ሦስት ነገሮችን ጥቀሳቸው።

3. በሚልክያስ ዘመን ካህናትና ሕዝቡ በጌታ ፊት የተወቀሱባቸውን ነገሮች ተመልክተናል። በአብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ተመሳሳይ የሚወቀሱበት ነገር ያለ ይመስልሃል? ካሉ ጥቀስ። ከቃሉ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ምን መፍትሄ ማምጣት እንደሚቻል ግለጽ።

4. «ጌታን ማገልገል ከባድ ነው፤ እንዴት መዝለቅ ይቻላል? » ይህ የብዙዎች አገልጋዮች ጥያቄ ይመስላል። ስለዚሁ ያለህን አመለካከትና መፍትሄ ይሆናል ብለህ የምታስበውን አሳብ ግለጽ (በቃሉ የተደገፈ ቢሆን)።



## የጥያቄዎች መልሶች

1. አገልግሎቱ፣ በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር የተሰጡ አራት ዓላማዎችንና የመሳሰሉትን
2. ነቢዩ ኢሳይያስና ዘካርያስ
3. ዘካርያስ ምዕራፍ 14
4. ሀ. በእምነት የጸደቀ ሆኖ ለጌታ የተሰጠ
   ለ. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተደግፎ የሚሠራ

## ትምህርት 23.3

1. ስለመጥምቁ ዮሐንስ መምጣት ይናገራል።
2. ፡ ፍቅሩን በመካድ
   - ለጌታ በሚቀርብ መሥዋዕት
   - በጌታ ፊት በድፍረት በመናገር
   - አሥራትንና በኩራትን ባለመስጠት (በመስረቅ)
   - «እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው» በማለት ወዘተ.

3. በዓለም መጨረሻ በጌታ ኢየሱስ በኩል በዓለም ላይ ሊመጣ ያለውን ታላቁን የፍርድ ቀን (ጊዜ)።